# የሕይወት ችግሮችን መፍታት

## ክርስቲያናዊ መንገድ

ከኢንተርናሽናል ኮርስፖንዳንስ ኢንስትቲዩት ጋር በመተባበር በዶሮቲ ጆንስ ተዘጋጅቶ በ"ሥነ መለኮት በቤቴ" አማካኝነት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተመለሰ የሕይወት ችግሮችን ስለመፍታትና ስለምክር አገልግሎት የሚያስተምር የመማሪያ መጽሐፍ።

1994 - አዲስ አበባ

ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ........................................ 2

### ክፍል አንድ፡ የችግር አፈታት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች

1. የችግሮች ምንጭ ........................................ 5
2. ክርስቲያናዊ የመፍትሔ መንገዶች ........................................ 24
3. ክርስቲያናዊ የመፍትሔ መርሆዎች ........................................ 45

### ክፍል ሁለት፡ በግንኙነት ውስጥ ያሉ ችግሮች

4. በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ያሉ ችግሮች ........................................ 66
5. የቤተሰብ ችግሮች ........................................ 66
6. የላጤነት ሕይወት ችግሮች ........................................ 111

### ክፍል ሦስት፡ ልዩ ችግሮች

7. ግብረ ሰዶማዊነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ........................................ 131
8. መደበትን መቋቋም ........................................ 149
9. ስቃይና ሞት ........................................ 169
10. ተስፋን ማጽናት ........................................ 191

የሙከራ ፈተና መልሶች ........................................ 206

# መግቢያ

አንድ የታወቀ ፋላስፋ ስለ ሕይወት ያለውን አመለካከት እንዲህ ብሎ ጻፈ። "ሕይወት በተለያዩ ጊዜያት መገፋትን፣ መረሳትን እንዲሁም የእንባ ገጠመኞችን ያዘለ ነው" አለ። በርግጥ ይህ አባባል ክርስቲያናዊ አመለካከትን ያልያዘ ሲሆን ሕይወት ከምንም ወደ ምንም የሚሸጋገርና በእንባ የተሞላ ሂደት እንደሆነ የሚያወሳ ነው። ነገር ግን እኛም ክርስቲያኖች የሆንነውም እንኳን እንባና ችግሮች የሕይወት ገጠመኞቻችን ናቸው። ከዚህም የተነሣ ችግሮቻችን እንዲፈቱ እርዳታን እንፈልጋለን።

የሕይወት ዓላማ ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሰዎች ለምን በመከራ ያልፋሉ? ለምንድን ነው በዓለማችን ሕመም፣ ሐዘንና ጥላቻ የሚፈራረቀው? የችግሮች ምንጩ ምንድን ነው? ክርስቲያኖች ችግሮችን እንዴት ማስወገድ ይችላሉ? በሕይወታችን ሁልጊዜ የሚከሰቱት ችግሮች መንስኤአቸው ኃጢአት ብቻ ነውን? ለችግሮቻችን መልስ ከየት እናገኛለን? በዚህ ክፍለ ትምህርት እነኚህንና ሌሎችን ጥያቄዎችን እንቃኛለን።

ለአንዳንድ ችግሮቻችን ግልጽና ሊያሳርፈን የሚችል ቀጥተኛ መልስ ላናገኝ እንችላለን። ይህም ባይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እኛ ለሚመጡት ለአብዛኛው ችግሮቻችን መመሪያን በመስጠት መፍትሔ ይሰጠናል፥ እንዲሁም ብዙ ችግሮቻችንን እንዴት እንደምናስወገድ ይጠቁመናል።

ክርስቲያኖች በችግሮች ተሸንፈው እንዲወድቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ወደ እርሱ ከመጣን፣ አቅጣጫን በመስጠት እንዲረዳን የችግር መፍትሔን፣ እንዲሁም ችግሮቻችንን በድል እንድናልፍ የሚያደርገን መንገድ አዘጋጅቷል።

ይህንን ትምህርት ስታጠና፥ አንተ ምታልፍበት የሕይወት ጎዳና የችግር መፍቻ መርሆዎችን ተጠቀምባቸው። ችግርህን እንዲረዳህ ለችግር ፈቺው ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈህ ከሰጠህ፥ አስደናቂ በረከትን ታገኛለህ። እንዲሁም በዚህ ትምህርት የተማርሃቸው መርሆዎች ችግር ያለባቸውን ሌሎችን ሰዎች ስታገለግል እንድትጠቀምባቸው ይረዳሃል።

የሕይወት ችግሮችን መፍታት - ክርስቲያናዊ መንገድ የተባለው ይህ ኮርስ ከክርስቲያናዊ አመለካከት አንጻር የችግር ምንጮችን፣ ችግርን የመፍታት ዘዴዎችንና መፍትሔ የሚገኝባቸውን መንገዶች የምናጠናበት ነው። ዋና ዋና የሕይወት ችግሮች በትምህርቱ ውስጥ ቀርበዋል። ከነዚህም መካከል በማህበራዊና በቤተሰብ ግንኙነት መካከል ያሉ ችግሮች ይገኙባቸዋል። የላጤነት፣ ከግብረ ሥጋዊነት ጋር የተያያዙና መከራና ሞትን የሚመለከቱ ችግሮችም ተካትተዋል። ለነዚህ ሁሉ ችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔ ተሰጥተዋል። ክርስቲያን ለራሱ ችግሮች መፍትሔ ለማግኘትም ሆነ

ሌሎች በችግር ውስጥ ያሉትን ለመርዳት የሚጠቀምባቸው መርሆዎች በትምህርቱ ውስጥ ተቀምጠዋል። የክርስቲያን እርግጠኛ ተስፋ የሆነውና ለችግሮች ሁሉ መፍቻ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በትምህርቱ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶበታል።

## የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

1. በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የችግር ምንጮች ምን እንዲሆኑ መግለጽ፤
2. ለችግሮችህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ላይ የተመሠረቱ የመፍትሔ መንገዶችን መግለጽ፤
3. በሕይወትህ ውስጥ ላሉ ችግሮች ትክክለኛ መፍትሔ ላይ ለመድረስ ሁለቱን የችግር ማቃለያ ዘዴዎች ማወቅና በሥራ ላይ ማዋል፤
4. ለአንድ ክርስቲያን ችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔዎች መስጠት።
5. ሌሎች ሰዎች ችግራቸውን በክርስቲያናዊ መንገድ እንዲመለከቱና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህን የተከተሉ መፍትሔዎችን እንዲፈልጉ መርዳት፤
6. ኢየሱስ ክርስቶስ ድል እንዲሰጥህና ድል አድራጊ እንዲያደርግህ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእርሱ መታመንና እርሱን ተስፋ ማድረግ መቻል አለብህ።

## የትምህርቱ አዘገጃጀትና የአጠናን ስልት

እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ይይዛል።

1. ርዕስ
2. መግቢያ
3. የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
4. የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች
5. የትምህርቱ ዝርዝር
6. ለጥናቱ የሚረዱ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች
7. የሙከራ ፈተና (ከትምህርቱ በስተመጨረሻ)
8. የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስና በመጽሐፉ መጨረሻም የሙከራ ፈተናዎች መልስ ቀርበዋል።



የትምህርቱ አከፋፈልና ዓላማዎች በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ሃሳብ ይሰጣሉ፤ ጥናቱን በምታጠናበት ወቅት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ነጥቦች ላይ እንድታተኩር ይረዱሃል።

በትምህርቱ ዝርዝር ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በዚህ የጥናት መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ክፍት ሥፍራዎችን በመሙላት ሊመለሱ የሚችሉ ናቸው። ሆኖም ረዘም ያሉ መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ መጻፍ ይገባል። መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ የምትጽፍ ከሆነ የጥናቱን ቁጥርና ርዕሱን መመዝገብህን እርግጠኛ ሁን።

የራስህን መልሶች ከመስጠትህ በፊት በመጽሐፉ የቀረቡትን መልሶች አትመልከት። የራስህን መልሶች የምትሰጥ ከሆነ ያጠናኸውን ጥናት በተሻለ ሁኔታ ትረዳዋለህ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን ከመለስህ በኋላ በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ። ከዚያ በኋላም በትክክል ያልመለስካቸውን አርማቸው። የቀረቡትን መልሶች በድንገት ተመልክተህ የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት እንዳትችል መልሶቹ የቀረቡት በቁጥር ቅደም ተከተል አይደለም። እነዚህ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በጥናቱ የቀረቡትን ዋና ዋና ሃሳቦች እንድታስታውስ ከመርዳቱም በላይ ከትምህርቱ ያገኘሃቸውን የሕይወት መርሆዎች ተግባራዊ እንድታደርግ ይረዱሃል።

# 1 ትምህርት

# የችግሮች ምንጭ

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል ልክ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት ነግሮአቸው ነበር። ከነገራቸውም ውስጥ አንዱ፣ "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16፡33) የሚል ነበር። ከዚያም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ በማለት ጸለየላቸው፣ "ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው . . . ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም" (ዮሐ. 17፡11፣ 15)።

በዓለም ውስጥ እስካለን ድረስ ችግሮች ይኖሩብናል። እነዚህ ችግሮች ከየት ይመጣሉ? እነዚህ ችግሮች እንዳይከሰቱ በመከላከል ረገድ ልናደርግ የምንችለው ምን ነገር አለ? እግዚአብሔርስ ለምን ክርስቲያኖች በመከራና በችግር እንዲሠቃዩ ይፈቅዳል?

በዚህ በክፍለ ትምህርት አንድ ውስጥ የችግሮቻችንን ምንጭ እና ለምን ሁላችንም ችግሮችን መጋፈጥ እንደሚገባን እንመለከታለን። ችግሮች ለምን እንደሚከሰቱ መረዳት የመፍትሔ መንገዶችን ለማግኘትና ችግሮቻችንን በክርስትና ሕይወት የበለጠ ለመጠንከር የተገኙ ዕድሎች አድርገን እንድንጠቀምባቸው ያስችለናል። ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠና በሕይወትህ ያሉትን ችግሮችና ምንጫቸውን አስብ። ምንጫቸውን ለይተህ ካወቅህ ወደ መፍትሔ መንገዝ ትችላለህ። እንዲሁም ችግሮቹን ለማስወገድ ይረዳሃል። ይህም ከሁሉ የበለጠ መፍትሔ ነው።



## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የኃጢአት ውጤት
- የውጭ ተፅእኖ ውጤት
- የራሳችን ምርጫ ውጤት
- እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ሃሳብ ውጤት

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- ኃጢአት የችግሮች ምንጭ ሊሆን የሚችልባቸውን ሦስት መንገዶች መግለጽ።
- ከቁጥጥራችን ውጭ በሆኑ ሁኔታዎች አማካይነት የሚከሰቱ ችግሮችን መዘርዘር።
- የግል ምርጫን በጥንቃቄ የማድረግን አስፈላጊነት መገንዘብ።
- በመከራና በችግር ውስጥ እንድናልፍ እግዚአብሔር ለምን እንደሚፈቅድ መግለጽ መቻል አለብህ።

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የመማሪያ መጽሐፉን መግቢያ እና የትምህርቱን ዓላማ በጥንቃቄ አንብብ።
2. የክፍለ ትምህርቱን መግቢያ፣ አከፋፈል እና ዓላማዎች አንብብ።
3. ዘፍጥረት 1፣ 2 እና 3ን አንብብ።
4. የክፍለ ትምህርቱን ዋና ክፍልና በውስጡ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ በማንበብ የተሰጡትን የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች ሙሉ መልስ።
5. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና ከወሰድክ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

# የኃጢአት ውጤት

*ዓላማ 1 የችግሮችን ዋነኛ መንስዔ ለይቶ ለማወቅ።*

## የአዳም ኃጢአት

አዳምና ሔዋን ፍፁም በሆነ ዓለም ውስጥ ፍፁማን ሰዎች ሆነው ነበር የተፈጠሩት (ዘፍ. 2)። ከእግዚአብሔር ጋር ፍፁም የሆነ ኅብረትም ነበራቸው፤ ችግሮችም አልነበሩባቸውም። ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን ለመታዘዝና ለማገልገል የሚያስችላቸውን የምርጫ ነፃነትና ሥልጣን ሰጥቶአቸው ነበር።

በዓለም ውስጥ የነበረው አንድ ክፉ ተጽዕኖ ኢየሱስ "ክፉው" ብሎ የጠራው ሰይጣን ነው (ዮሐ. 17፡15)። እርሱ በእባብ ተመስሎ በዔደን ገነት ነበር። ሰይጣን እንዴት በዔደን ገነት እንደተገኘ መጽሐፍ ቅዱስ ባይነግረንም እባብ (ሰይጣን) አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙ ለመፈተን ምን ያህል ክፉ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እናነባለን። ያለመታዘዛቸው በምድር ሁሉ ላይ ርግማን አመጣ። ምድርና የሰው ዘር ሁሉ በዚህ ኃጢአት ተበከሉ። የህመም፣ የመከራ፣ የችግር፣ የጥፋት፣ የልፋት መጀመሪያው ይህ ነው።

(1). ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እስካሁን ስለ ችግሮች ምንጭና ዋነኛ መንስዔ የተመለከትነውን እንደ ማጠቃለያ አሳብ የሚገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. የችግሮቻችን ሁሉ መንስዔ ሰይጣን ነው።
ለ. የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ነው።
ሐ. በምድር ሁሉ ላይ መርገምን ያመጡትና የችግሮች መጀመሪያ የሆኑት የሰይጣን ክፉ ተጽዕኖ እና የሰው አለመታዘዝ ናቸው።

## በኃጢአት የተበከለ ዓለም

*ዓላማ 2 በኃጢአት የተበከለ ዓለም ውስጥ ከመኖራችን የተነሳ ለሚከሰት ችግር ምሳሌ ለመስጠት።*

በኃጢአት ምክንያት በምድር ላይ የመጣው መርገም በዘፍ. 3፡16-19 ተመዝግቦአል። ሞት የዚህ መርገም ውጤት ነው። ከኃጢአት የተነሳ ምድር ፍፁም አይደለችም፤ ረሀብ፣ የጐርፍ መጥለቅለቅና የመሬት መንቀጥቀጥ የመሳሰሉ ጉዳቶች ሞልተውባታል። የምንመገበውን ምግብ ለማግኘት ከድርቅ፣ ከዱር አራዊት እና ከአንበጣዎች ጋር እንታገላለን። ሁላችን ገበሬዎች ባንሆንም ህልውናችን ከዚህ ትግል ጋር የተያያዘ ነው።



በኃጢአት ምክንያት አንዳንድ ህፃናት የአእምሮ ሕመምተኞች ወይም ሽባ ወይም በሌላ በሽታ የሚሠቃዩ ሆነው ይወለዳሉ።

(2). የምትኖርበትን አካባቢ አስብ፤ በኃጢአት ከተበከለ ዓለም የተነሳ የደረሰ ብህን ወይም በሌሎች ላይ ደርሶ ያየኸውን አንድ ችግር በምሳሌነት ስጥ።

## የራሳችን ኃጢአተኛ ባህርይ

*ዓላማ 3 ሰዎች በራሳቸው ኃጢአት ምክንያት የሚከሰቱትን ችግሮች ለማስወገድ ሲፈልጉ የሚወስዱትን አማራጭ ለመግለጽ።*

በሥነ ምግባር ብልሹነት የተያዘ የአንድ ትንሽ ልጅ ታሪክ ሰምተህ ይሆናል። እናቱ ለምን ጥፋት እንዳጠፋ በጠየቀችው ጊዜ የመለሰላት መልስ "እንዳጠፋ ያደረገኝ ሰይጣን ነው!" የሚል ነበር። ለችግሮቻችን ሁሉ ሰይጣንን መውቀስና እርሱን ተጠያቂ ማድረግ ቀላል ነው፤ ሐቁ ግን የአብዛኞዎቹ ችግሮቻችን መንስዔ የራሳችን ኃጢአተኛ ባህርይ መሆኑ ነው።

እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ የምንመርጥበት ኃይል ተሰጥቶናል። ኃጢአትን ስንሠራ በራሳችን የግል ምርጫ ነው፤ ለኃጢአታችንም በግል ኀላፊነት አለብን። በሮሜ 5፡12 እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን፤ "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ . . ."

(3). ኢሳ. 53፡6፣ ኢሳ. 64፡6፣ ምሳ. 20፡9፣ ሮሜ 3፡23 እና 1 ዮሐ. 1፡8ን አንብብ። ከሚከተሉት ውስጥ በነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍሎች ውስጥ የተደጋገመውን መልዕክት አጠቃሎ የያዘው ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ. አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች የበለጠ ኃጢአተኞች ናቸው።
ለ. ለራሳችን የኃጢአተኛ ባህርይ ኃላፊና ተጠያቂ አዳም ነው።
ሐ. ሰው ሁሉ የሚወለደው የኃጢአት ባህርይ ይዞ ነው፤ ለሚሠራውም ኃጢአት በደለኛ ነው።

እያንዳንዳችን ስንወለድ ኃጢአት የመሥራት ባህርይ ይዘን እንደሆነና መልካም እና ክፉ ለማድረግ ባለን ምርጫ ተጠያቂዎች እንደሆንን እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በግልጽ ያስረዳሉ። ከችግሮቻችን አብዛኞዎቹ የሚከሰቱት በሠራናቸው ኃጢአቶች፣ እንደ ቀልድ በተናገርናቸው ቃላት ወይም ራስ ወዳድነት፣ በድፍረት ኃጢአት መሥራት፣ ስስት፣ ቅናት፣ ወዘተ በመሳሰሉት ክፉ ዝንባሌዎች አማካይነት ነው።

በአንድ ወቅት ኢየሱስ ለረጅም ጊዜ ሕመምተኛ የነበረን ሰው ከፈወሰ በኋላ የተናገረውን በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ እናገኘዋለን። ኢየሱስ ይህን ሰው

በቤተ መቅደስ አግኝቶት የሰጠው ምክር እንዲህ የሚል ነበር፤ "እነሆ፥ ድነሃል ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትስራ" (ዮሐ. 5፡14)። በዚህ ሁኔታ የሰውየው ሕመም መንስዔ የራሱ ኃጢአት ነበር።

ጉጂ በሆኑ ሐሽሽ ወይም ሲጋራ፣ ከመጠን በላይ በመብላት እና በመጠጣት፣ በሥነ ምግባር ጉድለት፣ ወይም በሌሎች የኃጢአት ሥራዎች ሰውነታቸውን የሚጎዱ ሰዎች አደገኛ የሆነ አካላዊ ችግር ሊከሰትባቸው ይችላል። እግዚአብሔርን እና ቃሉን ባለመታዘዝ ኃጢአት ስንሠራ፣ የቤተሰብ መበታተን፣ ከሰዎች ጋር መጋጨት፣ ሐዘን፣ መከራ፣ ሕመም፣ ሞትም እንኳን በራሳችን ላይ ልናስከትል እንችላለን። ሮሜ 6፡23 "የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው" በማለት ይህን አሳብ እንድናስተውለው ያደርገናል። ይህ ክፍል የሚናገረው ደግሞ የሥጋን ሞት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊውንም ሞት ጭምር ነው፤ ይህም መንፈሳዊ ሞት ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ለችግሮቻችን የምንሰጠው ምላሽ ራሱ ሌላ ተጨማሪ ችግር ሊፈጥር ይችላል። መጥፎ አመለካከት ወይም የማጉረምረም መንፈስ ለችግሮቻችን የምንሰጣቸው ትክክለኛ ያልሆኑ ምላሾች ናቸው። በዚህ ጊዜ ችግሮቻችን ሊያሸንፉንና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንንም ግንኙነት ሊያሳጡን ይችላሉ። ወደፊት በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ቀና አመለካከት ችግሮቻችንን ወደ ድል እንድንለውጥ ይረዳናል፤ ውጤቱም መንፈሳዊ እድገት ይሆናል።

(4). በራሳችን ኃጢአት ምክንያት የተከሰቱብንን ችግሮች ለማስወገድ ምን ማድረግ እንችላለን?

በምድር ላይ ከኃጢአት ነፃ እና ፍፁም የሆነ ሕይወት በመኖር ከኃጢአት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ችግሮች ሁሉ ማስወገድ ይቻላል ብሎ ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው። ይህንን የራስህ ሕይወት በራሱ ሊነግርህ ይችላል። ምንም እንኳን ፍፁም ለመሆን በመሞከር በኃጢአት ላይ ድልን እየተቀዳጀህ ቢሆን፤ አሮጌው ኃጢአተኛ ባህሪህ አንዳንድ ጊዜ ብቅ እያለ ሊጥልህ ይችላል። በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከውድቀትህ የሚመነጩ ችግሮች ሊገጥሙህ ይችላሉ። የሚያስገርመው ድንቅ እውነት ግን፥ ኃጢአትን ብንሠራ እንኳን እግዚአብሔር ይወደናል፤ በኃጢአታችን ስንናዘዝና ለእርዳታም ወደ እርሱ ስንጮህ ለችግሮቻችን መፍትሔ እንድናገኝ ይረዳናል።

ወደ ኋላ በምናገኛቸው ትምህርቶች ኃጢአት እንዴት ችግሮችን እንደሚፈ ጥርና እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ወይም ለመቋቋም ምን ማድረግ እንደ ምንችል እንመለከታለን።



## የውጭ ተጽእኖ ውጤት

*ዓላማ 4 ከቁጥጥርህ ውጭ በሆነ የውጭ ተጽእና አማካይነት የሚከሰቱ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅ።*

የሰው ልጅ ችግሮች ከኃጢአት የሚመነጩ እንደሆኑ ተመልክተናል። በኃጢአት ምክንያት በተበከለ ዓለም ውስጥ እንኖራለን። ኃጢአት በዓለም ሁሉ ላይ መርገምን አምጥቷል። የሰይጣን ተፅእኖም በዓለም ውስጥ ምስቅ ልቅል ሕይወትን፣ ግራ መጋባትን፣ ችግርን እና ተስፋ ማጣትን አምጥቷል። ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ባህርይ ይዞ ነው የተወለደው (ሮሜ 3፡23)።

ይህ ማለት ታዲያ ሁልጊዜ ለችግሮቻችን መንስዔ የሚሆነው የራሳችን ኃጢአት ነው ማለት ነው? በፍፁም! የብዙ ችግሮቻችን መንስዔዎች ከቁጥጥራችን ውጭ የሆኑ ናቸው። ከእነዚህ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### የተፈጥሮ አደጋዎች

"ታይታኒክ" ተብላ የምትጠራው የእንግሊዝ መርከብ እ.ኤ.አ. በ1912 ዓ.ም. በተሠራች ጊዜ የሚወዳደራት ሌላ መርከብ አልነበረም፤ በዓለም ትልቋ መርከብ ነበረች። ኤክስፐርቶችም መርከቧ እንደማትሰጥም ተናግረውላት ነበር። ነገር ግን በዚያው ዓመት ሚያዚያ 14 ቀን 1912 ዓ.ም. የመጀመሪያ ጉዞዋን ከእንግሊዝ ወደ አሜሪካ በማድረግ ላይ እንዳለች ከበረዶ ክምር ጋር ተጋጭታ ሰጠመች። በውስጧ ከነበሩት 2200 ተጓዦች 1500ዎቹ ለሞት በቁ። በረዶው መርከቧን ለማስጠም የሚያበቃ ቀዳዳ ከ3 ደቂቃ ባነሰ ጊዜ አስከትሎ እንድትሰጥም ያደርጋታል ብሎ ማንም አልገመተም።

በዚህ አደጋ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉትን ችግሮች አስብ። የሚወዷቸውን በዚህ አደጋ ያጡ ብዙ ክርስቲያኖች እንደነበሩ ጥርጥር የለውም። ይህ አደጋ ያስከተላቸው ሐዘን፣ መከራ፣ ህመም፣ ወዘተ ከራስ ኃጢአት ጋር አይገናኙም፤ የተፈጥሮ አደጋ ያስከተላቸው ናቸው እንጂ።

የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ አውሎ ነፋስ፣ ወይም ረሃብን የመሰሉ አደጋዎች አጋጥመውህ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በቤተሰብህ ውስጥ ሞት፣ የአእምሮ መቃወስ፣ የገንዘብ እጦት ወይም ከቁጥጥርህ ውጭ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች ገጥመውህ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ የነዚህ ችግሮች ዋነኛ መንስዔ አዳምና ሔዋን በዔደን ገነት በሠሩት ኃጢአት አማካይነት በምድር ላይ የመጣው መርገም ነው። ነገር ግን በግል የሰራነው ኃጢአት ውጤት አይደሉም። እውነተኛ ክርስቲያኖችም ሆኑ የማያምኑ ሰዎች በኃጢአት በተረገመ ዓለም ውስጥ በመኖራቸው ብቻ ችግር እንደሚገጥማቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳል።

ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን መስጠት ይቻላል። በዳንኤል 3 ምንም እንኳን ውሳኔ አቸው ለሞት የሚያበቃ ቢሆንም፥ ንጉሡ ላቆመው የወርቅ ምስል ላለመስገድና እርሱንም ላለማምለክ ውሳኔ ስላደረጉት ሦስት ዕብራውያን ታሪክ እናነባለን። ንጉሡ እምቢተኛነታቸውን በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጥቶ ምክንያታቸውን እንዲገልጹ ጠየቃቸው። የእነርሱም ምላሽ ይህ ነበር።

"ናቡከነፆር ሆይ፥ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ" አሉት (ዳን. 3፡16-18)።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከሞት አድኖአቸው ኃይሉን አስመስክሮአል። እነዚህ ሦስት ሰዎች ግን እግዚአብሔርን ካለመታዘዝ ይልቅ ሞትን መርጠው ነበር!

ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ ስደት ቢበዛበትም ወንጌልን መስበክ ምርጫው አድርጎ ነበር። በአንድ ወቅት በልስጥራ ይሰብክ በነበረ ጊዜ ሕዝቡ ተቆጥተው ጳውሎስን ወገሩት፤ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጐተቱት (የሐዋ. 14፡19)።

(9). የሐዋ. 14፡20-21ን አንብብ። ጳውሎስ ከተወገረና እንዲሞት ከተተወ በኋላ ምን አደረገ?

(10). በዚያ ላሉት ደቀ መዛሙርት የጳውሎስ መልዕክት ምን ነበር (የሐዋ. 14፡22)?

ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን ስደት የሚያመጣበት ቢሆን ምርጫው ወንጌልን መስበክ ነበር። በዚህም ምክንያት ለረጅም ጊዜ በእስር ቤት ቆየ። በመጨረሻም ወንጌልን በሚጠሉ ሰዎች ተገደለ። በፊልጵ. 1፡12-14 ያሉት የጳውሎስ ቃላት ምን ያህል ደስ የሚያሰኙ ናቸው!

> ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። ስለዚህም እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንዲሆን በንጉሥ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገልጦአል፥ በጌታም ካሉት ወንድሞች የሚበዙት ስለ እስራቴ ታምነው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲነግሩ ያለ ፍርሃት ከፊት ይልቅ ይደፍራሉ።

የቤተክርስቲያን ታሪክ ክርስቲያናዊ ምስክርነታቸውን ከመተው ይልቅ መከራንና ሞትን ስለመረጡ ክርስቲያኖች ብዙ ምሳሌዎች ይሰጠናል። እንደ ጂም ኤሊየት ያሉ ሚሲዮናውያን እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ጂም ኤሊየት በደቡብ አሜሪካ ለሚገኙና አውካ ኢንዲያንስ ለሚባሉ ለአንድ



ጐሣ ወንጌልን ይዞ የሄደ ቢሆንም በእነርሱ እጅ ለህልፈተ ሕይወት በቅቷል። ጂም ከመሞቱ አጭር ጊዜ አስቀድሞ በጻፋቸው ቃላት ምርጫውን በግልጽ አስቀምጦአል።

*"ሊያጣው የማይችለውን ለማትረፍ ሲል ሊያቆየው የማይችለውን የሚሰጥ ሞኝ አይደለም።"*

ጂም ኤሊየት ከምድራዊ ጥቅም ይልቅ ዘላለማዊውን ለመምረጥ ፈቃደኛ ነበር። በጂም ሞት ምክንያት ሚስቱ ኤልዛቤት ከራቼል ሴይንት ጋር (ራቼል ሴይንት፥ ኔት የተባለ ወንድሟ ከጂም ኤሊየት ጋር የተገደለባት ሴት ናት።) የአውካ ጐሣ ነዋሪዎችን ማገልገል ቀጥለው ነበር። ከእነርሱም የሚበዙት ከእነዚህ ከተሰጡ ሴቶች ምስክርነት የተነሳ ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው ተቀበሉ።

> "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል" (ዮሐ. 12፡24-25)።

(11). ከሚከተሉት ውስጥ ችግር እንኳን የሚያስከትል ቢሆን መልካም ምርጫ ነው ብለህ የምታስበውን ከፊት ለፊቱ ያለውን ፊደል በማክበብ አመልክት።

ሀ. ጓደኛህ ወንጀል ፈጽሞ አንተ ግን ወንጀሉ በተፈጸመ ሰዓት ጓደኛህ ከአንተ ጋር እንደነበረ በመናገር እርሱን ለማዳን መረጥህ።
ለ. ልጅቷን በጣም ትወዳታለህ፤ ሆኖም ካላመነች ልጅ ጋር ጋብቻ ወደመፈጸም እንዳይመራህ ግንኙነታችሁን ለማቋረጥ ወሰንህ።
ሐ. ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ አሠሪህን ፈቃድ ከመጠየቅ ይልቅ ዘወትር እሁድ ለመሥራት ወሰንህ።
መ. የሚቀልዱብህ ያላመኑ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ከመመገብህ በፊት አንገትህን ዝቅ አድርገህ ስለምግብ እግዚአብሔርን ለማመስገን ወሰንህ።
ሠ. ጠቃሚ የሆኑ እውነታዎችን ሳታውቅ ውሳኔ ወሰንህ።

## እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ሃሳብ ውጤት

*ዓላማ 7 ሰይጣን እኛን የሚፈትንበትን ዓላማና እግዚአብሔር እኛን የሚፈትንበትን ዓላማ ልዩነት ለመግለጽ።*

ለምንድን ነው መልካም የሆኑ ሰዎች እንዲሠቃዩ እግዚአብሔር የሚፈቅደው? ለእኛ በእውነት ግድ የሚለው ከሆነ ለምን ከችግሮቻችን

አይታደገንም? ልትሸከመው የማትችል የሚመስል መከራ በደረሰብህ ጊዜ እንዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ጠይቀህ ታውቃለህ?

እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ከመከራችን ይታደገናል። ሦስቱን ዕብራውያን ሰዎች ከሚነድ ከእቶን እሳት እንዴት እንዳዳናቸው ተመልክተናል። አንተም ተአምራዊ ፈውስን ከእግዚአብሔር አግኝተህ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ የሚያስፈልግህን ለማሟላት እግዚአብሔር ባልተጠበቀ እና ሊገለጽ በማይችል መንገድ ጐብኝቶህ ይሆናል። ይህ ሲሆን ደስታችን ወደር የለውም፤ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ መከራ ወደኛ እንዲመጣ እንደሚፈቅድ ደግሞ በሚገባ እናውቃለን። ይህን የሚያደርገው በመከራችን ስለሚደሰት ሳይሆን ለእኛ ግድ ስለሚለውና የእርሱ ሃሳብ ከእኛ ጊዜያዊ ፈተና ባሻገር ስለሚሆን ነው። ችግሮች በሕይወታችን ያልፉ ዘንድ ለምን እንደሚፈቅድ እስቲ አንዳንድ ምክንያቶችን እንመልከት።

## እኛን ለማጥራት እና እምነታችንን ለማረጋገጥ

አንድ ያረጀ የባቡር ሐዲድ ድልድይ ነበረ ይባላል። ድልድዩ ባቡር በላዩ ላይ ቢሄድበት የሚፈርስና አደጋ የሚያስከትል በመሆኑ አንድ ኩባንያ ምቹ እና ጠንካራ አድርጐ እንደገና ሠራው። ሥራውም ሲጠናቀቅ የምረቃ በዓል ተዘጋጀ። በበዓሉ ላይ ከተከናወኑት ድርጊቶች መካከል ዋናው በዚያ ድልድይ ላይ ሁለት ባቡሮችን በአንድ ጊዜ ማስተላለፍ ነበር። ይህ እንዲከናወን ባለሥልጣናቱ ሲወስኑ ድልድዩን ለማፍረስ ፈልገው ይመስልሃል? በፍጹም! ዓላማቸው ድልድዩ አሁን በጣም ጠንካራና የማይፈርስ መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር።

እዚህ ጋ በጣም ጠቃሚ የሆነ አንድ ነጥብ አለ። እግዚአብሔር እኛን በክፉ ይፈትነናል? በፍጹም! ሰውን ክፉ ነገር እንዲያደርግ መፈተንና መልካሙን ከእርሱ ለማውጣት መፈተን ሁለቱ በጣም የተለያዩ ናቸው።

(12). *ያዕቆብ* 1:2-4 እና 12-17ን እንብበህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. ክርስቲያን መከራን እንዴት መጋፈጥ አለበት?
ለ. ለምን ይህ አመለካከት ሊኖረው ይገባል?
ሐ. እግዚአብሔር በክፉ ይፈትነናል?
መ. ለምንፈጽመው ክፉ ድርጊት ተጠያቂው ማነው? (ዮሐ. 17:15ን ተመልከት)።

"በመከራችሁ ጊዜ ደስ ይበላችሁ" የተባልንበት ምክንያት አለ። ይኸውም በነህምያ 8:10 ይገኛል፣ "የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ" በጌታ በእግዚአብሔር ያለን ደስታ ነው እንድንፀና እና በችግሮቻችን ላይ ድልን እንድንቀዳጅ ኃይል የሚሆነን።



(13). 1ጴጥ. 1:6-7ን አንብብ። ይህ ክፍል በማንኛውም ዓይነት መከራ ውስጥ ደስ እንዲለን ይነግረናል። የእነዚህ መከራዎች ዓላማ ምንድን ነው?

ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ወርቅ በእሳት ተፈትኖ እንደሚጠራ ይጠቁማል። እምነታችን ከወርቅ እጅግ የላቀ ዋጋ ያለው ነው፤ ዋጋው ዘላለማዊ በመሆኑም በምናልፍባቸው መከራዎች የጠራና የከበረ ነው።

እግዚአብሔር እንድንፈተን እንኳን ቢፈቅድ እርሱ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል። በ1ቆሮ. 10:13 እነዚህን እናገኛለን፦

1. እግዚአብሔር ለመጽናት እና በታማኝነት ለመቆየት ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አይፈቅድም።
2. በመከራችን እንድንታገሥ ኃይል ይሰጠናል።
3. የመውጫውን መንገድ ወይም መፍትሔውን ያዘጋጅልናል።

(14). እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ግለጽ።

ሀ. ሰይጣን ሲፈትነን ዓላማው ምንድነው?
ለ. እግዚአብሔር ሲፈትነን ዓላማው ምንድነው?

## ክርስቶስን እንድንመስል

*ዓላማ 8 ከችግሮቻችን ጋር በተገናዘበ መልኩ የሮሜ 8:17፣ 28-29ን መልዕክት ለማወቅ።*

የእግዚአብሔር ፍላጐት እኛ ኢየሱስን እንድንመስል ነው። በዚህ ምድር ላይ የምንኖረው ኑሮ በሰማያዊ መንግሥት ለምንኖረው ዘላለማዊ ሕይወት ዝግጅት ነው። እግዚአብሔርም በክርስትና ሕይወታችን የበሰልን እንድንሆን እና ልጁን እንድንመስል ሊረዳን ዝግጁ ነው። በቀና መንገድ ችግሮቻችንን የምንጋፈጥ ከሆነ የክርስቶስን ባህርይ በእኛ ውስጥ ለማሳደግ እግዚአብሔር በመልካም ይጠቀምባቸዋል።

በሞት አፋፍ ላይ የነበረ ዘመዳቸውን ለረጅም ጊዜ የመንከባበከብ ኃላፊነት የነበረባቸውን ሁለት ሴቶች አስታውሳለሁ። አንደኛዋ መራራና አጉረምራሚ ነበረች። በአጠገቧ ሊሆን የሚፈልግ ማንም አልነበረም። ሌላኛዋ ደግሞ ምንም እንኳን ችግሩ ለመሸከም ከባድ ቢሆንም፣ ታጋሽ፣ የፍቅር ሰው እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ከእግዚአብሔር ለሚገኘው ጸጋ ምስክር ነበረች። ችግሯን ወደ ድል የለወጠች ሴት ነበረች።

(15). ሮሜ 8:17፣ 28-29ን አንብበህ የሚያስተላልፉትን መልዕክት በትክክል የሚገልጹትን ዐረፍተ ነገሮች ከሚከተሉት ውስጥ ምረጥ።

ሀ. እግዚአብሔርን የምንወደው ከሆነ፣ መልካም ነገሮች ብቻ እንዲገጥሙን ያደርጋል።
ለ. ጌታን የሚወዱ እና ምሪትም እንደሚሰጣቸው በእርሱ የሚታመኑ ሰዎች ከሚያልፉበት ፈተና መንፈሳዊ ጥቅም ያገኛሉ።
ሐ. ክርስቶስን የመምሰል ሂደት አንዱ ክፍል በመከራው መካፈል ነው።
መ. የሚገጥሙንን ችግሮች ወደ መልካም በመለወጥ ውስጥ ያለው የእግዚ አብሔር ዓላማ ልጁን እንድንመስል ማድረግ ነው።

ጳውሎስ በ2ቆሮ. 4፡7-10 ይህንን አሳብ በጥሩ ሁኔታ ገልጾታል፦

> ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤ በሁሉ እንገፋለን እንጂ እንጨነቅም፣ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፣ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፣ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፣ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን።

ሳንጨነቅ፣ ተስፋ ሳንቆርጥ ወይም ሳንጠፋ ሸክማችንን መሸከም የሚያስችለን በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ዓላማውም ኢየሱስ በእኛ ውስጥ ይገለጥ ዘንድ ነው! እንዴት ያለ ታላቅ ድል ነው!

## ሌሎችን መርዳት ለማስቻል

***ዓላማ 9 መከራችን ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለን ግንኙነት እንዴት እንደሚጠቅም ለመግለጽ።***

እግዚአብሔር እኛ መከራን እንድንቀበል የሚፈቅድበት ሌላው ምክንያት ሌሎችን በተሻለ ሁኔታ ለመርዳት ዝግጁ እንድንሆን ነው። ብቸኝነትን የቀመሰ ሰው ብቸኝነት ያጠቃቸውን ሰዎች ማጽናናት ይችላል። ልጁ በሥቃይ ውስጥ ያለፈ ወላጅ፣ ልጆቻቸው ለሚሰቃዩባቸው ወላጆች የሚናገረው ርኅራኄ ይህ ነው አይባልም። እኛ ባለፍንበት መከራ የሚያልፉ ሰዎችን ስናገኝ በእነርሱ ቦታ ራሳችንን አስቀምጠን ስለምንገኝ ከእነርሱ ጋር መሆን አይከብደንም። እኛ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበርንበት ወቅት ያየነው የእግዚአብሔር ኃይል እና የቀመስነው በረከት ሌሎች ተስፋ ሳይቆርጡ ወደ እርሱ እንዲመለከቱ ምስክር ይሆናል።

ይህን አሳብ ጳውሎስ በ2ቆሮ. 1፡3-4 እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦

> የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽና ናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።



(16). ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል የሚያሳየው ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ነው?

ሀ. እኛ ባለፍንበት ዓይነት መከራ ውስጥ የሚያልፉትን ልንረዳቸው እንችል ዘንድ እግዚአብሔር ሆን ብሎ በእኛ ላይ መከራ ያመጣል።
ለ. እግዚአብሔር በመከራችን ስለ እኛ ግድ ይለዋል፤ ለሌሎችም በመከራ ውስጥ ላሉ እኛ ግድ እንዲለን ይፈልጋል።

## በእርሱ ላይ መደገፍን ሊያስተምረን

ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ኃይል እና እርዳታ ባይኖር ኖሮ ተሸክመውት የነበረውን መከራ ብቻቸውን ሊሸከሙት እንደማይችሉ ሲናገሩ ሰምቼአለሁ። በ1ጴጥ. 5፡7 ይህ አሳብ በአጽንኦት ተገልጾ እናገኘዋለን፦ "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት"

ሐዋርያው ጳውሎስ በመከራ ውስጥ ያለውን ጥቅም ለይቶ በማወቁ በ2ቆሮ. 1፡8-10 እንዲህ ብሏል፦

> በእስያ ስለ ደረሰብን መከራችን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ ዘንድ እንወዳለንና፤ ስለ ሕይወታችን እንኳ ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ከዓቅማችን በላይ ያለ ልክ ከብዶብን ነበር፤ አዎን፥ ሙታንን በሚያነሣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እንዳንታመን፥ እኛ ራሳችን የሞትን ፍርድ በውስጣችን ሰምተን ነበር። እርሱም ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፥ ያድነንማል፤ . . .

ጳውሎስ ባለፈባቸው መከራዎች ውስጥ ብቻ ሳይሆን ገና ወደፊት ሊገጥመው በሚችል አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን የተማረ ነበር።

(17). 2ቆሮ. 1፡8-10ን ከ1ቆሮ. 10፡13 ጋር በማወዳደር በአጽንኦት የተገለጸውን እውነት ጻፍ።

(18). መከራ ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለን ግንኙነት እንዴት ሊጠቅም እንደሚችል ግለጽ።

(19). በአሁኑ ሰዓት ያሉብህን ችግሮች ጊዜ ወስደህ አስብና በዝርዝር ጻፋቸው። ይህን ክፍል ትምህርት በመጠቀም የእያንዳንዱን ችግር ምንጭ ለይተህ ለማወቅ ሞክር፤ በእያንዳንዱም ችግር ትይዩ ምንጩን ጻፍ። ወደሚቀጥለው ክፍል ትምህርት ስንሸጋገር ለችግሮችህ መፍትሔዎችን የማገኛ ዘዴዎችን ማየት ትጀምራለህ።

7. ሐዋርያው ጳውሎስ እና ጂም ኤሊየት ከሁሉ በላይ ግድ ሊለን የሚገባን ________________ እንደሆነ ምስክሮች ናቸው።

ሀ. የግላችን ደስታ
ለ. ዘላለማዊ ዋጋዎች
ሐ. ችግሮችን ማስወገድ
መ. ፍላጐታችንን ማሟላት

8. መጽናት ማለት

ሀ. ችግርን ማስወገድ ማለት ነው።
ለ. በዓላማ መቀጠል እና እጅ አለመስጠት ማለት ነው።
ሐ. በራስ ጥረት ችግርን ማቃለል ማለት ነው።
መ. ለሰይጣን ፈተና እጅ መስጠት ማለት ነው።

9. እግዚአብሔር እኛን በመፈተን ውስጥ ያሰውን ዓላማ የማይገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. ይበልጥ ክርስቶስን እንድንመስል ማድረግ
ለ. ማጥራት
ሐ. ክፋት እንድናደርግ ይፈትነናል
መ. ማንጻት

10. የሚከተሉትን የችግር ምንጮች በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በመጻፍ ከታች ከቀረቡት ችግሮቹ ጋር አዛምድ፦

1. በኃጢአት የተበከለ ዓለም
2. የግል ኃጢአት
3. የውጭ ተጽዕኖ
4. የተሳሳቱ ውሳኔዎች
5. በጥንቃቄ የተወሰዱ ምርጫዎች
6. እግዚአብሔር በእኛ ሕይወት የሚያደርገው

____ሀ. "ያንን ሥራ ላለመሥራት ስወስን ትክክል የሆንኩ መስሎኝ ነበር፤ አሁን ግን ሳየው ትክክል አልነበርኩም፣ ምክንያቱም አሁን የምሠራበት መሥሪያ ቤት ሊዘጋ ነው"።
____ለ. "አሁን በሕመም ላይ ስሆን፣ የግል የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜዬን ዘንግቼው እንደነበር ተረዳሁ"
____ሐ. "የሚያሰክር መጠጥ ጠጥቶ ሲያሽከረክር አደጋ ደረሰበት"
____መ. "ለክረምት አዲስ ኮት ያስፈልገኛል፤ ነገር ግን ያጠራቀምሁትን ገንዘብ ለአንድ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቼ በእርዳታ ለመስጠት ተጠቀምሁበት።"
____ሠ. "በፈተና ሰዓት በማጭበርበሩ ምክንያት ትምህርቱን እንዳይቀጥል ተደረገ።"
____ረ. "በመንደራችን በተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን አጡ።"
____ሰ. "የመንደሩ ሰዎች በሙሉ ኮሌራ በተባለው የተስቦ በሽታ ሞቱ።"



# የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

10. "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል።"

1. ሐ

11. "ለ" እና "መ" ጥሩ መልሶች ናቸው። "ለ" ምን እንኳን ዋጋ ቢያስከፍል፤ ወደ እግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ይመራናል። "መ" እግዚአብሔርን ማክበር ያሳያል። ለእርሱ ያለንን ፍቅር ይመሰክራል።

2. የአንተ መልስ። በኔ አካባቢ ያለ ምሳሌ ለመጥቀስ ሰዎች በከባድ በሽታዎች ይጠቃሉ።

12. ሀ. በደስታ
 ለ. በጽናት ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲመጣ። (ጽናት ማለት በዓላማ መቀጠል እና እጅ አለመስጠት ማለት ነው። ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍል እንኳን ለክርስቲያን በክርስቲያናዊ ልምምድ በታማኝነት መቀጠል ማለት ነው።)
 ሐ. በጭራሽ!
 መ. እኛ ራሳችን (ያዕ. 1:14) "እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።"

3. ሐ

13. እምነታችን ተፈትና እውነተኛነቱ እንዲረጋገጥ።

4. እግዚአብሔርን እና ቃሉን መታዘዝ።

14. ሀ. ክፋትን እናደርግ ዘንድ ምክንያት መሆኑ፥ መውደቅ
 ለ. እንድንጸና፥ የእምነታችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ

5. ጦርነት፣ ረሃብ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ስደት፣ ሞት

15. ሀ. ሐሰት ለ. እውነት ሐ.እውነት መ. እውነት

6. በ"ሀ"፣ "ሐ"፣ "ረ" እና "ሰ" የቀረቡት ትክክለኛ መልሶች ናቸው። በ"ለ"፣ "መ" እና "ሠ" የቀረቡት መልሶች የግል ኃላፊነትን የመዘንጋት ሁናቴዎች ይታይባቸዋል።

16. ለ

7. ጥንቃቄ እና ማስተዋል የጐደለው ምርጫ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- በቅድሚያ ኃጢአትን አስወግድ
- መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያህ ይሁን
- ሌላ ረጂ ምንጮችህን ተጠቀም

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

**ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ**

- እያንዳንዱ ሰው እንዴት ከኃጢአት ችግር መፍትሔ እንደሚያገኝ መግለጽ፤
- ኢየሱስ ክርስቶስና ሌሎች የአዲስ ኪዳን አስተማሪዎችን ትምህርት ከአስርቱ ትዕዛዛት ጋር ማወዳደርና፥ ይህንንም ችግርን መፍትሔ ከመስጠት ጋር ማዛመድ፤
- ችግርን መፍትሔ ለመስጠት እግዚአብሔር የሰጠህን የተለያዩ ምንጮች መጠቀም መቻል አለብህ።

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1. ዘጸ. 20፡1-17 እና ማቴ. 5-7ን አንብብ፤ በክፍለ ትምህርቱ ውስጥም የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍሎች ሁሉ አንብብ።
2. በክፍለ ትምህርት አንድ ላይ የተሰጡትን መመሪያዎች ተጠቀም።
3. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና ከወሰድህ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።





# በቅድሚያ
# ኃጢአትን አስወግድ

*ዓላማ 1 የኃጢአትን ችግር ለማስወገድ የተሰጡትን መመሪያዎች ከራስህ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ።*

በክፍለ ትምህርት አንድ ሁላችን ኃጢአትን እንደሠራን፣ አንድም ጻድቅ እንደሌለና ለኃጢአታችንም ተወቃሾች መሆናችንን የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አንብበናል። የኃጢአት ደሞዝ ደግሞ ሞት (ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት) እንደሆነም አይተናል።

ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ችግር መፍትሔ ለመፈለግ ስንዘጋጅ በቅድሚያ የኃጢአትን ችግር ማስወገድ የመጀመሪያ ተግባር እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። ለዚህ ደግሞ ብቸኛው መንገድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ቀርቦ ኃጢአትን በመናዘዝ፣ በማመንና ከእርሱ ይቅርታን በመቀበል ነው። በመታዘዝም ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት ጤናማ ማድረግ እንችላለን።

**መናዘዝ**

(1). 1ዮሐ. 1፡9 እና ሮሜ 10፡9-10ን አንብበህ አንድ ኃጢአተኛ መናዘዝና መመስከር ያለበት ምን እንደሆነ ጻፍ።

(2). ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ስንናዘዝ ምን ይሆናል?

ኃጢአትን መናዘዝ ኃጢአተኞች መሆናችንን ማመንን፣ በኃጢአታችን መጸጸትንና ኃጢአት መሥራትን ለማቆም መስማማትን ያካትታል። በተጨማሪም ክርስቶስ የሕይወታችን ጌታ እንዲሆን መፈለጋችንን ያመለክታል።

**እምነት**

(3). አንድ ኃጢአተኛ ምን ማመን አለበት? (ሮሜ 10፡9ን ተመልከት)

በክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ እግዚአብሔር ሰውን የመዋጀትና ከእርሱም ጋር ኅብረት እንዲኖረው የማድረግ ዓላማውን አጠናቋል። ክርስቶስ የኃጢአታችን ማስተሰርያ ሆኖአል። ትንሣኤውም የዚህ ዕቅድ ዋና ክፍል ነው። በ1ቆሮ. 15፡17፣ 21-22 እንዲህ እናነባለን፦

> ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ። . . . ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆናአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።

ክርስቶስ ሞትን ድል ነሥቶ እና መቃብርን ፈንቅሉ እንደተነሣ ስናምን የኃጢአታችንን ይቅርታ የምንቀበልበትንና ኃጢአትንም ድል የምንነሣበትን መንገድ እግዚአብሔር እንዳዘጋጀልን ማመናችን ጭምር ነው። ፈተናን እንድንቋቋም እና በቅድስና እንድንኖር እኛን መርዳት የሚችል ኃይል እግዚአብሔር እንዳለው እናምናለን። ከዚህም በላይ በእርሱ ላይ በንደገፍ ሕይወታችንን እንደሚመራ እና ከእርሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር እንደሚያዘጋጀን እናምናለን።

(4). የክርስቶስ ትንሣኤ ለደኅንነታችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (ከአዳም ኃጢአት ጋር በተገናዘበ መልኩ መልስ)

## መታዘዝ

ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን ፍቅር የምናሳይበት መንገድ እርሱን እና ቃሉን መታዘዝ እንደሆነ ግልጽ ነው። ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ የመታዘዝን አስፈላጊነት በአጽንኦት ይነግራቸው ነበር።

> "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ . . . ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ . . . የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤" (ዮሐ. 14:15፣ 21፤ 23)።

(5). ለኃጢአትህ ችግር መፍትሔ አግኝተሃል? በሠንጠረዡ ውስጥ በተሰጡት መመዘኛዎች ራስህን ፈትን።

| | | እዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| ሀ | ሰው ሁሉ፥ እኔም ጭምር ኃጢአተኛ እንደሆንኩ እውቃለሁ። | | |
| ለ | ኃጢአቴን በእግዚአብሔር ፊት ተናዝዤአለሁ። | | |
| ሐ | ኢየሱስ ጌታዬ እንደሆነ መስክሬአለሁ። | | |
| መ | ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ እና ትንሣኤውም በኃጢአት፣ በሞት እና በመቃብር ላይ ድልን እንዳቀዳጀኝ እምናለሁ። | | |
| ሠ | ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአቴን ሊያስወግድ ከቻለ ለሌሎች ችግሮቼ መፍትሔ ለማግኘት ሊረዳኝ እንደሚችል እምናለሁ። | | |
| ረ | ለክርስቶስና ለቃሉ ታዛዥ መሆን እፈልጋለሁ። | | |
| ሰ | በመታዘዝ ችግርን ማስወገድ እንደሚቻል እምናለሁ። | | |



# መጽሐፍ ቅዱ፣ መመሪያህ ይሁን

*ዓላማ 2 ለችግሮቻችን መፍትሔ ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን መመሪያ ማድረግ የሚገባን ለምን እንደሆነ ሁለት ምክንያቶችን ለመስጠት።*

ክርስቲያኖች ከሆንን በኋላ ለችግሮቻችን መፍትሔ ለማግኘት በዘፈቀደ አንባዝንም፤ ከክርስትና የሕይወት መንገድ ጋር የሚጣጣመውን ከእግዚአብ ሔር ቃል መፍትሔ እንፈልጋለን እንጂ።

በመጀመሪያ ክርስቲያን ሕይወቱን ለጌታ ለመታዘዝ የሰጠ መሆን አለበት። ስለዚህ መፍትሔ ናቸው ብሎ የሚያስባቸውን አማራጮች በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በጌታ ኢየሱስና በደቀ መዛሙርቱ ትምህርት መፈተን ይኖርበታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረን መፍትሔ ግን ያለምንም ማመቻመች ውድቅ መሆን አለበት።

ሁለተኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ የተሰጠን የእግዚአብሔር የሥራ መመሪያችን ነው። አንድ ማሽን አምራች ድርጅት ምርቱን ገበያ ላይ ሲያውል የማሽኑን አጠቃቀም የሚገልጽ መመሪያ ከማሽኑ ጋር ያስቀምጣል። ይህም የአጠቃቀም መመሪያ ማሽኑ በትክክል እንዲሠራ ለማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ሰው የተሠራው በእግዚአብሔር ነው፥ ሰዎች ስኬታማ የሚሆኑበትንም መንገድ እርሱ ያውቃል። ይህንንም መንገድ ሰዎች ያውቁ ዘንድ በጽሑፍ አስቀምጧል። ይኸውም መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር የሰጠንን ይህንን መመሪያ ቸል ማለትም ሆነ መዘንጋት ችግርን ወደራሳችን መጋበዝ ማለት ነው። አለመታዘዝ እንዴት ችግር ሊያመጣ እንደሚችል በክፍለ ትምህርት አንድ ላይ ተመልክተናል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የኑሮ መመሪያ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ መዘርዘር አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በአሥርቱ ትእዛዛት (ዘጸ. 20፡1-17) እና በኢየሱስ የተራራው ስብከት (ማቴ. 5-7) ውስጥ የሚገኙትን ጥቅል መመሪያዎች በመጠኑ እንመለከታለን።

(6). መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያችን ሊሆን ይገባል፤ ለምን? ሁለት ምክንያቶችን ግለጽ።

## አሥርቱ ትእዛዛት

*ዓላማ 3 በባህርያችን ወይም በድርጊታችን የጣስናቸው ትእዛዛትና የሚያስከትሉትንም ችግሮች ለይቶ ለማወቅ።*

ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ቅጣትን ተቀብሎልናል፤ ከአሁን በኋላም ከሕግ በታች አይደለንም። ስለዚህም እኛ በመረጥነው መንገድ ሕይወታችንን

ናዊ መጽሐፎች አሉ። እንደዚህ ዓይነት መጽሐፎችን ሳነብና ሌሎች ችግሮቻቸውን ይፈቱ ዘንድ እግዚአብሔር እንዴት ምሪትን እንዳመጣላቸው ስማር እኔንም እንደሚመራኝ በማመን እበረታታለሁ። ክርስቲያን የሚያነባቸውን መጽሐፎችና መጽሔቶች፣ የቴሌቪዥንና የሬድዮ ፕሮግራሞች እንዲሁም የመዝናኛ መንገዶች በመምረጥ ሐሳቡን በሚገባ መቆጣጠር ይገባዋል።

አንደበትን መቆጣጠር ምናልባት ሁላችንም የምንቸገርበት ጉዳይ ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ በያዕ 3:2 እንዲህ ይለናል፦ "ሁላችን በብዙ ነገር እንሰናከላለንና፤ በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው" በዚህ ምዕራፍ ከቁጥር 3 ጀምረህ እስከ 12 ድረስ አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች አንደበት ከፍተኛ ጥፋትን የሚያደርስ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል ያስረግጣሉ። በርግጥም የማንቆጣጠረው ከሆነ ከፍተኛ የሆነን ችግር ያስከትልብናል።

(17). ምሳ. 10:19፤ 17:28 እና 30:32ን አንብብ። የእነዚህ ምሳሌዎች መልእክት ምንድነው? ትክክለኛውን መልስ ምረጥ።

ሀ. ከአንተ በላይ ጠቢብ ከሆነ ከማንም ጋር በፍጹም እንዳትነጋገር።
ለ. ለምትናገረው ተጠንቀቅ - አንደበትህን ጠብቅ።
ሐ. የምታስበውን በመናገር ምን ያህል ጠቢብ መሆንህን ማሳየት ትችላለህ
(18). የምሳ. 21:23 እና 10:14 መልእክት ምንድነው?

የሚከተሉት ያልተገራ አንደበት ጥቂት ውጤቶች ናቸው።

ሀ. *ወዳጆችን ያለያያል*(ምሳ. 16:28) "ሐሜተኛም የቅርብ ወዳጆችን ይለያያል"
ለ. *ፍጹም የሆነ ጉዳትን ያመጣል* (ምሳ. 18:8) "የሐሜተኛ ቃል እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ነው፤ ወደ ሰው ውስጣዊ ክፍል ዘልቆ ይገባል።"
ሐ. *በወንድማማች መካከል ጠብን ይፈጥራል* ምሳ. 6:16፣ 19 "እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው . . . በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር፥ በወንድማማች መካከልም ጠብን የሚዘራ።"

አንድ ጊዜ ሃሳብህንና ንግግርህን መቆጣጠር ከተማርክ ባህሪህንም ደግሞ መቆጣጠር ትችላለህ። የኃጢአት ባህሪህ ስህተት የሆነውን ነገር እንድትፈጽም ሊመራህ ስለሚችል የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያስፈልግሃል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አስፈላጊነትን አስተውሎታል። በሮሜ 7:18-19 እና 24-25 ያብራራዋል።

በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና፤ ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም . . . እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን



ያድነኛል? በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

(19). ኅሊናህንና ራስ መግዛትህን በተመለከተ እውነተኛ ዐረፍተ ነገር የሚናገረውን ፊደሉን አክብብ።

ሀ. ኅሊናዬ ከኃጢአት ይጠብቀኝ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠኝ "የውስጤ ድምጽ" ነው።
ለ. ኅሊናዬን አልሰማም ብልም ስህተት ስለሆኑ ነገሮች ግልጽ ማስጠንቀቂያ ለእኔ መስጠቱን ይቀጥላል።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ይመራኝና ያስተምረኝ ዘንድ እስከፈቀድኩኝ ድረስ ኅሊናዬ ትክክለኛውን ጥሪዎችን ይሰጠኝ ዘንድ መጠበቅ እችላለሁ።
መ. ለምናገረውና ለማደርገው ምንጩ የማስበው ነው።
ሠ. የማነባቸውና የማዳምጣቸው ነገሮች በሐሳቤ ዘላቂ ተጽዕና አይኖራቸውም።
ረ. አንደበቴን መግራትን ከተማርኩ ሌሎቹን የሕይወቴን ክፍሎች የመቆጣጠር ችግር አይኖርብኝም።
ሰ. ራስን መግዛትን በሚገባ ሁኔታ ለመለማመድ የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል በሕይወቴ ያስፈልገኛል።

## ሌሎች ሰዎች

*ዓላማ 9 ለሚገጥሙህ ችግሮች እርዳታን ከሌሎች ሰዎች ስለመፈለግ ስሜቶችህን በጥልቀት መመርመርና፤ ስሜቶችህን በዚህ ክፍለ ትምህርት ከተሰጡት አመለካከቶች ጋር ለማነጻጸር።*

ብዙዎቹ ችግሮችህ ኅሊናህን በመከተል፣ ልማዳዊ እውቀትንና ምክንያታዊነትን በመጠቀም ሊፈቱ ይችላሉ። ለሌሎች ችግሮችም በመጸለይና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መፍትሔዎችን ማግኘት ትችላለህ። አንዳንድ ጊዜ ችግሩ በጣም የከበደና ለሰው ማዋየት የማይቻል ይሆናል፤ ወደ እግዚአብሔር ብቻ ማቅረብና መፍትሔውን በልብህ ውስጥ ይሰራ ዘንድ መፍቀድ ይኖርብሃል። ይሁንና እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሰዎችን እንደ ራሱ መሳሪያ በማድረግ ለችግሮችህ መፍትሔ በመፈለግ ይረዳህ ዘንድ ይጠቀምባቸዋል።

*ወዳጆችና ተንከባካቢ ሰዎች፦* ጠቢብና የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ጓደኛ የሚያስፈልግህ ጊዜ ይኖራል። እነዚህ ሰዎች ታማኝና ምስጢር ጠባቂ መሆን አለባቸው። እንዲህ ዓይነት ወዳጆች በችግሩ ውስጥ በስሜት ተገፋፍተው አይሳተፉም። ከነገሩ ውጭ ስለሆኑ ችግሩን ከተለየ አቅጣጫ ሊመለከቱት ይችላሉ። ምክራቸው ሁልጊዜ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሊሆን ይገባል።

## የሙከራ ፈተና

ምርጫ። እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር ለማሟላት የተሻለ መልስ የሆነውን ምረጥ።

1. መናዘዝ ኃጢአትን እንዳደረግሁ መቀበልንና ______ ያጠቃልላል።

ሀ. እግዚአብሔር እንደሚወደኝ ማወቅን
ለ. ጐረቤቶቼን መውደድ እንዳለብኝ መረዳትን
ሐ. ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ መመስከርን

2. በሕይወቴ ከምንም በላይ የምጋፈጠው ችግር ______ ነው።

ሀ. ራስ ወዳድነት      ለ. የኃጢአት ችግር      ሐ. ራስን አለመግዛትን

3. የክርስቶስ ትንሣኤ ለኔ ድኅንነት አስፈላጊ የሆነበት

ሀ. ከሞት ቅጣት ነፃ የምወጣበትን መንገድ ስለሚያዘጋጅልኝ ነው።
ለ. ከአዳም ኃጢአትና ከእኔ የኃጢአት ባህርይ ስለሚዛመድ ነው።
ሐ. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ብቸኛው ማረጋገጫዬ ስለሆነ ነው።
መ. በኃጢአት ላይ ድልን ስለሚሰጠኝ ነው።

4. ለክርስቶስ ያለንን ፍቅር የምናረጋግጠው

ሀ. እንወድሃለን በማለት ነው።      ሐ. ችግሮችን በማስወገድ ነው።
ለ. መቆጣትን በማስወገድ ነው።      መ. ቃሉን በመታዘዝ ነው።

5. ለአንድ ችግር መፍትሔዎች ሊሆኑ የሚችሉ ሁሉ መመርመር የሚገባቸው

ሀ. በልማዳዊ እውቀት ነው።      ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ ነው።
ለ. በኀሊና ነው።      መ. በወዳጆች ምክር ነው።

**እውነትና ሐሰት፦** ከእውነተኛ ዐረፍተ ነገር ፊት "እ" የሚለውን ፊደል፤ ሐሰት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ደግሞ "ሐ" የሚለውን ፊደል ጻፍ።

6. መጽሐፍ ቅዱስ ችግሮችን ለማስወገድ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ይዟል።
7. ክርስቶስ የመጣው ሕግን ለመተካት ነው።
8. የክርስቶስ ትምህርት የብሉይ ኪዳንን ሕግ ከመፈጸም በቀር ከእኛ የሚጠበቀው ነገር የለም።
9. ክርስቶስ ማድረግ የሚገባንን ያህል መሆን መቻል እንዳለብን ትኩረት ሰጥቶበታል።
10. የተሳሳተ አመለካከት ማንኛውንም ችግር ሊያባብሰው ይችላል።



11. በልማዳዊ እውቀት ችግርን መፍታት ሲያዳግት ጸሎትና የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ብቻ አስፈላጊ ናቸው።
12. ከሁሉ የሚበልጠው ትዕዛዝ እንደበትህን መግራት ነው።
13. ሕግ በፍቅር ተፈጽሟል።
14. የሰው ኅሊና ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጋር ተመሳሳይ ነው።
15. ንግግራችንና ባህሪያችንን መቆጣጠር ከፈለግን ሐሳባችንን በቁጥጥር ውስጥ ማድረግ ይኖርብናል።
16. የጓደኛን ምክር ለመመርመር ጥሩ መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚስማማ መሆኑን መፈተሽ ነው።

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

11. በፍቅር

1. ስለ ኃጢአቱ ንስሐ መግባት አለበት፤ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ መመስከር አለበት።

12. በፍቅር

2. ኃጢአታችንን ይቅር ይለናል፣ ያነጻናል ከኃጢአት ቅጣት ነፃ ያደርገናል።

13. ሀ. 2      ለ. 5      ሐ. 4      መ. 1      ሠ. 3

3. እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት አስነስቶታል ብሎ ማመን አለበት።

14. ያስተምረናል።

4. ከአዳም ኃጢአት የተነሳ ሞት ወደ ዓለም መጣ። የእርሱ ኃጢያታዊ ባህርይም ስላለን በኃጢአት ተወልደናል። የክርስቶስ ትንሣኤ፥ ሞትን ከሚያስከትለው ከኃጢአት ቅጣት ነጻ መውጣትን አዘጋጅቶልናል። ከክርስቶስ የተነሣ የዘላለም ሕይወት ሊኖረን ይችላል።

15. ሀ እና ሐ

5. የአንተ መልስ። በህይወትህ ያለውን የኃጢአት ችግር መፍትሔ ከሰጠህ ለእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች በሙሉ "አዎ" ብለህ መመለስ መቻል ይገባሃል። ሌሎችን ችግሮች መፍትሔ መስጠት ከመሞከርህ በፊት ይህንን አስፈላጊ ችግር የመፍታት አስፈላጊነትን ትመለከታለህ?

16. ሀ. አዎ      ሐ. አዎ      ሠ. አዎ      ሰ. አዎ
ለ. አይደለም      መ. አይደለም      ረ. አዎ

# 3 ትምህርት

# ክርስቲያናዊ የመፍትሔ መርሆዎች

የጦር መሳሪያ በታጠቁ ዘበኞች በተከበበ እስር ቤት ብትሆንና እንደፈቀደህ የመግባትና የመውጣት መብትህን ብትነፈግ ምናልባት ብዙ ችግሮች እሉብኝ ትል ይሆናል። ለችግሩም አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነፃነት ብቻ እንደሆነ ታስብ ይሆናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን በመሰለ ሁኔታ ራሱን ሲያገኘው በፍጹም እንደ ችግር አልተመለከተውም፤ ይልቁንም ለሕይወቱ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ምርጫ እንደሆነ አድርጐ ተመልክቶታል። እግዚአብሔር የወንጌልን መሠረት ይመሰርትና ስለ ወንጌልም ይቆም ዘንድ እንደሰጠው ዕድል ተቀብሎታል (ፊልጵ. 1:7)። ይህ የተሰጠውንም ዕድል ስለ ክርስቶስ ከቤተ መንግሥት ጠባቂዎችና በከተማ ካሉ የሱ ተባባሪ አገልጋዮች ጋር ለመካፈል ይጠቀምበት ነበር። በክፍለ ትምህርት 1 ጳውሎስ ስለ እስሩ ያለውን አመለካከት ተመልክተናል። በእስር ቤትም ጌታ እንደ ሚጠቀምበት ስላወቀ ይደሰት ነበር።

ችግሮችን ለመጋፈጥ የተሻለው አመለካከት ጌታን መታመን ለመለማመድ፣ የእግዚአብሔር ወሰን የለሽ ታማኝነትን ለማረጋገጥና በእርሱም ማንነታችንን ለማረጋገጥ እንደተሰጡን እድሎች መመልከት ነው። ለሕይወት ችግሮች መፍትሔ ለመፈለግ ከጌታ ጋር ስትሰራ የክርስትና እምነትህ ጠንካራ ይሆናል፤ እርሱ ለሁሉም ችግሮች ትክክለኛ መፍትሔ አለው።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ችግርን ለመፍታት የሚረዱ ክርስቲያናዊ መርሆዎችን እንመለከታለን። እነዚህን መርሆዎች በመከተል እግዚአብ ሔር ከአንተ ጋር እንዲሰራ መጠበቅ ትችላለህ፥ አንተም በእያንዳንዱ ችግር ውስጥ በደስታና በድል ለመስራት መጠበቅ ትችላለህ።



## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- በክርስቲያናዊ አቀራረብ ጀምር
- ተገቢ ያልሆኑ ምላሾችን አስወግድ
- የተቀናበረ ዘዴን ተጠቀም
- ደስ ይበልህ ምስጋናን ስጥ

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ፡-

- ችግሮችን ለመፍታት በሚደረግ መንፈሳዊ ዝግጅት ውስጥ ምን እንደሚካተት መግለጽ መቻል።
- ለችግር ሁኔታዎች የተሳሳቱ ምላሾችን ምሳሌዎች መስጠት መቻል።
- በክርስቲያናዊ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ ችግርን የመፍታት ዘዴን መከተል።
- በእያንዳንዱ አጋጣሚዎች ለሚገጥምህ ችግር እግዚአብሔር ስለረዳህ ውዳሴህንና ምስጋናህን መግለጽ መቻል አስብህ።

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍለ ትምህርት አንድ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ትምህርቱን አጥና። የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ሁሉ ማንበብህን እርግጠኛ ሁን። በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የስጠነውን መልስ ከመመልከትህ በፊት እያንዳንዱን የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልስ።

2. የሙከራ ፈተናውን ውሰድና መልሶችህን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት ጋር አመሳክር።

የማይቀየም ሰው ለመሆን ፀሎትና ልምድን ይጠይቃል። ወደ ኋላ ተመልክተህ "ተገቢ ያልሆነን ምላሽ ሰላልሰጠሁ ደስተኛ ነኝ ይልቁንም ሊያስቀይመኝ ለፈለገው ፍቅርን ማሳየት ችያለሁ" ማለት እንዴት ዓይነት በረከት ነው።

(3). በቀኝ በኩል ለተሰጡት ተገቢ ላልሆኑ ምላሾች በግራ በኩል ከተሰጡት ትክክለኛ ስያሜአቸው ጋር አዛምድ። የመረጥከውን ፊደል በተሰጠው በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ ሙላ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ሥራውን ያላገኘሁት ከሱ ስህተት የተነሳ ነው። ሆን ብሎ እንዳይሳካ ያደረገው እርሱ ነው። | 1. ቁጣ |
| ለ. ማድረግ የምችለውን ሁሉ መጉዳትም ቢሆን እጎዳዋለሁ። | 2. ክስ |
| ሐ. እርሷ በጣም ሰለጐዳችኝ ዳግመኛ በፍጹም አላናግራትም። | 3. መቀየም |
| መ. ስለ መጥፎ ጸባይዋ በልቤ ያለውን ሁሉ ልክ ልኳን ነግሬያታለሁ። | 4. በቀል |

## ማፈግፈግ

ማፈግፈግ ወይም ወደኋላ ማለት ብዙ ዓይነት መልክ አለው። አንዳንድ ጊዜ ከችግር በመሸሽ መደበቂያ ቦታ መፈለግ እንደ ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ከገጠማቸው እውነታ የሆነ ነገር ራሳቸውን በአደንዛዥ፣ በመጠጥ፣ አስደሳች ነገር ለመፈለግ፣ ከለመጠን በመብላት ወይም በመስራትና፣ ሃይማኖት አጥባቂ በመሆን ወይም በሌሎች መንገዶች ለማምለጥ ይሞክራሉ። እውነትን ላለመጋፈጥ ከማናቸውም ነገር በስተጀርባ መሸሸግ ትችላለህ። (በርግጥ ክርስቲያን ችግር እንዳይፈጠር ሁኔታውን የሚተውበት ገንቢ የሆነ ማፈግፈግ አለ)።

ማፈግፈግ አንዳንድ ጊዜ በአካል መሸሽም ይሆናል። እኔ ስለ አንድ ስለ አላገባችና እስከአሁን ድረስ ከቤተሰቦቿ ጋር ስለምትኖር ወጣት አውቃለሁ። ምናልባትም በፍፁም እንደማታገባና በቅርቡም እድሜያቸው የገፉ ወላጆቿን የመንከባከብ ሃላፊነት ካገቡ ወንድሞቿና እህቶቿ ይልቅ የእሷ እንደሚሆን በማሰብ መጨነቅ ጀመረች። ከሐዘንና ከምሬትም የተነሳ የምትሄድበትን ቦታ አንድም ሰው ሳያውቅ ዓዟን ጠቅልላ ቤቷን ለቃ ወጣች።

የማፈግፈግ ሌላው መልክ ነገሩን መተው ነው። ባሏ ከሞተ ጀምሮ ድንገተኛ አደጋ ካልተከሰተ በቀር ቤቷን ትታ መውጣት፣ ቤተሰቦቿን



መጐብኘት የተወችን ባልቴት አውቃለሁ። ይህች ባልቴት በጣም ብቸኛ ከመሆኗም በላይ ደስተኛም አልነበረችም።

(4). ከዚህ በታች ከተሰጡት ዝንባሌዎች ውስጥ ችግሮቻቸውን በማፈግፈግ ወይም በመተው ለማምለጥ በሚሞክሩት ላይ የምትመለከተው የትኞቹን ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. ራስ ወዳድ አለመሆን | ሠ. ተስፋ |
| ለ. ራስ ወዳድነት | ረ. ምሬት |
| ሐ. በራስ ማዘን | ሰ. ቁጣ |
| መ. ደስታ | |

(5). የሚከተሉትን ጥያቄዎች አዎ ወይም አይደለም በማለት መልስ

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ሀ. ነገሮች አንተ በምትፈልገው መንገድ በማይሄዱበት ጊዜ በመቆጣት ምላሽን ትሰጣለህ? | | |
| ለ. ምንም እንኳን ጥፋቱ የአንተ ቢሆንም አንድ ነገር በተሳሳተ መንገድ ሲሄድ፣ ጥፋቱን በሌላ ሰው ላይ ለማድረግ ትሞራለህ? | | |
| ሐ. ሰዎች ሁልጊዜ ያስቀይሙሃል? | | |
| መ. ዘወትር አሉታዊ በሆነና በማጉረምረም መንፈስ ውስጥ ነው ያለኸው? | | |
| ሠ. አንድ ሰው ቢበድልህ ምላሹን እስክትሰጠው ድረስ የማታርፍ ዓይነት ሰው ነህ? | | |
| ረ. አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥምህ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ጉዳዩን ከመፍታት ይልቅ ለማፈግፈግ ወይም ወደኋላ ለማለት ሞክረሃል? | | |

## የሰው ጥረት በብቸኛነት

*ዓላማ 3 ችግርን በሰው ጥረት ብቻ ለመፍታት አለመሞከር አስፈላጊ እንደሆነ ለማስረዳት።*

ይህን ራስን በራስ የመርዳት ምላሽ ሙሉ በሙሉ አሉታዊ ስላልሆነ በመጨረሻ ለማብራራት ፈልጌያለሁ። እግዚአብሔር የሰዎችን መንፈስ ብርቱ፣ አዎንታዊ ኃይል ያለውና በሕይወት ውስጥ ከሚገጥሙን ችግሮች በላይ በሚያስደንቅ መንገድ ከፍ እንዲል አድርጉ ሰርቶታል። "አዎንታዊ" አስተሳሰብ ባይኖር ኖሮ ክርስቲያን ያልሆነው ዓለም ሊቆይ ወይም ሊተርፍ ባልቻለ ነበር። ሆኖም የሰዎችን መንፈስ የሕይወት ችግሮችን ለመፍቻ ዋና ምንጭ አድርጉ መደገፍ አስተማማኝ ክርስቲያናዊ መንገድ አይደለም! የእግዚአብሔር መሻት ለልጆቹ፣ በትንሣኤ በተነሣው በክርስቶስ ኃይል

ችግሮቻቸውን እንዲጋፈጡና፣ ችግሮቻቸውንም ኃይሉንና ፀጋውን የሚገልጥበት መንገድ አድርገው እንዲጠቀሙበት ነው።

ችግሮችን ለመፍታት በምትሞክርበት ጊዜ፣ ማስወገድ የሚገቡህን አጸፋዊ ምላሾችን ስትመለከት፣ በራስህ ጥረት ብቻ መፍትሔ ለመፈለግ መሞከር እንደሌለብህ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። በዚህ ፋንታ በጸሎት ወደ እግዚአብ ሔር ዘንድ አቅርባቸው።

ወደ እግዚአብሔር ይዘን ለመቅረብ አነስተኛ የምንላቸው ችግሮች የሉም። መኪናዬን በምነዳበት ጊዜ ጥንቃቄን በሚጠይቀው ጭንቅንቅ ውስጥ ለማቆሚያ ስፍራ እንኳን እጸልያለሁ! ይህ ሞኝነት ነውን? አይደለም! እግዚአብሔር የግዙፋን ዓለማት አስደናቂ ፈጣሪ ነው። ነገር ግን ድንቢጥ መቼ ወደ ምድር እንደምትወድቅ የሚያውቅና በራስህም ላይ ያለውን ጸጉር ቁጥርን የሚያውቅ አምላክ ነው (ማር. 10:29-31)። በሕይወትህ ውስጥ ስለሚገጥምህ አነስተኛ ችግሮች እርሱ ይጠነቀቅልሃል። ሊረዳህም ይፈልጋል። ስለ ሕይወት ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ማድረግ የምንችለው በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር በምሳሌ 3:5-8 የተሰጠውን ምክር መከተል ነው። ይህንን የምንባብ ክፍል (ምሳ. 3:5-8) አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተሻለውን መልስ ምረጥ።

(6). ይህ ምሳሌ እንድትታመን የሚነግርህ ነው።

ሀ. አውቃለሁ ብለህ የምታስበውን ለ. ጌታን

(7). ከዚህም በላይ በፍጹም መደገፍ እንደሌለብህ ይነግርሃል።

ሀ. በሌሎች ሰዎች ለ. በራስህ መረዳት ሐ. በስሜቶችህ

(8). በምትሰራው ሥራ ሁሉ ጌታን ከታመንክ እሱ መጠበቅ ትችላለህ።

ሀ. ትክክለኛውን መንገድ እንዲያሳይህ
ለ. አነስ ያሉ ችግሮችን የምትፈታበትን ኃይል እንዲሰጥህ

መፍትሔ የሌለው የሚመስል ችግር ገጥሞህ እግዚአብሔርን ታምነህ ወደ እርሱ ከማቅረብ ይልቅ ቀላል ችግሮችን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ይቀልህ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ተዓምራትን በሕይወትህ እንዲያደርግ ይህ ትልቅ እድል ነው፤ ራስህን በእርሱ እጅ አሳልፈህ መስጠት ከተማርህ፣ የእግዚአብሔር ኃይል የተወሰነ አይደለም። እርሱ አያሳዝንህም! (ኤፌ. 3:20፣ 1ዮሐ. 5:14-15 ተመልከት)።

(9). ችግሮችን በሰው ጥረት ብቻ ለመፍታት አለመሞከር አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?



# የተቀናበረ ዘዴን ተጠቀም

*ዓላማ 4 በተዘጋጁ ዘዴዎች መሠረት፣ አንድ የችግር ሁኔታን ለማቃለል ልትከተለው የምትችል የማመሳከርያ ዝርዝርን ማዘጋጀትና የማመሳከርያ ዝርዝሩን ለተሰጠው ችግር ተግባራዊ ለማድረግ።*

በክርስቲያናዊ መርሆዎች ላይ ያተኩረ ችግሮችን ለመፍታት የተቀናበረ ዘዴን ለመጠቀም በዚህ ትምህርት ውስጥ እስከዚህ ድረስ መሰረትን ጥለናል። ብዙ መጽሐፎች ሰዎችን በችግሮቻቸው ለመርዳት ተጽፈዋል። ይህ ውስብስብ ርዕስ ስለሆነ በዛ ያሉ አቀራረቦች አሉት። የኛ ዓላማ ልትከተላቸው የምትችላቸውን መመሪያዎች በመስጠት ስለ ችግሮችህ የተስተካከለ አመለካከት እንዲኖርህና ክርስቶስን በመሰለ መንፈስ እግዚአብሔር ችግሮችህን እንዲፈታ እንድትታመነው ለማድረግ ነው።

በተቀናበረ ዘዴ ውስጥ ችግርን ለመፍታት ያሉትን ስድስት ደረጃዎች ከተወያየን በኋላ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥና በዚህ ዘመን ያሉ ሁኔታዎችን በመጠቀም በስድስቱ ደረጃዎች ውስጥ እንድትሳተፍ እድል እንሰጥሃለን። በወደፊቱ ክፍለ ትምህርቶች ውስጥ ውስን ችግሮችን ስንወያይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔ ላይ ለመድረስና ደረጃዎቹን ተግባ ራዊ ለማድረግ እድሉ ይኖርሃል። በሕይወትህ ውስጥ ባሉ እውነተኛ ችግሮች ወይም ልትረዳቸው በምትፈልገው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ባሉ ችግሮች ተግባ ራዊ ታደርገው ዘንድ በዚህ መንገድ እንደምንረዳህ ተስፋ እናደርጋለን።

## ችግርን መፍቻ ደረጃዎች

| ዘዴ ሀ | ዘዴ ለ |
|---|---|
| 1. ችግሩን ለይተህ እወቅ<br>ሀ. የችግሩን ምንጭ ለይ<br>ለ. መነሻ የሆነውን ምክንያት ጠይቅ | (ፈጣን መፍትሔ የሌላቸው ለሚመስሉ ችግሮች) |
| 2. ችግርህን ለጌታ አስረክብ | 1. ችግሩን ለይ። |
| 3. መልስ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሔዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ተመልከት (የራስህን ምንጮች ተጠቀም) | 2. ለእግዚአብሔር አስረክብ። |
| 4. አማራጮቹ ሁሉ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤቶች ገምት። | 3. እግዚአብሔር ችግሩን ለመል ካም እንደሚያደርገው ጠብቅ። |
| 5. አንድ መፍትሔ ምረጥና እርምጃ ውሰድ። | |
| 6. የመፍትሔውን ውጤት ገምግምና አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያን አድርግ። | |

(12). በደረጃ 3 መሠረት ከጥያቄ 6-8 ያሉት የጥያቄ ዝርዝርህ ውስጥ መጨመር አለባቸው። እኔ የጻፍኳቸውን ከመመልከትህ በፊት የአንተን ጥያቄዎች መጻፍህን እርግጠኛ ሁን። ይህም የተማርከውን እንድታስ ታውስ ይረዳሃል።

*ደረጃ 4 ሁሉም አማራጮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤቶች አስተውል።*

ፍቺን ለችግሮቻቸው መፍትሔ አድርገው ስለወሰኑት ሁለት የትዳር ጓደኞች ሊከሰቱባቸው የሚችሉትን ውጤቶች አስብ። የትዳር መፍረስ ባልና ሚስትን ብቻ አይደለም የሚጐዳው፥ ልጆችንም ጭምር ነው። የተሳሳተ መፍትሔ ከተነሳህባቸው ችግሮች በላይ የሆኑ ችግሮችን ሊፈጥር ይችላል። ከዚህ የተነሳ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማይደገፉ መፍትሔዎችን ማስወገድ እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው። ከምትወስነው ውሳኔዎች የተነሳ ሊመጣ የሚችለውን ውጤት ለመወሰን ያሉህን ምንጮች ሁሉ ተጠቀም። (ትምህርት 2ን ተመልከት)።

(13). በደረጃ 4 መሠረት በማመሳከርያ ዝርዝር ውስጥ ጥያቄ 9ን ጨምር። የውሳኔህን ዘለዓለማዊ ዋጋና እንዲሁም አሁን በምድር ያለውን ዋጋ አስብ።

*ደረጃ 5 አንድ መፍትሔ ምረጥና እርምጃ ውሰድ።*

ችግርህን ለይተሃል ለእግዚአብሔርም አሳልፈህ ሰጥተሃል። ስለ ችግርህ ወይም ስለተዛማጅ ችግሮች የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ለማወቅ አጥንተሃል። አስፈላጊ ከሆነ ችግርህን ከክርስቲያን ጓደኛህ፣ ከመጋቢህ ወይም ከአማካሪ ጋር ተወያይተሃል። ባለህበት ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት የተሻለው ውሳኔ ላይ ደርሰሃል። አሁን በመረጥከው ውሳኔ ላይ እርምጃ የምትወስድበት ጊዜ ነው። በዚህ ደረጃ ችግርህን ለመፍታት በምትጠቀምበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚረዳህና ከአንተ ጋር እንደሚሆን እመን።

*ደረጃ 6 ውጤቶችን ገምግምና አስፈላጊ ለውጦችን አድርግ።*

ይህንን ደረጃ ያከልኩበት ምክንያት የመረጥናቸውን መፍትሔያዊ ውጤቶችን መገምገም ስለሚያስፈልገን ነው። አንዳንድ ጊዜ ችግርን ለመፍታት እርምጃ ከወሰድን በኋላ ጥሩ ምርጫ እንዳልወሰንና የበለጠ ማስተካከል የሚያስፈልገው ሆኖ እናገኘዋለን። ችግሮችህን ለእግዚአብሔር ሰጥተህ የእርሱን ምሪት ከጠየቅህ በኋላ ይሻላል ባልከው ውሳኔህ እርምጃን ስትወስድ፥ የአንተ መፍትሔ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት ቢሳነውም ተስፋ አትቁረጥ። ችግርን መፍታት የምትማረው ከልምድ ብዛት ነው። ከተፈጥሮ የምንወርሰው ተሰጥኦ አይደለም። ይልቁንም ራስህን ሙሉ



በሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መስጠትህንና ወደሚመራህ ማናቸውም ቦታ ለመከተል መዘጋጀትህን ውስጥህን የምትመለከትበት ጊዜ ነው።

(14). የማመሳከሪያ ዝርዝርችህን ለመደምደም ጥያቄ 10ን በደረጃ 6 መሠረት ጨምር።

አስታውስ የማይመቹ ሁኔታዎች ሁሉ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው ችግሮች አይደሉም። የማይለወጥ ከሆነ ለየት ያለ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልጋል። ለእንደዚህ ዓይነት ችግሮች መፍትሔ ዘዴን "ለ"ን እንመልከት።

**ዘዴ ለ**

*ደረጃ 1 ችግሩን ለይተህ እወቅ።*

በዘዴ ሀ ውስጥ እንዳለው አንድ ዓይነት ቅደም ተከተልን ተጠቀም።

*ደረጃ 2 ችግሩን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ስጠው።*

በዘዴ ሀ ውስጥ እንዳለው አንድ ዓይነት ቀደም ተከተልን ተጠቀም።

*ደረጃ 3 እግዚአብሔር ለአንተ መልካም እንደሚሠራ ጠብቅ።*

ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን ከእስር ቤት የብረት በር በስተኋላ ሲያገኘው ሁኔታውን መለወጥ እንደማይችለው ያውቀዋል። ቀደም ባለው በጳውሎስ አገልግሎት እንዳከናወነው በዚህ ጊዜ ከእስር ቤት ውስጥ እንዲወጣ አላደረገውም (የሐዋ ምዕራፍ 16)። ነገር ግን እግዚአብሔር በማናቸውም ሁኔታ ለእርሱ መልካም እንደሚያደርግለት ጳውሎስ ይጠብቃል። በውጤቱም እግዚአብሔር በእስር ቤት ወንጌልን ያሰራጭ ዘንድ ልዩ በሆነ መንገድ ተጠቅሞበታል።

ለእንደዚህ ዓይነት ችግሮች ተገቢ የሆነው መፍትሔ ሊለወጥ የማይቻለውን በደስታ መቀበልና ያለህበት ሁኔታ አንተን በመለወጥ ክርስቶስን ወደመምሰል፣ ለሌሎች የምታስብና የምትራራ እንዲያደርግህ መፍቀድ ነው። "እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ ሃሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" (ሮሜ 8፡28)። ይህንን ሁልጊዜ ለራስህ አስታውሰው። "ነገሮች እንዲህ ቢሆኑ ኖሮ ..." በሚል አስተሳሰብ ውስጥ መዋኘት ጤናማ አይደለም። እንደዚህ ዓይነት ሐሳቦች ጊዜንና ኃይልን አባካኝ ናቸው። በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ብትሆን እግዚአብሔር መልካምን ያደርግ ዘንድ መጠበቅ ትችላለህ።

(15). ከሚከተሉት ችግሮች ውስጥ ለየትኞቹ ዘዴ "ለ"ን ተግባራዊ ታደርጋለህ?

9. ሀ.

18. በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ለእርሱ መልካም እንዲሆን የሚሰራ እግዚአብሔርን የመታመን መርሆ።

9. ምክንያቱም የአንተ መረዳት ውስን ስለሆነ የተሻለውን መፍትሔ ላታውቅ ትችላለህ። ከዚህም በተጨማሪ የማይቻለውን ሊያከናውን በሚችል እግዚአብሔር ላይ እምነትህን በማኖር ብቻ የሚፈቱ አንዳንድ ችግሮች ስላሉ ነው።

19. ለ



# 4 በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ያሉ ችግሮች

ትምህርት

አልፎ አልፎ በሁለት ሀገሮች መካከል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች አምባሳደሮች ወደ ሀገሮቻቸው እንዲመለሱ ሲደረግ እንሰማለን። በዚሁ አለመስማማት ምክንያት አምባሳደሮች የሚገደሉበትም አጋጣሚ አለ። ይሁንና እንደዚህ ዓይነት ገጠመኞች ሁሌ የሚከሰቱ ሳይሆኑ አልፎ አልፎ የሚሆኑ ናቸው። ብዙውን ጊዜ በወዳጅ ሐገሮች መካከል አምባሳደሮች በጣም የተከበሩና ባለሙሉ በልጣን ተደርገው ይቆጠራሉ። የእነርሱም መልካም ባህርይ ለሐገራቸው ክብርን ያመጣል።

እንደዚህ ዓይነት አምባሳደር እንደሆንክ ታውቃለህን? አንተ የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ ነህ፤ ከዚህም የተነሳ የዚህን መንግሥት ንጉሥ ጌታ ኢየሱስን በምድር ላይ ትወክላለህ። የእግዚአብሔር ዓላማ የሰው ልጆችን ከራሱ ጋር ወደጠበቀ ኅብረት ማምጣት ነው። ይሁንና የሚያስደንቀው እውነታ አሁን፥ "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን" (2ቆሮ. 5:19-20) የሚለው ነው።

በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ በስራ ገበታችን፤ በትምህርት ቤት፤ በቤተ ክርስቲያናችን፤ በጉረቤቶቻችን ባሉ ችግሮች እኛ ማን እንደሆንና የማን እንደሆንን ካስተዋልን፥ እርምጃ መውሰድ የቀለለ ይሆንልናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነትና በሱ በኩል እርሱን ከማያውቁትና በራስ ወዳድነት ብቻ ከሚገፋፉ ሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረንን አንዳንድ ወሳኝ የችግር ክፍሎችን እንመለከታለን። ክርስቲያኖች የየቀኑ የሕይወት ገጠመኞቻቸው የሆኑት እነዚህ ችግሮች ላይ እንዴት ነው እርምጃ መውሰድ የሚገባቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማድረግና እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚገባን አዎንታዊ መመሪያዎችን ይሰጠናል።

### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የሰው የሆነውን መመኘት
- ለሥልጣን መጓጓት
- በክርስትና አለመብሰል
- ብልጽግናና ድህነት
- ኢፍትሐዊነት

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- የሰው የሆነውን መመኘት፣ ለሥልጣን መጓጓት፣ ክርስቲያናዊ አለመብሰልና ለኢ-ፍትሐዊነት ችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔዎችን ማስቀመጥ መቻል።

- ገንዘብንና ንብረትን በተመለከተ ክርስቲያናዊ አመለካከትን ወይም ግምትን መለየት መቻል።

- በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ለሚገጥሙህ ችግሮች መፍትሔዎችን ለማግኘት ችግርን የማቃለል ዘዴን በሕይወትህ ተግባራዊ ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

### የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍለ ትምህርት 1 በተሰጠው መመሪያ መሠረት ክፍለ ትምህርቱን አጥና። እያንዳንዱን የጥናት ጥያቄዎች መልስ። በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ የተሰጠውን መልስ ሳትመለከት ለመስራት ምክር።

2. በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ስለዚህ ሁሉንም ማንበብህን እርግጠኛ ሁን።



### የትምህርቱ ዝርዝር

## የሰው የሆነውን መመኘት

***ግብ 1 የሰው የሆነውን የመመኘት ችግር እንዳለብህና እንደሌለብህ ለማየት እንዲረዳህ የራስህን አመለካከት ለመመዘን።***

ማኅበራዊ በሆነ ዓለም ውስጥ ነው የምንኖረው። ይህም ማለት ዓለም በኑሮ፣ በሥራ ወይም በጨዋታ የእርስ በእርስ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች የፈጠሩዋቸው ማኅበረሰቦች የተሞላች ነች። በዚህ ዓለም ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱ ፈቃድ ተሰጥቶታል። እያንዳንዱም ሰው የራስ ወዳድነት፣ የራስ ምኞት፣ የግል ፍላጎትን የማርካትና በሌሎች ሰዎች ዘንድ ትልቅ ሆኖ የመታየት ዝንባሌዎችን በውርስ ይዟል። ከመጥፎ ባህሪያችን የተነሳ እርስ በእርሳችን ብዙ ችግሮችን መፍጠራችን የሚያስደንቅ አይደለም።

በግንኙነታችን ውስጥ ካሉት ከፍተኛ ችግሮች ውስጥ አንዱ የሰውን ነገር መመኘትና መፈለግ ወይም ስስታምነት ነው። የአንድን ሰው ኃይል፣ ወይም ሀብት፣ ወይም ሥልጣን፣ ወይም ጓደኞች፣ ወይም ማራኪነት፣ ወይም ተሰጥኦ እንፈልጋለን። በሌላው ሰው ላይ በመረማመድ ወይም ስለመጎዳቱ ሳይገደን ምርጥ የሆነውን ነገር ለራሳችን እንፈልጋለን። የዐሥርቱ ትዕዛዛት የመጨረሻው ክፍል በዚህ ሁኔታ ላይ ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

> "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት፣ ሎሌውንም፣ ገረዱንም፣ በሬውንም፣ አህያውንም፣ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ" (ዘጸ. 20፥17)።

ሁልጊዜ ራስህን ከሌሎች ሰዎችና ከስኬታቸው ጋር ታወዳድራለህን? ይህ በተወሰነ ደረጃ የሚረዳ ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና ተከታታይ በሆነ ሁከትና አለመርካት ውስጥ የሚያስጉዝህ ከሆነ የሚጎዳህ ሊሆን ይችላል። ከምታደንቃቸው ሁሉ ጋር ለመስተካከል ትሞክራለህን? የግድ አስፈላጊ መሆን የለበትም። በርግጥ ከሌሎች መማር ትችላለህ። ይህንን ሁላችንም እናደርገዋለን። በተመሳሳይ ሁኔታ የራስህን ድካም ማወቅና ማንነትህን መቀበል ይገባሃል። ጠንካራ ጐንህን በመረዳት ልታዳብራቸው ያስፈልግሃል። የማይቻለውን ነገር ግን ለማድረግ አትሻ።

እኔ የቫዮሊን ተጨዋች ሳልሆን፥ በሚጫወተውም ሰው ሳልቀናና ሳልመቀኝ፥ በኮንሰርት ላይ በሚደረግ የቫዮሊን ጨዋታ ደስ መሰኘት እችላለሁ። የጐረቤቴን አዲስ ቤት፣ መኪና ወይም ብስክሌት አደንቃለሁ። ከእርሱ ጋርም፥ ተመሳሳይ ነገር ይኖረኝ ዘንድ ሳልጓጓ፥ አብሬ እደሰታለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ "ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ" (ሮሜ 12፥15) በማለት ማድረግ የሚገባንን ይነግረናል። ለአንድ

ሰው ማዘን ከባድ አይደለም፤ ይሁንና በተለይ ቅናት የሚሰማህ ከሆነ ግን መደሰት እስቸጋሪ ነው።

የሰውን ነገር መመኘት ወደ ሌላ ችግር ፈጣሪ ወደሆኑ ኃጢአቶች ሊመራን ይችላል የምትፈልገውን ለማግኘት መዋሸት ወይም መስረቅ፣ ቁጣ፣ የክርስትና ምስክርነትህን መጣል፣ ቅናት፣ ተቃውሞ፣ ጥላቻ፣ በቀል፣ ማታለል . . . ስለዚህም እግዚአብሔር የሰውን ነገር መመኘትን በዐሥርቱ ትዕዛዛት መጨመሩ የሚያስገርም አይደለም።

(1). በክፍለ ትምህርት 2 ውስጥ የሰው የሆነውን ከመመኘት ጋር የተያያዙ ችግሮችን መፍትሔ ሊሰጥ የሚችልበትን አንድ መንገድ ተወያይ ተናል። የችግሩን ምንነትና መፍትሔውን የሚደግፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስን መጥቀስ ትችላለህን?

(2). ራስህን ፈትን። ከነዚህ ጥያቄዎች መካከል ለማንኛውም መልስህ "አዎ" ከሆነ፣ ያለብህን የሰው የሆነውን የመመኘት ችግር ለማስወገድ የመፍትሔ ደረጃዎችን ተግባራዊ ማድረግና ጌታ ወደ ፍቅር እመለከከት ይለውጥህ ዘንድ መጠየቅ ይኖርብሃል። ከተጻፈው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ገጠመኝ ካለህ ይህን ምልክት "X" ባደረግንበት ቦታ ሌሎች ስሞችን በመተካት ልታነብ ትችላለህ።

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ሀ. በሁሉ ነገር ስኬታማ የሆነ ጓደኛ አለኝ፤ ከርሱ ጋር ስሆን የበታችነት ይሰማኛል። | | |
| ለ. ባለኝ ተሰጥኦ ደስተኛ አይደለሁም፤ ሁልጊዜ እንደ "X" ተሰጥኦ ያለኝ እንድሆን እመኛለሁ። | | |
| ሐ. ድሀ መሆን ሰልችቶኛል። እንደ "X" ብዙ መልካም ነገሮች ይኖሩኝ ዘንድ እመኛለሁ። | | |
| መ. ቀጣሪዬ እኔ ከማገኘው በላይ እንክብካቤን ስለሚሰጠው በ "X" ላይ መቅናት እችላለሁ። | | |
| ሠ. ጓደኞቼ የሚመኙትንና የፈለጉትን ሁሉ ሲያገኙ እኔ የረባ ነገር ባለማግኘቴ በእግዚአብሔር ላይ ተናድጃለሁ። | | |
| ረ. ከሥራ ባልደረቦቼ አንዱ ዘስራው ስዘተት ሲነቀፍ ዘወትር ርካታን ይሰጠኛል። | | |
| ሰ. ሌላ ነገር ማሰብ እስኪያቅተኝ ድረስ እጅግ የምፈልገው ነገር "X" አለው። | | |

## ሰሥልጣን መጓጓት

***ዓላማ 2 የሥልጣን መሻትን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል ክርስቶስ ያስተማረውን ለማስተዋል።***



አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፡ "ለራሱ ክብርን ለማግኘት በማይጓጓ ሰው አማካኝነት የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ልትሰራ እንደምትችል ዓለም ልታይ ያስፈልጋታል"

ሰዎች በባህሪያችን በሌሎች ዘንድ ቦታ ማግኘትን፣ ምስጋናን፣ ሥልጣንን፣ ክበሬታን፣ እውቅናንና ኃይልን ማግኘት እንፈልጋለን። ለሰራኸው ሥራ ተገቢውን እውቅናን ባለማግኘት ስሜቶችህ ተጎድተው ያውቃሉን? እኔ አውቃለሁ። ምናልባት በአንድ ወቅት ይሁን በሌላ ሁሉም እንደዚህ ዓይነት የስሜት መጎዳት ያጋጥመዋል። ሁልጊዜ ራስ መሆን የሚፈልግና ለተሰራው ማንኛውም ሥራ ባለቤት ሆኖ ዋጋውን መቀበል የሚፈልግ ሰው ችግሮች ያጋጥሙታል። ሌላ ሰው ክብርንና እውቅናን ሲያገኝ ቅናት የሚሰማው ወይም እሱ በሰራው ወይም በድርጊቱ ያበረከተው ተሳትፎ ሳይስተዋል ሲቀር ብስጭት የሚሰማው ሰው ችግሮች ያጋጥሙታል።

ይሁንና ኢየሱስ ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳቶች እንዲሁም ሥልጣንን በመፈለግ ለሚመጡ ሌሎች ጉዳቶች ሁሉ ፈውስ አለው። መድኃኒቱ በእኛ ውስጥ የሚገኝና ለምናገለግለው አምላክ ያለን አመለካከት ነው።

ኢየሱስ በሰው ውስጥ ያለውን ያውቃል (ዮሐ. 2:24-25)። በሰው ውስጥ ያለውን የቅናትና ሥልጣን የመሻት ስሜትና ዝንባሌን ያውቃል። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረ ጊዜ ማን ታላቅ እንደሚሆን እርስ በእርሳቸው ተከራከሩ (ሉቃ. 22:24)። ሥልጣንን በስራቸው ባሉት ላይ በማሳየት ጌታ ለመሆን እንደሚፈልጉት የአህዛብ ነገሥታት እንዳይመስሉ ነገራቸው። "ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፣ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን" (ሉቃ. 22:25-26)።

ኢየሱስ አገልጋይ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በራሱ ምሳሌ አሳይቶአቸዋል። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረው የመጨረሻ እራት ኢየሱስ አንድ አገልጋይ እንደሚያደርገው እግራቸውን አጠበ። ይህንንም ድርጊት በማገባደጃው ላይ እንዲህ አለ፡-

> እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንስቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፥ እንዲህም አላቸው፡- ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፣ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም፥ መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም። ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ (ዮሐ. 13:12-17)።

(3). ከእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች መካከል ሥልጣንን በተመለከተ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ያስተምር የነበረውን የሚወክለው የትኛው ነው? እውነተኛውን ዐረፍተ ነገር የያዘውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ኢየሱስ ጌታና ሁሉን የሚገዛ ነው።
ለ. እርሱ ምን ያህል ትሁት መሆኑን ለማሳየት የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ።
ሐ. ኢየሱስ ከሁሉ በላይ ሆኖ ሳለ እግራቸውን በማጠብ ዝቅ ያለን ሥራ ሰራ።
መ. ምንም እንኳን እግዚአብሔር ደቀ መዛሙርቱን በታላቅ ሁኔታ የሚጠቀምባቸው ቢሆንም ራሳቸውን እንደ አገልጋይና መልእክተኛ መመልከት ይገባቸዋል እንጂ እንደ ታላላቅ ሰዎች መመልከት የለባቸውም።
ሠ. ከእነርሱ በታች ባሉት የእግርን ማጠብ ሥርዓትን መመስረት ነበረባቸው።
ረ. ራሳቸው አገልጋይና መልእክተኛ መሆናቸውን አውቀው የአገልጋይን ሥራ አንዱ ለሌላው ማድረግ አለባቸው።
ሰ. እርስ በርሳቸው እግር ከተጣጠቡ ኢየሱስ የበረከትን ተስፋ ሰጥቶአቸዋል።
ሸ. እርስ በርሳቸው አገልጋይ ከሆኑ ኢየሱስ የበረከትን ተስፋ ሰጥቶአቸዋል።

መራርነትን፣ ትዕቢትን የበላይነት ወይም የበታችነት ስሜቶችን ለማሸነፍ ይረዳን ዘንድ ከዚህ ልንማር የምንችለው ሁለት ትምህርቶች አሉ።

1. የመሪነት ኀላፊነት ያለው ሰው እንደሚያገለግል ሰው መሆን አለበት። አገልግሎቱ ክርስቶስን ከፍ የሚያደርግበት እንጂ ራሱን ከፍ የሚያደርግበት አይደለም።

2. ዝቅ ያለ ቦታ ያለው ሰው "ለክርስቶስ መሆኑን ተረድቶ" አስቸጋሪ በሚመስሉ ሁኔታዎች ውስጥም እንኳን ቢሆን የአገልጋይ አመለካከትን ጠብቆ፣ ሥራውን መፈጸም ይኖርበታል። የእግዚአብሔርን ታላቅነት በሕይወቱ ሁሉ እያየና በእርሱ ቁጥጥር ስር መሆኑን እያስታወሰ ካገለገለ እግዚአብሔር እርሱን ይባርከዋል።

ሥልጣን ላይ ትኩረትን ሳያደርጉ፥ የማገልገል ሕይወት ያለኝ ይበቃኛል ብሎ ለመኖርና በእርካታ ጌታን ለማስደሰት በትክክል ቁልፍ ነው። ታላቅ የመሆን መሻት አጥፊ ኃይል ነው፤ ሰላምን ያጠፋል፤ ግንኙነቶችን ያጠፋል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ያጠፋል። ክርስቶስን ለመግለጽ እውነተኛ ነፃነት በሙላት የሚመጣው በዚህ ዓለም ውስጥ ለሥልጣን ያለንን ትልቅ ፍላጐት ስናቆም ነው። እውነተኛ ሽልማታችን በዚህ ሕይወት ውስጥ የምናገኘው አይደለም። "በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል" (ሮሜ 2:7)። የላቀ ፍላጐታቸው መልካምን ነገር ለመስራት ለሆነ እግዚአብሔር ክብርን ይሰጣቸዋል።



(4). ሉቃ. 17:5-10ን አንብብ። በዚህ ታሪክ ውስጥ ክርስቶስ በግልጽ የሚያስተምረውን የሚያብራሩ ዐረፍተ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ለሰራናቸው ስራዎች መመስገንን መፈለግ የተለመደ ሲሆን፤ የራሳችንን ድርሻ ከተወጣን እውቅና ሊሰጠን ይገባል። ከዚህ የተነሳ ነው ስኬታማ መሆን የምንፈልገው።
ለ. እግዚአብሔር እናደርግ ዘንድ የተናገረንን ስናደርግ ውዳሴንና ክብርን ለራሳችን መፈለግ የለብንም፥ ይልቁንም "ልናደርገው የሚገባንን ነው ያደረግነው" የሚል አመለካከት ይኖረን ዘንድ ያስፈልጋል።
ሐ. የራሳቸውን ድርሻ ለፈጸሙ ሰዎች እውቅናንና ምስጋናን መስጠት አይገባንም። ምክንያቱም ይህ በጣም አስፈላጊና የበላይ የሆኑ ያህል እንዲሰማቸው ስለሚያደርግ ነው።

መልካምን ሥራ ስንሰራ ማረጋገጫን ለመቀበል መፈለግ በርግጥ የተለመደ ነው። ይሁንና መልካምን ለመስራት የሚያነሳሳን ክብርና እውቅናን ለማግኘት መፈለጋችን መሆን የለበትም። በሌላ መልኩ በመሪነት ሥልጣን ላይ ያለ ሰው ተገቢ በሆነ ቦታ ለተሰሩ ስራዎች ተገቢውን ዋጋ በመስጠት የሚከሰቱ ችግሮችን መቀነስ ይችላል። የሚያበረታታ ቃል ሰዎችን የበለጠ በትጋትና በቀና አመለካከት ይሰሩ ዘንድ ያነሳሳቸዋል።

ሁሉም ሰው መሪ ይሆን ዘንድ አልተጠራም። እግዚአብሔር የሚፈርደው ያለህበትን የሥልጣን ደረጃ ተመርኩዞ ሳይሆን፣ እንድትሠራው የተሰጠህን ሥራ ምን ያህል ጥሩ አድርገህ እንደሠራህ በማየት ነው (ማቴ. 25:14-30)። አንድ የታወቀ መዝሙር እንዲህ ይላል "ስለ ስራው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን" አንተም አብረህ "ስለ ሥራው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን" ትላለህ?

## በክርስትና አለመብሰል

### የአለመብሰል ምልክቶች

*ዓላማ 3 በኤፌሶን 4 እና 5 የሚገኙትን የክርስቲያናዊ አለመብሰል መፍትሔዎችን ለመፈለግና በሠንጠረዥ ውስጥ ለመጻፍ።*

ክርስቲያን በሆንክ ጊዜ ሰው መሆንህ አላበቃምና መሻቶችህ፣ ስሜቶችህ፣ ፍላጐቶችህ፣ ወይም ልትጐዳ የምትችል መሆንህ አብሮህ አለ። እነዚህ ከሌሎች ጋር ባለን ዕለታዊ ግንኙነት እያንዳንዳችን ልንታገላቸው የሚገቡን ስሜቶቻችን ናቸው። እነዚህን ድል መንሣት ጊዜን የሚጠይቅ፤ የክርስቲያናዊ መብሰል ሂደት ነው። በረድፍ መጀመሪያ መሆን የሚፈልጉ፣ የተሻለው መቀመጫ ይሰጣቸው ዘንድ የሚፈልጉ፣ ዘወትር እንደተናቁ የሚሰማቸውና ምንም ይሁን ከቀረበው ሁሉ የተሻለውን ነገር እስኪያገኙ ድረስ የሚያጉረመርሙ ሰዎችን ምናልባትም ክርስቲያኖችን ታውቃለህ።

(ኤፌ. 4:15-16 አንብብ)። ክርስቶስ ራስ እንደሆነ አስተውል። በእርሱ ቁጥጥር ስር ሁሉም የሰውነት ክፍሎች ይጋጠማሉ እንዲሁም በኅብረት ይሰራሉ። በኤፌ. 4:23 "በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ" ይልና በመጨረሻ በኤፌ. 6:10 ሐዋርያው ጳውሎስ "በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ" ይላል።

ከሁሉም በላይ ለእርሱ እንድንኖርና በኤፌሶን 4 እና 5 የተነገረንን እንድናደርግ ችሎታን የሚሰጠን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

(6). ይህ ለችግሮቻችን መፍትሔ የምንፈልግበትን አስፈላጊ ደረጃ የምናስቀምጥበት ሌላኛው መንገድ ነው (ክፍለ ትምህርት 2ን ተመልከት) የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ አዲስ ፍጥረት የሚያደርገን

ሀ. ከክርስቲያን ወዳጆቻችን ምክርን በማግኘት ነው።
ለ. በመናዘዝና በማመን አስቀድመን የኃጢአትን ችግር ስናስወግድ ነው።
ሐ. መልካም ጉረቤቶች ለመሆን ስንሞክር ነው።

*የፈቃድ ኃይል* ኤፌሶን 4:27 እንዲህ ይላል "ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት" ይህ በርግጠኝነት ዲያቢሎስ እድል ሊሰጠው እንደሚችል ያሳውቀናል። በኤፌሶን 4 እና 5 ውስጥ ማድረግ የሚገቡህን ነገሮች የሚገልጹ ብዙ ትዕዛዞች እንዳሉ አስተውል። እግዚአብሔር የራሱ ድርሻ አለው - የራሱንም ድርሻ በታማኝነት ያከናውነዋል። ይሁንና እኔና አንተ የራሳችንን ድርሻ ካላከናወንን ወደ ብስለት አናድግም፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሕብረትም ልናጣ እንችላለን። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለተሰጠው ትዕዛዞች ታዛገሮች በመሆን የፈቃዳችን ኃይል፣ ውጤታማ እንዲሆን እናደርጋለን። ወደ ክርስቲያናዊ መብሰል የምንደርሰውና የብስለት ችግርን ማሸነፍ የምንችለው በመታዘዝ ውስጥ ብቻ ነው።

(7). የክርስቲያናዊ ብስለትን ለማግኘት ምንጮቹን ከሚገልጹ እውነተኛ ዐረፍተ ነገሮች ፊት ለፊት ያሉትን ፊደሎች አክብብ።

ሀ. እኛን ሙሉ በሙሉ አዲስ ፍጥረት ለማድረግ የእግዚአብሔር ኃይል በማናቸውም መንገድ በራሳችን ባህሪ የተደገፈ አይደለም።
ለ. የራሳችንን ፈቃድ ኃይል፥ በክርስቶስ ለማመንና እርሱ የትንሣኤ ጌታችን መሆኑን ለመመስከር ትዕዛዞቹን ለመታዘዝ እንጠቀምበታለን።
ሐ. እርሱ ሙሉ በሙሉ አዲስ ፍጥረት ካደረገን በኋላ በክርስቶስ ኃይል አማካኝነት ብቻ መታዘዝ ይቻላል።
መ. የራሳችንን ድርሻ ማድረግ አለመቻል ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት እንዳናድግ ያቆመናል።
ሠ. ለክርስቲያናዊ ብስለት መታዘዝ ቁልፍ መሠረት ነው።
ረ. በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ችግሮች ላለመብሰል እርግጠኛ ምልክቶች ናቸው።



በኤፌሶን 6 ውስጥ ያለመብሰልን ለመዋጋት ስለሚያስፈልጉን መሳሪያዎች ጳውሎስ መናገሩን ቀጥሏል። እነርሱም እውነት፣ ጽድቅ (በትክክለኛው መንገድ መኖር) ቅድስና፣ ወንጌልን ለማወጅ ዝግጁ መሆን፣ እምነትና የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። የመጨረሻው ትዕዛዙ መጸለይ ነው (ኤፌ. 6:16)።

ክርስቲያናዊ ብስለት ቀጣይ የሆነን መንፈሳዊ እድገትን ያካትታል። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ውሳኔ ባደረግክ በእያንዳንዱ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወትህ እድገትን ትለማመዳለህ።

## ብልጽግናና ድህነት

*ዓላማ 5 ከብልጽግናና ከድህነት ጋር ለሚያያዙ ችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔዎችን ለመለየት።*

ገንዘብ ምንም ዓይነት ክፋትን የማያመጣ ነገር ይመስላል። አካላዊ ምቾትን፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ይገዛል፤ ከፈቀድንለት ጥሩን ነገር ያደርግልናል። ይሁንና በ1ጢሞ. 6:10 "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፣. . ." በማለት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰማይ ከሚናገረው ይልቅ በገንዘብ ምክንያት ስለሚመጣው መሳትና ክፉ ፈተና አብዝቶ ይናገራል።

ሰዎች ንብረትን ለራሳቸው ለማግኘት ሲሉ በሌላ ሰው ላይ ሁሉን ዓይነት ክፋትን ስለሚፈጽሙና በዚሁም የበደለኝነት ስሜት ስለሚሰማቸው ብልጽግናንና ድህነትን ከማኅበራዊ እግሮች ውስጥ አካተናቸዋል። ይህ ርዕስ ጉዳይ የሰው የሆነውን ነገር ከመመኘት (ስስታምነት) ጋር የተያያዘ ነው። ከብልጽግና ፍላጎትና ከድህነት ፍርሃት ጋር የተያያዙ በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚገኙትን ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ እዚህ ማካተት አስቸጋሪ ይሆናል። ይሁንና ይህ ትምህርት ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ችግሮችንና ከሌሎች ጋር ባለህ ግንኙነት የሚያመጣውን ተጽእኖ ለማስወገድ የሚረዱህን አንዳንድ መሠረታዊ መመሪያዎችን ይሰጥሃል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በመጀመሪያ ከብልጽግናና ከድህነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ከተመለከትን በኋላ በገንዘብ ላይ ባለን አመለካከትና ገንዘብ በእኛ በሚያደርግልን ላይ የተመሰረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔዎችን እንሰጣለን።

### ከብልጽግና ጋር የተያያዙ ችግሮች

❶. *ብልጽግና ባሪያ ያደርገናል።* ኢየሱስን ዘላለማዊ ሕይወት እንዴት እንደሚገኝ የጠየቀው ወጣት ሀብታም ሰው በብልጽግና ባርነት ውስጥ የነበረ በመሆኑ እያዘነ ሄደ (ማቴ. 19:16-22)። አንዳንድ ጊዜ ንብረቱን ከመቆጣጠር ይልቅ ንብረቱ እኛን ይቆጣጠረናል። ጊዜያችን በሙሉ፥

እቅርበናል። እያንዳንዱን መፍትሔ ከሚዛመደው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ጋር አዛምድ። የምርጫህን ቁጥር በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ ላይ ጻፍ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ለባለጠግነት ባርያ መሆን ማቴ. 19:21-22፥ 29 | 1. እግዚአብሔርን እመን። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ፈልግ የሚያስፈልግህን ይጨምርልሃል። |
| ለ. የበላይነት ስሜቶች ያዕ. 1:10 | 2. የእግዚአብሔር ሰው ከዚህ መሸሽና የእግዚአብሔርን ነገር መሻት ይኖርበታል። |
| ሐ. የተሰወጡ ወይም የተዛቡ እሴቶች ሉቃ. 12:32-34 | 3. እንደ እግዚአብሔር ልጅና የእግዚአብሔር አገልጋይነት ላለህ ከፍተኛ ስልጣን አመስጋኝ ሁን። |
| መ. ኃጢአትን ለመስራት፡ መፈተን 1ጢሞ. 6:9-11 | 4. ከምድራዊ ብልጽግና ይልቅ ዘለዓለማዊ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ላይ ትኩረት ይኑርህ፤ መዝገብህ ባለበት በዚያ ልብህ ይኑር |
| ሠ. ፍርሀትና ጭንቀት ማቴ. 6:25-34 | 5. እግዚአብሔርን መምሰል ባለህ ምድራዊ ብልጽግና የሚወሰን አይደለም። |
| ረ. ታማኝ ያለመሆን ፈተና ኢሳ. 33:15-16 | 8. ክርስቶስንና የእርሱን መንግሥት በሕይወትህ መጀመሪያ አድርግ። |
| ሰ. የበታችነት ሰሜቶች ያዕ. 1:9-10 | 7. እግዚአብሔር ምግብና መጠጥ ይሰጥሃል (እርሱ የሚያስፈልግህን ሁሉ ይስጥሃል)። |
| ሸ. ስለ እግዚአብሔር ሥጦታ የተሳሳቱ ሃሳቦች 1ጢሞ. 6:5-8 | 8. ራስህን እንደ አገልጋይ ተመልከት፥ በገንዘብህ አትመካ፣ በዝቅተኝነትህ ደስ ይበልህ። |

## ክርስቲያን ለገንዘብ ያለው ዋጋ

*ዓላማ 6 ክርስቲያን ገንዘብን በተመለከተ ሊኖረው ስለሚገባ ዋጋ መግለጫዎች ለመስጠትና ስህተቶችን ለማረም።*

ቁሳቁሳዊ ንብረቶችን በተመለከተ ሊኖረን ስለሚገባ ዋጋ ከዚህ በታች አንዳንድ አጠቃላይ መመርያዎች ቀርበዋል። እነዚህን አመለካከቶች በሕይወት ውስጥ ማዳበር እጅግ ብዙ ገንዘብ ወይም እጅግ አነስተኛ ገንዘብ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ለማስወገድ ይረዳሃል። የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንበብ ክፍሎችን ማንበብህን እርግጠኛ ሁን።

1. *የእግዚአብሔር ገንዘብ መጋቢ ወይም ባላደራ ነህ* (ሉቃ. 16:1-13)። ገንዘብን በተመለከተ በሚያከናውናቸው ነገሮች ታማኝ የሆነና የገቢውን የመጀመሪያ አንድ አስረኛ ለእግዚአብሔር መልሶ የሚሰጥ ክርስቲያን እንደሚባረክ ጽኑ እምነት አለኝ (ሚል. 3:8-11 ተመልከት)። እኛ ሕይወታችንን ለሱ አሳልፈን ስንሰጥ እግዚአብሔር ለየዕለቱ የሚያስፈልገንን ነገሮች ሊሰጠን ራሱን ግዴታ ውስጥ ከቷል። ግዴታዎችህን ለማሟላት ሁልጊዜ ገንዘብ የሚያስፈልግህ ሆኖ የሚሰማህ ከሆነ ወይም ያለማቋረጥ ያልተጠበቁ የወጭ ችግሮች እንደ በሽታ፣ ከስራ መፈናቀል ካሰብህ



እንዲህ ብለህ ራስህን ጠይቅ። "ለእግዚአብሔር ገንዘብ ታማኝ መጋቢ ነኝ? ከእርሱ ካገኘሁ አንድ አስረኛውን መልሼ እሰጣለሁን? ፍላጐቶቼን ሁሉ እንደሚያሟላ እርሱን አምነዋለሁን?"

2. *ለአንተ የሚያስፈልጉህን ነገር የማሟላት የእግዚአብሔር ግዴታ አንተ ለእርሱ መንግሥት ባለህ ሙሉ መስጠት ላይ የተመሰረተ ነው።* በማቴ. 6:25-34 ኢየሱስ በመደጋገም "አትጨነቁ . . . " ይለናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ለችግር መፍትሔ ይሆን ዘንድ "አትጨነቁ" ብዬ መጻፍ ለእኔ የሚዋጥ አይደለም፥ ምክንያቱም የሚያስፈልጉህን ለማሟላት እኔ ኃይል የለኝምና። እርሱ ግን "እባርካለሁ" ብሎ ሲል ያንን ተስፋ ለመፈጸም ኃይል አለው፥ ያደርገዋል።

(10). የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብና በእያንዳንዱ እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ግዴታ ጻፍ።

ሀ. ፊልጵስዩስ 4:19 ለ. ማቴዎስ 6:25-34 ሐ. ዕብራ. 13:5-6

3. *ሀብት አያድንህም*። በፍርድ ቀን ብልጽግና ዋጋ የሌለው ይሆናል (ምሳ. 11:4፤ ማቴ. 6:19-20)

4. *ክርስቲያንን ሊያስደስተው የሚገባ ጥቅም እግዚአብሔርን መምሰልና ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት ነው* (ሉቃ. 12:15፤ 1ጢሞ. 6:6-7)።

5. *እውነተኛ ዋጋ ያላቸው ነገሮች፥ መንፈሳዊና ዘለዓለማዊ ዋጋዎች ናቸው* (ቆላ. 3:1-4)።

6. *ለእግዚአብሔር በልግስና መስጠት ከሀብታምም ሆነ ከድሀ የሚጠበቅ ተግባር መንፈስ ነው*። እግዚአብሔር የምትሰጠውን ብቻ ሳይሆን በእጅህ የቀረውን የሚቆጥር ነው። ኢየሱስ ድሀዋን መበለት በቤተ መቅደስ ውስጥ ባለጠጐች ከሚሰጡት በላይ ሰጠች አለ (ሉቃ. 21:1-4)። ሐዋርያው ጳውሎስ በመቄዶንያ ያሉ ድሀ ሰዎች "ከደስታቸው ብዛትና ከልግስናቸው ባለጠግነት" ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው ስለሰጡ ያመሰግናቸዋል (2ቆሮ. 8:1-5)።

ጳውሎስ ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ለኢየሱስ ሲያስረክብ ለነገሮች የሚሰጠው ዋጋ ተለውጦ ሁሉም አዲስ እንደሆነ ተረድቷል። መጀመሪያ በጣም አስፈላጊ የነበረውን ነገር እንደ ከንቱ ቆጥሮታል። ከክርስቶስና ከትንሣኤው ኃይል ጋር ግንኙነት ያላቸው ነገሮች ብቻ አስፈላጊና ትልቅ ቦታ ያላቸው ይሆናሉ (ፊልጵ. 3:7-10)። እያንዳንዱ አማኝ ይህ እውነት እንደሆነ ይረዳል። የዚህ ዓለም ነገሮችን እንጠቀማለን፥ ይሁንና በእነርሱ እንዋጥም (1ቆሮ. 7:31)። በልባችን ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ ለእግዚአብሔር መስጠት ደስታና የተለየ ጥቅም ነው፤ ምክንያቱም ለእርሱ የሚገባው ነው።

(11). **የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በጥንቃቄ አንብባቸው። በእያንዳንዱ ውስጥ ትክክል ያልሆነ ነገር አለ። ገንዘብን በተመለከተ ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባውን አመለካከት እንዲያንጸባርቁ አስተካክለህ እንደገና ጻፋቸው።**

**ሀ. አሁን ያለኝ የሀብት መጠን በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት በምሆንበት ጊዜ ትልቅ ጥቅምና ቦታ ይኖረዋል።**
**ለ. እግዚአብሔር ባለጠጋ ሰው በገንዘቡ ላይ ጥሩ መጋቢ ወይም ባላደራ ይሆን ዘንድ ይጠይቃል።**
**ሐ. እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰው ማንኛውንም ፍላጐት ያሟላ ዘንድ ራሱን ግዴታ ውስጥ ከቷል።**
**መ. እግዚአብሔር እንዲጠብቀንና እንዲንከባከበን በሕይወታችን ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ መስጠት አለብን።**
**ሠ. ልግስና ከባለጠጋ ሰው ብቻ የሚጠበቅ ነው።**

# ኢ-ፍትሐዊነት

***ዓላማ 7 የኢ-ፍትሐዊነት ሰለባ የሆነ ክርስቲያን ምን ዓይነት ምላሽ ሊኖረው እንደሚገባ መመሪያ ለማስቀመጥ።***

**እስካሁን የተነጋገርንባቸው በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ያሉ ችግሮች ከራሳችን አመለካከትና ባህሪ ጋር የተያያዙ ናቸው። አሁን ደግሞ ሁላችንም እየገጠመን ያለውንና ከቁጥጥራችን ውጪ ስለሆነው ችግር መነጋገር እንፈልጋለን። አንድ ሰው በማይገባ፣ በመጥፎ ወይም በተሳሳተ ሁኔታ ሲመለከትህ የኢ-ፍትሐዊነት ችግር ገጥሞሃል ማለት ነው።**

**ለምሳሌ፦ ከአንድ ክርስቲያን ወንድም ጋር በንግድ ጉዳይ ትገናኙና አንተን መጠቀሚያ በማድረግ በተገቢው ሁኔታ ነገሩን ለማስተካከል አሻፈረኝ ይላል። በስራ ቦታ ቀጣሪህ ከአንተ ከሚፈልገው በላይ ጠንክረህ ጥሩ ሥራ ስትሰራ፣ የቅርብ ኃላፊህ ለተሠራው ሥራ ምሥጋናውን ወይም ዋጋውን ሊወስድ ይችላል። ወይም ምናልባት አንተ ጥሩ ስራ እየሠራህ በአንተ የሚቀና አንድ የሥራ ባልደረባህ በሥራህ ላይ ስንፍናና ቸልተኝነት እንደምታሳይ አድርጎ ሊያሳብቅ ይችላል። በትምህርት ቤት ውስጥ በማታለል የተያዘ ጓደኛህ ምንም እንኳን አንተ ባታደርገውም እንዳታለልክ አድርጎ ይናገራል። ምናልባትም ከአንተ በጣም የሚያንስ የሥራ ብቃት ያለው አንድ ሰው ከፍተኛ እድገት በማግኘቱ፥ እድገቱ የሚገባው ለእኔ ነበር የሚል ስሜት ሊሰማህ ይችላል።**

**በአንተ ላይ ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ነገር የተሠራበትን ብዙ ጊዜያትን ልታስብ እንደምትችል እርግጠኛ ነኝ። አስፈላጊው ጥያቄ እንዴት ነው ምላሽ የምትሰጠው? ትቆጣለህን? ስህተት ለፈጸመብህ ሰው በጥላቻ ትናገረዋለህን? ራስህን ታገላለህን? ለራስህ ታዝናለህን? ወይም ለሚያዳምጥህ ሁሉ**



**አቤቱታህን ታቀርባለህ? ለራስህ "መብቶች" መቆምና መብቶችህን ለማስከበር መሞከር የተለመደ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ክርስቲያን ምላሽን መስጠት የሚገባው እንዴት ነው? ለኢ-ፍትሐዊነት የክርስቲያን መፍትሔ ምንድነው?**

**ፖሊስ በነበረበት ጊዜ ወደ ጌታ የመጣ ጳውሎስ የሚባል ጓደኛ ነበረኝ። ወዲያውኑ ሕይወቱ በደስታ ተሞላ፥ ለሚያገኘው ሰው ሁሉ በክርስቶስ ያገኘውን ልምምድ መመስከር ፈለገ። አለቃው ከነበረው የሃምሳ አለቃ በቀር ደስታውን የሚጋፋ አንዳችም ነገር አልነበረም። ጓደኛዬ በጠዋት ልቡ በዝማሬ ተሞልቶ ወደ ሥራ ሲገባ አለቃው ተኮሳትሮ ትችት የሞላበት የንቀት ሠላምታ ይሰጠዋል። ሃምሣ አለቃው የጳውሎስን ሕይወት ከንቱ ለማድረግ የወሰነ ይመስላል። የጳውሎስ ምላሽ ጸጥ በማለት፣ በውስጡ በንዴት በመቃጠልና አንዳችም ባለመተንፈስ አለቃውን ሊበቀል የሚችልባቸውን መንገዶች ብቻ ማሰብ ነበር። አንድ ማለዳ ለጳውሎስ ድንገት ሃሳብ በአእምሮው ፈለቀለት፦ "ለምንድነው ደስታዬንና ድሴን እንዲወስድ የምፈቅድለት? የእርሱ መጥፎ አመለካከት የራሱ ችግር ነው፥ የኔ አይደለም! የሃምሳ አለቃው ምንም ያድርገኝ በጌታ መደሰት አለብኝ" አለ። በውጤቱም ጳውሎስ ለሃምሣ አለቃው ፍቅርንና ርኅራኄን ያሳየው ጀመር፥ ወዲያውኑ መልካም ወዳጅ ሊያደርገው ቻለ። ጓደኛዬ ጳውሎስ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያለውን እውነት ተምሯል።**

> **ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፣ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና" (ማቴ.** 5:10-12)።

**ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በክፍለ ትምህርታችን መጀመሪያ ላይ የተናገርነውን ያተኩርበታል። እኛ የክርስቶስ አምባሳደሮችና ለዓለም የእርሱ ተወካዮች ነን። የኛ መልካም ባህሪ ለሰማያዊ አባታችንና ለእርሱ መንግሥት ክብርን ያመጣል።**

**በርግጥ ባለመግባባት የሚፈጠርን ኢ-ፍትሐዊነት ማስተካከል የሚቻልበት ጊዜዎች ይኖራሉ። ይሁንና ኢ-ፍትሐዊነት በሚከሰትበት ጊዜ ክርስቶስን በመምሰል ችግሩ ያንተ እንዳልሆነ ነገር ግን የሌላ እንደሆነ በማስተዋልና ለአንተ የሚጠነቀቅልህና በልብህም ድልን የሚሰጥህ ሰማያዊ አባት እንዳለህ በማስተዋል ምላሽን መስጠት ትችላለህ። አንዳንድ ጊዜ ጌታ የፍትህ መጓደልን እንድትሸከም ይፈቅዳል፥ ይሁንና ለአንተ ዘላለማዊ በጎነት ይጠቀምበታል።**

(12). **የፍትሕ መጓደል ሰለባ የሆነ ክርስቲያን ምላሽ ለመስጠት ሊመራበት የሚገባውን መርህ ግለጽ።**

ሮሜ 12ን በጸሎትና በጥንቃቄ እንድታነብ ከማደፋፈር በቀር ለዚህ ክፍለ ትምህርት የተሻለ መደምደሚያ የለኝም። ይህ ምዕራፍ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ለሚፈልጉ በጥቂት ጥቅሶች ውስጥ የተሟላ ትዕዛዝ ይሰጣል። ደጋግመህ አንብበውና ለግንኙነቶችህ ሁሉ መመሪያ ይሁን።

(13). የሙከራ ፈተናውን ከመሥራትህ በፊት በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ያሉ የተሰያዩ ችግሮችን ከልስ። አንተ በዚህ ወቅት እያለፍክበት ያሉ ችግሮች ከተጠቀሱ ዘርዝራቸው። ለእያንዳንዱም ችግር መፍትሔን ለመፈለግ ክፍለ ትምህርት 1-3 በመመልከት ለችግር መፍትሔ የሚሰጡ ክርስቲያናዊ መርሆዎችን ተግባራዊ አድርግ። የምትሰጠው መፍትሔ በቃሉ የተደገፈ መሆኑን እርግጠኛ ሁን። የዚህ መልመጃ ዓላማ የተማርካቸውን መመሪያዎች በግል ሕይወትህ እንድትለማመዳቸው ለመርዳት ነው። እንዲህ በማድረግህ መንፈሣዊ በረከት ታገኛለህ። መልመጃውን በሕይወትህ ላሉ ችግሮች መፍትሔ ለማግኘት ስትል ከልባዊ ፍላጎት እንደምትሠራው አምናለሁ።

በሚቀጥለው ክፍለ ትምህርታችን በቤተሰብ ግንኙነቶች ውስጥ ባሉ ችግሮች ላይ እንወያያለን። ይህም እያንዳንዱን ክርስቲያን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። በጥናትህ ጌታ እንዲባርክህ እመኝልሃለሁ።



## የሙከራ ፈተና

ምርጫ ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ የተሻለ መልስ አለ። ከመረጥከው መልስ ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

1. የሰውን መመኘት

ሀ. ታማኝ አለመሆን ነው።
ለ. ራስህን ከሌሎች ጋር ማወዳደር ነው።
ሐ. ሌላ ሰው ያለውን ነገር መመኘት ነው።
መ. የተሻለ ለመሆን መሞከር ነው።

2. ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበው ምን ዓይነት አገልግሎት ሊኖራቸው እንደሚገባ ለማሳየት ነው?

ሀ. አንዱ ሌላውን ማገልገል
ለ. መሪነት
ሐ. ታላቅ ተፈላጊነት
መ. ከፍተኛ የሥልጣን ቦታ

3. ለክርስቲያናዊ ብስለት መሰረት የሚሆነው

ሀ. ንስሐ
ለ. የፈቃድ ኃይል
ሐ. ጥንካሬህን መገንባት
መ. የእግዚአብሔር ኃይል

4. ከነዚህ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ከባለጠግነት ጋር የማይያያዘው ችግር የትኛው ነው?

ሀ. የበላይነት ስሜቶች
ለ. የበታችነት ስሜቶች
ሐ. የተዛቡ እሴቶች
መ. ኃጢአትን ለማድረግ መፈተን

5. ብልጽግና እሳት ነው፤ ምክንያቱም ሀብት

ሀ. ለዘለዓለም አይዘልቅም
ለ. አያረካም
ሐ. ደስታን አያመጣም
መ. አስፈላጊ እንደሆንክ እንዲሰማህ አያደርግም

6. የሰውን ነገር ላለመመኘት መፍትሔው ፍቅር ነው። ምክንያቱም ፍቅር
ሀ. አይታበይም
ለ. ያምናል
ሐ. ይታገሣል
መ. አይቀናም

7. ክርስቲያን ሥልጣኑን አድርጎ ከተመለከተ ከፍተኛ ደረጃንና መታወቅን አይሻም።

ሀ. ሥልጣን ማግኛ
ለ. ክርስቶስን ከፍ የሚያደርግበት
ሐ. በትህትና የሚያኖረው
መ. ዝቅ የሚልበት

8. የእግዚአብሔር ገንዘብ መጋቢ ወይም አስተዳዳሪ ወይም ባላደራ ለመሆን

ሀ. የምትችለውን ያህል ማግኘት ስትችል ነው።
ለ. የምትፈልገው ሁሉ ሲኖርህ ነው።
ሐ. ያለህን ሁሉ ነገር ሸጠህ ለድሃ መስጠት አለብህ።
መ. የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስቀደምና በለጋስነት መስጠት አለብህ።

9. የሚያስፈልግህን ሁሉ የመስጠት የእግዚአብሔር ግዴታ የተመሰረተው

ሀ. ለማድረግ ባለው ኃይል ላይ ነው።
ለ. የሚያስፈልጉህ ነገሮች አስፈላጊነት ላይ ነው።
ሐ. ለርሱ መንግሥት ያለህ መስጠት ላይ ነው።
መ. ስለ እነርሱ በመጨነቅህና ባለመጨነቅህ ነው።

10. ለኢ-ፍትሐዊነት ክርስቲያናዊ መፍትሔ

ሀ. ኢ-ፍትሐዊነቱን በክርስቶስ መንገድ ተመልከተውና በእርሱ ላይ ድልን እንደሚሰጥህ በእግዚአብሔር ታመን።
ለ. ያስቀየመህን ሰው እግዚአብሔር እንዲቀጣው ጸልይ።
ሐ. ለመብቶችህ መከበር ቁም።
መ. ያስቀየመህን ሰው ተበቀል።

እውነት-ሐሰት። መልሱ እውነት ከሆነ በክፍት ቦታው "እ" ሐሰት ከሆነ "ሐ" ብለህ ጻፍ።

11. ኢየሱስ የሚያገለግል ሰው፥ እንደሚገዛ ሰው እንዲሆን አስተምሯል።
12. ሰው ለሥራ የሚያሳየው የትጋት መጠን በስራው አስፈላጊነት ላይ ይወሰናል።
13. የእውነተኛ አገልጋይ አመለካከት "ላደርገው የሚገባኝን ብቻ ነው የፈጸምኩት" የሚል ነው።
14. ጥሩ ስራ በማከናወኑ አንድን ሰው ማመስገን ስሕተት ነው።
15. የበሰለ ክርስቲያን ከችግሮች ነጻ ነው።
16. ክርስቲያናዊ ብስለትን ለማግኘት የተሻለው መንገድ እንድትበስል የሚረዱህን ነገሮች ማድረግ ነው።
17. ክርስቲያናዊ ብስለትን እንድናገኝ ማድረግ የሚገቡንን ብዙ ነገሮች እግዚአብሔር ሰጥቶናል።
18. ታዛዦች በመሆን የፈቃድ ኃይላችንን ውጤታማ እናደርገዋለን።
19. የብልጥግና እደጋው እግዚአብሔርን ከመታመን ይልቅ ሀብታችንን መታመን ነው።
20. ትልቅ እምነት ካለህ ሀብታም ትሆናለህ።



## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7. ሀ. ሐሰት    ሐ. እውነት    ሠ. እውነት
   ለ. እውነት    መ. እውነት    ረ. ሐሰት

1. መፍትሔው ፍቅር ሲሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ 1ቆር. 13 ነው (ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል፣ ሁሉን ይታገሣል፣ ያምናል፣ ተስፋ ያደርጋል። በሁሉ ይጸናል። አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ አይቀናም፣ አይመካም፣ በደልን አይቆጥርም፣ ስለዓመጻ ደስ አይለውም፣ ለዘወትር አይወድቅም)

8. ሀ

2. መልሶችህ በሕይወትህ ውስጥ ያለውን የሌላውን ሰው የመመኘትን ማንኛውንም ችግር ይገልጣልን? ከሆነ ይህንን ችግር ለማስተካከልና ተገቢ የሆነውን አመለካከት ለማዳበር እውነተኛን ፍላጐት ይዘህ ችግርን መፍትሔ መስጫ ደረጃዎችን ትመለከት ዘንድ እመክርሃለሁ። እነዚህ ደረጃዎች በክፍለ ትምህርት 3 ውስጥ ነው የተሰጡት።

9. ሀ. 6    ሐ. 4    ሠ. 1    ሰ. 3
   ለ. 8    መ. 2    ረ. 7    ሸ. 5

3. ሀ. እውነት    ሐ. እውነት    ሠ. ሐሰት    ሰ. ሐሰት
   ለ. ሐሰት    መ. እውነት    ረ. እውነት    ሸ. እውነት

10. ሀ. የሚያስፈልጉህን ነገሮች ሁሉ እርሱ ያሟላልሃል።
   ለ. በሕይወትህ የእርሱን መንግሥት ካስቀደምክ፥ የሚያስፈልግህን ነገሮች ሁሉ ይሰጥሃል።
   ሐ. እርሱ በፍጹም አይተውህም፣ አይጥልህም።

4. ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምረው የነበረውን ትምህርት መልስ "ለ" በትክክል ይገልጠዋል። ሌሎቹ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የሚቃረኑና የተሳሳቱ አመለካከቶችን ይወክላሉ።

11. ሀ. ያለኝ የሀብት ብዛት በእግዚአብሔር ፊት ስቀርብ ዋጋ የለውም።
   ለ. እግዚአብሔር ሀብታምና ድሀ በገንዘባቸው ላይ ጥሩ መጋቢ ይሆኑ ዘንድ ይፈልጋል።
   ሐ. በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት መጀመሪያ ላደረጉ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያሟላ ዘንድ ራሱን ግዴታ ውስጥ ከቷል።
   መ. እግዚአብሔርን በሕይወታችን ቀዳሚውን ስፍራ መስጠትና ይጠብቀን ዘንድ ልንታመነው እንችላለን።
   ሠ. ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ሀብታምም ሆነ ድሀ የልግስና መንፈስ እንዲኖረው ይገባል።

5. ሀ. 8 መ. 9 ሰ. 4 በ. 3
ለ. 5 ሠ. 1 ሸ. 2 ተ. 7
ሐ. 11 ረ. 6 ቀ. 10

12. የአንተ መልስ። እነዚህን ሐሳቦች ያካተተ መሆን አለበት። ለማንኛውም የፍትህ መጓደል፥ ክርስቲያን ለእርሱ ለሚጠነቀቀው ሰማያዊ አባቱ ተወካይ መሆኑን በማስታወስ፥ ክርስቶስን በመለለ መንገድ ምላሽን መስጠት ይችላል።

6. ለ

13. የአንተ መልስ።



# 5 ትምህርት

# የቤተሰብ ችግሮች

አንድ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ የስምንት ዓመት እድሜ ያላቸውን ተማሪዎች መንግሥተ ሰማያት ምን እንደሚመስል ለማስረዳት ትሞክር ነበር። ውይይቱንም እንዲህ በማለት ደመደመች "መንግሥተ ሰማያትን ከኔ ቤት ጋር ማወዳደር እወዳለሁ። በፍቅር የተሞላ ቦታ፣ ሰላምና ተቀባይነትን ላገኝ የምችልበት ስፍራ፥ አዎ መንግሥተ ሰማያት በቤት ውስጥ እንደመሆን ነው።"

ከተማሪዎቹ መካከል አንዱ ትንሽ ልጅ ባፈጠጡ ዓይኖቹና በተኮሳተረ ፊት ወደ እርሷ ተመልክቶ "መንግሥተ ሰማያት ልክ እንደኔ ቤት ከሆነ ወደዚያ መሄድን ከቶ አልፈልግም" አላት።

ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ ቤተሰብ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሰው ሥርዐትና በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ስርዐት መሠረታቸው በቤተሰብ ውስጥ ያለው ሥርዐት ነው። እግዚአብሔር፥ ባል፣ ሚስትና ልጆች ለሚኖራቸው ኃላፊነት የተለየ መመሪያዎችን ሰጥቷል። እነዚህ መመሪያዎች ሲፈጸሙ፥ ቤተሰብ ጠንካራ ይሆናል፤ እያንዳንዱ አባል ሙሉ ደስታን ያገኛል። ከእነዚህ መመሪያዎች አንዳቸውም ቸል ቢባሉ ቤተሰቡ በችግር ውስጥ ሊሆንና እንዲሁም መለያየት ሊከሰት ይችላል።

በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የዓለማችን ክፍል ቤተሰብ በርግጥ በችግር ውስጥ ነው ያለው። በአንዳንድ ሀገሮች ከሚፈጽሙት ጋብቻዎች ውስጥ ሀምሳ በመቶ የሚሆኑት በፍቺ ይፈጸማሉ። በሌሎች ሀገሮች የሚስት ሥፍራ ከቤት ውስጥ አገልጋይ በመጠኑ ብቻ ከፍ ያለ ነው። ደስተኛ ባልሆነ ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ልጆች በሚያገቡበት ወቅት ተመሳሳይ የሆነን ደስታ የማይሰፍንበትን ቤተሰብ ይመሰርታሉ። የቤተሰብን አንድነት የሚያውኩ አንዳንድ ችግሮች ምንድናቸው? መጽሐፍ ቅዱስስ ስለ እነዚህ ጉዳዮች ምን ይላል? ይህ የክፍለ ትምህርት 5 ርዕሳችን ነው። መንግሥተ ሰማያት እንደ አንተ ቤት ቢሆን፥ ወደዚያ መሄድን ትሻለህ? ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠና ተገቢ በሆነ ቦታ ላይ በግል ሕይወትህ ተግባራዊ ታደርግ ዘንድ አበረታታሃለሁ።

(1). ከላይ ላነበብናቸው ጥያቄዎች የተሻለ መልስ ይሆናል ብለህ የምታስበው የትኛው ነው?

ሀ. በእነዚህ በእያንዳንዱ ምሳሌዎች ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ስምምነቶች ሊኖሩ ይችላሉ።
ለ. ተጻራሪ የሆኑ ግምቶች ስላሉአቸው በእነዚህ በማናቸውም መካከል ምንም ዓይነት ስምምነት ሊኖር አይችልም።
ሐ. እያንዳንዱ የሌላውን ደንቦች እስካከበረ ድረስ በአንድነት መስራት ይችላሉ።

በእርግጥ የእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልስ እውነትና ሐሰት፣ ብርሀንና ጨለማ፣ ክርስቶስና ሰይጣን መስማማት ወይም ጓደኞሞች መሆን አይችሉም ነው። አማኝና የማያምን ሰው ለሰዎች አስፈላጊ በሆኑ መሠረታዊ ነገሮች በቀር ሊመሳሰሉበት የሚችል አንዳች ነገር የላቸውም። ጋብቻን በጣም የፈለገ ወጣትና ይህንን አስፈላጊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ቸል ለማለት የፈቀደ፥ ሕይወቱን ለችግርና ልቡን ለማቁሰል መዳረጉ ነው። የእግዚአብሔር መንገድ ተወዳዳሪ የሌለው ከመሆኑም ባሻገር እሱን ከታዘዝነው የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ እሱ ያሟላልናል። በሚቀጥለው ክፍለ ትምህርት ውስጥ ያላገባ ሰው ችግሮች ላይ በሚያተኩረው ትምህርት ውስጥ ሰፋ ባለ መልኩ እንነጋገራለን።

ያላመነ (ች) ያገባ ክርስቲያንን፣ ምናልባትም ክርስቲያን ከመሆኑ ቀደም ብሎ ሊሆን ይችላል፥ በሚመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 7:12-16 አንዳንድ የተለዩ ትዕዛዞችን ሰጥቷል። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምታነብ ከሆነ የማያምነው የትዳር ጓደኛ መቀጠል እስከፈለገ ድረስ ክርስቲያኑ በጋብቻው ጸንቶ መቆም እንዳለበት ሲያበረታታ ታገኘዋለህ። ክርስቲያኑ መለያየትን የሚሻ መሆን የለበትም። እግዚአብሔር የሚያስፈልገውን ጸጋና ፍቅር ሊሰጠው ይችላል፥ ማን ያውቃል የማያምነው ሰው በመጨረሻ ሊድን ይችላል። "የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ወንድም ቢሆን ወይም እኅት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም። እግዚአብሔር ግን በሰላም ጠርቶናል" (1ቆሮ. 7:15)።

(2). አሁን በተገለጸው ሁኔታ ውስጥ ክርስቲያን ከማያምን ሰው ጋር በጋብቻ መጽናት እንዳለበት ትዕዛዝ የተሰጠው ለምንድነው ብለህ ታስባለህ? (ማቴ. 19:4-6ን ተመልከት)።

በብዙ ቤቶች ውስጥ የመንፈሳዊ መሪነትን ኃላፊነት መቀበል ያለባት እናት ነች ተብሎ ይታሰባል። ይህ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ነው፤ እግዚአብሔር ባል የቤት ራስ እንዲሆን ሲል ይህ መንፈሳዊ መሪነትንም ያጠቃልላል። ልጆች ብዙውን ጊዜ የአባታቸውን ምሳሌነት ይመለከታሉ። አባትም ቤተሰቡ ከእርሱ መንፈሳዊ ደረጃ በላይ ከፍ ይሉ ዘንድ አይጠብቅም።



በቤተሰብ ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ ችግሮች መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን በመታዘዝ ብቻ ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ በቤተሰብ ውስጥ በሥራ ላይ የሚውሉ ክርስቲያናዊ መርሆችን እንወያያለን። በቤተሰብ ሕይወት አካባቢ ችግር ካለብህ እነዚህን መርሆዎች በራስህ ሕይወት ተግባራዊ በማድረግ ልትለውጣቸው ትችላለህ።

(3). በባልና በሚስት መካከል ያለውን መንፈሳዊ ልዩነቶች ለማስተካከል ወይም ለመከላከል የሚረዱ ሁለት መሠረታዊ መርሆዎችን ተወያይተናል። በራስህ አባባል አስቀምጣቸው።

## የወሲብ ፍላጐቶች መለያየት

*ዓላማ 2 ባለትዳሮች የግብረ ሥጋ ፍላጐትን በተመለከተ የሚገጥማቸውን ልዩነቶች ለመፍታት የሚችሉበትን አመለካከት ለመለየት።*

አንዳንድ ጊዜ በጋብቻ ውስጥ የአንደኛው የትዳር አጋር የወሲብ ፍላጐት ከሌላኛው የበለጠ ነው። በመስማማት ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በቀር፥ የወሲብ ግንኙነትን መካድ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚቃረን ነው (1ቆሮ. 7:5)። አንዱ ሌላውን ማስደሰት የሚፈልጉ ባልና ሚስት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አንዱ ለሌላው የሚገዛ መሆን አለበት (1ቆሮ. 7:3-4)። ደግሞም አንዱ የሌላውን ፍላጎት የሚያስተውልና ንቁ መሆን አለበት። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምንም እንኳን የጋብቻ ግብ ባይሆንም አንዱ የፍቅርና የመዋደድ መግለጫ ነው።

በጋብቻ ውስጥ ያለ የወሲብ ግንኙነትን በተመለከተ በክፍለ ትምህርት 7 ሰፋ ባለ ሁኔታ እንወያይበታለን። በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የሚከተሉ ባለትዳሮች በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት በሌሎች ጉዳዮችም ላይ ያሏቸውን ችግሮች ለማቃለልና አንድነትን ለመፍጠር የሚረዳ ሆኖ ያገኙታል።

(4). ከቀረቡት አስተያየቶች ውስጥ የትዳር ጓደኞሞችን የወሲብ ፍላጎት መለያየት ችግር ለመፍታት በበለጠ ሁኔታ የሚረዳው የትኛው ነው?

ሀ. ሁልጊዜ ተገገር የሆነች ሚስት
ለ. አንዱ ሌላውን የማስደሰት ፍላጐት
ሐ. በመስማማት የወሲብ ግንኙነትን በጣም የተወሰነ ማድረግ

## ታማኝነትን ማጉደል

*ዓላማ 3 ዝሙትን በተመለከተ የክርስቲያን ምላሽ ምን መምሰል እንደ ሚገባው የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ለማየት።*

ምናልባት ትዳርን በከፍተኛ ሁኔታ ከሚጐዳው ዋነኛ ችግር ታማኝ አለመሆን (ዝሙት) ነው። ይህም በክፍለ ትምህርት 7 የምንወያይበት ነው። በክፍለ ትምህርት 2 እንደተመለከትነው ዝሙት በብሉይ ኪዳንም ይሁን በአዲስ ኪዳን በጥብቅ የተከለከለ ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ዝሙትን ልንመለከተው የምንፈልገው ከንጹሁ ወይም ከተበዳዩ የትዳር ጓደኛ አንጻር ነው። የትዳር ጓደኛ ዝሙትን ቢፈፅም እንዴት ነው ምላሽ የምትሰጠው ወዲያውኑ ወደፍቺ ትሄዳለህ? በደሉ በተደጋጋሚ ቢቀጥል በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ትቆያለህን? ይህን ችግር መመልከት የሚገቡን ሦስት አቅጣጫዎች አሉ።

1. የትዳር ጓደኛሽ (ህ) በተደጋጋሚ የዝሙትን ተግባር ከፈጸመ በትዳር የመቀጠል ግዴታ ሊኖር ይችላልን? በማቴ. 19:9 በሚገኙት የኢየሱስ ቃሎች መሠረት ፍች በዝሙት ምክንያት ብቻ የተፈቀደ ነው። "እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል" ስለዚህም ባል ወይም ሚስት ታማኝ ካልሆነች ከትዳር ጓደኛ ጋር ለመቀጠል ምንም ዓይነት ግዴጅ የለባቸውም።

2. ጋብቻው ታማኝ ካለመሆን የተነሳ ከፈረሰ በደል የደረሰበት የትዳር ጓደኛ እንደገና ማግባት ይችላልን? የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በተሰጠው የምንባብ ክፍል አተረጓጉም አይስማሙም። አንዳንዶች በማቴ. 19:9 ያሉት የኢየሱስ ቃሎች በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ዳግም ጋብቻን ይፈቅዳል ይላሉ። በእነርሱ አተረጓጉም መሰረት አንድ ጊዜ አንድ ሰው ዝሙትን ከፈጸመ ከትዳር ጓደኛው ጋር "አንድ ሥጋ" የሚያደርጋቸውን አንድነት አፍርሶታል። ስለዚህ ሌላኛው የትዳር አጋር በዚህ አንድነት ሊታሰር አይችልም። ምክንያቱ ይህ ከሆነ የተጐዳው የትዳር አጋር በአንዳንድ ሁኔታዎች ከጋብቻ ያልታገደ ሌላ ሰው ለማግባት ነፃ ይሆናል።

ሌላው አተረጓጉም በዝሙት ምክንያት ፍች የተፈቀደ ሲሆን ዳግም ጋብቻ ግን የተፈቀደ አይደለም የሚል ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሰፋ ባለ መልኩ በፍቺ ርዕስ ላይ እንነጋገራለን።

3. ለዝሙት ተግባር ብዙ ነገሮች የራሳቸውን ድርሻ ሊያበረክቱ ይችላሉ። እንደኛው የጋብቻ አጋር የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ምናልባት ይከላከል ይሆናል። ይህ ደግሞ እሱን ወይንም እሷን ፍላጐታቸውን ለማሟላት ወደሌላ እንዲመለከቱ ምክንያት ይሆናል። በመንፈሳዊ ነገር ያልተዘጋጀ የትዳር አጋር ወደፈተና ውስጥ የሚገባበት ጊዜያት ሊኖሩ ይችላሉ። በርግጥ ሁሉም ኃጢአት ስለሆነ እግዚአብሔር የትኛውንም ተግባር ከምክንያቱ የተነሣ ይቅር አይለውም። ነገር ግን ታማኝ ያልሆነው የትዳር አጋር በሥራው ከልብ ተጸጽቶ ኃጢአቱን ቢናዘዝ የተጐዳው የትዳር ጓደኛ ይቅር ማለትና የግንኙነት አንድነታቸውን ማደስ ይኖርበታልን?



ይህ ምናልባት አንድ ሰው በሕይወት ውስጥ ሊገጥመው ከሚችለውና ይቅርታን ለመስጠት እጅግ አስቸጋሪ ከሆነው በደል ውስጥ አንዱ ነው። የተጎዳው ሰው ሐዘኑ ወደ ውስጥ ዘልቆ ሊሰማውና ልቡ ሊሰበር ስለሚችል እንደገና ማመን ያስቸግረዋል። ነገር ግን የይቅርታ መርህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ሁሉ ኃይልን ካዘሉ ትምህርቶች አንደኛው ነው። ክርስቶስ ይቅርታን ብቻ አላስተማረም (ማር. 6:14)። ነገር ግን እሱ ራሱ ይቅር ብሏል (ሉቃ. 7:47-50)። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል። ነገር ግን ኃጢአተኞችን አብዝቶ ስለሚወድ የሚወደውን ልጁን እንዲቀበል፣ እንዲሰደብና ኃጢአታችንም ይቅር ይባል ዘንድ በእንጨት መስቀል ላይ እንዲሰቀል ፈቀደ። ክርስቶስ በዝሙት ኃጢአት የተያዘችውን ሴት ይቅር አላት (ዮሐ. 8:3-11)።

ክርስቶስ ለእኛ እንዳሳየን የይቅርታ መጠንን ለትዳር ጓደኞችንም ከማሳየት በላይ ምን ዓይነት ታላቅ ፍቅር ሊገኝ ይቻላል? ትዳሩ ከመፍረስ የሚድን፣ ቤተሰቡ ከመበታተን የሚጠበቅ ከሆነ፣ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላውና ለጌታ ቃል ኪዳናቸው ማደስ የሚችሉ ከሆነ፥ ይቅር ማለት የቻለውን ሰው እግዚአብሔር ይባርከዋል። ከእንደዚህ ዓይነት የይቅርታ ጊዜ በኋላ፥ የትኛውም የትዳር ጓደኛ ስለጉዳዩ እርስ በርስ ወይም ከሌላ ሰው ጋር እንደገና በማንሳት መወያየት የለባቸውም። ወደዚህ ኃጢአት ውስጥ የከተተን የሰይጣን ኃይል እንደሆነ ከማሰብ በቀር የተፈጠረው ሁኔታ ይቅር መባል አለበት፥ መረሳትም አለበት።

(5). ከነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ክርስቲያን የሱ ወይም የርሷ የትዳር ጓደኛ ዝሙትን ቢፈፅም እንዴት መመለስ እንደሚገባቸው የሚያሳዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን የያዙት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ክርስቲያን ከትዳር ጓደኛው ጋር መቀጠል አለበት።
ለ. አንደኛው የትዳር ጓደኛ ዝሙትን ከፈጸመ ሌላኛው እንዲፈታና ሌላ ክርስቲያን እንዲያገባ ይገደዳል።
ሐ. አንድ የትዳር ጓደኛ የዝሙትን ኃጢአት ከፈጸመ ሌላኛው ለመለየት ነጻ ነው።
መ. የዝሙት ኃጢአት ይቅር ሊባል ቃል ኪዳኑም ሊታደስ ይቻላል።

(6). አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በማቴ. 19:9 የሚገኘውን የኢየ
• ሱስን ትምህርት ፈቃድ እንደሆነ አድርገው ይተረጉሙታል።

ሀ. ዝሙት ያደረገ የትዳር ጓደኛ እንዲፈታና እንደገና እንዲያገባ
ለ. በደል የደረሰበት የትዳር ጓደኛ እንዲፈታና እንደገና እንዲያገባ
ሐ. ሁለቱም የትዳር ጓደኛሞች እንደገና እንዲያገቡ

## ፍች

*ዓላማ 4 ክርስቲያን ተግባራዊ የሚያደርጋቸው የፍችን አጠቃላይ መመርያ ለመግለጽ።*

ፍችን በተመለከተ የእግዚአብሔር ሃሳብ በሚልክያስ 2:13-16 በግልጽ ተቀምጧል። "ፍችን እጠላለሁ ይላል የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር፤ ልብሱን በግፍ ድርጊት የሚሸፍነውንም ሰው እጠላለሁ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት። ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤ ታማኝነታችሁም አይጓደል።"

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ታማኝ ሊሆኑ የሚገባበትን አንዱን ምክንያት እግዚአብሔር ሲገልጽ ልጆቻቸው እውነተኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይሆኑ ዘንድ ነው። በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ የሚገኙ ልጆች በተለየ መልኩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። የፍች ሰለባ በሆኑ ልጆች ላይ ከፍተኛ ችግሮች ይነሱባቸዋል። በተለያዩ ወንጀሎች በመሳተፋቸው በጥበቃ ሥር የተቀመጡ አርባ ወጣት አጥፊዎችን ያስተማረ መጋቢ አውቃለሁ። መጋቢው እነዚህ ሁሉ ልጆች ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር እንዳለ ነገረኝ፤ ይህም ነገር የሁሉም ወላጆች የተፋቱ መሆናቸው ነበር። በእርግጥ ወላጆቻቸው የተፋቱ ልጆች ሁሉ ወደ ወንጀል ፊታቸውን አያዞሩም። ይሁንና ብዙዎቹ በአንድ መንገድ ይሁን በሌላ በዚህ ሁኔታ ይሰቃያሉ።

የፍች አጠቃላይ መመሪያ እነዚህ ናቸው፦

1. ፍቺ ለክርስቲያን የተከለከለ ነው (1ቆሮ. 7:10-11)
2. ከተፋቱ ሰዎች ጋር የሚከናወን ጋብቻ የተከለከለ ነው (ሉቃ. 16:18፤ ማቴ. 5:32፣ 19:9 እና 1ቆሮ. 7:11)
3. የተፋቱ ሰዎች እንደገና ማግባት አይችሉም (1ቆሮ. 7:10-11)።

ቀደም ሲል በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ፍችና ዳግም ጋብቻ ለክርስቲያን ሊፈቀድ የሚችልበትን አንድ ምክንያት ተወያይተናል። በዚህም ሁኔታ ውስጥ እንኳን ሲከናወን መከራ ማስከተሉ የማይቀር ነው፤ የልጆች ሕይወትና የክርስቲያናዊ ምስክርነት ማበላሸትን ዋጋ ያስከፍላል።

ፍች ከተከሰተ በኋላ አንደኛው የትዳር ጓደኛ እንደገና በማግባቱ የጋብቻን ቃል ኪዳን ማደስ በማይቻልበት ጊዜ የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ለተፈታው ወገን የመጽናናትና የርዳታ ምንጭ ሊሆንለት ይችላል። እግዚአብሔር ወደ እርሱ ርዳታ ፍለጋ በሚጮኹት ላይ ጀርባውን አያዞርም። ሕይወትን እንደገና ለማበጀትና ፍች ያስከተላቸውን ችግሮች ለማስወገድ ብርታትን ይሰጣል። በክፍለ ትምህርት 6 ይህንን ጉዳይ ከተፈታው ሰው አቅጣጫ እንመለከተዋለን።



ከብዙ ዓመታት በፊት በሌላ ትዳር ፍቺ የገጠማቸው ሁለት ሰዎች ተገናኝተው እንደተጋቡ አውቃለሁ። ከተጋቡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ክርስቲያን ሆኑ። ባልየው ፈትቶ በማግባቱ፥ በሁለተኛ ጋብቻው ውስጥ የሚኖረው የማመንዘር ኑሮ እንደሆነ በማሰብ የበደለኝነት ስሜት እየተሰማው ተቸገረ። ይህንን የመሰለን ሁኔታ በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ትዕዛዝን ሰጥቷል።

(7). 1ቆሮ. 7:17-24ን አንብብ። ከላይ ለተገለጠው ክስተት ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እንዴት ተግባራዊ ይሆናል?

(8). ቀደም ያሉ ትምህርቶችን ሳትመለከት ፍችን በተመለከተ ለክርስቲያን ተግባራዊ የሚሆኑ አጠቃላይ መመሪያዎችን አስቀምጥ።

## ሌሎች የጋብቻ ችግሮች

*ዓላማ 5 ለእያንዳንዱ ችግር ትክክለኛውን መፍትሔ ከችግሩ ክስተት ጋር ለማዛመድ።*

በቤት ውስጥ አለመደሰትንና መለያየትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ብዙ ሌሎች ችግሮችን በዚህ ቦታ በግልፅ እንጠቅሳለን።

1. *አንዱ ሌላውን የማክበርና የመተማመን ጉድለት።* በሌሎች ሰዎች ፊት ሚስቱን በማዋረድ ደስ የሚለው የሚመስልን አንድ ባል አውቃለሁ። በሌሎች ሰዎች ፊት የሚናገረውን በመቃወም ወይም በማረም፥ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ባሏን ዝቅ ዝቅ ማድረግ፥ የምትሻ የምትመስልን ሚስትም አውቃለሁ። ምናልባት ይህንን ዘዴ የሚጠቀሙበት ምክንያት የባላቸው (የሚስታቸው) ፍቅርን ያለማሳየትና፣ ያለመገዛት ምላሽ ለመስጠት ይሆናል። ይሁንና በማንኙነት ውስጥ የሚከሰቱትን ችግሮች ለመፍታት ይህ ክርስቲያናዊ መንገድ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በወደደበት መጠን ባል ሚስቱን መውደድ ይገባዋል (ኤፌ. 5:25-28) ሚስትም ባሏን መፍራትና ማክበር ይገባታል (ኤፌ. 5:33) የሚለው ነው።

ባልም ሆነ ሚስት ሌላው የቅናት ስሜት ሊፈጥርበት የሚችልበትን ማናቸውንም ምክንያት ማከናወን የለበትም። ይህ ችግር ያለባቸው ክርስቲያን ባለትዳሮች በግልጽ መወያየትና የቅናት ስሜት እንዲፈጠር የሚጋብዙ ማናቸውንም ሁኔታዎች ማስወገድ አለባቸው። ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው በተከታታይ የሚቀና ሰው እንደዚህ ዓይነት ስሜቶችን እንዲያስወግድና በትዳር ጓደኛው ላይ ያለውን እምነት እንዲያዳብር እንዲረዳው ጌታን መጠየቅ ይገባዋል።

ሐ. እርስ በእርስ መተማመንና የሚታመን መሆን
መ. ብዙውን ጊዜ ከቤተሰብ ጋር ማሳለፍ
ሠ. ክርስቲያናዊ መርሆዎችን መታዘዝና እንድነትን ማሳየት
ረ. ሰው የመጀመሪያውን ቅድሚያ መስጠት የሚገባው ለራሱ ቤተሰብ ፍላጐት ሲሆን በመቀጠልም የቅርብ ዘመዶችን ከበድ ያሉ ችግሮችን ነው
ሰ. አንዱ ለሌላው ማካፈል

3. የገንዘብ ችግሮች
4. አለማክበር
5. ልጆችን በማሠልጠን ያለ ልዩነት
6. የተግባቦት ጉድለት
7. ቅናት

## የልጆች ችግሮች

*ዓላማ 6 ወላጆች ልጆችን በማሠልጠን ሊኖራቸው የሚገባውን ኃላፊነት ለመግለጽ።*

### አለመታዘዝ

የልጆች ለወላጆች አለመታዘዝ አንዱ የመጨረሻው ዘመን ምልክት ነው። የተስፋ ቃል ያለው ብቸኛው ትእዛዝ ይህ ነው። "እባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር እድሜህ እንዲረዝም" (ዘጸ. 20:12)። ልጆች ወላጆቻቸው ከሚያቀርቡላቸው ጠንቃቃ ምሪትና ሥነ ሥርዓት መታዘዝን መማር አለባቸው። "ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው፤ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" (ምሳ. 22:6)። ሥልጠና ድንገት የሚከሰት አይደለም። ውሳኔንና የሚከሰተውን ሁኔታ ለመቆጣጠር ፈቃደኝነትን ይጠይቃል። "ያልተቀጣ ብላቴና ግን እናቱን ያሳፍራል" (ምሳ. 29:15)። ወላጆች ልጆቻቸውን በወጣትነት ጊዜያቸው የመቆጣጠር መብት እንዲኖራቸው ከፈለጉ፥ በልጅነታቸው የሕይወት ዘመናት አለመታዘዝን መፍቀድ አይኖርባቸውም።

ዛሬ የብዙ ወላጆች ልብ በአመጸኛ ወጣት ልጆቻቸው የተነሳ አዝኗል። ሐዘኑን ደግሞ የሚያባብሰው የወጣቶቹ አደንዛዥ እጾችን ወይም የአልኮል ውጤቶችን መሰማመድ ወይም ደግሞ የወሲብ ግንኙነት ልምምዶች ውስጥ መግባታቸው ነው። ክርስቲያን ወላጆች ያላገባች ልጃቸው በማርገዟ ወይም ልጃቸው የእጸ ሱሰኛ በመሆኗ ወይም ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በማያስከብር መንገድ እርካታን ፈልገው ቤታቸውን ትተው በመሄዳቸው ሊቸገሩና ሲጎዱ ቤተክርስቲያንም የዚህ ተፅእኖ ተካፋይ ትሆናለች።

ቤተሰብህ በእንደዚህ ዓይነት ችግር የሚሰቃይ ከሆነ እምነትህን እንድታጠነክርና ተስፋ እንዳትቆርጥ አበረታታሃለሁ። እግዚአብሔር ስለ



አንተ ያስባልና የአንተንም አመጸኛ ልጅ ይወደዋል። በሉቃ. 15:11-32 ላይ ከሚገኘው ከአባካኙ ልጅ ታሪክ መጽናናትን ታገኛለህ።

በዚህ ታሪክ ውስጥ አባትየው ልጁን ቤቱን ትቶ ከመሄዱ ለመከላከል አልሞከረም። ይሁንና ልጁ ሲሄድ ሲመለከት ልቡ በከፍተኛ ሁኔታ አዝኖ ነበር። ቀንና ሌሊትም እንደ ጸለየ እምናለሁ። በተከሰተው ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ለእርሱ መልካም አድርጐ ይሠራው ዘንድ መጠበቅን አላቋረጠም። በየቀኑ ምን ያህል ጊዜ ወደ መንገድ በመውጣት የልጁን መመለስ እንደጠበቀ ትገምታለህን? መጽሐፍ ቅዱስ፥ ገንዘቡን ሁሉ ካባከነና የነበረውን ነገር ሁሉ ካጣ በኋላ በመጨረሻ ልጁ ወደቤት ለመመለስ እንደወሰነ ይናገራል። "ተነሥቶም ወደአባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አቀፈውና ሳመው" (ቁ. 20)።

ክርስቲያን ወላጆች በምሳ. 22:6 ውስጥ ያለው የተስፋ ቃል መብታችን ነው ማለት ይችላሉ። ማድረግ የምትችለው ነገር ችግር ያለበትን ልጅ ለጌታ አሳልፈህ መስጠት ብቻ የሚሆንበት ጊዜ አለ፥ እርሱን ማመን ብቻ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ነገር ግን ልጅህ ለእርዳታ ወደ አንተ በመጣ ጊዜ ሁሉ ችግሩን ለማስወገድ ይችል ዘንድ ለመርዳት የተዘጋጀህ ሁን። አባት፥ ንስሃ የገባን ኃጢአተኛ በመልካም ይቀበላል። ምንም ያህል የከፋ ነገር ቢፈጽም ግድ አይለውም። ክርስቲያን ወላጆች አመጸኛ ልጆቻቸው እርዳታን በጠየቁ ጊዜ ፍቅርንና ርኅራኄን ማሳየት አለባቸው።

### የሥልጠናና የዲሲፕሊን መጓደል

ብዙ ጊዜ ወላጆች እናትም አባትም ከቤት ውጭ ሠራተኛ ይሆናሉ። እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ልጆችን የማሠልጠንና ሥርዓትን የማስያዝ ኃላፊነት ለመወጣት አቅማቸው ውስን ይሆናል። እግዚአብሔር ለእነርሱ የሰጣቸውን ኃላፊነት ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያንና ትምህርት ቤት እንድትፈጽምላቸው ይጠብቃሉ። ልጆችን ማሠልጠን ከበድ ያለ ሥራ ነው። እንዴት መኖር እንደሚገባው ብቻ በመናገር ልጅን መምራት አትችልም። እያንዳንዱን ስሕተት ለማስተካከል መልካም ጐኑንና ደካማ ጐኑን ለማሳየትና የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን እንድታስተምረው አብረኸው መሥራት አለብህ። ይህ ልጁ ቤቱን ለመልቀቅ ተገቢው እድሜ ላይ እስኪደርስና የጉልምስናን ኃላፊነት መቀበል እስኪችል ድረስ የሚዘልቅ ተግባር ነው።

### የፍቅርና የመረዳት ጉድለት

እያንዳንዱ ሰው የመፈቀርና የመወደድ ፍላጐት አለው። ፍቅራቸውን በማይገልጹ ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ልጆች ፍቅራቸውን ለሌላ ለመግለጽ አስቸጋሪ ሆኖ ያገኙታል። ወላጆች ሁልጊዜ ልጆቻቸውን እንደሚወዷቸው ለማሳየት ጊዜን መውሰድ ይኖርባቸዋል።

ወላጆች ከልጆቻቸው ከአቅማቸው በላይ የሆነ ነገር እንዲፈጽሙ ሲጠብቁ ወይም ደግሞ ከመጠን በላይ ልቅ እንዲሆኑና እንደፈለጉ እንዲሆኑ በሚፈቅዱላቸው ጊዜ ልጆቻቸውን በሚገባ እንዳልተረዷቸው ወይም እንዳላወቋቸው ግልጽ ነው። እነዚህ ሁለቱም ከመጠን ያለፈ የጽንፈኝነት ችግሮች ናቸው። ሁልጊዜ የሚተች ወይም የሚያቃልሉት ልጅ ከእርሱ ጋር እስከ ጉልምስና የሚሻገር የአለመተማመን ስሜት ይፈጠርበታል። ልጆችን በማሠልጠን አዎንታዊ አቀራረብ መያዝ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ይረዳል።

እያንዳንዱ ልጅ ምሥጋናና አድናቆት ሲሰጠው ጥሩ ምላሽን ይሰጣል። ለተሠራው ስሕተት እርማት ሲሰጥ፣ ተገቢን ነገር በመሥራት ከመጣው ምሥጋና ጋር ሚዛኑ መጠበቅ ይኖርበታል። በክፍለ ትምህርት 2 ያጠናሃቸው የፍቅር ሕጎች ወላጆች ለልጆቻቸው ባላቸው አመለካከትና እንክብካቤ ውስጥ ተግባራዊ መሆን አለበት። እያንዳንዱ ልጅ የቱንም ያህል ዕድሜ ይኑረው በእንክብካቤ የመያዝ መብት አለው።

(13). የልጆችን አለመታዘዝ፣ የሥልጠናና የፍቅር ጉድለትን ወላጆች እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚገባቸው በተሻለ ሁኔታ ከእነዚህ ዐ ረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚያጠቃልለው የትኛው ነው?

ሀ. ወላጆች አለመታዘዝን መፍቀድ የለባቸውም፤ ነገር ግን በጥንቃቄ ልጆቻቸውን ማሠልጠንና እንደሚወደዱ ማሳየት ይኖርባቸዋል።
ለ. ወላጆች ልጃቸው በማይታዘዝ ጊዜ ማድረግ የሚገባቸው በጣም አስፈላጊ ነገር መቅጣት ነው።

## ለቤተሰብ ችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔዎች

### *ዓላማ 7 የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ሥልጣንና ኃላፊነት ጠቅለል አድርጎ ለመግለጽ።*

ይህንን ትምህርት ሳጠቃልል የባልን፣ የሚስትን፣ የልጆችን ኃላፊነት በተመለከተ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን ባጭሩ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ። እነዚህን መርሆዎች መከተል በቤተሰብ ውስጥ የሚከሰተውን ብዙ ችግሮች ለመፍታት ይረዳሃል። ለተቃና ክርስቲያናዊ ቤተሰብ የእግዚአብሔር መንገዶች ናቸው።

## የባል ኃላፊነቶች

1. *አቅጣጫን መስጠት።* መጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ ባል ለቤተሰቡ ከጌታ ምሪትን ይቀበላል። አብርሃም ቤቱን እንዲተውና እግዚአብሔር ወደ መረጠው ምድር እንዲጓዝ ከእግዚአብሔር ምሪትን ተቀበለ (ዘፍ. 12:1)።



ያዕቆብ ወደ አባቱ ምድር እንዲመለስ ጌታ መርቶቷል (ዘፍ. 31:3)። ዮሴፍ ቤተሰቡን ማዳን ይችል ዘንድ ወደ ግብጽ እንዲያመልጥ በእግዚአብሔር ተመርቷል (ማቴ. 2:13)።

ክርስቲያን ቤተሰብ ያለውን የሥልጣን ሥርዓት ለመግለጽ ይችል ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን መርቶታል። "ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ" (1ቆሮ. 11:3፥ 8-12)። "ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና (ኤፌ. 8:1)።

ባል በቤት ውስጥ መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ለሚስቱና ለልጆቹ ፍላጐት፥ ከእግዚአብሔር ለሚመጣው ምሪት ንቁ መሆን አለበት። ይህ ማለት ራስ ለቀረው የአካል ክፍል መልዕክት ለማስተላለፍ ንቁ መሆን እንዳለበት ዓይነት ነው። ለክርስቶስ ሙሉ በሙሉ በመገዛት የሚኖር ሰው ጌታን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ቤተሰቡን እንዴት መምራት እንዳለበት ያውቃል። ይህ ደግሞ መንፈሳዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ምሪትን ያካትታል "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን" (ኢያ. 24:15)። (የሐዋ. 16:31ን ተመልከት)። ሚስቱና ልጆቹ፥ ለጌታ በመገዛት ሥልጣኑን በደስታ ይደግፉታል።

2. *ማዘጋጀት፡-* ባል የቤተሰቡን ቁሳቁሳዊ ፍላጐቶችና ጥበቃን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት (1ጢሞ. 5:8)።

3. *ማፍቀር።* ባል ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቱን መውደድ አለበት (ኤፌ. 5:25፣ 28)። ክርስቶስ እንዴት ነው ቤተክርስቲያንን የወደደው?

ሀ. *ራሱን አሳልፎ ሰእርሷ ሰጠ፡-* (ኤፌ. 5:25፤ ሮሜ 5:8) ይህ ደግሞ ሚስቱ ትጠቀም ዘንድ እርሱ መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ የባል መሥዋዕታዊ ፍቅር ነው።
ለ. *እርሷን ለመቀደስ* (ኤፌ. 5:26) የባል ፍቅር፥ ሚስትን በመንፈሳዊ ጉዞዋ ከክርስቶስ ጋር ከፍ የሚያደርግና የሚያበረታታ መሆን አለበት።
ሐ. *ከውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት* (ኤፌ. 5:26) የባል ፍቅር ሁለቱም ይነጹና ያድጉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ከሚስቱ ጋር መካፈልን ማካተት ይኖርበታል።
መ. *ቅዱስና ነውር የሌለባት አድርጎ ሰራሱ እንዲያቀርባት* (ኤፌ. 5:27)። የሚስቱን መንፈሳዊ ጥቅም ዓላማው ያደረገ ፍቅር፥ ሚስቱ መንፈሳዊ፣ ነቀፋ የሌለባት በመሆን ወደ ባል ይንጸባረቃል።
ሠ. *ክርስቶስ በመጀመሪያ ወደደን* (1ዮሐ. 4:19)። ፍቅርን መግለጥን ለማነሳሳት ባል ቀዳሚ መሆን ይገባዋል።
ረ. *እንደራሱ አካል* (ኤፌ. 5:29) ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ተብላ ትታወቃለች (ሮሜ 12:5)። ይህ የፍቅር መግለጫ ሰው ለራሱ አካል የሚያደርገውን ነገሮች ሁሉ ሲያካትት፥ ለሚስቱ

በእያንዳንዱ መንገድ እንዲጠነቀቅላትና የሚያስፈልጋትን እንዲ ያሟላላት ምክንያት የሆነበትን ፍቅርንም ያከትታል። ይህ ፍቅር ለእርሷ ባለው ታማኝነት (ምሳ. 5:15፥ 18፥ 19፤ ሚል. 2:15-16)፣ አስተዋይ በመሆን (1ጴጥ. 3:7፤ ቆላ. 3:19)፣ አድናቆትን በማሳየት (ምሳ. 31:28-31) ይረጋገጣል።

(14). በነዚህ ሁሉ መንገዶች ባል ሚስቱን መውደድ እጅግ አስፈላጊ የሚሆንበት ሰምንድነው ብለህ ታስባለህ?

## የሚስት ኃላፊነቶች

አዲስ ኪዳን ሴቶች ከወንዶች በታች ናቸው ብሎ አያስተምርም። "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" (ገላ. 3:28)። ይህ ምንባብ ባሪያዎችን፣ ነፃ ሰዎችን፣ አይሁዶችንና የግሪክ ሰዎችን እንዲሁም ወንድንና ሴትን ጠቅሷል። ካላቸው ልዩነት ውጭ፥ ክርስቶስ ሁሉንም በእኩል ደረጃ እንደሚቀበል ያስተምራል። የወንድ ራስነት የኃላፊነት መዋቅር ሥርዓት ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ ኅብረተሰብ መሪ ሊኖረው ይገባል፥ እግዚአብሔር ወንድ በቤተሰብ ውስጥ መሪ እንዲሆን መርጧል።

መሪ እንዲኖር ካስፈለገ ተከታይ መኖር አለበት። ሚስት በመገዛት የባሏን አመራር መከተል አለባት፡ "ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ" (ኤፌ. 5:24)። ሚስት ለጌታ እንደምትገዛ ለማሳየት (5:22) ባሏን በማክበር (5:33)፣ በተገቢ ሁኔታ (ቆላ. 3:18) ልትገዛ ይገባል። ለጌታ የምትሰጪው ተመሳሳይ የመስጠትና የመማረክ ምላሽ ለባልሽም የምትሰጪው መሆን አለበት። ባሏን ከፍ አድርጋ የምትመለከት ክርስቲያን ሚስት ታከብረዋለች። ከሌሎች ይልቅ እሱንና የእርሱን አጋርነት ትመርጣለች፣ ታደንቀዋለች። ባሏ አማኝ ካልሆነ ሳትናገር በባህሪዋ ታሸንፈዋለች (1ጴጥ. 3:1)። ይህ ማለት በክርስቲያናዊ መርህ የፀና ሕይወት የማያምነን ባል ያለ ቃላቶች ልውውጥ ያሸንፈዋል።

በቲቶ. 2:3-5 ሌሎች የሚስት ኃላፊነቶች እንደተሰጡ እናገኛለን። በእድሜ የገፉ ሴቶች ወጣቶችን የሚያስተምሯቸው ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ በእድሜ የገፉ ሴቶች ሕይወታቸው ምሳሌ መሆን እንደሚችል እርግጠኛ መሆን ይገባቸዋል። በአኗኗራቸው የተከበሩ፥ የማያሙ ወይም ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ መሆን አለባቸው። ይህ ሲሆን ወጣት ሚስቶችን ማስተማር ይችላሉ።

(15). ቲቶ 2:3-5 አንብብና በእድሜ የገፉ ሴቶች ወጣት ሴቶችን ማስተማር የሚገባቸውን ሰባት መልካም ነገሮች ዘርዝር።



## የወላጆች ኃላፊነት

1. *ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማርና ለማሰልጠን ኃላፊ ናቸው።* (ምሳ. 22:6፤ ኤፌ. 6:4) ማሰልጠን፥ ምሳሌነትን፣ ትምህርትን፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መቅጣትን የሚያካትት አቀራረብን ይይዛል። ልጆች ከአካባቢያቸው ከሚመለከቱት፣ ከአስተማሪዎቻቸው ትምህርት ይማራሉ። አንዳንድ ጊዜ በተገቢው ሁኔታ በመቀጣትም ይማራሉ (ምሳ. 29:15፣ 17)።

2. *የልጆች ቅጣት ተገቢ መሆን አለበት* "እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጓአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው" (ኤፌ. 6:4) "አባቶች ሆይ፥ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው" (ቆላ. 3:21) ልጆች ስህተት መሆኑን ለማያውቁት ድርጊት መቀጣት የለባቸውም። በቁጣም መቀጣት የለባቸውም። ወጥ የሆነ ነገር መኖር አለበት። እርግጠኛ ለሆነው ጥፋታቸው ተገቢ የሆነ ቅጣት እንዳለባቸው እንዲያውቁ መደረግ አለበት። ይህ ማለት ልጁ ቅጣት የሚገባው ሲሆን ወላጅ ልጁን ለመቅጣት ጊዜን መውሰድ ይገባዋል። ከዚህም በተጨማሪ ልጁን ለምን እንደተቀጣ ማስረዳት አለበት። ስለጉዳቱም ከልጁ ጋር መጸለይ አለበት (ዕብ. 12:6-9፤ 2ጢሞ. 3:16-17)።

ዲሲፕሊን ለልጆች ሕይወት ነው። አንድ ልጅ በወላጆቹ ስልጣን ሥር ማደር ካልቻለ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ራሱን ዝቅ አድርጐ ማቅረብ አይችልም (ምሳ. 19:18፣ 23:13-14፣ 29:17ን ተመልከት)።

3. *ሥልጠናና ዲሲፕሊን በፍቅር መከናወን አለበት።* ወላጆች አመለካከ ታቸውንና አስተሳሰባቸውን ከሰማያዊ አባት ጋር ማመሳሰል አለባቸው። "ቢያሳዝንም እንደ ምሕረቱ ብዛት ይራራል፤ የሰውን ልጆች ከልቡ አያስጨንቅም፥ አያሳዝንምም" (ሰቆ. 3:32-33)።

(16). ዕብ. 12:5-11 አንብብና እግዚአብሔር ልጆቹን ለምን እንደሚቀጣና ወላጆች ሰምን ልጆቻቸውን መቅጣት እንደሚገባቸው ከሚያብራራው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ልጆቹን መገሰጽ ስለሚወድ።
ለ. ልጆቹን ስለሚወድ።
ሐ. የእርሱ ልጆች ስለሆኑ ነው (ለእነርሱ ኃላፊ ነው)።
መ. በእነርሱ ስለተናደደ ሊቀጣቸው ስለሚፈልግ ነው።
ሠ. የእነርሱን ክብር ለማግኘት ነው።
ረ. የእርሱን ቅድስና ይካፈሉ ዘንድ ለእነርሱ ጥቅም ነው።
ሰ. እንዲሰሟቸውና እንዲያሟቸው ስለሚፈልግ ነው።
ሸ. ጽድቅንና ቅድስናን ለማፍራት ነው።

ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ልጁ ለቤተሰቦቹ ቅጣት ያለው ምላሽ በልጁ የበስተኋላ ሕይወት ለእግዚአብሔር መገዛቱና የእርሱን ቅጣትና ሥነ ሥርዓት በመቀበሉ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ እንደሚኖረው እናያለን።

## የልጆች ኃላፊነት

ከልጆች በመጀመሪያ የሚጠበቀው ወላጆቻቸውን ማክበርና መታዘዝ ነው (ዘጸ. 20:12፤ ኤፌ. 6:1-3)። ወላጆቻቸውን በሚታዘዙ ልጆች ላይ የእግዚአብሔር በረከት ይሆናል (ኤር. 35:6-7፥ 18-19)። ወላጆቻቸውን በመታዘዝ የሚያድጉ ልጆች በወደፊቱ ሕይወታቸው ልጆቻቸውን በሚገባ ማሠልጠን የሚችሉ ይሆናሉ።

ወላጆችህን ማክበር የልጅነትህ ጊዜ ሲያበቃ የሚቆም አይደለም። ወጣት ሰው ወደራሱ ዓለም በሚገባበት ወቅት የአባትና የእናቱን ትዕዛዞችና ትምህርቶችን ማስታወስ አለበት። ከወላጆቹ ትምህርት ጥቅምን የሚያገኝ ወጣት ሰው ታላቅ ደስታን ለወላጆቹ ይፈጥርላቸዋል (ምሳ. 23:22-25)።

በብሉይ ኪዳን ወላጆቻቸውን በማይታዘዙ ወይም በማያከብሩ ልጆች ላይ የከበደ ቅጣት ይመጣ ነበር (ዘጸ. 21:15፣ ዘሌ. 20:9፣ ዘዳ. 21:18-21፣ ምሳ. 28:24፤ 30:17ን ተመልከት)።

(17). በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ የእያንዳንዱን ቤተሰብ አባላት ሥልጣንና በቤተሰብ ውስጥ እያንዳንዱ አባላት ያላቸውን አብይ ኃላፊነቶች ጻፍ።




| ስልጣን | አብይ ኃላፊነቶች |
|---|---|
| ሀ | |
| ለ | |
| ሐ | |

እነዚህ መለኮታዊ ትእዛዞች፥ የቤተሰብ አባላት ኃላፊነቶች ቸል በተባሉ ጊዜ፥ ችግር መነሣቱ የሚያስደንቅ አይሆንም። የእግዚአብሔር የአሠራር አወቃቀር ውጤታማ ሥራ ይሠራል፥ በእነዚህ መርሆዎች የሚኖር ቤተሰብ



ፍቅርን፣ ደስታንና ሰኬትን ያውቃል። እንደዚህ ዓይነት ቤተሰብ ይሆን ያለህ? ካልሆነ፥ እግዚአብሔር ቤተሰብህ እንዲሆን የሚፈልገውን ለማድረግ ምን ማከናወን ትችላለህ? ከራስህ መጀመር ትችላለህ፣ አንተ እግዚአብሔር ለቤተሰብህ የሰጠህን ኃላፊነቶች ስታሟላ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ ቀላል ይሆናል። ለውጥ በቀላሉ ወይም በፍጥነት የሚከናወን አይደለም። ይሁንና ውጤቱ ሁሉንም ዋጋ ያለው ያደርገዋል።

(18). ቀደም ባለው ትምህርት እንዳደረግነው የዚህን ክፍለ ትምህርት መርሆዎች በቤተሰብህ ውስጥ ላለህ ችግር መፍትሔ ለማግኘት ተግባራዊ ታደርገው ዘንድ እናበረታታሃለን። የእግዚአብሔር ቃል የማያልቅ የርዳታ ምንጭ ነው። ቃሉን ከቤተሰብህ ጋር አንብቡ፥ እርሱ ለልባችሁ ይናገራችኋል።

## የሙከራ ፈተና

ምርጫ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተስማሚውን አንድ መልስ ምረጥ።

1. ባል ከሚስቱ ጋር ያለውን ሥልጣን በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር የምንችለው ______________ ነው።

ሀ. እናትን ከልጆቿ ጋር
ለ. ቤተ ክርስቲያንን ከክርስቶስ ጋር
ሐ. ክርስቶስን ከቤተ ክርስቲያን ጋር

2. በተገቢው ሁኔታ ልጆችን ማሠልጠን የሚያካትተው

ሀ. ቅጣትንና ማመስገንን
ለ. ማስተማር፣ ሥነ ሥርዓት ማስያዝንና ፍቅርን
ሐ. ነፃነትን ያለልክ መፍቀድን
መ. ትችትን

3. ፍች የሚፈቀደው በምን ምክንያት ብቻ ነው?

ሀ. ዝሙት
ለ. ያላመነን ላገባ ሰው
ሐ. በልጆች ላይ ባለመስማማት
መ. ቅናት

4. በፍች ምክንያት ይበልጡኑ ተጐጅዎች

ሀ. ባል
ለ. ሚስት
ሐ. በደል የደረሰበት የትዳር አጋር
መ. ልጆች

5. ቀደም ሲል የፈታ ሰው ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ቢያገባና በመቀጠልም ጌታን ቢቀበል

ሀ. ወደቀድሞው ሚስቱ መመለስ አለበት።
ለ. ሁለተኛውን ጋብቻ በመተው ብቻውን መኖር አለበት።
ሐ. ጌታን ሲቀበል በነበረበት ሁኔታ መቀጠል አለበት።

6. አንደኛው የትዳር ጓደኛ ሌላኛውን ዝቅ ዝቅ አድርጎ በሚመለከትበት ጊዜ በትዳር ውስጥ የጐደለው፡

ሀ. መሪነት
ለ. ፍቅርና አክብሮት
ሐ. እምነት
መ. አንድነት



7. በቤት ውስጥ ያለ የገንዘብ እጥረት ችግር ሊወገድ የሚችለው የትዳር ጓደኛሞች፡

ሀ. ለረጅም ሰዓት ለመስራት ሲስማሙ ነው።
ለ. ሚስት ወጭዎችን እንድትቆጣጠር ሲስማሙ ነው።
ሐ. አስራታቸውን በቅድሚያ ለመክፈል ሲስማሙ ነው።
መ. ያልተጠበቁ ወጭዎችን ሲያስወግዱ ነው።

እውነትና - ሐሰት። እውነተኛ ከሆነው ዐረፍተ ነገር በፊት "እ" የሚለውን ፊደል፤ ሐሰተኛ ከሆነው ዐረፍተ ነገር በፊት "ሐ" የሚለውን ፊደል ጻፍ።

______8. እናት የቤቱ መንፈሳዊ መሪ መሆን አለባት።

______9. ከቤት ውጭ ባሉ እንቅስቃሴዎች አብዝቶ መጠመድ ቤተሰቡ አብሮ ተገቢ የሆነ ጊዜን እንዳያሳልፍ የሚከላከል ችግር ነው።

______10. ታዛዥ ልጅ ከአመጸኛ ልጅ ይልቅ እግዚአብሔርን የሚያገለግል መሆኑ ግልጽ ነው።

______11. ያላመነን ሰው ያገባ ክርስቲያን ባስፈለገው ጊዜ ለመፍታት ነፃ ነው።

______12. ሰው የመጀመሪያ ቅድሚያ መስጠት የሚገባው ጉዳይ ለወላጆቹ ነው።

______13. ወላጆች አመጸኛ የሆነ ልጃቸውን ለመርዳት ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን ይገባቸዋል።

______14. ቤተሰቡን መምራት፣ የሚያስፈልጋቸውን ማሟላትና ማቅረብ የባል ኃላፊነት ነው።

______15. የቤተሰብ ራስ የመሆን ኃላፊነት ስኬታማ ይሆን ዘንድ በፍቅር መታጀብ ይኖርበታል።

# የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

10. እያንዳንዱ መሪ የራሱን ቤተሰብ በሚገባ ሁኔታ ማስተዳደርና ልጆቹ እንደሚታዘዙትና እንደሚያከብሩት መመልከት አለበት (ቁ. 4፣5፣ 12)።

1. ለ

11. ለ

2. ምክንያቱም አንድ ሥጋ ስለሆኑና ይህም እስከ ሕይወት ፍጻሜ የሚዘልቅ መስጠት በመሆኑ ነው።

12. ሀ. 3 | መ. 1 | ሰ. 6
ለ. 4 | ሠ. 5
ሐ. 7 | ረ. 2

3. ሀ. ክርስቲያን ማግባት የሚገባው ክርስቲያን የሆነችን ነው።
ለ. ባል የቤቱ መንፈሳዊ መሪ መሆን አለበት።

13. ሀ

4. ለ

14. የአንተ መልስ። እኔ እንዲህ እመልሰው ነበር። ባል በሚስቱ ላይ ራስነት ተሰጥቶታል። ይህንን ኃላፊነት መፈጸም የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ፍቅር ነው።

5. ሀ. ሐሰት | ሐ. እውነት
ለ. ሐሰት | መ. እውነት

15. እያንዳንዷ ሚስት ባሏን መውደድ አለባት፥ ልጆቿን መውደድ አለባት። ራሷን የምትቆጣጠር መሆን አለባት። ንጹህ፣ በቤት የምታገለግል፣ ርኅሩኅና ለባሏ የምትገዛ መሆን አለባት።

6. ለ

16. ሀ. ውሸት | መ. ሐሰት | ሰ. ሐሰት
ለ. እውነት | ሠ. እውነት | ሸ. እውነት
ሐ. እውነት | ረ. እውነት

7. እነዚህ የትዳር ጓደኞች ደኅንነትን በተቀበሉበት ወቅት በነበሩበት ሁኔታ መሆን ይገባቸዋል። ይህም በጋብቻቸው መጽናትና በንስሐና በክርስቶስ እንደ አዲስ መወለድ ምክንያት እግዚአብሔር የሰጣቸውን አንድነት መቀበል ይገባቸዋል።



17. ሀ. ባል፦ የምሪትን አቅጣጫ መስጠት፣ የሚያስፈልገውን ማቅረብ፣ ሚስትንና ልጆቹን መውደድና ልጆቹን ማሠልጠንን ይፈጽማል።
ለ. ሚስት፦ ለባሏ አመራር ትገዛለች፣ ቤቷን ትንከባከባለች፣ ባሏንና ልጆቿን ትወዳለች፣ ልጆቿን በማሠልጠን ታግዛለች።
ሐ. ልጆች ቤተሰቦቻቸውን ይታዘዛሉ፣ ያከብራሉ።

8. ክርስቲያን መፋታትን ተከልክሏል። ክርስቲያን ፈትን ማግባት አይችልም። የተፋቱ ሰዎች ዳግም ጋብቻን አያከናውኑም።

18. የአንተ መልስ።

9. መ

# 6 የላጤነት ሕይወት ችግሮች

ትምህርት

ጋብቻ አስፈላጊ በሆነበትና በጥንድነት በሚኖር ህብረተሰብ መካከል ነው የምንኖረው። ብዙውን ጊዜ ላጤ ከመሆን ጋር የተያያዘ ኀፍረት አለ። ብዙ ሰዎች አንድ ሰው ካላገባ በዚያ ሰው አንድ እንከን የሆነ ነገር መኖር አለበት ብለው ያስባሉ! ይህ አዲስ ሃሳብ አይደለም። በብሉይ ኪዳን የላጤነት ሕይወት በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት እንደሌለው ሆኖ ይቆጠር ነበር (መሳ. 11:38፣ ኢሳ. 4:1 እና ኤር. 16:9 ተመልከት)።

በክፍለ ትምህርት 4 ውስጥ በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ያሉ ችግሮችን ተወያይተናል። እነዚህ ደግሞ ያገባም ይሁን ያላገባም ሰዎች ሁሉ የሚገጥሟቸው ችግሮች ናቸው። በክፍለ ትምህርት 5 በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ባሉ ችግሮች ላይ ትኩረትን አድርገናል። ብቻውን ወይም ያለ ትዳር ጓደኛ የሚኖር ሰው ሌሎች ተጨማሪ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ። እነዚህም ከበድ ያለ ብቸኝነት፣ መደበት፣ ፍርሃት፣ ውሳኔዎችን ለብቻ መጋፈጥ፣ የፍቅርና የመወደድ ፍላጐት፣ መገዛት የሚገባው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጐት ናቸው።

የላጤነት ሕይወት አሉታዊ የሆነ ልምምድ መስሎ መታየት የለበትም። ያላገባ ሰው ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ልዩ ስጦታ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጿል ማቴ. 19:12 እና 1ቆሮ. 7:7)። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የላጤነት ሕይወት ያሰውን አንዳንድ እጅግ አዎንታዊ ዋጋዎችና ላላገባ ሰው የሚያበረክቱትን እርኪና ትርጉም ያለው የሕይወት ጉዳና እናገኛለን። ያላገባ ሰው ከራሱ ችግሮች ጋር ብቻውን መባዘን የለበትም፤ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መለኮታዊ ችግር የሚፈታው የኢየሱስ ክርስቶስ ርዳታ ብቻ ሳይሆን፥ ቤተክርስቲያንም ለእርዳታና ለብርታት አስደናቂ ምንጭ መሆን እንደምትችል እናገኛለን።



## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ችግሮቹን መግለጽ
- የላጤነት ሕይወት ጥቅሞች
- ለማግባት ወይም ላለማግባት መወሰን
- የተለዩ ችግሮችን መጋፈጥ
- ቤተ ክርስቲያን እንዴት መርዳት ትችላለች?

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- ያላገባ ሰው ችግሮችን መግለጽና ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሔ ለመፈለግ የሚረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማመልከት፤
- የላጤነት ሕይወት ዋጋዎችን ማስተዋል፤
- ችግሮችን ለመፍታት ስትሞክር ለላጤው ሰው ቀና አመለካከት አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት፤
- የላጤ ሰው ፍላጐቶችን ለማሟላት ቤተ ክርስቲያን መርዳት የምትችልባቸውን መንገዶች መግለጽ መቻል አለብህ።

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍለ ትምህርት አንድ በትምህርቱ መመሪያ ውስጥ የተሰጠውን የጥናት እቅድ በመከተል ክፍለ ትምህርቱን አጥና።
2. የሙከራ ፈተናውን ውሰድና መልሶችህን አመሳክር።
3. ከክፍለ ትምህርት 4 እስከ 6 የቀረበውን ትምህርት በመጨረሻ ከልስ።

# ችግሮችን መግለጽ

*ዓላማ 1 ያላገባ ሰው ባሉት ችግሮች ላይ ለማማከር ሊረዱ የሚችሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማጥናት።*

በጋብቻ ውስጥ የሌሉ ሰዎች በኅብረተሰባችን ውስጥ የሚገለጹት ላጤዎች በመባል ነው። በሦስት መደቦች ይመደባሉ።

1. ቀደም ሲል ያላገቡ
2. ትዳራቸውን የፈቱ
3. የትዳር ጓደኞቻቸው የሞተባቸው

1. ***ቀደም ሲል ያላገቡ።*** በብዙ የዓለማችን ክፍል ውስጥ በቤተሰብ ውስጥ ላላገቡ ጉልማሶች መጠለያና ባልንጀራነትን የቤተሰቡ አባል፣ ማለትም ወንድም፥ እህት ወይም የቅርብ ዘመዶች ያሟላሉ። ይሁንና በአሁኑ ጊዜ ብዙ ጉልማሶች በሥራና በሌሎች ምክንያቶች ከቤተሰባቸው በመለየት ወደ ከተማዎች በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው። በዚህም ምክንያት በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተሰባቸው ጥበቃና ሕብረት ውጭ ብቸኛ ይሆናሉ።

ማርታ ደረሰ 28 ዓመቷ ሲሆን ገና አላገባችም። ወደ ከተማ የመጣችው ሥራ ለመፈለግ ሲሆን በአንዲት አነስተኛ ክፍል ውስጥ ትኖራለች። በአንድ መሥሪያ ቤት ፀሐፊ ሆና የምትሰራ ሲሆን እምልኮዋንም የምትከታተልበት ቤተ ክርስቲያን አግኝታለች። ይሁንና ደስተኛ አይደለችም። እንዲህ ትላለች "ብዙዎቹ ጓደኞቼ ያገቡ በመሆናቸው በእነርሱ ጉዳዮች ውስጥ አያሳትፉኝም። በሥራ ወይም በቤተክርስቲያን ከማሳልፈው ውጭ ያሉትን ጊዜያት በአብዛኛው በብቸኝነት አሳልፋለሁ። አንዳንድ ጊዜ ብቸኝነቱ ጠልቶ ስለሚሰማኝ ለመተኛት እንኳን እቸገራለሁ። ስለ እኔ አንዳችም የሚጠነቀቅ ሰው የለም። መፈቀርን እፈልጋለሁ፤ ቤተሰብና ልጆች ይኖሩኝ ዘንድ እፈልጋለሁ።"

ያላገባችውና የ38 ዓመት እድሜ ያላት ሰናይት እንዲህ ትላለች። "ብዙውን ጊዜ ላጤ መሆኔን ትኩረት ሰጥቼ አልጨነቅበትም። በሥራዬ እደሰታለሁ፥ በቤተክርስቲያን ውስጥ በብዙ አገልግሎቶች እሳተፋለሁ። በኳየር ውስጥ እዘምራለሁ፣ የሰንበት ትምህርት አስተምራለሁ፤ ከሰዎች ጋር በመሥራት እደሰታለሁ። በእርግጥ ባገባና ቤተሰብ ቢኖረኝ እወዳለሁ። ላገባ የምችልባቸው እድሎች ነበሩኝ፥ ይሁንና ለእኔ ትክክል የነበሩ አይመስሉም። የወደፊት ሕይወቴን ለእግዚአብሔር ሰጥቻለሁ፤ ለሕይወቴ ያለውን የእርሱን እቅድ እቀበላለሁ። የእኔ ዋነኛ ችግር ሰዎች ባለማግባቴ ስለሚሳለቁብኝ ወይም ስኬታማ ሕይወት ይኖረኝ ዘንድ ማግባት እንዳለብኝ ስለሚነግሩኝ ነው። በማኅበረሰባችን ውስጥ ሰዎች እንዲያገቡ ከፍተኛ ግፊት አለ። ይህ



ደግሞ በእኔ ላይ የሆነ ችግር እንዳለ እንዲሰማኝና በነጠላነቴ ደስተኛ እንዳልሆን ያደርገኛል።"

ተወልደ ከክርስቲያን ልጃገረዶች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነቶችን ማዳበር የሚችልበት ብዙ አጋጣሚዎች የነበሩትና ማግባት የሚፈልግ ወጣት ነው። ይሁንና ግንኙነቱ ዳብሮ ወደ ጋብቻ የሚያመራ መስሎ ሲታየው ፍርሃት ስለሚወርሰው ከልጅቷ ጋር ያለውን ግንኙነት እየቀነሰ ይሸሻል። ይህንንም ሲገልጽ "ጋብቻ ከፍተኛ ኃላፊነት ነው፥ አሳዛኝ የሆነ ስሕተትን እሰራለሁ ብዬ እፈራለሁ። ወይም ለቤተሰቤ ማሟላት የሚገባኝን ያህል አይቻለኝ ይሆን ብዬ እሰጋለሁ። የቀረውን ሕይወቴን ለሌላ ሰው አሳልፌ ለመስጠት መዘጋጀቴን እርግጠኛ አይደለሁም።"

በአርባዎቹ የሚገኝ ሌላው ሰው ያረጁና ለብዙ ዓመታት በጤንነት ጉድለት የሚቸገሩትን እናቱን መንከባከብ ስላለበት አለማግባት መርጧል። ማግባትን እጅግ አድርጐ የሚወድ ቢሆንም፥ የራሱ ኃላፊነት አድርጐ በሚቆጥረው ጉዳይ ላይ፣ በእናቱ እንክብካቤና የህክምና ወጭዎች ሸክም ውስጥ ሚስቱን መከተት እንደሌለበት ሆኖ ይሰማዋል።

እነዚህ አራት ምሳሌዎች የብዙ ያላገቡ ሰዎችን ችግሮች ለመግለጽ ምሳሌ ይሆናሉ። ከነዚህም ችግሮች መካከል ራስን ያለአግባብ ዝቅ አድርጐ ማየት፣ የመገፋት ስሜት፣ የማግባት ግፊትን፣ ኃላፊነትን መፍራት፣ ቤተሰብ የመመሥረት መሻትን ስለ ወደፊቱ ለማቀድ አለመፈለግ፣ ተፈላጊ የመሆን ምኞትን በምሳሌነት ያሳያሉ። ብዙውን ጊዜ ላጤ ሴቶች ሊጠብቋቸው የሚችሉ ባሎች ስለሌሏቸው ሰዎች በእነርሱ ላይ ጥቅምን ለማግኘት ብቻ እንደሚቀርቧቸው ይሰማቸዋል።

(1). በተሰጡት አራቱ ምሳሌዎች ውስጥ የሚገኙት ሰዎች ሁሉ የሚጋሯቸው አመለካከት የትኛው ነው?

| | |
|---|---|
| *ሀ.* ፍርሀት | *ሐ.* ደብቃኛል ማለት |
| ለ. እርግጠኛ አለመሆን | *መ.* ተስፋ መቁረጥ |

2. ***ትዳራቸውን የፈቱ።*** በክፍለ ትምህርት 5 ውስጥ ስለፍች ሰፋ ባለ መልኩ ተወያይተናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የምንሰጠው ትኩረት የተፈታ ሰው እንደ ላጤ ሰው በሚጋፈጣቸው ችግሮች ላይ ነው።

መስከረም ባሏ ከፈታት በኋላ ወዲያውኑ ሌላ አግብቷል። ታሪኳ እንዲህ ነው "ባሌን እጅግ አድርጌ እወደው ነበር፤ ነገር ግን ክርስቲያን ከሆንኩኝ በኋላ ብዙውን ጊዜውን ከቤት ውጭ ማሳለፍ ጀመረ። ክርስቲያን ማድረግ የለበትም ብዬ የሚሰማኝን ነገሮች እንዳደርግ ፈለገ። ትዳራችን ደስታ የሞላበት እንዲሆን ብሞክርም እሱ እኔን ለመፍታት ወሰነ። ትዳራችን ስለፈረሰ ሐዘንና በደለኝነት ተሰማኝ፤ እጅግ አድርጌ በማምነው ሰው መገፋቴም ተሰማኝ። አሁን ሁለት ልጆቼን ለመንከባከብ መሥራት

አለብኝ፣ የተፈታሁ በመሆኔም ሰዎች የሚነቅፉኝና የሚተቹኝ መስሎ ይሰማኛል። በቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ለማግኘት አፍራለሁ። ብቸኛ ሆኜ ለልጆቼ ቤታችንን የደስታ ቤት እንዴት ማድረግ እችላለሁ?"

የተፋታ ሰው የመገፋት ወይም የጭካኔ ፍርድ እንደተከናወነበት የሚሰማው ስሜቶች ሊኖሩት ይችላል። እሱ ወይም እርሷ በስቃይ፣ ተስፋን በማጣት፣ በድንገት ከተፈጠረ ለውጥ የተነሳ አዲስ ኑሮ ወይም ሕይወት በመለማመድ ወይም ልጆችን ብቻቸውን የመንከባከብ ኃላፊነት ሊኖራቸው ይችላል። የተፈታ ሰው ቁጣን፣ መራርነትን፣ የበታችነትን ስሜት፣ የብቸኝነትን ስሜት፣ ከመለየት የተነሳ የሚከሰትን ሐዘን ታግሎ ማሸነፍ ይኖርበታል።

3. *የትዳር ጓደኛቸው የሞተባቸው* ባሏ ለረጅም ጊዜ ከታመመ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየ ጓደኛዬ መበለት ሆናለች። በመጨረሻዎቹ የበሽታው ወራቶች ካለማቋረጥ እንክብካቤን አድርጋለታለች። አሁን እንዲህ ትላለች "ሕይወቴ እጅግ ባዶ ነው። የማደርገው ምንም መልካም ነገር የለም የምኖርበትም ምንም ምክንያት የለም። ባለቤቴ መላ ሕይወቴ ነበር። ማንነቴን ያጣሁኝ ያህል ነው የሚሰማኝ። አዕምሮዬ በባሌ አስቃቂ በሽታዎች ትዝታ ተሞልቷል። ልጆቼም ስላገቡ ከእኔ ጋር አይኖሩም። አንዳችም ሰው እኔን አሁን አይፈልገኝም።"

ሌላም ባለቤቱ የሞተችበት ሰው እንዲህ በማለት ነገረኝ "ከፍተኛው ችግሬ ወደ መኖሪያ ቤቴ፣ ወደ ባዶ ክፍሌ ስሄድ የሚሰማኝ የብቸኝነት ስሜት ነው። ምግብ ማዘጋጀትና ብቻዬን መመገብ ፍላጐት ስለሌለኝ ክብደት ቀንሻለሁ።"

ሐዘን፣ ብቸኝነት፣ ከፍተኛ የሆነ የሕይወት አቅጣጫ ለውጥ፣ የገንዘብ ችግሮች ወይም ኑሮን በአዲስ መልክ ማመቻቸት (በተለይ ለሴቶች)፣ ለመኖር ምክንያት ማጣት፣ የመጣል፣ የመተው ስሜት፥ የመበለት ሰውን አንዳንድ ችግሮች ያንጸባርቃሉ። የፍቅርና የመወደድ ፍላጐት የሁሉ ሰው ፍላጐት ነው። እያንዳንዱ ሰው በሌላ ሰው መፈለግን ይሻል።

(2). ከዚህ በታች የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብና በሚከተሉት ችግሮች ውስጥ ያለውን ሰው ለመርዳት የተሻለ ነው ብለህ የምታስበውን አንዱን ምረጥ።

ሀ. በሌላ ሰው ክፉ ድርጊት ምክንያት መከራ መቀበል። መዝ. 91:4፣ 1ጴጥ. 4:12-19፣ ዕብ. 2:18።
ለ. መገፋት። 2ቆሮ. 12:9፣ ኢሳ. 53:3፣ ዮሐ. 1:11፣ መዝ. 130:4-5
ሐ. ፍርሃት። ዘዳ. 33:12፣ 1ዮሐ. 1:9፣ ኢያ. 1:9፣ 2ቆሮ. 12:10
መ. ሐዘን። መዝ. 18:29፣ 66:10-12፣ 2ቆሮ. 1:3-4፥ 6



(3). መዝሙር 66:10-12ን አንብብ።

ሀ. አንድን ሰው ለመርዳት ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መጠቀም ተገቢ የሚሆነው መቼ ነው?
ለ. እንዴት ሊረዳ ይችላል?

(4). ኢሳይያስ 54:4-10 አንብብ።

ሀ. አንድን ሰው ለመርዳት ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መጠቀም ተገቢ የሚሆነው መቼ ነው?
ለ. እንዴት ሊረዳ ይችላል?

(5). የምታውቃቸው ያላገቡ ሦስት ሰዎችን ስምና በአንተ አስተሳሰብ እነዚህ ሰዎች እያለፉበት ያለውን ችግሮች በተለየ ማስታወሻ ደብተር ላይ ዘርዝር። (ላጤ ከሆንክ ላጤ በመሆንህ ያሉብህን ማናቸውንም ችግር ዘርዝር) ለእያንዳንዱም ሁኔታ የሚረዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለማግኘት ሞክርና ከዘረዘርከው ችግሮች በመቀጠል ጻፈው።

## የላጤነት ሕይወት ጥቅሞች

*ዓላማ 2 የላጤነት ሕይወት ያለውን ጥቅሞች ለመግለጽ።*

ለላጤነት ችግሮች ሊኖሩ የሚችሉ መፍትሔዎችን ከመመልከታችን በፊት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጠውን የላጤነት ሕይወት አንዳንድ ዋጋዎችን እንመልከት። እነዚህ ዋጋዎች ለአማራጭ መፍትሔዎች ግንዛቤን ይሰጡናል።

1. *የላጤነት ሕይወት ተቀባይነት ያለው አማራጭ መንገድ ነው።* የላጤነትን ሕይወት ስንነጋገር የምናወራው ገና የጋብቻ ልምምድ ውስጥ ፈጽሞ ስላልገባ ሰው ነው። በክፍለ ትምህርት 7 በሰዎች ግብረ ሥጋዊነት ሕይወት ውይይታችን ውስጥ አለማግባትን ሰፋ ባለ መልኩ እንነጋገራለን።

በዓለም ሊከሰት ከሚችለው ሐዘንና ያገቡ ሰዎች በየዕለቱ ሊኖራቸው ከሚችለው ችግሮች የተነሳ ሐዋርያው ጳውሎስ ላጤ ሰዎች በላጤነት ሕይወት መቀጠላቸው ምናልባት የተሻለ እንደሆነ አድርጐ ሐሳቡን አቅ ርቧል። ያላገቡ ሰዎች የቤተሰብ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች ከሚያጋጥሟቸው ጭንቀቶችና ችግሮች ነፃ ናቸው (1ቆሮ. 7:26-32)። ሁሉም ሰው ላጤ ሆኖ እንዲቀር ይህንን አላለም። ነገር ግን በላጤነት ለመዝለቅ ለሚፈልጉ መልካም እንደሆነ ለማሳሰብ ነው (1ቆሮ. 7:35)።

2. *የላጤነት ሕይወት ልዩ ሥጦታ ነው።* ላጤነት ወይም አለማግባት ሥጦታው ላላቸው ብቻ የሚሆን ነው። እኔ ላጤነት ለማንኛውም ላላገባና

ለሚፈልገው ሰው፣ በሚፈልገውና እስከሚፈልገው ጊዜ ድረስ እግዚአብሔር በነፃ የሚሰጠው ስጦታ ነው ብዬ አምናለሁ። ኢየሱስ፣ በኋላም ጳውሎስ ይህንን ስጦታ ከላጤነትና ከጋብቻ አቅጣጫ ጠቅሰውታል። እግዚአብሔር አንተና እኔን ይወዳል። ምንም ይሁን በየትኛውም የሕይወታችን ሰዓት ውስጥ ለእርሱ ሥጦታ የተለየ ፍላጐት ይኑረን፣ እግዚአብሔር ለሚያስፈልጉን ፍላጐቶች ሁሉ የራሱን ሥጦታ አዘጋጅቷል። ደቀ መዛሙርት አለማግባት የተሻለ እንደሆነ ሀሳብን ሲያቀርቡ ኢየሱስ እንዲህ ነበር የመለሰው።

> እርሱ ግን፦ "ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም። በእናታቸው ማኅፀን ውስጥ ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፤ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፤ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው" አላቸው (ማቴ. 19:11-12)።

በጋብቻ ያልተጠመደ ላጤ ሰው ጊዜውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት የሰጠ፣ ለቤተክርስቲያን ልዩ ስጦታ ነው። ጋብቻን ለመመስረት ሰፊ እድል የነበራቸው ነገር ግን ጊዜያቸውን በወንጌል አገልግሎት ለመጠቀም የመረጡ ብዙ የተሰጡ ሰዎችን አውቃለሁ። አንዳንዶቹ በወንጌል ሥርጭት ላይ በመሆናቸው ከትውልድ አገራቸው ርቀው ይገኛሉ፡ ይህንን ምርጫ የመረጡት ይህንን ካልፈጸሙ እግዚአብሔር ይሠሩት ዘንድ የጠራቸውን ሥራ ማከናወን እንደማይችሉ ስለተገነዘቡ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለእንዲህ ዓይነት ሰዎች ጥሩ ምሳሌ ነው። እንዲህ ይላል "ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው። አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ" (1ቆሮ. 7:7)።

3. *የላጤነት ሕይወት መልካም ዕድልም ነው።* ቀደም ባለው ክፍል ኢየሱስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ብለው አንዳንዶች እንደማያገቡ እንደጠቀሰ አስተውል። ጳውሎስም ለዚሁ ምክንያት የላጤነት ሕይወት የሚመረጥ እንደሆነ በ1ቆሮ. 7:32-35 ትኩረትን ሰጥቶበታል። ያላገባ ሰው ራሱን በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ለመክተት ነፃ እንደሆነ፣ ያገባ ሰው ግን ወደ ሁለት አቅጣጫ እንደሚጐተት ጠቅሷል። በተመሳሳይ መንገድ ያገባች ሴት ትኩረትን የምትሰጠው ባሏን በማስደሰት ላይ ሲሆን፣ ያላገባች ሴት ግን ወደ ኋላ አንዳች ነገር ሳይዛት፣ ራሷን ሙሉ በሙሉ ለጌታ ሥራ ለመስጠት ነፃ ነች።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የተጠራው ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ እንዲሰጥ መሆኑ እውን ነው። ላጤ ለሆኑት ይህንን መስጠታቸውን መግለጽ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታዎች ሲኖሩ፣ ቤተሰባቸውን ለሚንከባከቡ ይህ ደግሞ ምቹ ላይሆን ይችላል።

(6). ማቴዎስ 6:33ን አንብብና ለማግባት ከፍተኛ ፍላጐት ካለው ክርስቲያን ላጤ ሰው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አስረዳ።



(7). ለላጤ ሕይወት ዋጋን ከሚሰጥ ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ያላገቡ ሰዎች ከጭንቀቶችና ከችግሮች ነፃ ናቸው።
ለ. የላጤነት ሕይወት ተቀባይነት ያለው ብቻ ሳይሆን አስቸጋሪን ጊዜ በማሳለፍ ላይ ለነበሩት ለቆሮንቶስ ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ይመርጡት ዘንድ ያበረታታቸው ነበር።
ሐ. በላጤነት የሚዘልቁ ሰዎች ብዙውን ጊዜያቸውን ለእግዚአብሔር ለመስጠት የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ አላቸው።
መ. እያንዳንዱ ሰው በላጤነት የመዝለቅ ስጦታን ተሰጥቶታል።
ሠ. ያገባ ሰው ትኩረቱን ለእግዚአብሔር በሚሰጠው አገልግሎትና ለቤተሰቡ መክፈል አለበት።
ረ. ላጤ ሰው ለቤተክርስቲያን የተለየ ሥጦታ ነው።

ለእግዚአብሔር ሥራ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ለመስጠት ሲሉ ላለማግባት የመረጡትን፣ የሚያስፈልጋቸውን እንደሚሰጣቸውና በሙሉ ልባቸው እንዲያገለግሉት ሳያቋርጥ እንደሚረዳቸው ይገነዘባሉ። እንደዚህ ዓይነት ውሳኔን ለሚወስኑና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ለሚሰጡ የእርሱ ሽልማት ታላቅ ነው "ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል" (ማቴ. 19:29)።

## ለማግባት ወይም ላለማግባት መወሰን

***ዓላማ 3 ለማግባት ወይም ላለማግባት ውሳኔን የሚያደርግ ሰው የሚመራበትን መርህ ለማየት።***

ላጤ የሆኑ አንዳንድ ሰዎች ላጤነትን በምርጫ እንዳልተቀበሉት ይሰማቸዋል። ቀደም ሲል በተመለከትነው ምሳሌ ውስጥ የተፈታችው ሴት መፈታትን አልመረጠችም። መበለት የሆነችውም ሴት በምርጫዋ አልነበረም። እነዚህ ሊቆጣጠሯቸው ያልቻሏቸው ችግሮች ናቸው። ምንም ያላገባውም ሰው ላጤ ሆኖ መዝለቅን ላይመርጥ ይችላል።

ለሚገጥሙን ለእያንዳንዱ ችግር የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ እንደሆነ ቀደም ብለን ትኩረት በመስጠት ተመልክተናል። እግዚአብሔር ልንሸከመው ከምንችለው በላይ ቀንበርን እንሸከም ዘንድ አይጠይቀንም። የሚገጥመን እያንዳንዱ ፈተና ወደ እርሱ የበለጠ እንድንቀርብ፣ የእርሱን ጥበቃና ፍቅር እንድንለማመድ ምቹ አጋጣሚ ነው። ችግሮቻችንን ለይተን ካወቅን፣ ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠትና ለእኛ በጐ ያደርገው ዘንድ መጠበቅ አለብን። እርሱ በፍጹም አይተወንም።

ከሰውየው ከራሱ ከውስጥ የሚመጣ ወይም ከሌሎች የሚመጣ የጋብቻ ግፊት ብዙውን ጊዜ ሰዎች ጋብቻን ለማከናወን ጽድቅ የሌለበት መንገድ እንዲጠቀሙ ያደርጋል። ወይም እግዚአብሔር የመረጠውን ሳይሆን እንዲሁ ያገኙትን የትዳር ጓደኛ ያገባሉ። ከተሻለውና ከበለጠው ነገር ባነሰ ነገር ረክተህ አትቀመጥ። የእግዚአብሔር ፈቃድ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ሰዎች እንድንሆን እንጂ መጀመሪያ እንድናገባ እንዳልሆነ በመረዳት ቅድሚያውን ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን።

እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ እቅድ ተገቢ የሆነ ጊዜ እንዳለው መርሳት የማይገባን እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በችኮላ ወይም ሰውየው እንደሚገባው ሳይዘጋጅ ወደ ጋብቻ ለመግባት የሚደረጉ ጥድፊያዎች ከግብ ሳይደርሱ እንደቀሩ እንመለከታለን። አንዳንድ ጊዜ አንዳቸው ሌላቸውን ሲጎዱና ሲያሳዝኑ ይገኛሉ፤ ወይም የጋብቻን ሕይወት ግፊት ለመቆጣጠር ያልበሰሉ ይሆናሉ። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶችን በመጠቀም ጌታ የላጤዎችን ማኅበራዊ ፍላጉቶች ሊያሟላ ይችላል፤ ያሟላልም። ላጤ ሰዎች የጌታ ፈቃድ ባልሆነ ግንኙነቶች ውስጥ እንዲገቡ ግፊት ሊደረግባቸው አይገባም። ሁላችንም ያገባንም ብንሆን ያላገባን ጠንካራና የበሰለ ክርስቲያናዊ ባህሪን ለማዳበር መትጋት ይገባናል። ስለዚህ ጉዳይ በክፍለ ትምህርት 4 ተነጋግረናል። ላጤ ሆንክ ያገባህ የእግዚአብሔር መለኪያዎቹ ተመሳሳይ ናቸው። እግዚአብሔር ላጤን ወደ ጋብቻ ከመራ መሠረቱ በደህና ሁኔታ ይመሠረታል።

አንዲት ክርስቲያን እህት የቀረበላትን ሁለት የጋብቻ ጥያቄዎች ለሕይወቷ የእግዚአብሔር ምሪቶች እንደሆኑ ስላላመነች አልተቀበለቻቸውም። አንዱንም የጋብቻ ጥያቄ ብትቀበል ልታከናውነው ለማትችለው ለተለየ አገልግሎት እግዚአብሔር ጠርቷት ነበርና። ለአስር ዓመታት እግዚአብሔርን በታማኝነት አገለገለች። ይሁንና የብቸኝነት ዓመታት ወደሆኑት ወደ አርባዎቹ እድሜ ስትቃረብ ጉጂ የሆነ የሰዎች አስተያየትና እርጅናን ለብቻ የመጋፈጥ ፍርሃት ተስፋ እንድትቆርጥ ምክንያት ሆነባት። በዚያው ወቅት ክርስቲያን ያልሆነን ሰው ተዋውቃ ግንኙነታቸውን ለማዳበር ፈቃደኛ ሆነች። ክርስቲያን ለመሆን ደስተኛ አለመሆኑን ግልጽ አድርጉ ቢነግራትም ይህንኑ ሰው አገባችው። ከዚህ ጊዜ በኋላ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ አልቻለችም። ጊዜዋን ሁሉ የሰዋችው የተለያየ እምነት ባለበት ቤት ውስጥ ኑሮዋን ደስተኛ ለማድረግ በመሞከር ላይ ነበር።

(8). በተገለጸው ምሳሌ ውስጥ የትኛው የእግዚአብሔር ሕግ ነው የተጣሰው?

የወጣትነትና የጉልምስናዋን ወቅት ሁሉ ኋላ ቀር በሆኑ በአፍሪካ መንደሮች በሚሲዮናዊነት ያሳለፈች እድሜዋ የገፋ ሴትን አውቃለሁ። በዚሁ አካባቢ ወንድ ሚሲዮናዊ ባልነበረበት ለብዙ ዓመታት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሥራና በወንጌል ሥርጭት ብቻዋን ሠርታለች። ይህንንም ያደረገችው ይህ አገልግሎት በሕይወቷ ይፈጸም ዘንድ



የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ስለምታውቅ ነበር። በ64 ዓመቷ የመጨረሻው የአፍሪካ አገልግሎቷን ለመፈጸም በሃገሯ ስትዘጋጅ ሳለች በጡረታ ካለና ሚስቱ ከሞተችበት ሚሲዮናዊ ጋር ተገናኘችና ፍቅራቸው እየጠነከረ በመምጣቱ ወደ አገልግሎት ስፍራዋ ከተመለሰች ከአጭር ጊዜ በኋላ ተከትሏት ሄደ። ሃገሬ ብላ በምታገለግለው በዚያ ምድር የቅጋቡ ሲሆን በዚህ ወቅት ወንጌልን በመስበክና ክርስቲያን አገልጋዮችን በማሠልጠን አብረው ይሰራሉ።

በሕይወቷ ስለተከሰተው ለውጥ ስትነግረኝ እንዲህ አለች "በሚያስደንቅ ደስታ ውስጥ ነኝ" እግዚአብሔር መስጠቷንና ታማኝነቷን በጣም ልዩ በሆነ መንገድ ባርኮታል። በእርግጠኝነት ባሳለፈቻቸው ዘመናት ብቸኝነትን፣ ተስፋ መቁረጥን፣ መገፋትን፣ የገንዘብ እጥረትንና በስጋት ውስጥ መቆየትን አሳልፋለች ይሁንና ከምድር ዋጋ ይልቅ ዘለዓለማዊን ዋጋ ስለመረጠች፥ እግዚአብሔርም አልረሳትም።

(9). ይህ ታሪክ ለእኛ የሚገልጠው፡

ሀ. እግዚአብሔርን ላስቀደሙ ሁሉ እጮኛን ያዘጋጅላቸዋል።
ለ. እያንዳንዱ ያገባ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።
ሐ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቅድሚያ የሰጡ ሁሉ፥ ምንም ይሁን በተገቢው። ሰዓት የሚያስፈልጋቸውን ያሟላላቸው ዘንድ በእርሱ ሊታመኑ ይችላሉ።

ያላገቡ፣ የትዳር ጓደኛ የሞተባቸውና የፈቱ ሰዎች ጋብቻን መፈለግ ይኖርባቸዋልን? ቀደም ሲል ያላገባ ላጤን ሰው ከጋብቻ የሚከለክል አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንደሌለ ቀድሞውኑ ተመልክ ተናል። ሐዋርያው ጳውሎስ መበለቶች እንደገና እንዳያገቡ ሲያበረታታ፣ ከመረጡ ግን ማግባት የተፈቀደላቸው እንደሆነ ይናገራል (1ቆሮ. 7፡8-9)።

በክፍለ ትምህርት 5 ፍችን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን ተወያይተናል። ይህንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ባይሆንም በአጠቃላይ ዳግም ጋብቻ፣ ለፈታ ክርስቲያን የተከለከለ ሆኖ እንደቀረበ አሳይተናል። ጋብቻ ሊፈቀድ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ አንዱ የትዳር አጋር የዝሙትን ተግባር በመፈጸም የትዳር አንድነታቸውን ያፈረሰ እንደሆነ ብቻ ነው። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ብትሻ በውሳኔህ ውስጥ ይመራሃል፤ እርሱን የሚያስደስት፣ የበለጸገና ሙሉ የሆነ ሕይወትን ይሰጥሃል።

(10). ለማግባት ወይም ላለማግባት ውሳኔን የሚያደርግ ሰው ሊመራበት የሚችልበትን መርህ ጻፍ።

# የተለዩ ችግሮችን መጋፈጥ

## *ዓላማ 4 የላጤ ሰው ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ።*

በዚህ ክፍለ ትምህርት ቀደም ባለው ክፍል ምንም እንኳን ያሉበት ሁኔታ በጣም ተመሳሳይ ቢሆንም አንደኛዋ ደስተኛ ሌላኛዋ ሐዘንተኛ ስለሆነች ሁለት ላጤ ሴቶች የተሰጠውን ምሳሌያዊ ማብራሪያ አስተውለሃልን? ችግራቸው ከእነርሱ ውጭ የሆነ ሳይሆን በራሳቸው ውስጥ እንደሆነ ያመለክታል። እንደ ነጠላ ሰው የሚያጋጥሙህን ችግሮች ለመፍታት የሚረዱህ አንዳንድ መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. *ወደ ራስህ ተመልከት።* ያለህበትን ሁኔታ መለወጥ አትችል ይሆናል፥ ይሁንና የምትመለከትበትን መንገድ መቀየር ትችላለህ። የጌታ ደስታ ለአንተ ብርታትህ እንደሆነ አስተውል! "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" (ፊል. 4:13)።

2. *በክርስቶስ ውስጥ ያለህን ስፍራ አስተውል።* ሕይወቱን ለአንተ ሰጥቷል! ይወድሃል፤ አንተ በእርሱ ሙሉ ነህ (ቆላ. 2:10)። አንተ ለቤተክርስቲያን የእርሱ መልካም ስጦታ ነህ። በእርሱ አገልግሎት ውስጥ አንተ ራስህን ለመስጠት ያለህን የተለየ ነፃነት ተጠቀምበት። ለእርሱ አገልጋይ ትሆን ዘንድ ይህንን እድል ስለሰጠህ አመስግነው፥ ለእርሱ መሆን የምትችለውን ሁሉ ሁን።

3. *ሌሎችን በመርዳት ተሳተፍ።* ከአንተ በላይ በስቃይ ውስጥ ያሉ ብቸኛ የሆኑ፣ ከአንተ በላይ የሚጨነቁ ብዙ ሰዎች አሉ። የእነርሱን ሸክም ማቃለል የምትችልባቸውን መንገዶች ተመልከት። ተግባቢ ሁን፤ በስራ ተጠመድ፤ ሁልጊዜ ወደፊት የምትመለከተው አንድ ነገር ይኑርህ።

ባሏ የሞተባት አንዲት ጓደኛ አለችኝ። ባሏ ከሞተ በኋላ ለብዙ ዓመታት እረፍት የሌለበትን ሕይወት አሳልፋለች። በማለዳ በመነሳት በቀኑ ውሉ ውስጥ ያለ እረፍት ስትደክም ትውላለች። በየቀኑ እንደዚህ ማሳለፍ የምትፈልግበት ምክንያት እንዲደክማትና ማታ መተኛት እንዲያስችላት ነበር። እንዲህ ዓይነት ሕይወት እግዚአብሔርን የማያስደስት እንደሆነ ቀስ በቀስ ማስተዋል ጀመረች። በራሷ በማዘንና ንስሃ በመግባት የየቀኑ ሕይወቷን ጠቃሚ በሆኑ ተግባሮች ትሞላ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳት ጠየቀችው። አሁን በእያንዳንዷ ምሽት ወደ መኝታ ከማምራቷ በፊት በሚቀጥለው ቀን የምታከናውናቸውን ጉዳዮች በዝርዝር ታስቀምጣለች። በዝርዝሯ የመጀመሪያው ብቻዋን ከእግዚአብሔር ጋር መጽሐፍ ቅዱሷን በማንበብ፣ በማሰላሰልና በጸሎት የምታሳልፍበት ጊዜ ነው። በየቀኑ ለሚኖራት ስራ በቂ የሆነ ጊዜ ከወሰነች በኋላ፥ በሽተኞችን መጉብኘት፣ መጋቢውን መጉብኘት፣ በበሽታ ወይንም በችግር ውስጥ ላለ ሰው በሳህን



ምግብን አዘጋጅታ መውሰድ፣ ሥራ የበዛባቸውን እናቶችን በሥራ ማገዝ የመሳሰሉትን ሌሎችን የምትረዳበትን እቅድ በመቀጠል ታስቀምጣለች። ይህንን ማከናወን በጀመረች በኋላ በእያንዳንዱ ቀን የምትሠራቸው መልካም ሥራዎች ስላሏት ሕይወቷ ስኬታማና ደስተኛ ሆነ። አዳዲስ ወዳጅነቶችን በየጊዜው ካለማቋረጥ ማግኘት ጀመረች። በሐዘን የተሞላ የነበረውን የሕይወቷን ገጽታ ዘለዓለማዊ ዋጋ ያላቸውን ጉዳዮች ለማከናወን የሚረዳት ጥሩ አጋጣሚ አድርጋ ለውጣዋለች። ይህንን ለማከናወን የተለየ ተፈጥሮአዊ ስጦታ አላስፈለጋትም፤ እሷ ያደረገችው ነገር እግዚአብሔር የሰጣትን ስጦታ ብቻ መጠቀም ነበር።

ምናልባት ለመኖር የሚያስፈልግህን ለማግኘት በማያስደስት ወይም ጊዜን አባካኝ የሆነን ሥራ መሥራት ይኖርብህ ይሆንና እንደዚች ባልቴት ብዙ ነፃ የሆነ ጊዜ አይኖርህ ይሆናል። ስራህን የክርስቶስን ፍቅር ለማሳየት ተጠቀምበት። በሥራህ እርሱን ማክበር የምትችልባቸውን መንገዶች አስብ። ትኩረትህን ሁሉ በእርሱ ላይ ስታደርግ ሕይወትህን በደስታና በሰላም እርሱ ይሞላዋል።

4. *መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ፣ ለጥሞናና ለጸሎት ስፈ ጊዜ ይኑርህ፤* አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ በሆነ ሥራ ደክማ፣ ከዕለቱ ሜና የተነሳ ተስፋ ቆርጣ፣ ከባሏ በመለየቷ የጠለቀ ሐዘንና ብቸኝነት ተሰምቷት ወደ ቤት የምትመለስ መበለትን አውቃለሁ። እነዚህን መጥፎ ጊዜያት ማሸነፍ እንዳለባት ተምራለች። ምን ይሆን ፈውሱ? የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ነው! ከፍ ባለ ድምጽ ማንበብ፣ ባለህ አጋጣሚ ሁሉ አንብበው። በቴፕ የተቀዳ መጽሐፍ ቅዱስ ሲነበብ አዳምጥ። የተቻለህን ያህል ወደ አዕምሮህ ውስጥ አስገባው፤ ያለህበት ሁኔታ ህያው በሆነው በክርስቶስ ኃይል ይለወጣል። ቃሉ በልባቸው ለተሰበሩ መጽናናትን ያመጣል። እረፍት ለሌላቸው እረፍትን፣ ተስፋ ለሌላቸው ተስፋን ያመጣል። ከሸክምህ በላይ ከፍ ያደርግህና ለነገ ብርታትን ይሰጥሃል። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥና በጸሎት እርሱን በምትጠብቅበት ጊዜ ይናገርሃል። የእርሱ ፍቅር ከአንተ ውስጥ ሲፈስ ልብህ ተትረፍርፎ እንዲሞላ ያደርገዋል።

5. *በመጨረሻ ችግሮችህን ለመፍታት በዚህ ጥናት የመጀመሪያ ክፍል የተሰጠህን ክርስቲያናዊ መርሆዎች ተግባራዊ አድርግ።* ግልጽ የሆነ መፍትሔ ካለ፥ ችግሩን ለመፍታት ስትሞክር እግዚአብሔር መልሱን ያሳይሃል። መፍትሔን የማታይ ከሆነ ችግሩን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ስጥ፥ እግዚአብሔር ለአንተ በጐ አድርጐ ያከናውነው ዘንድ ታመነው። ያለህበት ሁኔታ ምንም ይሁን በድልና በደስታ የተሞላ ክርስቲያናዊ ሕይወትን መኖር ትችላለህ። መከራህ በበዛ መጠን እግዚአብሔር ፈቃዱን ይፈጽም ዘንድ በማመንና በመታዘዝ ስትፈቅድለት ለሌሎች ያለህ ምስክርነት እጅግ ታላቅ ይሆናል።

(11). ለሚከተሉት ችግሮች መፍትሔዎችን ለመፈለግ ይረዳ ዘንድ የትኛው መመሪያ ተግባራዊ መሆን ይገባዋል?

ሀ. ባሏ ከፈታት ጊዜ ጀምሮ ማርታ ራሷን አንድ ዋጋ እንዳለው ሰው አድርጋ የመመልከት ችግር አለባት። የሷ ማንነት በባሏ ውስጥ የተሟጠጠ በመሆኑ ከፍች በኋላ ለሷ በሕይወቷ ውስጥ ቀሪ የሆነ ምንም ዓይነት ዓላማ ያላት አይመስላትም። ሊረዳት የሚችለው ምንድነው?

ለ. አለማየሁ በኮሌጅ ውስጥ የክፍል ጓደኛው ከሆነች ልጃገረድ ጋር ፍቅር የያዘው ወጣት ነው። ተጫጭተው የነበረ ሲሆን ለጋብቻ ትንሽ ጊዜ ሲቀራቸው ልታገባው እንደማትችል ነገረችው። ሐዘኑን ለመርሳትና ደስታን ለማግኘት ከሌሎች የኮሌጅ ተማሪዎች ጋር የተጣመረ ሲሆን ብቻውን ሲሆን ከፍተኛ ድምጽ ያላቸውን ሙዚቃዎች በመክፈትና በመዝፈን ችግሩን ላለማሰብ ያስችሉኛል ብሎ ያሰባቸውን ማንኛውንም ነገሮች በመስራት ጊዜውን ያሳልፋል። ዓለማየሁ ክርስቲያን ቢሆንም እንዳቸውም የሚያደርጋቸው ነገሮች አላስደሰቱትም። ይልቁንም እረፍት ማጣቱና ደስተኛ አለመሆኑ ብዙውን ጊዜ ይሰማዋል። የበለጠ ሊረዳው የሚችል መመሪያ ምንድነው?

ሐ. አረጋሽ የታመሙና ባላቸው የሞቱባቸውን እናቷን ለመንከባከብ የኮሌጅ ትምህርቷን አቋርጣ ቤት መቀመጥ ስለነበረባት ምሬት በውስጧ ገብቷል። ሕይወት ትክክል ያልሆነ እንደሆነ ይሰማታል።

መ. ለምለም ባሏ ከሞተ ጊዜ ጀምሮ ስራዋን ሁሉ እንዲያከናውኑላት በቤተሰቦቿ፣ በጓደኞቿና በጐረቤቶቿ ላይ ጥገኛ ሆናለች። ቤቷን በፍጹም ለቃ አትወጣም፥ ሰዎች ብዙውን ጊዜ እንዲጎበኟት፣ የሚያስፈልጋትን ምግብ እንዲያቀርቡላት፣ የምትጠይቃቸውን ሁሉ እንዲሠሩላት ትጠብቃለች። ትኩረትን ለራሷ ብቻ የሰጠች ትመስላለች። ሰዎች ስለ እርሷ እንደማይጠነቀቁላት፣ እርሷ የተሰቃየችውን ያህል ማንም እንዳልተሰቃየ በምሬት ትናገራለች። ለምለም በጣም ተስፋ ቆርጣለች።

ሠ. ደበበ ከኮሌጅ ገና መመረቁ ሲሆን ወደ አገልግሎት ለመግባት በመዘጋጀት ላይ ነው። ይሁንና ገበሬ የሆነው አባቱ በቅርቡ ስለወደቀ ጀርባው ላይ ስብራት አጋጥሞታል። ለረጅም ወራት ከዚህ በሽታ የተነሳ የእርሻውን ሥራ መስራት አይችልም። ከዚህም የተነሳ፥ ሥራውን ተነስቶ ብቻውን መስራት እስኪችል ድረስ፥ ደበበ እንዲረዳው ጠይቆታል። ደበበ ባለበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ዋና መሪ በሆኑት በአንዱ ረዳት መጋቢ እንዲሆን ጥያቄ ቀርቦለታል። ይህንን የመሰለ መልካም እድል ቸል ቢለው ዳግመኛ ሊያገኘው እንደማይችል በማሰብ ፈርቷል።



# ቤተ ክርስቲያን እንዴት መርዳት ትችላለች?

***ዓላማ 5 ቤተክርስቲያን ላጤ አባላቶቿን ለመርዳት መከተል የሚገባትን መርሆዎችን ለማስተዋል።***

በቅርቡ በአንድ ቤተክርስቲያን ይህን የመሰለ ማስታወቂያ ተለጥፎ አነበብኩኝ። "በስህተትም ይሁን በዕቅድ ላጤ የሆናችሁ እድሜያችሁ ከ19-90 የሆነ ሁሉ ወደ አዲሱ የላጤዎች ክፍላችን ኑ" በስህተት የሚለው የሚያሳየው ለጋብቻ ጠያቂ ከማጣት የተነሳ ላጤ መሆንን ሲሆን፣ በዕቅድ የሚለው ደግሞ በራስ ውሳኔ ላጤ ለመሆን በራስህ መምረጥህን ያመለክታል። ይህ ዐረፍተ ነገር ለላጤ ሰው ፍላጐቶችና ለሰብአዊነት ክብር በከፍተኛ ሁኔታ አለመጠንቀቅን ገልጾ ያሳያል። የዚች ቤተክርስቲያን ትክክለኛ ሐሳብ ብቸኛ የሆኑ ሰዎችን መርዳት ሲሆን፣ ልትደርሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች የመረዳትና እነዚህን ሰዎች እንዴት መርዳት እንደሚገባቸው እውቀት ያንሳታል።

ሌላው ቤተክርስቲያን ደግሞ "ለጥንዶችና ለነጠላዎች" የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል አለው። ጥንዶች የተጋቡ ሰዎችን ሲያመለክት፣ ነጠላ መተውንና አለመፈለግን ያሳያል።

ቤተክርስቲያን ለላጤ ሰው ውጤታማ የሆነና አስፈላጊ የሆነ አገልግሎት ሊኖራት ይችላል። መልእክቶች ክርስቲያኖች አንዱ ሌላውን ያገለግል ዘንድ ያበረታታሉ። የሚከተሉት ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

| | |
|---|---|
| ገላትያ 6፡2 | "ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም። እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ" |
| ኤፌሶን 4፡32 | "እርስ በእርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ" |
| ገላትያ 6፡10 | "እንግዲያስ ጊዜን ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ" |
| ያዕቆብ 5፡16 | "እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ" |
| ሮሜ 12፡5፥10፥13፥15 | "እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን . . . በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ . . . በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ . . . ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ" |

ፊልጵስዩስ 2:4 "እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ"

አንዲት ቤተክርስቲያን ነጠላ የሆኑትን አባሎቿን እያንዳንዱ የቤተሰብ ሕብረት በመከፋፈል አልፎ አልፎ ምግብ እንደጋበዟቸው፥ በመዝናኛ ጊዜ ወይም በሌሎችም የአንድነት ጊዜያቸው እንዲያካትቷቸው ታበረታታለች። ሌላኛዋ ቤተክርስቲያን አባላቶቿን ከ10-15 በመከፋፈል እያንዳንዱ ሕብረት ያገቡ ሰዎችንና ነጠላ ሰዎችን እንዲያካትት በማድረጓ እነዚህ ሕብረቶች ለአንድነት ጊዜና ቃሉን ለመካፈል ለበርካታ ጊዜያት ይገናኛሉ። ሕብረቶቹ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች ሌሎችን ሰዎች የማወቅ እድል እንዲያገኙ በየሦስት ወሩ እንደገና በአዲስ መልክ ይዋቀራሉ።

ለወጣት ላጤዎች ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ቃሉን ለመካፈል፣ የተለዩ ጊዜዎችን ማዘጋጀትና በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግና ሕብረትን በማድረግ የሚረዳ ይሆናል። እድሜያቸው የገፋ ላጤዎች ባገቡ ሰዎችና በላጤ ሰዎች በተደባለቁ ህብረቶች ውስጥ መሆን የበለጠ ምቹ ሆኖ ሊሰማቸው ይችላል። ያገቡ አማኞች ርዳታቸውን መለገስ የሚችሉበት የተሻለው መንገድ ለላጤ አማኞች ስሜቶችና የተለዩ ፍላጐቶች ንቁ መሆንን በማዳበር ነው።

ጉልማሳ ላጤዎች ያላቸውን ተሰጥኦ መጠቀም በሚቻልበት ትርጉም ባለው በቤተክርስቲያን እንቅስቃሴዎች በማሳተፍ የበለጠውን ጊዜያቸውን ለአገልግሎት ተግባር በመስጠት ነጻነታቸውን እንዲጠቀሙ ማደረግ ተገቢ ነው። እነዚህ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢና ለሌሎችም መሪዎች የሚያስደንቁ ረዳቶች ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይ ከመሳተፍ ወደማፈግፈግ በሚያዘነብሉትና ዓይነአፋር በሆኑት ላይ ትኩረትን አድርግ። ምናልባት እነዚህ ሊሸከሙት በማይችሉት ጉዳት እየተሰቃዩና እንደሚወደዱ ማረጋገጫን ይፈልጉ ይሆናል።

እንዲህ የሚል አንድ የታወቀ ዜማ አለ።

*እኔ ደንጋይ ነኝ እኔ ደሴት ነኝ።*
*ህመም የማይሰማው ድንጋይ።*
*ምንም የማያለቅስ ደሴት።*

ይህ ግጥም በርግጥ በሕይወት ውስጥ ባሉ ግንኙነቶች በከፍተኛ ሁኔታ የተጐዳ የላጤ ሰው ጩኸት ነው። ክርስቶስ እንዳስተማረን በአንዳንዶች የምንካድበት አስቸጋሪ ሁኔታ ሊኖር ቢችልም እንኳን ከሰዎች ጋር ጥሩ ሕብረት ይኖረን ዘንድ ያስፈልጋል። ልናጣው ከምንችለው በላይ የምናገኘው እጅግ የላቀ ነው።



በሁሉም እድሜ ውስጥ ከሚገኙ ላጤ ሰዎች ጋር ወዳጅነትን ለመመስረት ጊዜን የሚሰጡ ባለትዳሮች አዲስ አመለካከትን በመማር በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ የሚገኘውን የበዛ ልዩነት ማድነቅ ይችላሉ። ለክርስቲያን ኅብረትና አንድነት አስፈላጊው ነገር እሱ ወይም እርሷ የክርስቶስ መሆናቸው እንጂ የሰውየው ማኅበራዊ አቋም ወይም የጋብቻ ሁኔታ መሰረት ሊሆን እንደማይችል እያንዳንዱ ሰው ማወቅ ይኖርበታል።

(12). ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ቤተክርስቲያን ላጤ አባላቶቿን ለመርዳት ትችል ዘንድ መከተል የሚገባትን ጥሩ መርሆዎች የሚወክሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. የቤተ ክርስቲያን ዋናው ትኩረት የቤተሰብ ህብረቶች ፍላጐቶችን ማሟላት መሆን ይገባል።
ለ. ላጤ ሰዎች ከቤተሰቦች ጋር በሚከናወኑ ሥራዎች መካተት ይገባቸዋል፡
ሐ. በእድሜ ገደብ ሰዎችን ከመመደብ ይልቅ ያገቡ ወይም ላጤዎች በማለት ሰዎችን በሕብረት መለየት የተሻለ ነው።
መ. ሰዎች ትርጉም የለሽ የሆነ መንገድ ወይም የግል ክብራቸውን በሚያሳጣ መንገድ ስያሜ እንዳይሰጣቸው ትልቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።
ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ የሆኑት እርስ በርሳቸው የመደጋገፍን ትኩረት ያደርጉ ዘንድ ያበረታታል።
ረ. ላጤ ሰው ከፍተኛ ነጻነት ስላለው ትርጉም ባለው አገልግሎት ለምታሳትፍ ቤተክርስቲያን በረከት መሆን ይችላል።
ሰ. የክርስቲያን ህብረት የክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ ሊያካትት ይገባል።

የሚከተሉትን ሦስት ክፍል ትምህርቶች በያዘው በመጨረሻው ክፍል በሕይወት ልምምዳችን ውስጥ ሁላችንም በተወሰነ ደረጃ የምንጋፈጠውን የተለዩ የችግር ሁኔታዎች እንመለከታለን። ከዚህ የጥናት ክፍል ብዙ እንዳወቅህና የመጨረሻው ክፍል የክርስቶስ መሆንና በክንፎቹ ጥላ ሥር ማረፍ እንዴት የከበረ እንደሆነ እንድታስተውል እንደሚረዳህ ተስፋ እናደርጋለን። ይህንን ጥናትህን ስትቀጥል ጌታ እንዲባርክህ እመኝልሃለሁ።

---

## የሙከራ ፈተና

ምርጫ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሻለውን መልስ ምረጥ፡፡

1. የመገፋት ስሜት በበለጠ ሁኔታ የሚሰማው

ሀ. ባለቤቱ የሞተችበት ባል
ለ. ያላገባ ሰው
ሐ. የተፈታ ሰው

2. ሐዋርያው ጳውሎስ ላጤ ሰዎች በላጤነት ቢዘልቁ የተሻለ ነው ያለበት ምክንያት

ሀ. ላጤ ሰዎች ካገቡ ሰዎች ይልቅ ለረጅም ጊዜ ስለሚኖሩ ነው፡፡
ለ. የላጤነት ሕይወት ደስታ የተሞላበት ስለሆነ ነው፡፡
ሐ. ጋብቻ ለግብረገብ የለሽነት እንደ አማራጭ ሆኖ መታየት ስለሚገባው ነው፡፡
መ. ላጤ ሰዎች ሐሳባቸው ሳይባክን ለእግዚአብሔር ሥራ የበለጠ ጊዜ የመስጠት ችሎታ ስላላቸው ነው፡፡

3. የላጤነት ሕይወት እንደ ልዩ ሥጦታ የተቆጠረው ለምንድነው?

ሀ. ከማግባት ይልቅ ጊዜያቸውን ለመንግሥተ ለማየት ለመሠዋት የመረጡ ሰዎች ለቤተክርስቲያን የተለዩ በረከቶች ስለሆኑ ነው፡፡
ለ. ማንም ላጤ ሆኖ መዝለቅ ይችላል፣ ይሁንና ይህንን ለማድረግ ጥቂቶች ብቻ ይመርጣሉ፡፡
ሐ. ሳያገቡ እስከ መጨረሻው ለመኖር መምረጥ እግዚአብሔር ለነዚያ ሰዎች የሚሰጠው ሥጦታ ነው፡፡

4. በላጤ ሰው ሕይወት ውስጥ የመጀመሪያ ቅድሚያ ሊኖረው የሚገባ ምንድነው?

ሀ. ክርስቲያንን ማግባት
ለ. በሕይወቱ ያለ የእግዚአብሔር ፈቃድ
ሐ. ሌሎችን የሚያስደስትን ነገር መሥራት
መ. ብቸኝነትን መቋቋም

5. የእግዚአብሔር ፈቃድ መጀመሪያ እኛ

ሀ. ላጤ እንድንሆን ነው፡፡
ለ. እግዚአብሔርን እንድንመስል ነው፡፡
ሐ. ያገባን እንድንሆን ነው፡፡



6. ለጠንካራ ጋብቻ ትክክለኛው መሠረቱ

ሀ. የተለያዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ናቸው፡፡
ለ. ለረጅም ዓመት በቤተክርስቲያን መስራት ነው፡፡
ሐ. ጠንካራና የበሰለ ክርስቲያናዊ ባህሪን ማዳበር ነው፡፡

7. ለክርስቲያን ላጤ ሰው ከእነዚህ መካከል እጅግ መጥፎ የሆነው ምርጫ የቱ ነው?

ሀ. ጋብቻን ቢሻ እንኳን ላጤ ሆኖ መዝለቅ፡፡
ለ. አማኝ ያልሆነን ማግባት፡፡
ሐ. ከሌሎች ላጤ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረትን መፈለግ፡፡

8. መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ ጋብቻን የሚከለክለው

ሀ. የፈታን ሰው
ለ. የትዳር ጓደኛቸው የሞተባቸውን
ሐ. ላጤ ሰውን
መ. ጃንደረባ ሰውን

9. ለማግባትና ላለማግባት ከመወሰን በፊት የመጀመሪያው ደረጃ መሆን ያለበት

ሀ. ክርስቲያን የትዳር ጓደኛ መፈለግ
ለ. በእድሜ የገፉ ክርስቲያኖችን ምክር መከተል
ሐ. ለራስህ ጥንቃቄ የተሞላበት የሕይወት ጉዳናን መከተል
መ. በሕይወትህ ላለው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ መስጠት

10. ከነዚህ መርሆዎች ውስጥ ቤተክርስቲያንን የላጤ ሰዎችን ፍላጐት ለማሟላት ይመራት ዘንድ በጣም አስፈላጊው የትኛው ነው?

ሀ. የእያንዳንዱን የተለየ ፍላጐት ለማገልገል ያገቡና ያላገቡ ብሎ በመከፋፈል ሰየብቻ በህብረት መታቀፍ ይኖርባቸዋል፡፡
ለ. ላጤ ሰዎችን በቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲጣበቡ አድርግ፣ እነርሱም ደስተኛ ይሆናሉ፡፡
ሐ. ለክርስቲያን ህብረትና አንድነት መሠረቱ እሱ ወይም እርሷ የክርስቶስ የመሆናቸው እውነታ እንጂ የሰዎቹ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ማዕረግ አይደለም፡፡

11. *አጭር መልስ* ላጤ ሰው ላሉበት ችግሮች መፍትሔ ያገኝ ዘንድ የሚረዱትን አምስት መመሪያዎችን ዘርዝር፡፡

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7. ሀ. ሐሰት
   ለ. እውነት
   ሐ. እውነት
   መ. ሐሰት
   ሠ. እውነት
   ረ. እውነት

1. ለ. (ፍርሃትን ጠቅሰህ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በሁለተኛው ምሳሌ ሰናይት የወደፊቱን ለእግዚአብሔር አሳልፋ ስለሰጠች ፍርሃት አይታይባትም።)

8. ክርስቲያን ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ መጠመድ የለበትም (2ቆሮ. 6:14)።

2. ሀ. 1ጴጥ. 4:12-19
   ለ. ኢሳ. 53:3፤ ዮሐ. 1:11
   ሐ. ዘዳ. 33:12፤ ኢያ. 1:9
   መ. 2ቆሮ. 1:3-4፥ 6

9. ሐ

3. ሀ. ከራሱ ስህተት የተነሳ ከፍተኛ ፈተና ውስጥ እያለፈ ላለ ለየትኛውም ሰው ተገቢ ይሆናል።
   ለ. እግዚአብሔር እንድንፈተን ቢፈቅድም እንኳን ከፈተናው ውስጥ በድል እንደሚያወጣን ይገልጻል።

10. የአንተ መልስ። ይህንን ሃሳብ ማካተት ይኖርበታል። ለማግባት ወይም ላለማግባት ለመወሰን የመጀመሪያው ደረጃ በሕይወትህ እግዚአብሔር ላለው ፈቃድ ሙሉ መስጠትን ማድረግ ነው። ከዚህ በመቀጠል እግዚአብሔር ፈቃዱ ምን እንደሆን በልብህ ያረጋግጥልህ ዘንድ ፍቀድለት። እሱ በትክክለኛው መንገድ ውስጥ ይመራሃል።

4. ሀ. የትዳር ጓደኛ ለሞተበት ሰው የተገባ ይሆናል።
   ለ. እግዚአብሔር ሐዘናችንን የሚያውቅና ሩህሩህ እንደሆነ ይገልጻል። እርሱን ከታመነው ሐዘናችንን ወደ ደስታ ይለውጠዋል።

11. የአንተ መልሶች። የእኔ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ማርታ ከሁሉም በፊት በክርስቶስ ያላትን ማንነት በመጀመሪያ ማስተዋል ይኖርባታል።
ለ. ዓለማየሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ጊዜውን፣ የጥሞና ጊዜውንና ከወንዶችም ሆነ ከሴቶች አማኞች ጋር የነበረውን ህብረት ቢያሳድግ የበለጠ ተጠቃሚ ይሆን ነበር።
ሐ. አረጋሽ ልቧን መመርመርና ሁኔታዎችን የምትቃኝበትን እይታ መለወጥ ይገባታል። ይህ ወቅት ለእናቷ ያላትን ፍቅርና ለእርሷ የቀረበች መሆኗን የበለጠ የምትጨምርበት ወቅት ነው።



መ. ለምለም ሌሎችን በመርዳት ውስጥ በመሳተፍ ትጠቀም ነበር። የሚያስፈልጋት ነገር ስለተሟላ፥ ጤናማ ስለሆነች፥ ሌሎችን ማገልገል የምትችል በመሆኗ አመስጋኝ መሆን ይገባታል።
ሠ. ደበበ በዚህ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለመለየትና ችግርን መፍትሔ ለመስጠት ክርስቲያናዊ መርሆዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይገባዋል። ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ከሚያጠፋው ጊዜ ይልቅ ምናልባት ከአባቱ ጋር የሚያጠፋው ጊዜ ለእርሱ መልካም ሥልጠና ይሆናል። ወይም ከአባቱ ጋር ሊሰራ የሚችል አንድን ሰው የማግኘት እድል ሊኖር ይችላል። አስፈላጊው ጉዳይ እርሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማግኘቱ ነው።

5. የአንተ መልስ። ይህን ጥያቄ በሚገባ እንዳሰብክበትና ለችግሮቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርዳታዎችን ለመፈለግ እንደሞከርክ ተስፋ አደርጋለሁ።

12. ሀ. ጥሩ መርሆ አይደለም።
    ለ. ጥሩ መርሆ ነው።
    ሐ. ጥሩ መርሆ አይደለም።
    መ. ጥሩ መርሆ ነው።
    ሠ. ጥሩ መርሆ ነው።
    ረ. ጥሩ መርሆ ነው።
    ሰ. ጥሩ መርሆ ነው።

6. ጋብቻን በመሻት ሁልጊዜ ከማሰብ ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥትና እርሱ ለሕይወታችን ያለውን ፈቃድ መሻት ይኖርብናል። ይህንን የምናደርግ ከሆነ ለእኛ እጅግ መልካም የሆነውን ነገር በሕይወታችን ይጨምራል። ይህም ጋብቻን ሊያካትት ሊችል፥ ባይሆንም እንኳን እግዚአብሔር ሕይወታችንን እየተቆጣጠረና ለእኛ በጐ የሆነውን ነገር እየሰራ እንደሆነ እናውቃለን።

# 7 ግብረ ስጋዊነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ

ትምህርት

በሕይወት ውስጥ ካሉት በጣም አስደሳች ግንኙነቶች አንዱና ዋናው የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት በጋብቻ አንድ ስጋ መሆናቸው ነው። የሰዎች የግብረ ስጋ ግንኙነት የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን፥ ልጆችን ወደዚህች ዓለም ለማምጣት የሚያስችል ብቻ ሳይሆን በወንድና በሴት መካከል የቀረበ ጥምረትና አንድነት እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው።

በሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩት አንዳንዶቹ የሕይወት ከፍተኛ ችግሮች ወንዶችና ሴቶች ግብረ ስጋዊነታቸውን አግባብ ባልሆነ መንገድ ከመጠቀማቸው የተነሳ ነው። ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ከተገለጠው ጥበብና ሰውነታቸውን አስገዝተው ለመጠበቅ ከሚያስችላቸው ከእርሱ ኃይል ውጭ በግብረ ስጋዊነታቸው ላይ እርምጃን ለመውሰድ ይሞክራሉ። በውጤቱም ባልተቀደሰና አካልንም ስሜትንም በሚጐዳ የሕይወት ጉዳና ውስጥ ተጠምደው ራሳቸውን ያገኙታል።

እግዚአብሔር በውስጣችን ያለውን ኃይለኛ የግብረ ስጋዊነት ግፊት ለመቆጣጠር የምንችልበትን በጣም ግልጽ የሆኑ ትዕዛዞችን ሳይሰጠን አልተወንም። ያገባህም ብትሆን ላጤ ይህንን የሕይወትህን ክፍል መግራትን ትለማመድ ዘንድ ከአንተ ይጠበቃል። በቃሉ ውስጥ የሰጠን ትእዛዞች ግብረ ስጋዊነትን ለመለማመድ ድንበር ያስቀምጣሉ። አለመታዘዝ በደለኝነትን፣ ሀፍረትን፣ ስቃይንና ኃጢአትን ወደ ሕይወትህ ያመጣል። መታዘዝ ግን የእርሱ ስጦታ በሆነው ግብረ ስጋዊነት እግዚአብሔርን በደስታና በንጽህና ማገልገል እንድትችል ያደርግሃል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ግብረ ስጋዊነትን ለመግለጽ እግዚአብሔር ያስቀመጣቸውን ወሰኖች እንወያያለን፥ በክርስቲያን አማኝ ሕይወት ውስጥ ግብረ ስጋዊነትን የሚመራባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ምን እንደሆኑ እንመለከታለን።



## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ግብረ ስጋዊነትና ከጋብቻ ውጪ መሆን
- ግብረ ስጋዊነትና ጋብቻ
- ተገቢ ያልሆኑ ግብረስጋዊ ልምምዶች
- በግብረ ስጋዊ ችግሮች ላይ እርምጃ መውሰድ

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ

- በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ግብረ ስጋዊነትን ሊገዛው የሚችለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን ማስቀመጥ፤
- ግብረ ስጋዊ ንጽህና በእግዚአብሔር ለሚጸድቅ ጋብቻ ብቸኛው አማራጭ የሆነበትን ምክንያት ማብራራት፤
- በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዙ የግብረ ስጋዊ ልምምዶችን አደጋዎች መረዳት፤
- ለተሰጡት ግብረ ስጋዊ ችግሮች፥ ችግርን መፍትሔ መስጫ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ መቻል አለብህ።

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለዚህ ክፍለ ትምህርት መነሻ እንዲሆንህ 1ቆሮ. 6፥12-7፥40 እና ኤፌ. 5፥22-33ን አንብብ።
2. በክፍለ ትምህርት 1 የተሰጠውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ክፍለ ትምህርቱን አጥና።
3. የሙከራ ፈተናውን ውሰድና መልሶችህን አመሳክር።

# ግብረ ስጋዊነትና ከጋብቻ (ከግብረ ስጋዊነት) ውጭ መሆን

***ዓላማ 1 ግብረ ስጋዊነትንና ከግብረ ስጋዊነት ውጭ መሆንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህን ለማስቀመጥ።***

በብዙ የዓለማችን ክፍል ያልተጋቡ ወንዶችና ሴቶች የአጭር ጊዜ ግንኙነትን ለመመስረት ወይም ግብረ ስጋዊ "ፍላጉታቸውን" ለማርካት ሲሉ ለተወሰኑ ጊዜያት አብሮ መኖር የተለመደ ድርጊት ነው። የግብረ ስጋ ግንኙነትን ዓለም እጅግ የሚማርክ እድርጋ ስለምታሳይ ወጣቶች የግብረ ስጋ ግንኙነትን እስኪለማመዱ ድረስ አስፈላጊ ነገር ከሕይወታቸው እንደጎደለና ስኬታማ እንዳልሆኑ ይሰማቸዋል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ንጽህና (አለማግባትና ከወሲብ ግንኙነት መቆጠብ) ቦታ የማይሰጠውና ማንም የማይፈልገው መስሉ ይታያል።

ከግብረ ስጋዊነት ውጭ ሆኖ መኖር ለሰው ይቻላልን? በእርግጥም ይቻላል። በሌሉች የሕይወታችን ክፍሉች እንዳደረግነው ሁሉ በዚህም ሁኔታ ውስጥ ፈተናን ለማስወገድ ወደ እግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል መቅረብ እንችላለን። በክፍለ ትምህርት 1 የተወያየንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 1ቆሮ. 10:13ን ከግብረ ስጋዊና ከሌሉች ፍላጉቶቻችን ጋር በማዛመድ በሕይወታችን ልንጠቀምበት እንችላለን። እግዚአብሔር ኃጢአትን ላለማድረግ ፈተናን የምትቋቋምበትን ኃይል ይሰጥሃል፥ ይህም ከጋብቻ ውጭ የሚከናወን የግብረ ስጋ ግንኙነት ኃጢአትን ያካትታል።

(1). እንደ 1ቆሮ. 10:13 እግዚአብሔር የግብረ ስጋ ግንኙነት ኃጢአት ፈተናን ለመቋቋም እንድትችል እንዴት ነው የሚረዳህ?

እግዚአብሔር ከጋብቻ ውጭ ያለ የግብረ ስጋ ግንኙነትን የሚከለክለው ለምንድነው? ብዙ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን፥ ሁሉም ግን እርሱ ለአንተ ካለው ፍቅርና ጥንቃቄ የተነሳ መሆኑን ያመለክታሉ። እግዚአብሔር ዛሬ በዙሪያችን ከምንመለከታቸው ከእነዚህ ከባድ ችግሮች ሊከላከልህ ይፈልጋል። እነርሱም

1. *ሕጋዊ ያልሆኑ ልጆች፡-* ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች ሊንከባከቧቸውና የወላጅነትን ኃላፊነትን ሊወጡላቸው የሚችሉ ሁለቱንም እናትንና አባትን የማግኘት መብት አይታደሉም፣ ብዙውን ጊዜ ችል የተባሉና ፍቅርን የተነፈጉ ናቸው።

2. *የውርጃ መጨመር፡-* ብዙ ሴቶች ከጋብቻ ውጭ ልጆችን ከመውለድ ይልቅ ያረገዙትን በህክምና ዘዴ ማስወገድን ይመርጣሉ። ይህ ደግሞ



ያልተወለደን ልጅ ሕይወት ከማሳጣት የተነሳ የበደለኝነትን ስሜት ስለሚጭር ለከባድ መንፈሳዊ ጉስቁልናና የስሜት ስቃይ ይዳርጋቸዋል።

3. *የአባለዘር በሽታዎች መጨመር፡-* በድንገተኛ ግንኙነት የግብረስጋ ግንኙነትን የሚፈጽሙ ሰዎች እንደ ቂጢኝና ጨብጥ ለመሳሰሉት ገና በማህፀን ያሉ ልጆችን ለሚጉዱና፣ ለእውርነት ምክንያት በሚሆኑና ለሌላ አካላዊ ወይንም አዕምሮአዊ ችግሮች በሚያጋልጡ የአባላዘር በሽታዎች ለመያዝ ያላቸው እድል የሰፋ ነው። ከዚህ ሁሉ የከፋው ግን ኤይድስ ነው። መድኃኒት ያልተገኘለት ከመሆኑም በላይ በኤድስ የተያዙ ሁሉ ዕጣቸው ሞት ነው። ኤይድስ በአሁኑ ወቅት በዓለም ዙሪያ ሁሉ በፍጥነት እየተስፋፋ በመሆኑ የሰው ልጅ እንደ ቅጠል እየረገፈ ይገኛል። እግዚአብሔር ከኤድስም ሆነ ከሌሉች የአባላዘር በሽታዎች እንድትጠበቅና በሕይወት እንድትኖር ፈቃዱ ነው።

4. *የሀሊና ጠባሳ፡-* እግዚአብሔር የግብረ ስጋ ግንኙነት ቋሚ ከሆነ የፍቅር ግንኙነት ውጭ እንዲፈጸም አላቀደም። በግብረ ስጋ ግንኙነት ተጋሪዎች መካከል የፍቅር ግንኙነት በማይኖርበት ጊዜያት ውጤቱ የመገፋት ስሜት ወይንም መዋረድና ክብርን ማጣት ይሆናል። የበደለኝነት ስሜት በአዕምሮ አለመደሰትንና ራስን መውቀስን ያስከትላል።

(2). የበደለኝነት ስሜቶች ብዙውን ጊዜ የሚያስጠነቅቁን

*ሀ.* ተስፋ እንደሌለን መሆኑን ነው።
ለ. ኃጢአት እንደማያስጨንቀን ነው።
ሐ. እግዚአብሔር የሰጠንን ሀሊናችንን ማዳመጥ እንደሚገባን ነው።

ከግብረ ስጋ ግንኙነት ንጹህ መሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ለተረጋገጠ ጋብቻ ብቸኛው አማራጭ ነው። በ1ቆሮ. 7 ሐዋርያው ጳውሎስ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ውጭ መዝለቅ የማይችሉትን እንዲያገቡ ይመክራል። ሳይወድ ላጤ ሆኖ በግብረ ስጋ ንጽህና ለመኖር ለሚሞክርና ስለ ግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም ስለማግባት በውኑ ለሚያልም ሰው የበለጠ ችግርን ወደራስ መጋበዝ ነው። በክፍለ ትምህርት 6 ለክርስቶስ የተሰጠ ላጤ ሰው ለቤተክርስቲያን ስጦታ እንደሆነ ተመልክተናል። ላጤ ሰው የግብረስጋ ግንኙነት ንጽህናን በመጠበቅ ከጌታ ጋር መተባበር የሚችልበት ጥሩው መንገድ ሃሳቡ ወደዚህ ነገር እንዳይወሰድ በመጠበቅ ነው (ያዕ. 1:14-15)። በክፍለ ትምህርት 2 ውስጥ ኃጢአትን ታደርግ ዘንድ እንዳትፈተን አሳቦችህን መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ተነጋግረናል፤ ራስህን በንጽህና ለመጠበቅ አዕምሮህን ካዘጋጀህ ይህንን በተመለከተ ጌታ ይረዳሃል። ሕይወትህን በደስታና ጌታን በመታዘዝ ምራ። በሁሉም አቅጣጫ ስለ ወደፊቱ በምታስበው ሁሉ በጌታ ላይ ታመን። በምትወስደው በእያንዳንዱ እርምጃ እርሱ ይረዳሃል።

በግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጐቶች ላይ በተገቢ አሳቤ እርምጃን ለመውሰድ እንድትችል የሚረዳህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይህ ነው።

> ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳን አይሠለጥንብኝም። መብል ለሆድ ነው፤ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንንም ያንንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሥጋ ነው፤ ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖር የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም። ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ (1ቆሮ. 6:12-13፥ 19-20)።

እግዚአብሔር በግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጐት ውስጥ የምንዋልልበትን ሳይሆን ልንቆጣጠረው የምንችልበትን መንገድ ሰጥቶናል። ይህም መንገድ የተከበረና የተቀደሰ መንገድ ይባላል። ይህም የግብረ ስጋ ግንኙነት ውጥረቶችን አስፈላጊ በሆኑ እንቅስቃሴዎች እንዲረግብ ማድረግን ያካትታል። የተከበረ መንገድ ማለት "መሠረታዊ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጐቶች በማህበረሰቡ ተቀባይነት ወዳላቸው ተግባሮች ሳይታወቅ የሚለወጡበት የአዕምሮ ሂደት" በመባል ይተረጐማል። በስራ፣ በጨዋታ፣ በማህበረሰቡና በሃይማኖታዊ ተግባሮች በመሳተፍ እርካታ ይገኛል። የግብረ ስጋ ግንኙነት ኃይሎች ጥቅምን ሊያበረክቱ ወደሚችሉ ወደ ኪነጥበብ፣ ስነጽሑፍ፣ ሙዚቃ፣ አትሌቲክስ፣ ፀሎት፣ የጥሞና ጥናት፣ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ወይም አዕምሮንና ፍላጐትን ሊይዝ ወደሚችል ትርጉም ወዳለው እንቅስቃሴ ሊተላለፍ ይችላሉ።

(3). አንድ ሰው የግብረ ስጋ ግንኙነት ንጽህናውን መጠበቅ የሚችልበትን ሁለት መንገዶች ጥቀስ።

የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጐት በራሱ ኃጢአት አለመሆኑ መጠቀስ ይገባል፤ የሰውነታችን አንዱ ባህሪና ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው። ይሁንና እስከ ጋብቻ ቀን ድረስ ሙሉ በሙሉ በማስገዛት መጠበቅ ይኖርበታል። ጌታ በቅድሚያ የእርሱን መንግሥትና የእርሱን ቅድስና ለሚሻ ላላገባ ሰው ስኬታማና በድል የተሞላ ሕይወትን ይሰጠዋል (ማቴ. 6:33)። ላጤ ሆነህ ትዘልቅ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በዚህ ጉዳይ ራስህን በመግዛት "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአዕምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" (ሮሜ 12:1-2) የሚለውን ክፍል ተግባራዊ ታደርገው ዘንድ ያስችልሃል።



(4). ከግብረ ስጋ ግንኙነት ውጪ የሆነ ሰው የሚያስወግዳቸው አራት ችግሮች ምንድናቸው?

ሐዋርያው ጳውሎስ ከግብረ ስጋ ግንኙነት የመራቅ ስጦታ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ይህ ስጦታ ያላቸው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፈው ሲሰጡና ሃሳባቸው ሳይከፋፈል ሲያገለግሉት ለእግዚአብሔር መንግሥት ልዩ ስጦታ ይሆናሉ በማለት ያስረዳል።

## ግብረ ስጋዊነትና ጋብቻ

*ዓላማ 2 ግብረ ስጋዊነትንና ጋብቻን የተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህን ለመረዳት።*

የግብረ ስጋ ግንኙነት የተለመደና የከበረ የጋብቻ ክፍል ነው። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ በማለት ይነግረናል። "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል" (ዕብ. 13:4)።

ሐዋርያው ጳውሎስ የሰዎችን ብርቱ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጐት በመገንዘብ ይህንን ፍላጐት መቆጣጠር የተሳናቸውን በኃጢአት እንዳይፈተኑ እንዲያገቡ ያበረታታቸዋል (1ቆሮ. 7:9)።
የግብረ ስጋ ግንኙነት በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ አስፈላጊ ቦታ እንዲኖረው አድርጎ ሲፈጥር የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድነው?

አንዱ ዓላማ በርግጥም *ዘርን ለማብዛት ነው*። ምድር በሰው ትሞላ ዘንድ የእግዚአብሔር እቅድ ስለነበር ልጆችን ይወልዱ ዘንድ የአካላዊ ውህደት መሻትን ሰጣቸው።

ለአብዛኛው ህያዋን ፍጥረታት የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚከናወነው ሴቷ ማርገዝ በምትችልበት ወቅቶች ብቻ ነው። ይሁንና እግዚአብሔር ሰዎችን፥ ወንዶችንና ሴቶችን፥ ሴቷ መጽነስ በማትችልባቸው ወቅቶች እንኳን የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጐት እንዲኖራቸው አድርጐ ፈጠራቸው። ስለዚህም የግብረ ስጋ ግንኙነት ልጆችን ወደዚህ ዓለም ለማምጣት ዓላማ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሌላው የግብረ ስጋ ተግባር ዓላማ *አንድነት መፍጠር ነው*። ይህ አንድነት ግብረ ስጋዊ ፍቅርን በመለዋወጥ የሚገኝን ደስታን ያካትታል። ባልና ሚስት በዚህ እርካታ ሁልጊዜ ይደሰቱ ዘንድ እግዚአብሔር መብትን ሰጥቶአቸዋል።

ይህ አንድነት በማቴ. 19:4-6 ውስጥ በኢየሱስ ተጠቅሷል። ይህንኑ የኢየሱስን ቃሎች ሐዋርያው ጳውሎስ በጋብቻ ውህደት ውስጥ ያለውን

አስደናቂ አንድነት በመጥቀስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን ጋር ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት ለማሳየት ጠቅሶታል።

> "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል። ከሚስቱም ጋር ይተባበራል። ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ" (ኤፌ. 5፡31-32)።

በ1ቆሮ. 6፡15 ውስጥ ይህ አንድነት በአንድ መልኩ ዝሙትን ለመከላከል ጠንካራ መከራከሪያ ሆኖ አገልግሏል። ጳውሎስ ሲያብራራ በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ ሁለቱ ተባባሪዎች አንድ ስለሚሆኑ፥ የአማኞች ሰውነት የክርስቶስ አካል አንድ ክፍልና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደመሆኑ የዝሙት ኃጢአት በክርስቶስና እንዲሁም ዝሙትን በሚፈጽመው ሰው በራሱ ላይ የሚሠራ ኃጢአት ነው።

(6). በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ የግብረ ስጋ ግንኙነት ዓላማዎች ተጠቅሰዋል?

ሀ. ዘፍ. 1፡26 ለ ዘፍ. 2፡24

የእግዚአብሔር ቃል በጋብቻ ውስጥ ያለን የግብረ ስጋ ግንኙነት በተመለከተ ግልጽ ትዕዛዛትን ይሰጣል። እንደሚከተለው በማሳጠር እናስቀምጠዋለን።

1. *ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ያለ አንድነት ነው።* ይህም በኢየሱስ ቃሎች ውስጥ ተረጋግጧል (ማቴ. 19፡4-6)።

> "ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው አላነበባችሁም? እንዲህም አለ፤ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ የተባለው በዚህ ምክንያት አይደለምን? ከእንግዲህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም"

ስለዚህ የግብረ ስጋ ግንኙነት በባልና በሚስት መካከል ብቻ የተፈቀደ ነው። ይህ እስከ ሕይወት ፍጻሜ የሚዘልቅ ግንኙነት ነው። ከሁለት አንዱ ከሌላ ሰው ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነትን ከፈጸመ ይህንን የፈጸመው የዝሙት ኃጢአት በደለኛ ነው።

2. *መተሳሰብ በጋብቻ ውስጥ ላለ የግብረ ስጋ ግንኙነት መመሪያ ነው* (1ቆሮ. 7፡3-4)። ባልና ሚስት እያንዳንዱ የሌላውን ፍላጐት በፍቅር፣ በጋራ አክብሮትና በመረዳት መመልከት ይኖርባቸዋል። ጳውሎስ በጣም ግልጽ አድርጐ ሚስት በራሷ ሰውነት ሥልጣን እንደሌላት ነገር ግን የባሏ እንደሆነ ተናግሯል። በተመሳሳይ መንገድም ባል በራሱ ሰውነት ሥልጣን



እንደሌለው፤ ነገር ግን የሚስቱ እንደሆነ ተናግሯል። እነርሱም "ለእያንዳንዳቸው በክርስቶስ ፍርሀት የተገዙ" መሆን አለባቸው (ኤፌ. 5፡21)፡

በኤፌሶን 5 ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን የጠበቀ የጋብቻን ግንኙነት ምሳሌ በማድረግ ጳውሎስ በክርስቶስና በቤተክርስቲያን ያለውን መገዛትና ፍቅር እንዲያመለክት ያነሳሳዋል።

> ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ። ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ። . . . የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል . . . ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲሁ እንደራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ (ኤፌ. 5፡22-25፥ 28፥ 33)።

መጽሐፍ ቅዱስ በጋራ የመተሳሰብን ሐሳብ በጥሩ ሁኔታ ይገልጸዋል። ሚስት ለባሏ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ጨምሮ የምትገዛ ስትሆን ባሏ ይህንን መብት ነፍጋ ከሚያሳያት በበለጠ ሁኔታ ፍቅርን የሚያሳያት ይሆናል። በተመሳሳይ መንገድ በስራው ሁሉ ለሚስቱ ፍቅርን የሚያሳይ ባል ለፍላጐቶቹ በመገዛት ምላሿን የሚያገኝ ይሆናል።

3. *በጋራ መስማማት ካልሆነ በቀር ባልና ሚስት ከግብረ ስጋ ግንኙነት መከላከል የለባቸውም።* ስምምነቱም ለአጭር ወቅትና ለጸሎት ዓላማ ብቻ መሆን ይገባዋል (1ቆሮ. 7፡5)።

የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊቋረጥ የሚችልባቸው ተቀባይነት ያላቸው ሌሎች ምክንያቶች አሉ። እነርሱም በሥራ ምክንያት ወደሌላ ሥፍራ መጓዝ፣ የጠነከረ ህመም ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶች ይኖራሉ። ይሁንና በጋብቻ ውስጥ ከግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብ ያለ በቂ ምክንያትና ከጋራ ስምምነት ውጭ መከናወን የለበትም።

(7). ይህንን በተመለከተ ጳውሎስ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው? (1ቆሮ. 7፡5)

4. *የግብረ ስጋ ግንኙነት ጋብቻን ይጠብቃል።* ከሁለት አንዳቸው ለእርሱ ወይም ለእርሷ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ተገቢውን ምላሽ ካለመስጠታቸው የተነሳ ስንት ጊዜ ዝሙት እንደሚፈጸም ሳስብ አደነቃለሁ። በጋብቻ ውስጥ ያለ የግብረ ስጋ ግንኙነት፤ በአግባቡ የሚፈጸም ከሆነ ራስን ካለመቆጣጠር ወይም ከመራርነት የተነሳ ሌላ ቦታ ርካታን በመፈለግ ለሰይጣን ፈተና ተላልፎ እንዳይሰጡ ሊጠብቃቸው ይገባል።

እርስ በእርስ በሚዋደዱና በሚከባበሩ ባልና ሚስት መካከል ያለ አካላዊ አንድነት፣ ለጠንካራ ጋብቻና ለጠንካራ ቤተሰብ መገንባት ምክንያት ይሆናል። ወላጆች እርስ በእርሳቸው ያላቸው ፍቅርና መዋደድ፣ ተመሳሳይ ምላሽ በሚሰጡ ልጆቻቸው ይንጸባረቃል።

(8). ግብረ ስጋዊነትንና ጋብቻን በተመለከተ ከእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስ ጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ መርሆዎች ጋር የሚስማሙት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. የግብረ ስጋ ግንኙነት ብቸኛ ዓላማ ዘርን ማብዛት ነው።
ለ. ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እስከ ሕይወት ፍጻሜ የሚዘልቅ ግንኙነት ነው።
ሐ. የተጋቡ ሰዎች ከግብረ ስጋ ግንኙነት መከላከል ያለባቸው በጋራ በመስማማትና ለአጭር ጊዜ መሆን ይገባዋል።
መ. መገዛትና ፍቅር በጋብቻ ውስጥ ለሚታይ የጋራ መስማማት፣ አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው።
ሠ. ሁለቱ አንድ ስጋ ሲሆኑ የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድነትን ይሰጣል።
ረ. ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎታቸውን በማሟላት ጋብቻቸውን መጠበቅ ይችላሉ።
ሰ. ባል ለሚስቱ ፍቅር ካላሳያት መገዛት አይጠበቅባትም።

## ተገቢ ያልሆኑ
## የግብረ ስጋ ልምምዶች

*ዓላማ 3 ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ተገቢ ያልሆኑ ከተባሉ የግብረስጋ ግንኙነቶች ለምን መቆጠብ እንዳለበት ምክንያቶችን ለመስጠት።*

እግዚአብሔር ከግብረገብነት ውጭ መሆንን ይጠላል። በቃሉ ውስጥ ምን እንደተፈቀደና ምን እንዳልተፈቀደ ግልጽ የሆኑ ትእዛዞችን ሰጥቷል። በብሉይ ኪዳን ዘመን በእስራኤል መካከል የማመንዝር ተግባር የፈጸሙ በሞት ይቀጡ ነበር።

(9). ዘሌ. 20:10-21 እና 1ቆሮ. 6:12-7:40ን አንብብ። በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት የግብረ ስጋ ግንኙነት በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሚባለው በማንና በማን መካከል ብቻ ሲሆን ነው?

ሀ. ቀረቤታ ባላቸው ጓደኞች
ለ. የቤተሰብ አባሎች
ሐ. በባልና በሚስት

ዘሌዋውያን 20 ባልና ሚስት ዝምድና ያላቸው መሆን እንደሌለባቸው ግልጽ ያደርጋል። ቅርብ የሥጋ ዝምድና ባላቸው መካከል የሚደረግ



የግብረ ስጋ ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ በጥብቅ የተከለከለ ነው። በዓለማችን በሚገኙ በብዙዎቹ ማኅበረሰብም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

በዓለማችን ውስጥ እየተዘወተሩ ያሉና ዋነኛ ችግሮች የሆኑትን ሦስት ድርጊቶች ወይም ልምምዶች በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ልንወያይባቸው እንፈልጋለን። እነዚህም *ማመንዘር፣ ዝሙትና ግብረ ሰዶማዊነት* ናቸው። በእነዚህ አካባቢዎች ሊመጣ ከሚችለው የፈተና አደጋ ራሳቸውን መጠበቅ ይችሉ ዘንድ ወይም በእንደዚህ ዓይነት የግብረ ስጋ ግንኙነት ኃጢአት ውስጥ የተሳተፉትን መርዳት እንዲችሉ ክርስቲያኖች የተጠነቀቁ መሆን ይገባቸዋል።

## ማመንዘር

ማመንዘር አንድ ያገባ ሰው ወይም ያገባች ሴት በትዳር ካልተጣመሩት ሰው ጋር የሚፈጽሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። ባገባ ሰውና ሚስቱ ባልሆነች ሴት መካከል ወይም ባገባች ሴትና ባልዋ ባልሆነ ሰው መካከል ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ባገባ ሰውና ባላገባች ሴት፣ ወይም ባገባች ሴትና ባላገባ ወንድ መካከልም ሊሆን ይችላል።

ከአስርቱ ትዕዛዛት አንዱ ይህ ነው። "አታመንዝር" (ዘጸ. 20:14) ይህ ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለብዙ ጊዜ በመደጋገም ትዕዛዙ ትኩረት ተሰጥቶበታል (ማቴ. 5:27-28፣ 19:9፤ ሮሜ 13:9፤ 1ቆሮ. 8:9-10ን ተመልከት)

(10). ምሳሌ 6:32ን አንብብ ዝሙትን ስለሚፈጽም ሰው ምንድነው የሚለው?

(11). በ1ቆሮ. 8:18-20 ዝሙትንና ማመንዘርን መፈጸም የማይገባ ስለመሆኑ የተሰጠው ምክንያት ምንድን ነው?

በማቴዎስ 5:27-28 ውስጥ የሚገኙት የኢየሱስ ቃሎች ሐሳባችንን በጥንቃቄ መጠበቅ እንዳለብንና በዚህ የሕይወታችን ክፍል ወደፈተና ሊመሩን የሚችሉ ማናቸውንም አጋጣሚዎች ማስወገድ እንደሚገባን ለእያንዳንዳችን የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። እንዲህ በማለት ነበር የተናገረው "እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል" ብዙዎቹ የዝሙት ተግባሮች ጥንቃቄ የጎደላቸው ንግግሮችና ባህርያት ውጤቶች ናቸው። በመጀመሪያ በንጹህ መንፈስ፣ ከጅርባ ሌላ ምንም ነገር ሳይኖራቸው ይደረጉና ውሉ ሲያድር ግን ለፈተና የሚያጋልጡ ሆነው ይገኛሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ ፈተና እንደንሸሽና በፍጥነት እንድንርቅ ይነግረናል (1ቆሮ. 6:18)። በየቀኑ በመንፈሳዊ ነገር መዘጋጀት ከተቃራኒ ፆታ ጋር ባለህ ግንኙነት ሁሉ ራስህን ክርስቶስን በሚመስል መንገድ መምራት እንድትችል ይረዳሃል። (ስለ መንፈሳዊ ዝግጅት በክፍለ ትምህርት 3 ተወያይተናል)።

የቤተክርስቲያን ጠንካራ መሪ የነበረን አንድን ሰው አውቃለሁ። ለአንዲት ባሏ ለሞተባትና ሁለት ልጆች ላሏት ባልቴት ስላዘነ ብዙ ጊዜ ምግብ ይዞላት ይሄዳል፤ ወይም ቤቷ ጥገና ካስፈለገው ይጠግንላታል። ይህም የቀረበ ወዳጅነት እንዲኖራቸውና ይህም ግንኙነት በፈተና እስከተሸነፈ ድረስ ቀስ በቀስ እንዲያድግ በርን ከፈተ። የሰውየው ምስክርነት ተበላሸ፣ ሰውየውም ሆነ ሴትየዋ በቤተሰቦቻቸውና በጓደኞቻቸው አይን ማፈርያ ሆኑ፣ ከፍተኛ የሆነ ስቃይም ደረሰባቸው። ምንም እንኳን ንስሐ ቢገቡና፥ እርስ በርስ መገናኘትን ቢያቆሙም፥ በሕይወታቸውና በሌሎችም ሕይወት ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ተከናውኗል። እንደ መንፈሳዊ አገልግሎት የተቀጠረው ጅማሬ በጥፋት ተደመደመ።

(12). ጥያቄ 10ና 11ን እንደገና ተመልከት። ከላይ ባለው አንቀጽ ከተገለጸው ሁኔታ ጋር አዛምድ።

## ዝሙት

ዝሙት ከባልና ከሚስት ውጭ ያሉትን የግብረ ስጋ ግንኙነቶችን እንዲሁም ባልተጋቡ ሰዎች መካከል ያለውን የግብረ ስጋ ግንኙነቶች ያመለክታል። ይህንን ቀደም ሲል ስለግብረ ስጋ ግንኙነት ንጽህና ስንመለከት ተወያይተንበታል። ባልተጋቡ ሰዎች መካከል ያለ የግብረ ስጋ ግንኙነቶች ቅድመ - ጋብቻ ግብረ ስጋ ግንኙነቶች በመባል ይጠቀሳሉ።

(13). ከዝሙት ስለ መቆጠብ የሰጠናቸው አራት ምክንያቶች ምንድናቸው?

(14). 1ቆሮ. 7:2፣ 8-9ን አንብብ። ያላገቡ ሰዎች የግብረ ስጋ ግንኙነት ለመፈጸም ከተፈተኑ ማድረግ የሚገባቸው ምንድነው?

ሐዋርያው ጳውሎስ 1ቆሮ. 6ን እንዲህ በማለት ይደመድመዋል። "በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" ኃጢአትን የተሞላ ሰውነት ለእግዚአብሔር ክብርን አያመጣም። አንተ ልታከብረው የምትችለው ከግብረ ስጋ ግንኙነት ኃጢአት ነፃ ሆነህ ራስህን በንጽህና ስትጠብቅ ነው። የድኅነትህን ቅጣት በሥጋው በመሰቃየትና በመሞት የከፈለውን ኢየሱስን ታከብረዋለህ።

(15). ራስህን በቅድስና እንድትጠብቅ የሚገባበት እጅግ አስፈላጊው ምክንያት ምንድነው?

## ግብረ ሰዶማዊነት

***ዓላማ 4 ግብረ ሰዶማዊነት የኃጢአት ተግባር መሆኑን እንዴት እንደምናውቅ ለማብራራት።***



በአንዳንድ የዓለማችን ክፍል ግብረ ሰዶማዊነት (አንድ ዓይነት ጾታ ባላቸው ሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንደ አንድ አማራጭ የሕይወት ጉዳና በግልጽ ሕዝብ እንዲያውቀው ይደረጋል። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ግብረ ሰዶማዊነት ኃጢአት እንደሆነ ይናገራል።

1. *እግዚአብሔር ከመሠረተው የግብረ ስጋዊነት መርሆዎች ተጻራሪ በመሆኑ ኃጢአት ነው።* በተፈጠረበት ጊዜ የሰው ግብረ ስጋዊነት የታቀደው አንድ ለአንድና በተቃራኒ ጾታዎች (በወንድና በሴት) መካከል ይሆን ዘንድ ነው። ሰዎች ግብረ ሰዶማዊ ለመሆን ሲመርጡ እግዚአብሔር ለግብረ ስጋዊነት ያወጣውን መርህ ይተውታል። ሮሜ 1:18-32 ይህ እንዴት እንደ ተከሰተ ያብራራል። "የሚያሳፍርን ነገር አደረጉ፤ የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ለወጡ፣ እግዚአብሔርም በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው።" ሮሜ 1:28 እንዲህ ይላል "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።"

2. *መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ከፋት ስለሚጠቅሰው ኃጢአት ነው።* "ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች በሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ . . . የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም" (1ቆር. 6:9-10)። (ዘሌ. 18:22-23፤ ሮሜ 1:21-27ን በተጨማሪ ተመልከት)።

3. *ከመለኮታዊ ፍርድ የሚመጣ ኃጢአት ነው።* "እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና (ሮሜ 1:18)። (ዘፍ. 19:4-11፣ 24-25ን ተመልከት)። ዘፍጥረት 19 ግብረ ሰዶማዊነት በተስፋፋበት በሰዶም ከተማ የእግዚአብሔርን ጠንካራ ፍርድ ይገልጻል (2ጴጥ. 2:6ና ይሁዳ 7ን ተመልከት)።

ግብረ ሰዶማዊነት ተስፋ የሌለው ሁኔታ አይደለም። የግብረ ሰዶማዊነት ኃጢአት የሚነፃና ይቅር የሚባል ነው። በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ቀደም ሲል ግብረ ሰዶማውያን የነበሩና ከዚህ የኃጢአት እስራት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነፃ የወጡ ሰዎች ነበሩ። በ1ቆር. 6:9 ውስጥ ጳውሎስ ግብረ ሰዶማዊያንን የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማይወርሱ ጋር ይዘረዝረዋል። በቁጥር 11 ላይ እንዲህ ብሏል፦ "ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።"

(16). ይህንን ዐረፍተ ነገር አጠናቅቅ። ግብረ ሰዶማዊነት የኃጢአት ልምምድ እንደሆነ እናውቃለን፤ ምክንያቱም. . . . . . . . . . . .

## የሙከራ ፈተና

ምርጫ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ የተሻለ መልስ ብቻ አለ። ከምርጫህ በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

1. ራስህን በንጽህና የምትጠብቅበት እጅግ አስፈላጊ ምክንያት

ሀ. የግብረ ስጋ ግንኙነት ችግሮችን ለማስወገድ
ለ. በሰውነትህ እግዚአብሔርን ለማክበር
ሐ. በሰዎች ፊት መልካም መሆንን ለማስመስከር
መ. ንጹህ ጓደኛን ለማግኘት

2. በጋብቻ ውስጥ ያለ የግብረስጋ ግንኙነት ዓላማው

ሀ. ዘርን ለማግኘት ነው።
ለ. አንድነትን ለማግኘት ነው።
ሐ. ዘርንና አንድነትን ለማግኘት ነው።
መ. ለመዝናት ነው።

3. ከነዚህ ውስጥ ከክርስቶስና ከቤተክርስቲያን ጋር የሚነፃፀረው የትኛው ነው?

ሀ. የወላጆችና የልጆች ግንኙነት
ለ. ከግብረስጋ ግንኙነት ውጭ የሆነና ክርስቲያናዊ አገልግሎት
ሐ. ዘርን ማብዛት
መ. የጋብቻ ግንኙነት

4. በግብረ ስጋ ኃጢአት ውስጥ የወደቀን ሰው ለመመለስ በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ እጅግ አስፈላጊው

ሀ. በደለኝነት እንዲሰማው ማድረግ
ለ. ኃጢአቱን ትቶ ማለፍ
ሐ. የሚናዘዝን ኃጢአተኛ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚል እንዲረዳ ማድረግ
መ. ስህተተኛ መሆኑን እንዲያውቅ ማድረግ

5. ከእነዚህ ውስጥ የግብረስጋ ኃጢአት ውጤት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የስሜት ጠባሳና ስቃይ
ለ. ንጹህ ሕይወት
ሐ. ሕጋዊ ያልሆኑ ልጆች
መ. የአባላዘር በሽታዎች



6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ያልተቀመጠን ነገር እንድታደርግ ስትፈተን ከእነዚህ የትኛውን ጥያቄ ለራስህ ትጠይቃለህ?

ሀ. እግዚአብሔርን ያከብራልን?
ለ. ርካታን ይሰጠኛልን?
ሐ. ምን አተርፍበታለሁ?
መ. ለእኔ የተፈቀደ ነውን?

7. የግብረ ስጋ ፍላጐት

ሀ. ኃጢአት ነው።
ለ. ልንቆጣጠር የማንችለው ነገር ነው።
ሐ. የሚያሳፍር ነው።
መ. ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው።

8. በጋብቻ ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሕግ__________ መሆን አለበት።

ሀ. መተሳሰብ
ለ. ከግብረ ስጋ መራቅ
ሐ. ዘርን ማብዛት

9. አጭር መልስ። ግብረ ሰዶማዊነት ለምን ኃጢአት እንደሆነ የምናውቅበትን 3 ምክንያቶች አስቀምጥ።

10. በዚህ ክፍለ ትምህርትና በክፍለ ትምህርት 2 ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንብብና ይህንን ዐረፍተ ነገር ያስቀመጡ ሰዎችን ለመርዳት የእግዚአብሔር ቃል ስለ ችግራቸው ምን እንደሚል ለማወቅ የሚያስችልህን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስጥ።

ሀ. "እስካሁን ልንጋባ አልቻልንም፤ ነገር ግን እንፋቀራለን፥ ስለዚህ የግብረ ስጋ ግንኙነትን መፈጸም ትክክል ነው።"

ለ. "ባለቤቴ በፍጹም እንደሚወደኝ ሳይነግረኝ ወይም አንዳችም ፍቅር ሳያሳየኝ እርሱን ለማርካት የምሞክረው ለምንድነው?"

ሐ. "ስላረገዝኩና ጓደኛዬ ሊያገባኝ ስለማይፈልግ፣ ማስወረድ ይኖርብኛል።"

መ. "ግብረ ሰዶማዊ ሆኜ ክርስቲያን መሆን እችላለሁ ብዬ አስባለሁ።"

ሠ. "የኃጢአት ሕይወት ስላለኝ ክርስቲያን መሆን አልችልም። እግዚአብ ሔር በፍጹም አይቀበለኝም።"

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

11. ይህንን የሚያደርግ ሰው የእግዚአብሔር በሆነውና በራሱ ሰውነት ላይ ኃጢአትን እያደረገ ነው። ስለዚህ እርሱ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን እያደረገ ነው።

1. እርሱ የፈተናውን መውጫ መንገድ ያዘጋጅልሃልና ለፈተናው ከመማረክህ በፊት መታገስ ያስፈልግሃል።

12. በጥያቄ 10 እና 11 የተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚገልጹት በተፈጠረው ሁኔታ ውስጥ ሰውየውና ሴትየዋ ላይ ምን እንደተከሠተ ነው።

2. ሐ

13. ሕጋዊ ያልሆኑ ልጆችን መውለድ፣ ውርጃ፣ የአባላዘር በሽታዎችንና የስሜትን ጠባሳዎች ከመከሰት (እንዲሁም መለኮታዊ ፍርድን የሚያስከትል ኃጢአት ስለሆነ ከዝሙት መቆጠብ አለብን) ለመቆጠብ።

3. መንፈሱን በመጠበቅና ለተከበረ ነገር በማዋል።

14. ራሳቸውን መግዛት መለማመድ ይኖርባቸዋል፥ ወይም ማግባት ይኖርባቸዋል።

4. ሕጋዊ ያልሆኑ ልጆችን መውለድ፣ ውርጃ በአባላዘር በሽታ መያዝን እና ከስሜት መጎዳት የተነሳ የሚመጣ ስቃይን ያስወግዳል።

15. እግዚአብሔርን ለማክበር

5. የአንተ መልስ። እነዚህ ሃሳቦች ሊካተቱ ይገባል። ከግብረ ስጋ ግንኙነት ውጭ መሆን የጋብቻ ብቸኛው አማራጭ ነው። ላጤ ክርስቲያን ከግብረስጋ ግንኙነት ውጭ ይሆን ዘንድ ይጠበቃል። የእርሱ አካል የእግዚአብሔር ነው፣ የመንፈስ ቅዱስም ቤተመቅደስ ነው። የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጐቶቹን ሁልጊዜ በማስገዛት መጠበቅ አለበት።

18. ከእግዚአብሔር የግብረ ስጋ መርህ ጋር አይስማማም። መጽሐፍ ቅዱስ ክፋት ነው ይለዋል። በመለኮታዊ ፍርድ ስርም ይሆናል።

6. ሀ. አንድነት
   ለ. ዘርን ማብዛት



17. የአንተ መልስ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ልምምድ የሚለውንና እንዴት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በእግዚአብሔር መንፈስ በመታጠብ፣ መቀደስና መለወጥ እንደሚችል አሳየዋለሁ።

7. ራስህን መቆጣጠር እንዳይሳንህና በኃጢአት እንዳትፈተን

18. ሀ. በዝሙት ተግባር ስለተያዘች ነበር።
   ለ. እንደ ሕጉ መሠረት በድንጋይ እንድትወገር።
   ሐ. ይቅርታ ማድረግ ነው።
   መ. "እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ" አላት።

8. ሀ. አይስማማም ሐ. ይስማማል ሠ. ይስማማል ሰ. አይስማማም
   ለ. ይስማማል መ. ይስማማል ረ. ይስማማል

19. ኃጢአቷን ሁሉ ይቅር በማለት።

9. ሐ

20. እንደ መንፈስ ቅዱስ ምሪት መኖር አለብን

10. ፍርድ ያገለዋል፣ ራሱን ያጠፋል፤ ጥፋትን፣ አለ መከበርንና ኀፍረትን በራሱ ላይ ያመጣል።

# መደበትን መቋቋም

## *ዓላማ 1 መደበትን በትክክለኛ መንገድ ለመግለጽና ለማብራራት።*

መደበት ምንድነው? አንድ የህክምና ዶክተር እንዲህ በማለት ይገልጸዋል። "ዓለም ሁሉ በተስፋ ማጣት ውስጥ የተዘፈቀ ይመስላል፤ የሚብሰው ደግሞ ነገሮች ሁሉ በርግጥም ይሆናሉ ብለህ የምታስበውን ያህል መጥፎ መሆናቸውን ወደ ማመን ትመጣለህ!" የህክምናው ዶክተር አሉታዊ ሐሳቦች መደበትን ያመጣሉ ብሎ ያምናል።

ዌብስተር የተባለው መዝገበ ቃላት ለመደበት የሚከተለውን ትርጉም ይሰጣል፦ *ሐዘን፣ አለመደሰት፣ በማዘን የሚሰማን ሁኔታ፣ ከእንቅስቃሴ መገደብ፣ ለማሰብና ትኩረትን ለመስጠት መቸገር፣ የስነ አእምሮ ቀውስ፣ የተስፋ መቁረጥ ስሜት፣ የስራ አቅም ማጣት ወይም ጉልበት መቀነስ የንቁነት ወይም የስራ ማሽቆልቆል።*

ብዙዎቻችን አልፎ አልፎ በመደበት ውስጥ እናልፋለን። ሕይወት ድንገት ደስታ የሌለበት ይመስላል፣ ችግሮቻችን ያጥለቀልቁናል፤ በከፍተኛ ሁኔታ በራሳችን በማዘን የከንቱነትና ተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ እንዘፈቃለን።

አንዲት ሴት ባሏን በድንገተኛ ሞት ካጣች ከትንሽ ወቅት በኋላ እንዴት መደበት ውስጥ እንደገባችና መደበት ምን እንደሆነ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸዋለች።

"ባለቤቴ በሞተ ጊዜ በቤተሰቦቼና በሚወዱኝ፣ በሚጠነቀቁልኝ ጓደኞቼ ተከብቤ ነበርና፣ እግዚአብሔር ለእኔ ቅርብ ሆኖ ይሰማኝ ነበር። ባለቤቴ በታመመባቸው ረጅም የሕመም ዘመናትና ከሞተ በኋላም ባሉት ጊዜያት አምላኬ ብርታትን ሰጠኝ። ብዙ ሰዎች ክርስቶስ በሐዘን ውስጥ ላሉ ሰዎች ስለሚሰጣቸው ሰላምና እርጋታ ምስክር መሆን እንደምችል አስተያየታቸውን ሰጡ። እሱ አፅናንቶኛል፣ ጠብቆኛል፣ እንዲሁም መርቶኛል።"

"ቀናቶች ሲያልፉ በሚያስደንቅና ስኬታማ በሆነ አገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ ሆንኩኝ ከቤተሰቦቼና ከቅርብ ጓደኞቼ የተለየሁ ብሆንም እንኳን ሕይወቴ ደስታን የተሞላ ከመሆኑ ባሻገር እኔም ራሴን በስራ ጠመድኩት። በዚህ ሁኔታ አንድ ዓመት አለፈ። በምሠራበት መሥሪያ ቤት የሠራተኞች ዝውውር ነበርና አንዳንዶች በስራዬ ላይ ችግር ለመፍጠር ሞከሩ ከዚህም የተነሳ በእኔ ላይ ለሚሠነዘር ማንኛውም ትችት ይጎዳኝ ጀመር። ማግኘት አለብኝ ብየ የማስበውን ምሥጋና ሳላገኝ ስቀር እንደተዋረድኩኝ መቁጠር ጀመርኩኝ። ከስራዬ ውጭ ያሉትን ጊዜያቶች የማሳልፈው ብቻየን ነበርና በጣም በምወዳቸው ሰዎች የተተውኩና ብቸኛነቴ ይሰማኝ ጀመር።



"በዚሁ ወቅት እጅግ የማደንቀውና ለእኔ ጥሩ ኃሳብ አለው ብዬ የማስበው ሰው ለከፍተኛ ጉዳት ዳረገኝ። ምላሼም ያንን ስብራት ሊጨምር ከሚችል ከማንኛውም ነገር መራቅ ነበር። ወደ መደበት ያመጣኝ ሁኔታ የጀመረው በዚህ መልክ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ በባለቤቴ ሞት ሁለመናዬን የሞላ ሐዘን በሕይወቴ አለፈ። እንደማልወደድ፣ ዋጋ እንደሌለኝና አላስፈላጊ እንዳልሆንኩ ተሰማኝ። በሕይወት የምኖርበት አንዳችም ዋጋ ያለው ነገር የሌለ መሰለኝ። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፣ መጸለይ ወይም ከክርስቲያን ጓደኞች ማናቸውንም ምክርን መቀበል አልፈለግኩም፥ ከከንቱነቴና ከመከራዬ ጋር ብቻዬን መሆን ነበር የፈለኩት።"

መደበት በሕይወትህ አልፎ የምታውቅ ከሆነ በዚህች ሴት የተገለጹትን አንዳንድ ስሜቶች ትለያቸዋለህ። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አንድ በመደበት ውስጥ የገባ ሰው ከሚያሳያቸው ምልክቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

1. የሰውነት ድካም - እንቅልፍ ማጣት
2. አተኩሮ የማሰብ ችግር
3. በተለምዶ በሚደሰትባቸው ነገሮች የግብረ ስጋ ግንኙነትን ጨምሮ ፍላጐትን ማጣት።
4. ብቸኝነትን መምረጥ
5. ውሳኔዎችን ለማድረግ መቸገር
6. ስለራሱና ስለሌሎች አሉታዊ አመለካከት መያዝ
7. መደበቱ እንደ አልሰር የመሳሰሉ በሽታዎችን ሊያስከትል ይችላል።
8. ብዙውን ጊዜ የሚያደርጋቸው ውሳኔዎች በስሜት ግብታዊና የተሳሳቱ ይሆናሉ (ለምሳሌ ራስን ለመግደል መወሰን)።
9. ከበድ ያለ ሐዘንና ተስፋ መቁረጥ።
10. እንቅስቃሴዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳሉ።

በእርግጥ በሕይወታችን ውስጥ ከጊዜ ወደጊዜ የሐዘን፣ የፍራቻ ወይም እርግጠኛ ያለመሆን ስሜት እንዲሰማን ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ይከሰታሉ። ሁላችንም መልካምና መጥፎ ጊዜያት አሉን፤ መልካም ነገር የሚሰማንና ሁሉም ነገር በሕይወታችን ፍጹም የሚመስለን ወቅቶችና ጊዜያት አሉ፥ ሁሉም ነገር ወደ ስህተት የሚያመራ የሚመስለን ወቅቶች ደግሞ አሉን። እነዚህ የስሜት መውጣትና መውረድ ሊባሉ ይችላሉ። በተለምዶ እነዚህ ስሜቶች ለረጅም ጊዜ አይዘልቁም። አሉታዊ ውጤት ሳያስከትልብን ከመጥፎ ጊዜያት በፍጥነት እንወጣለን። መደበት በሌላ መልኩ ወደ እኛ ቀስ በቀስ በመምጣት ረዘም ላለ ጊዜ የሚዘልቅብን የአእምሮአችን ሁኔታ ነው።

መደበቱ ወደ እኛ የመጣበትን ምክንያት መለየትና ልንቋቋመው ወይም ልናሸንፈው የምንችልበትን መንገዶች ማግኘት ይኖርብናል። በዚህ ክፍለ ትምህርት ቀጣዩ ክፍል አንዳንድ የመደበት አብይ ምክንያቶችንና እንዴት መጋፈጥ እንደሚገባን እንወያያለን።

(1). ከነዚህ ዐረፍተ ነገሮች መካከል ስለ መደበት ትክክለኛውን ትርጉም የሚሰጡት የትኞቹ ናቸው? ከምትመርጠው ከእያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የመደበት ምልክቶች ጉልበት ማጣትና ከእንቅስቃሴዎች መቀነስ ነው።
ለ. ማናቸውም የሐዘን ወይም የብቸኝነት ስሜት መደበት ነው።
ሐ. አንዳንድ ጊዜ የሁኔታዎች መደራረብ መደበትን ያመጣል።
መ. የተደበተ ሰው ብዙውን ጊዜ ስለ ራሱ ከፍተኛ አስተሳሰብ አለው።
ሠ. መገለል ብዙውን ጊዜ የመደበት ምልክት ነው።
ረ. የተደበተ ሰው ከደስተኞች ሰዎች ጋር መሆን ያስደስተዋል።
ሰ. የተደበተ ሰው ፈጣንና ደካማ የሆኑ ውሳኔዎችን የማድረግ ዝንባሌ አለው።

(2). ምልክቱ የሚቆይበትን የጊዜ ርዝመት በማየት ሰውየው በመደበት እየተሰቃየ መሆኑን እንዴት ሊያመለክት ይችላል?

## መንስዔውንና ፈውሱን ማግኘት

ብዙ ነገሮች ለመደበት የራሳቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። ባለፈው ክፍለ ትምህርት ወደ መደበት ሊመሩ የሚችሉትን እንደ የገንዘብ ችግር፣ ከልጆች ጋር የሚፈጠር ችግር፣ ብቸኝነት፣ የግንኙነት መበላሸት ወይም አለመግባባቶች የመሳሰሉትን ተወያይተናል። መደበት ብዙውን ጊዜ በአንድ ችግር ብቻ የሚከሰት ሳይሆን ሰውየው በመጨረሻ ሊሸከማቸው የማይችላቸው የብዙ እንቅፋቶች ጥርቅም ነው።

በዚህ ክፍል ወደ መደበት ሊመሩ የሚችሉ አንዳንድ አጠቃላይ ችግሮችንና እነዚህን በመሳሰሉ ችግሮች ላይ ክርስቲያን እንዴት ድልን ማግኘት እንደሚችል ለማወቅ ትኩረትን እናደርጋለን።

## በሽታዎች

*ዓላማ 2 መደበት ከበሽታዎች ጋር ሊዛመድ የሚችልበትን ሦስት መንገዶች ለመግለጽ።*

አንድ የሥነ አእምሮ ጠቢብ እንዲህ ብሏል "በሽተኛ ወደ እኔ በተደበተ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሲመጣ በመጀመሪያ አካላዊ ምርመራን እንዲያደርግ ወደ ሀኪም እልከዋለሁ" መደበት ህክምና የሚያስፈልገው የአንድ አካላዊ በሽታ ምልክት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ አንድን ከባድ በሽታ ለመቻል ሲሞክር የሚመጣም ሊሆን ይችላል። ለውዬው ቀስ በቀስ እጅግ ከባድ በሽታ እንዳለበት ባወቀ ጊዜ ከሚያልፍባቸው ደረጃዎች አንዱ ነው። ይህንን በሚቀጥለው ክፍለ ትምህርታችን ሰፋ ባለ ሁኔታ እንወያይበታለን።



አንዳንድ ጊዜ ወደ መታመምና መደበት እስኪያደርሰን ድረስ ከመጠን ያለፈን ስራ በመስራት ሰውነታችን እንዲዝል እናደርጋለን። በክርስቲያናዊ አገልግሎት የተሰማሩትም ከሚገባው በላይ በመሥራትና ሰውነታቸውን በማድከም በመደበት ውስጥ ሊያልፉ ይችላሉ። አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመፈፀም ቀንና ሌሊት ያለ ዕረፍት ለረጅም ጊዜ በመሥራት ራሳቸውን ከጥቅም ውጪ እስከማድረግ ደረጃ የደረሱ መጋቢዎችንና ሚስቶቻቸውን ተመልክቻለሁ። በማር. 6፡30-31 ይህንን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ ደቀ መዛሙርት በገቡ ጊዜ ኢየሱስ የእረፍትን ሕክምና ያዝላቸዋል።

> ሐዋርያትም ወደ ኢየሱስ ተሰብስበው ያደረጉትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት። እናንተ ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳ ኑና ጥቂት ዕረፉ አላቸው። የሚመጡና የሚሄዱ ብዙዎች ነበሩና፥ ለመብላት እንኳ ጊዜ አጡ።

ሰውነታችን እንደሚገባው ይሠራ ዘንድ ተገቢ የሆነ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የተመጣጠነ ምግብና በቂ እረፍትን ይፈልጋል። ከነዚህ መካከል አንዳቸውን ብንነፍገው መሥራት ባንችልና ሁሉን ነገር ተስፋ በመቁረጥ ማቆም ብንፈልግ አስደናቂ አይሆንም።

በበሽታ ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ መደበትን ለመቋቋም የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ምንጭ ነው። "በተጨነቁ ጊዜም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥ ከመከራቸውም አዳናቸው። ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፥ ከጥፋታቸውም አዳናቸው" (መዝ. 107፡19-20)።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ኃይል በተከናወኑ የፈውስ ምስክርነቶች የተሞላ ነው። እነዚህ ምስክርነቶች ተስፋ በምንቆርጥባቸው ወቅቶች ጌታን በችግሮቻችን እንድንጠራ፣ ቃሉ የሚያስፈልገንን ነገር ያገለግለን ዘንድና ፈውስን እንደሚያመጣልን እንድንታመን ያበረታቱናል።

(3). መደበት ከበሽታ ጋር ሊዛመድ የሚችልባቸውን ሦስት መንገዶች ጥቀስ።

(4). በእነዚህ በእያንዳንዱ ምክንያት መደበትን ለመቋቋም የመጀመሪያ ደረጃ መሆን ያለበት ምንድነው?

## ጫና (ውጥረት)

*ዓላማ 3 ከጫና የተነሣ የሚመጣውን መደበት ክርስቲያን መቋቋም የሚችልበትን መንገድ ለማየት።*

ጫና "የአካልን ወይም የአዕምሮን ውጥረት የሚፈጥርና ለበሽታ መንስኤ ሊሆን የሚችል አካላዊ፣ ኬሚካላዊ ወይም ስሜታዊ ውጤት ነው" በማለት ይገለጻል። አንድ ችግር በሌላው ላይ ሲደራረብ ሰውዬው የአካል፣

የኬሚካል ወይም የስሜት ውጥረት ይደርስበታል።" ብዙውን ጊዜ ውጤቱ መደበት ነው።

አንድ የሥነ አእምሮ ጠቢብ የተለያዩ ክስተቶች በሰው ሕይወት ላይ ያላቸውን የተፅእኖ ደረጃ ለመለየት መለኪያ መጠኖችን አዘጋጅቷል። ከዚህ የሚከተሉት በመለኪያው ላይ የተዘረዘሩ ክስተቶች ሲሆኑ በሕይወት ላይም ያላቸው የተፅእኖ መጠን በመቶኛ በሚከተለው ሁኔታ ተቀምጧል።

| ክስተቶች | የተፅእኖ መጠን |
|---|---|
| የትዳር ጓደኛ መሞት | 100 |
| ፍች | 73 |
| የቅርብ ቤተሰብ አባል ሞት | 63 |
| የግል ጉዳት ወይም በሽታዎች | 53 |
| ጋብቻ | 50 |
| ከሥራ መፈናቀል | 47 |
| ወደ ተለየ የሥራ መስክ መዛወር | 36 |
| የሥራ ኃላፊነትን መለወጥ | 29 |
| የልጅ ቤትን ትቶ መሄድ | 29 |
| የላቀ የግል ሥራ ክንውን | 28 |
| መኖሪያ ቦታን መቀየር | 20 |
| በቤተክርስቲያን ያለን አገልግሎት መለወጥ | 19 |
| እረፍት | 12 |
| የገና በዓል | 12 |

ይህ የሥነ አእምሮ ጠቢብ በምርምሩ አንድ ሰው በሁለት ዓመት ውስጥ ሕይወትን በሚለውጡ ክስተት ከ300 ነጥብ በላይ የተፅእኖ መጠን ከደረሰበት ለአንድ ትልቅ በሽታ የመጋለጥ ዕድሉ ትልቅ ነው ሲል አብራርቷል። (ኢንትሮዳክሽን ቱ ሳይኮሎጂ፣ 1976፣ ገጽ 146)።

ጫና ወይም ውጥረትን ከሚፈጥሩ ነገሮች ውስጥ ሐዘን ከፍተኛውን ደረጃ ይይዛል፥ መከራ፣ እንዲሁም የሚወዱትን በሞት ማጣት ዋነኛ ሐዘንን ከሚያስከትሉ ነገሮች መካከል ናቸው። እነዚህ ከላይ የተመለከቱት ብዙዎቻችንን በሕይወት ዘመናችን የሚገጥሙን ጫናዎች ወይም ውጥረቶች ናቸው። እነዚህን እንዴት አድርገን ምላሽ መስጠት እንደሚገባን የሚወስነው ያለን መንፈሳዊ ዝግጅት ነው (ክፍለ ትምህርት 3 ተመልከት)፡

አንድን ነገር ከማጣት በኋላ የሐዘን ወቅት መምጣቱ የተለመደ ሂደት ነው። ይሁንና የተፈጠረው ጫና ወይም ውጥረት የግድ ወደ በሽታና ወደ መደበት ይመራል ብዬ አላምንም። ከመንፈስ ቅዱስ ብርታትንና መጽናናትን መቀበል እንችላለን። እነዚህን ጥቅሶች አስተውል።



ነህምያ 8፡10 "ሂዱ፥ የሰባውንም ብሉ፥ ጣፋጩንም ጠጡ፥ ለእነዚያም ላልተዘጋጀላቸው እድል ፈንታቸውን ስደዱ፤ ዛሬ ለጌታችን የተቀደሰ ቀን ነው። አትዘኑ" አላቸው።

ዮሐንስ 16፡22 "እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደ ገና እያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል፤ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።"

(5). የተሻለውን መልስ ምረጥ። እነዚህ ጥቅሶች የሚነግሩን

ሀ. ክርስቲያኖች የሚወዱት ሰው በሞት ሲለያቸው ወደ ሐዘን መግባታቸው ተገቢ አይደለም።
ለ. የሐዘን ጊዜ ቢኖርም ጌታ ሐዘናችንን በደስታ መለወጥ ይችላል።
ሐ. በአንድ ጊዜ ማዘንንና የጌታን ደስታ ማወቅ የማይቻል ነው።

ከፍተኛ የጭንቀት ምልክት በሕይወትህ ውስጥ ማየት ከጀመርክ ጭንቀቱን ለማስወገድ የምትችለውን ሁሉ አድርግ። ሸክምህን ለማቃለል ማድረግ የምትችለው አንዳችም ነገር ከሌለ ቃሉን የማንበብ ጊዜህን ጨምር፤ የጌታን መልስ ጠብቅ፣ ሸክምህንም ያነሳልህ ዘንድ ፍቀድለት። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት የተናገራቸው ቃሎች ዛሬም ለአንተ የተሰፋ ቃሎች ናቸው።

> ልባችሁ አይታወክ፣ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። . . . ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም (ዮሐ. 14፡1፥27)።

ከዓለም ስንኖር ጫና ህመምና ስቃይ እንደሚያጋጥመን ማወቅ አለብን፤ ኢየሱስ ግን ለእነዚህ ሁሉ ፈውስን አዘጋጅቷል። እኛ ይህንን የእርሱን ሰላምና ደስታ መጠየቅ ብቻ ይኖርብናል።

(6). ከጫና የተነሳ የሚመጣን መደበት ለመቋቋም ከእነዚህ መመሪያዎች ውስጥ በበለጠ ሁኔታ ክርስቲያንን የሚረዱት የትኞቹ ናቸው? የተሻለውን መልስ ምረጥ።

ሀ. ክርስቲያን ጫና የሚፈጥሩ ሕይወት ለዋጭ ክስተቶችን ያስወግድ ዘንድ እንዲረዳው እግዚአብሔርን መጠየቅ ይኖርበታል።
ለ. ሕይወትን ለዋጭ ክስተቶች በሕይወቱ ውጥረትን እንዳይፈጥሩ ክርስ ቲያን ስሜቱን መቆጣጠር መማር ይኖርበታል።
ሐ. መጫጫን ሲጨምር በተመሳሳይ ሁኔታ መንፈሳዊ ዝግጁነታችን መጨመር ይኖርበታል። እግዚአብሔር እንዲናገረን ለቃሉ ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠትና በፀሎት ብዙ ጊዜ ማሳለፍ ይኖርብናል።

መ. ምንም ዓይነት ክስተት በሕይወቱ ቢያልፍም በእውነት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ክርስቲያን መጫሚን እያጋጥመውም።

## ፍርሀትና ተስፋ መቁረጥ

*ዓላማ 4 ተስፋ መቁረጥን ለሚያስከትሉ አስፈሪ ሁኔታዎች ክርስቲያን ማዳበር የሚገባውን አመለካከት ለማብራራት።*

በፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ዘመን ውስጥ ነው የምንኖረው። በማናቸውም ሰዓት ሊያጠፋን የሚችል ኑክሊየር ቦምብ ሊለቀቅ ይችል ይሆናል። ካንሰር እያንዳንዱን ቤተሰብ የሚያጠቃና ፈውስ ያልተገኘለት አስፈሪ በሽታ ነው። ወንጀል ከማናቸውም ዘመን ይልቅ እያደገ የመጣበትና የዋሃን ካለጥፋ ታቸው የሚሰቃዩበት ወቅት ነው። በብዙ የዓለማችን ክፍል ሰዎች በምሽት መንገድ ላይ መሆንን ይሰጋሉ። ስራችንን እናጣለን ብለን እንሰጋለን። እናረጃለን ብለን እንፈራለን፣ ሀመምን እንፈራለን። የምንወዳቸው ሰዎች አንዳች ያጋጥማቸው ይሆን ብለን እንፈራለን።

በፍርሀት በምንዋጥበት ጊዜ መደበት ይቆጣጠረናል። እንደዚህ ዓይነት ፍርሀት ተስፋ መቁረጥን ያስከትላል። ኑሮን ለመቀጠል የምንሞክርበት ምክንያት ይጠፋል፣ ደስተኛ ለመሆን የምንሞክርበት ምክንያት ይጠፋል፣ ምክንያቱም ሕይወት ተስፋ የለሽ ይሆናልና። መከራ ከሞላበት ሁኔታ የምናመልጥበት ምንም ዓይነት መንገድ ያለ አይመስለንም። ለእኛ መልካም የሆነ አንዳችም ነገር የሚፈጠር አይመስለንም። በዚህ ወቅት ነው በመደበት ውስጥ ያለ ሰው ከፍራቻ ሕይወቱ የሚወጣበት መንገድ ራስን ማጥፋት እንደሆነ የሚያስበው።

(7). የእንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ስህተቱ ምን ላይ ነው?

የፍርሀት ፈውሱ ፍቅር ነው። እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆነ ከፍራቻችን ያወጣን ዘንድ በእርሱ ላይ እምነት ይኖረናል። 1ዮሐ. 4:16-18 እንዲህ ይለናል።

> እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል። አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ ከፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል። እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል። በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና። ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍርሃት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።

**ልብህ በፍርሀት በተሞላ ጊዜ እግዚአብሔር ፍርሀቱን ያወጣልህ ዘንድና በዘለዓለማዊው ፍቅሩ ይለውጥልህ ዘንድ ጠይቀው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን ቃል በማሰብ ተበረታታ "በእኔ ሳላችሁ ሰላም**



እንዲሆንላችሁ ይህንን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16:33)።

(8). ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ ተስፋ እንዲቆርጥ ምክንያት ሊሆኑ ለሚችሉ አስፈሪ ክስተቶች ምን ዓይነት አመለካከትን ማዳበር ይገባዋል?

## በደለኛነትና መፀፀት

*ዓላማ 5 ከኃጢአት ጋር ለተያያዘ በደለኝነት፣ በደልንና ከበደል የተነሳ ለሚመጣ ፀፀት ለእያንዳንዳቸው የሚሆንን መፍትሔ ለማሳየት።*

ብዙውን ጊዜ ፀፀት በፈጸምናቸው ወይም መፈጸም ይገባን በነበሩ ነገሮች ከማዘናችን የተነሳ ከሚፈጠረው የበደልና የፀፀት ስሜቶች ጋር የሚመጣ ነው። ልጃቸው ቤታቸውን ትቶ የሄደና በኃጢአት ሕይወት ውስጥ ከመዘፈቁ የተነሳ እያዘኑ የነበሩ ወላጆች አጋጥመውኛል። በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ልጃቸው በኃጢአት ስለወደቀ ለጥፋቱ ራሳቸውን ተጠያቂ አድርገዋል። ልጁ ሞተር ሳይክል እንዲገዛ የፈቀደው አባት፣ ልጁ ሞተር ሳይክሉን ሲያሽከረክር በመኪና ተገጭቶ በመሞቱ በፀፀትና በበደል ስሜት ተውጧል። "እምቢ ብለው ኖሮ" በማለት አባት በመደጋገም ያለቅሳል። ሌሎችም ለአንድ ሰው ተገቢ ያልሆነ ቃል በመናገራቸው ወይም በማድረጋቸው መሪር የሆነ በደለኝነት ይሰማቸዋል።

በዚህ ቦታ ሁለት ዓይነት በደለኝነትን እናያለን። ከኃጢአት ድርጊት የተነሳ የሚፈጠር እውነተኛ የበደለኝነት ስሜትና ልንቆጣጠራቸው በማንችላቸው ነገሮች በደለኛ ሳንሆን ራሳችንን በደለኛ የምናደርግበት ጊዜም አለ። እውነተኛ በደል ከእግዚአብሔር፣ ከሌሎች ሰዎችና ከራሳችን ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ የሚፈጠር ጤናማ የበደለኝነት ስሜት ነው። ይህ የበደል ስሜት ለመናዘዝ ከፍተኛ ፍላጐትን የሚያሳይና ሁልጊዜም ለይቅርታ ምላሽን የሚሰጥ ነው። በደለኛ ሳይሆኑ ራስን በደለኛ ማድረግ ብዙውን ጊዜ ከሕግና ከሥርዓት ጋር የተዛመዱ ናቸው። ይህም መናዘዝ ቢታይበትም አልፎ አልፎ ብቻ ለይቅርታ ምላሽን ይሰጣል። ሁለቱም ዓይነት በደለኝነት ተመሳሳይ ስሜት ሲያሳድሩ በተለያየ ችግሮች የሚከሰቱና ለይቅርታም የተለያየ ዓይነት ምላሽን የሚሰጡ ናቸው። ሁለቱም ዓይነት በደለኝነት መደበትን ሲያስከትሉ ፈውሳቸው የተለያየ ነው።

*ከኃጢአት ጋር የተያያዘ በደለኝነት፡-* ክርስቲያን ለተፈጸመ ኃጢአት ራስን በመኰነን መኖር የለበትም። ህሊናችን ሲወቅሰን በእምላካችን በእግዚአብ ሔር ፊት በመንግሥተ ሰማያት ስለ እኛ የሚማልድ ጠበቃ አለን (1ዮሐ. 2:1-2)። "በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው" (1ዮሐ. 1:9)።

የኃጢአትን ሸክም መሸከም የሚያስፈልገን አንዳችም ምክንያት የለም። ንስሐ ግባ፣ ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝና የእርሱን ምህረት

ተቀበል። ይህንን ካደረክ በኋላ የኃጢአቱ ነገር የማብቃቱንና ከበስተኋላህ የመሆኑን እውነታን ተቀበልና ስለ እርሱም ማሰብን እርሳ።

*በደለኛ ሳይሆኑ ራስን በደለኛ ማድረግ፦ ትንሽ ልጇን ይዛ ለሽርሽር ስለወጣች ስለ አንዲት ወጣት ሴት ሰምቻለሁ። ጐረቤቷን በማግኘቷ በእግረኛ መንገድ ላይ ቆመው ሲነጋገሩ ልጁ በአጠገባቸው ይጫወት ነበር። በድንገት ልጁ መኪና መንገድ ውስጥ በመግባቱ በመኪና ተገጭቶ ወዲያውኑ ሞተ። ወጣቷ እናት በሐዘን ተዋጠች፤ እንደዚህ ዓይነት ነገር እንዲከናወን በመፍቀዷ የበደለኝነት ሸክም ተጫናት። ጊዜያቶች እየጨመሩ ሲሄዱ ከሰዎች ብዙ እየራቀችና እየተደበተች መጣች። በዚህ አደጋ መከሰት የተሰማትን የጥፋተኝነት ስሜት መቆጣጠርና መያዝ አልቻለችም።*

በርግጥም መሪር ፀፀትን የሚፈጥሩብን ብዙ ገጠመኞች በኑሮአችን ውስጥ ይከሰታሉ። ወደኋላ በመመልከት ነገሮችን በተለየ ሁኔታ ብናከናውናቸው ኖሮ የተፈጠረውን ነገር ልንለውጠው እንችል ነበር ብለን እናስባለን። የትዳር ጓደኛ የሞተባቸው ሰዎች ባለቤታቸውን ሊያስደስቱ ይችሉ የነበሩባቸውን ብዙ መንገዶች እያሰቡ ይፀፀታሉ። ወላጆች ልጆቻቸው ጥሩ ልጆች እንዲሆኑ አድርገው ማሳደግ ይችሉ እንደነበር በማሰብ ብዙውን ጊዜ በበደለኝነትና በፀፀት ይሞላሉ።

*ያለፈውን ነገር መለወጥ ስለማንችል፥ ወደ ፊት ተመሳሳይ ጥፋትን እንዳናጠፋ ልንማር የምንችልበት አጋጣሚ ብቻ ስለሆኑ፥ እነዚህ ሁሉ ፀፀቶች ከንቱ ጥረቶች ናቸው። ከቁጥጥራችን በላይ የሆነ ክስተት በሕይወታችን ውስጥ ከተፈፀመ ስህተትን የሠራን በደለኞች እንዳልሆንንና ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ጥበቃ የተሰጠ መሆኑን ማስተዋል ይኖርብናል። እሱ በምህረቱና በጸጋው እጅግ ከባድ የሆነን ኃጢአት ይቅር የሚል ከሆነ እኛ በፀፀትና ራስን በመኰነን ለሞሉን አስቸጋሪ ሁኔታዎች የእርሱን ይቅርታ መቀበል አይገባንምን?*

*መዝሙረኛው ዳዊት ምንም ዓይነት ስህተትን ቢፈጽም ወደ እግዚአብሔር መመለስና ይቅርታን መቀበል እንደሚችል ያውቃል።* በመዝ. 130፡1-4፥ 7 እንዲህ ይላል፡

> አቤቱ፥ እንተን ከጥልቅ ጠራሁህ
> አቤቱ፡ ድምፄን ስማ
> ጆሮህ የልመናዬን ቃል የሚያደምጥ ይሁን።
> አቤቱ፥ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ፥
> አቤቱ፥ ማን ይቆማል?
> ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና . . .
> ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት፥
> በእርሱም ዘንድ ብዙ ማዳን ነውና
> እስራኤል በእግዚአብሔር ይታመን
> እርሱም እስራኤልን ከኃጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።



በሕይወትህ ውስጥ የተከሰተው ምንም ነገር ይሁን በጌታ ሙሉ መዳን አለ። እርሱ ይቅርታን ለማድረግ ቸርና ፈቃደኛ ከሆነ አንተ ራስህን ይቅር አትልምን? ፀፀቶችህንና አላስፈላጊ የበደለኝነት ስሜትህን ወደ ኋላህ ተወው። ውድቀቶችህን በጌታ ላይ በመጣልና የእርሱን ፀጋ በመቀበል የሚገኘውን አስደናቂ መፈታት ለሌሎች የምታስተምርበት አጋጣሚ አድርገህ ተጠቀምባቸው።

(9). በዚህ ጥያቄ ውስጥ በግራ በኩል የሚገኙትን ምሳሌዎችና መፍትሔዎች በቀኝ በኩል ከሚገኙት የበደል ዓይነቶች ጋር አዛምድ። በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ ምርጫህን የሚወክለውን ቁጥር አስቀምጥ።

| | |
|---|---|
| ____ *ሀ.* እናቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ ስትሞት ከቤት ርቆ በጉዞ ላይ የነበረ ወጣት። | 1. ከኃጢአት የተነሳ የሚከሰት በደለኝነት ስሜት |
| ____ *ለ.* ንስሐ ግባ፣ ተናዘዝና ይቅርታን ተቀበል። | 2. ከመፀፀት የተነሳ የሚከሰት በደለኝነት ስሜት |
| ____ *ሐ.* ያላገባችና ቀደም ሲል ውርጃ የፈፀመች ሴት። | |
| ____ *መ.* አካለ ስንኩል የሆነ ልጅ የወለደች እናት። | |
| ____ *ሠ.* ራስህን ይቅር በል። | |

## *መራርነትና ቂም*

*ዓላማ 6 ለመራርነት ወይም ለቂም ማቴዎስ 5፡10-11 እንደ መፍትሔ ተግባራዊ ለማድረግ።*

እንደመራራነትና ቂመኛነት የክርስቲያንን መንፈሳዊ ድል የሚሰርቅ አንዳች ነገር የለም። *መራራነት* እያንዳንዱን የሕይወትህን ክፍል የሚበላ ነቀዝ ነው። ከዚህ በኋላ ተግባርህ ሁሉ የሚመራው ካስቀየመህ ሰው የተነሳ በተፈጠረብህ ጥላቻና ቂም ይሆናል። *መራርነትና ቂም* የቁጣ ሁለት አቅጣጫዎች ናቸው።

በቅርቡ *መላ* ሕይወቱ ለረጅም ጊዜ በመራራ ፈተና ስለተሞላ ስለ አንድ መልካም ክርስቲያን አነበብኩኝ። ልጁ በጨቅላ እድሜው ሞተበት፣ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ቤቱ በመቃጠሉ የነበረውን ንብረት ሁሉ አጣ፣ በትንሽ ጊዜ ልዩነት ውስጥ ለረጅም ጊዜ በአሰቃቂ በሽታ ስትሰቃይ የነበረችው ሚስቱ ከፍተኛ ወጪን የጠየቀ ህክምና ከተደረገላት በኋላ ሞተች። በእነዚህ በእያንዳንዱ ፈተና የመንፈስ ፍሬ በሕይወቱ ይታይ ነበር። ለብዙ ዓመታት በሚያመልክበት ቤተክርስቲያን የጐልማሶች የሰንበት ትምህርት ክፍልን በማስተማር ሲያገለግል በነበረው የተለየ ንፁህና ገር መንፈስና በተሰጠ እምነቱ የብዙ ሰዎች ሕይወት ተነክቷል።

አንድ ቀን በሚያስተምርበት ክፍል የተቀመጠ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዲያቆን የሰውየው የማስተማር አገልግሎት የነበረውን ውጤታማነትን እንዳጣ ተገነዘበ። ይህም ዲያቆን አስተማሪያቸው በፊት እንደሚያስተምረው ማስተማር እንደማይችል በማስረዳት አዲስ አስተማሪ ሊኖራቸው እንደ ሚያስፈልግ ለሌሎች ማሳሰብ ጀመረ። የክፍሉ ተማሪዎች በእርሱ ትምህርት እንዳልተደሰቱ ወሬው ወደ እርሱ በደረሰ ጊዜ እጅግ አዘነ። ከዚህም የተነሳ ትችቱን በሰነዘረው ሰው ላይ መራራ መንፈስና ቂም አበቀለ። ይህ አሰመግባባት እስኪፈጠር ድረስ በሕይወቱ የደረሱትን ፈተናዎች መታገስ የቻለው ሰው በራሱ ሕይወት ጥቃት ሲከናወን ሊቀበለው አልቻለም። በቤተ ክርስቲያን የነበረውን ተሳትፎ ሁሉ አቋረጠ፤ ከፍተኛ በሆነ መደበት ውስጥ ገባ። መራርነቱ እስኪማርከው ድረስ ሐሳቡን ሁሉ ይገዛ ዘንድ ፈቀደ። አስተሳሰቡ ሁሉ በመራራነት ስለተሞላ ሕይወቱና አካሄዱ ተበላሸበት በአንድ ወቅት ለቤተክርስቲያን በረከት የነበረው ሰው አሁን ነቀፋ ሆነ።

በክፍለ ትምህርት 4 ስለ ኢፍትሐዊነትና ክርስቲያን እንዴት ምላሽን መስጠት እንደሚገባው ተመልክተናል። ይህ ሰው በማቴ 5:10-12 የተጻፈውን ለችግሩ ተግባራዊ ማድረግ ቢችል ኖሮ ወደ እርሱ የመጣውን መራርነትና መደበትን ማስወገድ በቻለ ነበር። ኤፌ. 4:31 "መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገዱ።" "የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጐድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ" በዕብ. 12:15 እነዚህን ቃሎች እናነባለን።

(10). ትክክለኛውን ምላሽ ምረጥ። መራርነትና ቂም ወደ መደበት የሚመሩንና መንፈሣዊ ድላችንን የሚነጥቁን ብቻ ሳይሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚነግሩን

ሀ. በብዙ ሰዎች ላይ ችግርን የሚፈጥሩና ጉዳትን የሚያመጡ አስተሳሰቦችም ናቸው።
ለ. አልፎ አልፎ ይሆናሉ ብለን ልንጠብቃቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው፤ ምክንያቱም ሰዎች እኛን ለመጉዳት ነገሮችን ይፈጽማሉና።
ሐ. የመራርነት ስሜቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት የሚሆኑ የሰውየው ስህተቶች ናቸው።

ለመራርነት ወይም ለቂም መንፈስ ብቸኛው መፍትሔ ይቅርታ ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ በማለት ተናግሮአቸዋል። "ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም" (ማቴ. 6:14-15)። በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ በማለት ተናግሮአቸዋል "ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ" (ሉቃ. 6:27)። ይህንን መመሪያ በመከተል መጥፎ ነገር ላደረገብህ ሰው የምትጸልይ ከሆነ



የመራርነት ስሜትን በሰው ላይ መያዝ የማይቻልህ ይሆናል። ክፉን ላደረገብህ በምትጸልይበት ወቅት ጌታ ትክክለኛ ፍቅርን ይሰጥሃል።

መራርነት በእግዚአብሔር ላይ ሊፈጠርም ይችላል። ይህ ደግሞ ትክክለኛ የሆነውን የችግሩን ምንጭ ለማግኘት ከመጣር ይልቅ በእኛ ላይ ለደረሰው ችግሮች ሁሉ እሱን ጥፋተኛ ከማድረግ የሚመጣ ነው። ልቡን የመራርነት ወደብ የሚያደርግ ሰው በመደበት መሸነፉ የሚያስደንቅ አይደለም። መራርነት አካላችንን የሚጐዳ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊነታችንንም የሚያደርቅ ነው። መራርነት እንዲቆጣጠረው ለፈቀደ ሰው ከፍተኛ ጉዳት ተፈጽሞበታል። ለዚህ ሁኔታ ወደ መራርነት እንዲገባ ተጠያቂ የሚሆነው ሰው የሰራውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ላይገነዘበው ይችላል።

(11). ማቴ. 5:10-12ን አንብብና ለመራርነትና ለቂም ችግር ተግባራዊ በማድረግ በዚህ ችግር ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ አብራራ።

## መደበትን መከላከል

*ዓላማ 7 መደበትን ለመከላከል የሚቻልባቸውን መንገዶች ለማወቅ።*

መደበትን መከላከል የሚቻልበት አንዳች መንገድ ይኖር ይሆን? ወደ እኛ መምጣቱን ተመልክተን ደረጃዎችን በመከተል አስቀድመን ማስወገድስ እንችላለን? ክርስቲያን መደበትን ለመቋቋምና እሱን ከመቆጣጠሩ በፊት ምልክቶቹን የሚለይበት መንገዶች እንዳሉ እምናለሁ።

መደበትን የመከላከያ መንገዶችን በምናስብበት ጊዜ በአእምሮአችን መያዝ የሚገባን አንዳንድ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. በሕይወታችን ውስጥ ያልተናዘዝነው አንዳች ኃጢአት እንዲኖር መፍቀድ የለብንም። ኃጢአት መደበትንና ሐዘንን ያመጣል። መደበትን ከእኛ ማራቂያ ብቸኛው መንገድ ኃጢአቱን ከእኛ ማራቅ ነው።

2. መደበት ሁሉ ኃጢአት አይደለም። ክርስቶስ ስለ ኢየሩሳሌም ባለቀሰ ጊዜ ጥልቅ ሐዘን ውስጥ አልፏል (ሉቃ. 19:41)። ጌቴሴማኒ ወደምትባል ሥፍራ በመጣ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይነግረናል "ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ከእርሱ ጋር ወስዶ ሊደነግጥም ሊተክዝም ጀመረና፦ ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች በዚህ ቆዩ ትጉም አላቸው" (ማር. 14:33-34)። ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን አልሰራም ይሁንና ከፍተኛ የሆነ መደበትን ያውቃል (ኢዮ. 3)። ሐዘን ወደ ውስጥ ከገባ መደበትን ያስከትላል። በሐዘናችን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ስንመለከት ሐዘናችንን በእርሱ ደስታ ይለውጣል።

3. እኛ አካላዊ እንዲሁም መንፈሳውያን ፍጥረታት ነን። ከመጠን ያለፈ ኃላፊነትና የአካል ድካም፣ ተገቢ ያልሆነ እረፍት፣ ያልተመጣጠነ ምግብና እንቅስቃሴ ወደ መደበት ሊመሩን ይችላሉ። መንፈሳዊ ሕይወታችንን ቸል ማለት፣ አምልኮን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን፣ ማሰላሰልና ጸሎትን ቸል ማለት ያዳከመንና ለሰይጣን ጥቃት ምቹ ያደርገናል።

4. ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ በተቻለ ፍጥነት የችግሩን መንስዔና ተገቢ የሆነውን መፍትሔ መፈለግ ይኖርብናል። መፍትሔ ያልተሰጣቸው ችግሮች ሲደራረቡ በቀላሉ እንሸነፋለን።

5. ችግር ወዳለባቸው ሰዎች መሄድና እነርሱን መርዳት ፈውስ ይሆናል። ወደ ራስህ ውስጥ ከመመልከትና በራስህ ከፍተኛ ሐዘንና ስቃይ ውስጥ ከመዋጥ ይልቅ ወደ ውጭ ተመልከት። የምትታገሰው ፈተና ለሌሎች ለተጐዱ ሰዎች ንቁ እንድትሆንና የክርስቶስን ፍቅር በሕይወታቸው መግለጫ መንገድ እንድትሆን ይረዳሃል። ጌታን በማገልገልና ሌሎችንም በመርዳት ያለህበት መደበት በደስታ ይለወጣል። ለዚህ ነው አማኞች አንዱ ለሌላው ትኩረትን በሚያደርጉበትና በሚያገለግሉበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን የሚያስፈልግህ።

6. ይቅርታን በሕይወቱ የተለማመደ ሰው ከመራርነት ወይም ከቂም ቁጣ መውጣትን ያውቃል። ፍቅር ምን እንደሆነና ምን እንዳልሆነ በትክክል ተምሯል (1ቆሮ. 13)። በ1ቆሮ. 10:13 ውስጥ የሚገኝ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋ በመከራዬ ጊዜያቶች ይመለከተኝ ዘንድ ወደ እርሱ ችሎት እንድቀርብና እርሱም በፍጹም እንዳልተወኝ እንድገነዘብ ረድቶኛል።

> ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።

(12). ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መደበትን ለመከላከል ምን ዓይነት መርህ ማውጣት እንችላለን።

አንዳንድ ጊዜ ሰውየው መደበትን መቋቋም ወይም መከላከል እንዲችል ክርስቲያን አማካሪ ያስፈልጋል። እዚህ በጠቀስናቸው በማናቸውም መንገዶች መፈታትን ማግኘት ካልቻልክ እንደዚህ ዓይነት እርዳታን ለመስጠት የሰለጠነ ሰውን እርዳታ ለማግኘት ወደ ኋላ አትበል።

(13). መደበትን የመከላከያ መንገዶችን በተመለከተ ከእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች መካከል የትኞቹ ትክክል ናቸው? ከምትመርጠው ከእያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ይቅርታ ከበደለኝነት ስሜትና ከመራርነት ነፃ መውጣትን ያስገኛል።



ለ. ያልተፈቱ ችግሮች መደበት በቀላሉ እንዲከሰት የሚያደርጉ ሁኔታ ዎችን ይፈጥራሉ።

ሐ. መንፈሳዊነትን ቸል ማለት አካልን ቸል ከማለት ይልቅ ወደ መደበት ያመራል።

መ. መደበት ሁልጊዜ ከኃጢአት ጋር የተያያዘ ነው።

ሠ. ወደ ራሳችን ወይም ወደ ውስጥ ከመመልከት ይልቅ ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር ብንመለከት መደበትን መቋቋም እንችላለን።

ረ. በጌቴሴማኒ ምሳሌ ውስጥ ኢየሱስ እንዴት መደበትን መቋቋም እንደም ንችል አሳይቶናል።

ሰ. የራሳችን መከራ አንዳንድ ጊዜ በመከራ ውስጥ ያሉትን ሌሎችን በተሻለ ሁኔታ እንድናገለግል ይረዳናል።

## ሌሎችን መርዳት

*ዓላማ 8 በመደበት ስቃይ ውስጥ ያሉ ሌሎችን አዎንታዊ ርዳታ ለመስጠት የሚያስችሉ ተግባሮች ለማስተዋል።*

ኢዮብ ከፍተኛ በሆነ ፈተና ውስጥ ሲያሳልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ጓደኞቹ "የደረሰበትን ክፉ ነገር ሁሉ ሰምተው ከየአገራቸው መጡ። እነርሱም ቴማናዊው ኤልፋዝ፣ ሹሐዊው በልዳዶስ፣ ነዕማታዊው ሶፋር ነበሩ። እነርሱም ሊያዝኑለትና ሊያጽናኑት በአንድነት ወደ እርሱ ለመምጣት ተስማሙ። ከሩቅም ሆነው ዓይናቸውን ባነሡ ጊዜ አላወቁትም፤ ድምጻቸውንም አሰምተው አለቀሱ፤ እያንዳንዳቸውም መጐናጸፊያቸውን ቀደዱ፤ ወደ ላይም ወደ ራሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ። ሰባት ቀንና ሰባት ሌሊትም ከእርሱ ጋር በምድር ላይ ተቀመጡ፤ ሕመሙም እጅግ እንደ በዛ አይተዋልና ከእነርሱ አንድ ቃል የሚናገረው አልነበረም" (ኢዮ. 2:11-13)።

የኢዮብን መጽሐፍ ማንበብ ከቀጠልክ የኢዮብ ጓደኞች በስቃዩ ውስጥ በዝምታ እንዳልቀጠሉ ታገኛቸዋለህ። ይልቁንም ጥፋተኝነቱን በመደራረብ ተስፋ መቁረጡን ሲያበዙትና በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን እንዳደረገ ሲከሱት ትመለከታለህ።

በከፍተኛ መደበት ውስጥ ያለን ሰው ለመርዳት የተሻለው መንገድ በፍቅር ለእርሱ በመጠንቀቅና ለእርሱ ያለህን ተቆርቋሪነትና ርዳታህን ለማሳየት በአጠገቡ መገኘት ነው። የኢዮብ ጓደኞች እንዳደረጉት በመከራ ውስጥ ያለ ሰው በሐዘኑ ላይ ሐዘን የሚጨምርበትን ሰው አይፈልግም። በእንደዚህ ዓ ይነት ችግር ያለ ሰው የማይኰንነን ጓደኛ ይልቁንም የመደበቱን ምክንያት ለማግኘት የሚረዳውንና መደበቱን ሊጋፈጥ በሚዘጋጅበት ጊዜና የሚደበትበትን ሁኔታዎች ለመቋቋም አስፈላጊ ተግባራዊ እርምጃዎችን ሲወስድ የሚረዳውን ጓደኛ ነው የሚፈልገው።

መደበት ያስታን ማጣት፣ ንቁነትን ማጣት፣ የማዘን ስሜትና መስራት የማንችልበት ወቅት እንደሆነ ገልጸናል። ብዙውን ጊዜ የተደበተ ሰው ያለበትን ሁኔታ ተቋቁሞ ለማሸነፍ ጉልበት ወይም ጥረት ለማድረግ ፈቃደኝነት ያንሰዋል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ላለ ሰው "እየተጐዳህ እንደሆነ አውቃለሁ፤ እንደማስብልህ እንድታውቅ እፈልጋለሁ። አንተን ለመርዳት የምችለው አንዳች ነገር አለን?" በማለት አብሮ ለመጸለይ፣ ለማልቀስ፣ ለማጽናናትና ፍቅርን ለማሳየት የተዘጋጀ ሰው ያንን በመደብት ጥልቀት ውስጥ ያለን ነፍስ በክርስቶስ ወደ ተባረከው ድል ከፍ ለማድረግ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ መሳሪያ ይሆናል።

የረጂው አንዱ የሥራ ድርሻ ማጽናናትና ተስፋን መስጠት ነው። ያልተናዘዘበት ኃጢአት ካለ መንፈስ ቅዱስ እንዲናገረውና ወደ ንስሐ እንዲመራው ፍቀድለት። በክርስቶስ ነፃ መውጣት አለ። ሕይወት ልንሸከመው ከምንችለው በላይ ሸክም ሲመስለን እነዚህን የጳውሎስ ቃሎች እንዳችን ለሌላችን እናስታውስ።

> በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም. . .ስለዚህ አንታክትም፤ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና (2ቆሮ. 4፡8-9፣ 16-17)።

(14). ከእነዚህ ከሚከተሉት አመለካከቶች ውስጥ በመደብት ስቃይ ውስጥ ላለ ሰው አዎንታዊ ርዳታን የሚለግሱት የትኞቹ ናቸው? ከምርጫህ በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ግድ እንደሚለን ማሳየት
ለ. አፍቃሪ መሆን
ሐ. ፈራጅ መሆን
መ. የተደበተበትን ምክንያት ማቅረብ
ሠ. ማዳመጥ
ረ. በቅርብ መገኘት
ሰ. ሐዘኑን ለመካፈል ፈቃደኛ መሆን
ሸ. ብቻውን መተው
ቀ. የተደበተውን ሰው መርዳት
በ. እርዳታን መስጠት
ተ. ማፅናናትና ተስፋ መስጠት
ቸ. ማበረታታት



## የሙከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት፦ ክፍት በሆነው ቦታ ዐረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እ" የሚለውን ፊደል ጻፍ። ዐረፍተ ነገሩ ሐሰት ከሆነ "ሐ" የሚለውን ጻፍ።

______1. መደበት አሉታዊ ሀሳቦችን ማሰብ፣ ስሜቶችንና ምላሾችን ያካትታል።
______2. መደበት ማንኛውም ዓይነት የሐዘን ስሜት ወይም በሰውየው ሕይወት የሚያልፍ ተስፋ መቁረጥ ነው።
______3. የተደበተ ሰው በቀላሉ ውሳኔን ማድረግ ይችላል።
______4. እንቅልፍ ማጣት በሚያስደስት ነገር መደሰት አለመቻልና ጥልቅ ሐዘን የመደበት ሦስት ምልክቶች ናቸው።
______5. መደበት የሌላ ህመም ምልክትና ውጤት ሊሆን ይችላል።
______6. በሰውየው ላይ በሚጨመሩት የጫና መጠንና ሰውየው በከፍተኛ ህመም ወይም መደበት የመሰቃየቱ ሁኔታ ቀጥተኛ ግንኙነት አለው።
______7. መደበት አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከቁጥጥራቸው ውጪ ክስተቶች ሲከናወኑ ራሳቸውን ጥፋተኛ ከማድረጋቸው የተነሳ ሊመጣ ይችላል።
______8. ብዙውን ጊዜ ለራስ ጥሩ ግንዛቤ መኖር መደበትን ያስከትላል።
______9. በዮሐ. 14፡1 ካሉት የኢየሱስ ቃሎች እግዚአብሔርን በመታመን የተጨነቀች ልብ እንደምትፈወስ ዋስትና አለን።
______10. ጫናን ለመቀነስ የተሻለው መንገድ በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙህን ችግሮች ለመጋፈጥ በራስህ በኩል መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ ነው።
______11. ለፍርሀት መድሃኒቱ ድፍረት ነው።
______12. የበደለኝነት ስሜት በሚኖረን ጊዜ አንድ የተሳሳተን ነገር እንደ ፈጸምን እናውቃለን።
______13. የክርስቶስን ይቅርታ የተቀበለና ራሱንም ይቅር ያለ ሰው ካጋጠመው ፀፀትና የበደል ስሜት ነፃ መውጣት ይችላል።
______14. በቂምና በመራርነት ስሜቶች እጅጉን የተጐዳ ሰው ስሜቶቹ በልቡ ውስጥ እንዲቆዩ የሚፈቅድ ነው።
______15. በሌላ ሰው ላይ የሚኖርን የመራርነት ስሜት ለማስወገድ የተሻለው መንገድ ለዚያ ሰው መጸለይ ነው።

አጭር መልስ። በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ መደበትን ለመከላከል የሚጠቅሙ መርሆዎችን ለመግለጽ የሚያስችለውን አንድ ቃል ሙላ።

16. ለ________________ እና ________________ ጤናችን እንክብካቤን ካደረግን በመደበት ለመሰቃየት ያለው ዕድል እጅግ ያነስ ይሆናል።
17. ያልተናዘዝንበት ________________ በሕይወታችን ይኖር ዘንድ በፍጹም መፍቀድ አይገባንም።

# 9 ትምህርት

# ሥቃይና ሞት

አንድ ትንሽ ልጅ ይህንን ደብዳቤ ለእግዚአብሔር ጻፈ። "ውድ እግዚአብ ሔር ሆይ በርግጥም ከሞት በኋላ ሕይወት ካለ ለምንድነው መሞት የሚገባን?"።

ስለ ሞት ማሰብን እንወድም። የምትወደው ሰው "ዛሬ እኔ በምሞትበት ቀን ማድረግ የሚገባህን ነገር መነጋገር እፈልጋለሁ" ቢልህ ወደ ውይይቱ በፈቃደኝነት ትገባለህን? ወይስ ስለዚህ ስለማያስደስት ርዕስ መነጋገርን ለማቆም ትሞክራለህ? እኛ ወይንም አንድ የምንወደው ሰው አንድ ቀን በርግጥ የመሞታችንን እውነታ መቀበል አስቸጋሪ ሆኖ እናገኘዋለን። እኛ ስለ መሞት መናገርን ከተውን በእኛ ላይ ሊከናወን እንደማይችል ወደ ማሰብ እናዘነብላለን።

ለክርስቲያን ሞት እንደ ችግር መታየት የለበትም። ሐዋርያው ጳውሎስ "ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና" (ፊልጵ. 1:21) እንዳለው ሞት መጨረሻው ሳይሆን መጀመሪያው ነው! ለወጣትም ይሁን ላረጁ ሰዎች ሕመምንና ስቃይን ስለምንፈራ የመሞት ሂደት አስፈሪ ነገር ነው።

በክፍለ ትምህርት 1 ውስጥ "ክርስቲያኖች ለምን ይሰቃያሉ?" "ለምንድነው በህመም ውስጥ የምናልፈው?" "ለምንድነው ሕይወት በመከራ የተሞላው?" የሚሉትን ጥያቄዎች ተመልክተናል። አሁን ዓላማችን ስቃይና ሞት ወደ ሰዎች ሕይወት የሚመጡበትንና ክርስቲያን እንደነዚህ ያሉ ችግሮችን እንዴት መቅረብ እንደሚገባው መወያየት ነው። በዘላለማዊ ዋጋዎቻችን ብርሃን ለንመለከታቸው ስቃይ ለተሞላባቸው ልምምዶቻችን የምንሰጠው ምላሽ እጅግ አስፈላጊ ነው።



የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የህመምና የስቃይ ጥቅሞች
- ከስቃይና ከሞት ጋር የሚዛመዱ ችግሮች
- በስቃይና በሞት አፋፍ ላይ ያለን ሰው መርዳት
- ከሞት ጋር የተዛመዱ ችግሮች
- ክርስቲያናዊ አመለካከት

---

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- የሕመምንና የስቃይን ጥቅሞች መግለጽ፤
- በሥቃይ፣ በበሽታዎችና በሞት ምክንያት የሚመጡ ችግሮችን መግለጽ፤
- በሥቃይና በሞት አፋፍ ላይ ያለን ሰው ክርስቲያን መርዳት የሚችልባቸውን መንገዶች ምሳሌ መስጠት፤
- ሥቃይና ሞትን በተመለከተ ክርስቲያናዊ አመለካከትን የሚያሳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆን መግለጽ መቻል አለብህ።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ኢሳይያስ 52:13-15ና ኢሳይያስ 53ን አንብብ። ለተጨማሪ ምንባብ መጽሐፈ ኢዮብን አንብብ።
2. በተለመደው መንገድ የትምህርቱን ዝርዝር አጥና፤ እያንዳንዱን የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ ከመመልከትህ በፊት መልስ።
3. የመከራ ፈተናውን ውሰድና መልሶችህን አመሳክር።

# የህመምና የስቃይ ጥቅሞች

*ዓላማ 1 የህመምና የስቃይን ጥቅሞች የሚገልጹ ሦስት ምሳሌዎችን ለመስጠት።*

"ሕመምና ስቃይ እንዴት ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ?" ብለህ ምናልባት ታስብ ይሆናል። ሕመም የኃጢአት ወደ ዓለም መግባት ውጤት ከሆነ ሙሉ በሙሉ ክፉት አይደለምን? አንድ ነገር ክፉት ከሆነ አንዳች ጥቅም ሊኖረው ይችላልን? አዎ፥ ከሕመም ሊገኙ የሚችሉ አካላዊና መንፈሳዊ ጠባይ ያላቸው አንዳንድ ጥቅሞች አሉ።

## አካላዊ ጥቅም

ህጻን ልጅ እሳት አደገኛ መሆኑን እንዴት ነው የሚማረው? እጁን ወደ እሳቱ ቀረብ በማድረግ! ይህንን ሲያደርግ ህመም የምንለው ነገር ይሰማዋል። ህመም ይጐዳል። ህመም ሲሰማን ህመሙን ለማቆም አንድ ነገር ለማድረግ እንፈልጋለን። ህመም የሚከሰተው እርምጃ መውሰድ የሚገባን ችግር እንዳለ ለመጠቆም ነው። ህጻኑ ከእሳቱ የተነሳ ህመም ሲሰማው እጆቹን ከእሳቱ አቅራቢያ በፍጥነት በማራቅ ችግሩ ላይ እርምጃ ይወስዳል። በማንኛውም የሰውነታችን ክፍል ህመም ሲኖር ለምን ሕመም እንደተሰማን ለማግኘትና እንዴት ማስወገድ እንደሚገባን ለማግኘት የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ሰው በህመም ውስጥ ያልፍ ዘንድ ፈቃዱ አልነበረም። ይሁንና በሰው ኃጢአት ምክንያት ለውነታችንን ከሚጐዱን ወይም ከሚያጠፉን ነገሮች ማስጠንቀቂያ ይሆንልን ዘንድ እግዚአብሔር የሕመምን ስሜት አደረገልን። ህመም የማይሰማን ቢሆን ኖሮ ራሳችንን ከበሽታዎች፣ ከበሽታ ተህዋሲያንና በሰውነታችን ላይ ከሚሰነዘሩ ጥቃቶች መከላከል አንችልም ነበር።

## መንፈሳዊ ጥቅሞች

ሲ.ኤስ.ሌዊስ እንዲህ አለ "እግዚአብሔር በደስታችን ውስጥ በሹክሹክታ በህሊናችን ይናገራል በህመማችን ጊዜ ግን በጩኸት ይናገራል" ህመም ስቃይን ስለሚፈጥር ቸል ማለት የማይቻል ነው።

(1). የሕመም መንፈሳዊ ጥቅም ከአካላዊ ጥቅም ጋር ተመሳሳይ ነው። ምን እንደሆነ በራስህ አባባል ግለጸው።

አንዳንድ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱት ያልጠበቁ አደገኛ ነገሮች ሲገጥማቸው ብቻ ነው። ነገሮች ሁሉ በመልካም የሚጓዙ ከሆኑ በራሳቸው



ብቃት ያላቸው ያህል ይሰማቸዋል። ይሁንና ስቃይ፥ መቆጣጠር ከሚችሉት ከራሳቸው ኃይል ውጭ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ እንዲያስተውሉ ያደርጋቸዋል፤ ተስፋ በመቁረጥ ወደ እግዚአብሔር ለእርዳታ ይመለከታሉ። እርሱ አምላክ ስለሆነና ምስጋናችን የሚገባው ስለሆነ እምነታችንን በእርሱ ላይ ስናኖርና ስናመልከው በእርግጥም ይደሰታል። የራሳችንን መንገድ እየተጓዝን ጌታችን የመሆኑን መብቱን ስንዘነጋ እንኳን እኛን እጅግ መውደዱና በተቻለ መንገድ ሁሉ እኛን ወደ እርሱ መሳቡ ምን ያህል የሚያስደንቅ ነው። እግዚአብሔር በህመምና በስቃይ ሊቀርበኝና ከኃጢአትና ከዘላለም ሞት ሊታደገኝ ከቻለ ይህ ድንቅ የሆነ የስቃይ ጥቅም አይደለምን? ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ የሚለው "ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ" (ሮሜ 8፡18)።

በህይወታችን ውስጥ ልንወስን የምንችለው አስፈላጊው ውሳኔ እሱን ማፍቀርና ማገልገል እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል። ይህንን መልካም ውሳኔ መወሰን ካልቻልን ፍጻሜአችን ተስፋ የሌለውና የዘላለም ስቃይ ይሆናል። እግዚአብሔር መከራ እንድንቀበል በመፍቀድ ቀልባችንን ለመያዝና ለፈቃዱ ለመታዘዝ ካስቻለን በጣም እንደሚወደን በመረዳት ማመስገን አለብን።

(2). በተሻለ ሁኔታ ዐረፍተ ነገሩን የሚያሟላውን ምረጥ? ከላይ የተመለከተውን ሐሳብ በምሳሌ ለማቅረብ ብንፈልግ ማወዳደር ያለብን
ሀ. ልጁን ባለመዝለፍና ባለመቅጣት ፍቅሩን ከሚለግስ አፍቃሪ አባት ጋር ነው።
ለ. እንዲታዘዘው ለልጁ የተሻለውን ሁሉ ከሚሰጥ አፍቃሪ አባት ጋር ነው፡
ሐ. እንዴት ራሱን መምራት እንደሚያስፈልገው ለማስተማር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ልጁን ከሚቀጣ አፍቃሪ አባት ጋር ነው።

በክፍለ ትምህርት 1 ውስጥ የተወያየነው የስቃይ ሌላው ጥቅም የተሰቃዩ ሰዎች ጥሩ አጽናኚዎች ይሆናሉ (2ቆሮ. 1፡3-6 ተመልከት)። እኛን ያጋጠመን ዓይነት ስቃይን ለሚካፈሉ ሰዎች ራሳችንን ማቅረብ እንችላለን። እንደ ክርስቶስ አካል አባልነታችን አንዳችን የሌላውን ሸክም እንድንሸከም (ገላ. 6፡2)፣ ከሚያለቅሱ ጋር እንድናለቅስ (ሮሜ 12፡13)፣ ለተጐዱ ሁሉ እንድንጸለይ (ያዕ. 5፡16) ታዘናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን በ1ቆሮ. 12 ላይ ይናገራል።

> "አካልም አንድ እንደሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት. . . አንድም ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ . . . እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ" (12፥ 26፥ 27)።

በክፍለ ትምህርት 1 ውስጥ ስቃይ ሊያነፃን፣ እምነታችንን ለማረጋገጥና (1ጴጥ. 1፡6-7) የክርስቶስን ባህሪ በእኛ ውስጥ ለማዳበር እንደሚመጣ

ተመልክተናል (2ቆሮ. 4:7-10)። ለእኛ ካለው ዘላለማዊ ጥቅም አንጻር መንፈሳዊ ጥቅሙ እንድንሸከመው ከተሰጠን ማንኛውም ህመምና መከራ ይልቅ ይበልጣል።

(3). አካላዊና መንፈሳዊ ዋጋ ያለውን የህመም ጥቅም ምሳሌ ስጥ።

(4). ሌሎች ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት የህመም መንፈሳዊ ጥቅሞችን ስጥ።

## ከስቃይና ከሞት ጋር የሚዛመዱ ችግሮች

በሌሎች ክፍለ ትምህርቶች ውስጥ እንደተመለከትነው ስቃይ ብዙ ዓይነት ገፅታ ሊኖረው ይችላል። አካላዊ ወይም ስሜታዊ ባህርይ ሊኖረው ይችላል። ከበሽታ፣ ከኢ-ፍትሐዊነት፣ ሊጎዳን ከሚችል ከተፈጥሮ አደጋ፣ በግል ከሠራነው ኃጢአት የተነሣና በተለያዩ ሌሎች ምክንያቶች ልንሠቃይ እንችላለን። በዚህ ትምህርት እስከ አሁን እንድንሠቃይ ምክንያት የሚሆኑ በተወሰኑ ችግሮች ላይ ተወያይተናል። አሁን ሀሳባችንን በህመም በሽታዎችና ከሞት ጋር በሚዛመዱ ችግሮች ላይ ማተኮር እንፈልጋለን።

### ህመም

*ዓላማ 2 ኢዮብ በታላቅ ህመም ውስጥ በጽናትና በትዕግሥት እንዲያልፍ ያስቻለውን አዎንታዊ አመለካከት ለመግለጽ።*

ህመምን መፍራትና ለማስወገድ መሞከር ተለምዷዊ ጉዳይ ነው። በሆስፒታሎች መተላለፊያ ኮሪደሮች ውስጥ እየተጓዙ የተጎዱ ሰዎችን ስቃይ መመልከት እጅግ የሚያሳዝን ነው። አንድ መጋቢ የአእምሮ በሽተኞችን ሆስፒታል እንዲጎበኝ ተነገረው። ከገሀዱ ዓለም ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያጡ፣ አንዳንዶች ራሳቸውንና ሌሎችን እንዳይጎዱ ከአልጋቸው ጋር ታስረው ሲመለከት ከስቃያቸውና ከሐዘናቸው የተነሳ ልቡ ተሰበረ። በኋላም ወደ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል በመሔድ የጦርነት ሰለባ የሆኑ ወጣቶችን በህመም ሲሰቃዩ ተመለከተ። አንዳንዶች አይናቸው ታውሯል፣ ሌሎች እጃቸውን ወይም እግራቸውን አጥተዋል፣ ሌሎች ሽባ ሆነዋል። ሥቃያቸውን በማየት እንደገና እጅግ አዘነ።

ህመም በተለመደው መንገድ መንቀሳቀስ እንዳንችል ያደርገናል። ባህሪያችንን፣ ለሌሎች ያለንን አስተሳሰብና ለራሳችን ያለንን ግምት ሊጎዳው ይችላል። ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅ ህመም ተስፋ መቁረጥን ሊያስከትል ይችላል።

የኢዮብ መጽሐፍ ከትልቅ ህመም የተነሳ የሚሰቃይ ሰው የሚያልፍበትን የጥንት ምሳሌ ይሰጠናል። ኢዮብ ንብረቱን ሁሉ ያጣ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ተከታታይና አስቃቂ በሆነ ጥፋት ልጆቹ በሙሉ ሞቱ። በሚያሰቅቅ



ቁስሎች ለውነቱ ተወሮ አካሉ ተሠቃየ፣ ሥቃዩ ወደ ጠለቀ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ከተተው እግዚአብሔር ከእርሱ እጅግ እንደ ራቀ የተሰማው ወቅቶች ነበሩ። ይሁንና በዚህ ሁሉ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ አደረገ። ከችግሩ ውጭ እግዚአብሔርን አመለከ (ኢዮ. 1:21-22)።

ኢዮብ እንዳደረገው ሁሉ እያንዳንዱ ሰው ለህመም ተመሳሳይ ምላሽን አይሰጥም። ቁጣ፣ ምሬት፣ ጥርጣሬና ፍርሀት ሊኖሩ ይችላሉ። ምናልባት አንዳንዶች በአዎንታዊ ሌሎች በአሉታዊ መንገድ ለህመም ምላሽን የሰጡ የብዙ ክርስቲያኖችን ምሳሌ ማቅረብ ትችል ይሆናል።

(5). ለህመም አሉታዊ ምላሽ የሚሆኑ አምስት ነገሮችን ጥቀስ።

(6). ኢዮብ ታላቅ መከራን በትዕግሥት እየተቀበለ አዎንታዊ አስተሳሰብ እንዲኖረው ያደረገው ምንድነው?

### በሽታ

*ዓላማ 3 በግልህ በታመምህ ጊዜ የምታውቃቸውንና በታመሙ ሰዎች ዘንድ የሚታዩ የተለመዱ ችግሮችን ለማወዳደር።*

በሽታ በተለያየ ደረጃ ሁላችንንም የሚጎዳ ነው። በህክምና ቴክኖሎጂ የሕይወትን ተስፋ የሚያለመልሙ ብዙ እርምጃዎች አሉ። የሰው ልጅ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተዋግቶ ብዙ በሽታዎችን ድል ነስቷል። ይሁንና በሽታ አሁንም ቢሆን ወጣቱንና ሽማግሌውን፣ ሐብታሙንና ድሀውን፣ መልካሙንና መጥፎውን እየመታ ነው። በሽተኛው ሊያጋጥመው ከሚችሉት የተለመዱ ችግሮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የገንዘብ ችግሮች (የህክምና ወጭዎች፣ ለመስራትና ገንዘብ ለማግኘት አለመቻል።)
2. ለሌሎች ሸክም ከመሆን የተነሳ የሚመነጭ ጭንቀት
3. የመሞት ፍራቻ፣ ስለ ወደፊቱ እርግጠኛ አለመሆን
4. ከተለመዱ እንቅስቃሴዎችና ሥራዎች መገለል
5. ከመታመምና ከመሠቃየት የተነሳ የሚመጣ ምሬትና ተስፋ መቁረጥ
6. ጤናማ በሆኑት ላይ መቅናት
7. የእቅድ መሠናከል

ለበሽተኛው ሰው ኃላፊነት የሚወስዱ ሰዎች ከእነዚህ ችግሮች መካከል አንዳንዶችን ሊጋሩ ይችላሉ። በተጨማሪም በሽተኛውን ከተስፋ መቁረጥ ማዳን ካለመቻላቸው የተነሳ በተለየ መንገድ ሊሰቃዩ ይችላሉ።

(7). ከላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች መካከል በግል ሕይወትህ ያጋጠሙህ ከሆነ ይህንን ምልክት ከፊት ለፊቱ አስቀምጥ /✓/

ሀ. ከበሽታ ጋር የተያያዙ ሌሎች ማንኛውም ችግሮች ከነበሩብህ ዘርዝር።
ለ. ለነዚህ ለማናቸውም ችግሮች መፍትሔን ካገኘህ ምን እንደነበሩ ጥቀስ። መልስህ ረጅም ከሆነ ማስታወሻ ደብተርህን መጠቀም ያስፈልግሃል።

## ወደ ሞት መንገዘ

*ዓላማ 4 የማይፈወሱ ወይም የመጨረሻ ደረጃ ላይ ያሉ በሽታዎችን መለየትና ወንጌል እንዴት ልዩነት መፍጠር እንደሚችል ለማስተዋል።*

ኤልሳቤጥ ኩብለር ሮስ የተባለች የህክምና ዶክተር፥ ገዳይ በሆኑ በሽታዎች በመሞት አፋፍ ላይ ባሉ ሰዎች ላይ የሚፈጠሩ የአመለካከት ችግሮችን በተመለከተ ምርምርን አከናውናለች። (1969፣ ምዕራፍ 3-8) እየሞቱ እንደሆነ በሚያውቁ ሰዎች ዘንድ የጋራ የሆኑ አመለካከቶች እንዳሉና አመለካከታቸውም በተለያየ የለውጥ ደረጃዎች ውስጥ እንደሚያልፍ በምርምሯ አግኝታለች።

*ደረጃ 1 - መካድ፦* የመጀመሪያው ምላሽ "ይህ እውነት ሊሆን አይችልም። ይህ በእኔ ላይ ሊከሰት አይችልም" የሚል ነው። መካድ ሞት መምጣቱን በምናውቅ ጊዜ በሚፈጠረው ድንጋጤ የምንወስደው እርምጃ ነው። ብዙውን ጊዜ በሽተኛ የሆኑ ሰዎች ዶክተሩ ሊነግራቸው የሚችለውን በመፍራት ወደ ህክምና መሄድን ይፈራሉ። ይህ የክህደት አንዱ መንገድ ነው።

ለክርስቲያኖች ይህ ምናልባት የመሞታችን ሐሳብ ክርስቶስ በእርሱ ስቃይና መከራ ለእኛ ፈውስን ስለማዘጋጀቱ ከምናውቀው ጋር ስለሚቃረን ነው። በኔ በራሴ ልምምድ እየሞቱ መሆናቸውን ከሚያውቁና ነገር ግን እስከመጨረሻው የመሞቻቸው ሰዓት እግዚአብሔር እንደሚፈውሳቸው ከታመኑ ሰዎች ጋር በቅርብ ነበርኩኝ። በሚገድሉ በሽታዎች የተያዙና በተዓምር የተፈወሱ ብዙ ሰዎችንም አውቃለሁ። በሚጨርስ በሽታ የተያዙ ሰዎችን ሁልጊዜ ለፈውስ እንዲጸልዩና ለሚሆነው ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲታመኑ ልናበረታታቸውና አብረናቸው ልንጸለይና ልናምን ይገባናል።

ብዙውን ጊዜ ለብቻ መገለል መካድን ያስከትላል፤ የታመመ ሰው የራሱ ጊዜ ሊያስፈልገው ስለሚችል እንዲሁም ሞት ሊያስከትል በሚችል ሁኔታ ላይ ስላለ ለበሽተኛው የተለዩ ፍላጐቶች ንቁ መሆን ይገባናል።

*ደረጃ 2 - ቁጣ፦* ሁለተኛው ምላሽ "ለምን እኔ" የሚል ነው። ሰውየው ተዓምር እስካልተፈጠረ ድረስ መሞቱ እንደሆነ ባስተዋለ ጊዜ በሐሳቡ ላይ ማመጽ ተገቢ የሆነ ይመስለዋል። በውስጣችን ያለው የመኖር ፈቃድ እጅግ ብርቱ ነው። ይህ የሰውነታችን ጠባይ አንዱ ክፍል ነው። ለቁጣ ብዙ ምክንያቶች አሉ። በሽታ ሥራውን፣ የወደፊቱን እቅዶቹን፣ ህልሞቹን ስለሚያስተጓጉልበት፣ ሌሎች ሰዎች በተሟላ ሕይወት ስለሚኖሩና የእርሱ ሕይወት በአጭሩ ስለተቀጠፈ፣ በሕይወቱ ማድረግ የሚፈልጋቸው ገና ብዙ



ነገሮች ስላሉ ከሚያፈቅራቸው መለየት ስለማይፈልግ በምሬትና በቁጣ ሊሞላ ይችላል።

(8). ክርስቲያን እንደሚሞት ማወቁን ላለመቀበል እምቢ ማለት ስህተት ነውን? መልስህን አብራራ።

*ደረጃ 3 - መሟገት፦* ብዙ በመሞት ጉዞ ላይ ያሉ ሰዎች በዚህ ደረጃ ውስጥ ያልፋሉ፤ በተለይ ከእግዚአብሔር ጋር መሟገት ይሞክራሉ። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች የሚንከባከብና የሚረዳ ክርስቲያን በሽተኛው ከበደል ነፃ እንዲሆንና ፈውስ ቢኖርም ባይኖርም ለሕይወቱ ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲቀበል ሊረዳው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔር እየቀጣቸው እንደሆነ ይሰማቸዋል። ቀደም ባለው ክፍል እንደተመለከትነው ሊቀጣንና ወደ እርሱ ሊያቀርበን ሲፈልግ በእርግጥም ችግሮች በሕይወታችን እንዲያልፉ ይፈቅዳል። ነገር ግን የእርሱ ጸጋ ከእርሱ ጋር በምናደርገው መሟገት አይወሰንም።

*ደረጃ 4 መደበት፦* በሚገድል በሽታ በመሞት ላይ ያለ ሰው በሽታውን መካድ ሊያቅተው የበሽታው ምልክት እየጨመረና በሽታው እጅግ አስቃቂ እየሆነ ሲመጣ የመጨረሻ ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ እንዳለ ይሰማዋል። በሽታው በሕይወቱ ብዙ ለውጦችን አስከትሏል። የሥራ መልቀቅን፣ የገንዘብ እጥረትን፣ ስቃይንና ሌሎችንም፣ በመጨረሻም በብቃት መታገል ያቅተውና ወደ መደበት ውስጥ ይገባል። ይህ መደበት መጀመሪያ ካለፈባቸው ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው። ይሁንና እንደ ዶክተር ኩብለር ሮስ አባባል በሽተኛው ሰው ከሁሉም ነገርና ከሚያፈቅራቸው ሰዎች ሁሉ መለየቱን በማወቅ የሚያዝንበት ሌላ የመደበት ደረጃ አለ። ይህ ሰውየውን እንኳን ደስ አለህ የምንለው ወቅት ሳይሆን የምናጽናናውና አስፈላጊም ከሆነ አብረነው የምናለቅስበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ሰውየውን ሊመጣ ላለው ያዘጋጀዋል፤ ሊሞት እንደሚችል እውነታውን መቀበል እንዲችል ይረዳዋል።

*ደረጃ 5 - መቀበል፦* በመጨረሻ በመሞት ላይ ያለው ሰው የመቀበል ደረጃ ላይ ይደርሳል፤ ይህ የመሞቱን ሃሳብ ራሱ የሚተውበትና በአካባቢው ስለ ሚከናወነው ነገር ሁሉ ፍላጐቱ የሚቀንስበት ጊዜ ነው። ከሌሎች ሰዎች ሊለይና ሊርቅ ይችላል። ቁጣውን ትቷል፤ ደስተኛ ባይመስልም ከመሞቱ ሐሳብ ጋር በሰላም ያለ ይመስላል። ይህ ወቅት በቅርቡ ያሉ ሰዎች አብዝተው ሊያጽናኑት የሚገባበት ወቅት ነው።

አንዳንድ ሰዎች በእነዚህ በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ እንደሚያልፉ ወይም ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላኛው ወደፊትና ወደኋላ እንደሚመላለሱም ተስተውሏል። ሌላው የሰው ዘር ሁሉ የሚጋራው ተመሳሳይ ምላሽ አላቸው። ይህም ምላሽ ተስፋ ነው። እንዲህ የሚል የቆየ አባባል አለ "የተስፋ ምንጭ በሰዎች ልብ ውስጥ ዘለዓለማዊ ነው" በመሞት ላይ ያለ ሰው ሀኪሞች በምርመራቸው እንደተሳሳቱ፣ ተስፋ

ያደርጋል። ወይም የበሽታው ምልክት እንደሚጠፋ ወይም ለበሽታው ወዲያውኑ ፈውስ እንደሚኖር ተስፋ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ክርስቲያን የሆኑትም ሆነ ያልሆኑት የሚሰጡት ምላሽ ነው። ተስፋ በእያንዳንዱ ደረጃዎች የምትሮጥ ስሜቱንም አስቸጋሪ ከመሆን የምትጠብቅ ናት። በርግጥ ክርስቲያን በእግዚአብሔር እምነት ላይ የተመሠረተ የተባረከ ተስፋ አለው። ስለ ክርስቲያን ተስፋ በሚቀጥለው ክፍለ ትምህርታችን እንወያያለን። ለሁሉም የሕይወት ችግሮች ታላቅ ማርከሻችን ናት።

> "የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው።"
> ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ . . . በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
> 1ቆሮ. 15:26፥ 54፥ 57

*ሌሎች ችግሮች፦* የመሞት ሂደት ውስጥ አብረው የሚመጡ ተግባራዊ ጠባይ ያላቸው ሌሎች ብዙ ችግሮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

❶. አንድ ሰው የመሞቱን እውነታ መደበቅ መፈለግ። አንድ ሰው እንዲህ አለኝ "እንደምሞት ለማንም አልናገርም፤ ምክንያቱም ሰዎች ካወቁ በተለየ ሁኔታ ነው የሚመለከቱኝ። እስከምችልበት ደረጃ ድረስ ሕይወቴን እንደ ተለመደው ሁኔታ መጠበቅ እፈልጋለሁ"

❷. ያላለቁ ጉዳዮችን ማን ኃላፊነት እንደሚወስድ መጨነቅ፣ በቤተሰብ ላይ ምን እንደሚከሰትና ሌሎችም ጭንቀቶች። አንዲት ነርስ እንዲህ በማለት ተናግራለች። "ቤተሰብ ቁልፎች የት እንዳሉ፣ ገንዘብ የት እንዳለ፣ ምን ያህል ኢንሹራንስ እንዳለ፣ በጣም አስፈላጊ የሆኑ የቤተሰብ መረጃ ወረቀቶች.. .የት እንዳሉ ማወቅ ያስፈልገዋል።" "አንተ እዚህ እንዳልሆንክ አድርገህ አስብ። ቤተሰቦችህ ምንድነው ማወቅ የሚያስፈልጋቸው?" ብላ አስተያየቷን አቅርባለች።

❸. ከህክምና ክፍያዎች ወይም የወር ደሞዝ ገቢ ማጣት ጋር የተዛ መዱ የገንዘብ ችግሮች።

❹. የቤተሰብ አባሎች ሞት ሊከሰት እንደሚችልና እንዴት ቤተሰቡን ሊጐዳው እንደሚችል ለመወያየት ማንገራገር። በመሞት ላይ ያለው ሰው ያለበትን ሁኔታ አሳሳቢነት የማወቅ መብትና ከቤተሰቦቹ ጋር መነጋገር የመቻል መብት አለው።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮችን ልታሰብ ትችላለህ። በተጨማሪም ከመለያየት፣ ከሐዘን



ወይም ስለ ፈውስ ከቀረበው የጸሎት ጥያቄ አለመመለስ ጋር የተቆራኙ የሚሞተው ሰውና የቤተሰቡ ስሜታዊና መንፈሳዊ ችግሮች አሉ።

(9). በምትሞትበት አጋጣሚ ቤተሰቦችህ ያውቁ ዘንድ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ዝርዝር አዘጋጅ። ይህንን በማስታወሻ ደብተርህ ጻፈው።

አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ከቤተሰብ ጋር ልትወያይበት የምትችልበት ጥሩ ጊዜ ጤንነት ኖሮህ ከስሜታዊነት ውጭ በዓላማ ስታከናውነው ነው። ንብረቶች ካሉህ ኑዛዜህን በማስቀመጥ ባለቤትህንና ልጆችህን በተሻለ ሁኔታ መንከባከብ ትችላለህ። ባልና ሚስት ድንገት ከሁለት አንዱ ወይም ሁለቱ ቢሞቱ የልጆቻቸውን የወደፊት እንክብካቤ ለመጠበቅ በህብረት የተቻላቸውን ያህል እቅዱን መያዝ ይኖርባቸዋል። ይህ ቸል ሊባል የማይገባው አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

(10). ከሞት ጋር የተያያዙ ተግባራዊ ችግሮችን ለማቃለል እንዴት በተሻለ ሁኔታ መዘጋጀት ትችላለህ?

(11). በቀኝ በኩል ሰውየው ከመሞቱ እውነታ ጋር ሊያልፍባቸው የሚችልባቸው ደረጃዎች ተዘርዝረዋል። በግራ በኩል የእያንዳንዱ ደረጃዎች ምልክቶች ተዘርዝረዋል። በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ ደረጃዎቹን ከምልክቶቹ ጋር የሚያስማማውን ቁጥር ፃፍ።

| | |
|---|---|
| ________ሀ. በእውነታው ላይ በግልጽ የሚነገር ማመጽ። | 1. መካድ |
| ________ለ. ሁኔታውን ለመለወጥ አንድ ነገር ይከሰታል የሚል እምነት። | 2. ቁጣ |
| ________ሐ. ስለ በሽታው ማሰብን መተውና የሰላም ስሜት። | 3. መሟገት |
| ________መ. እውነታን ለመቀበል እምቢ ማለት። | 4. መደበት |
| ________ሠ. እግዚአብሔር ጣልቃ የሚገባ ከሆነ የተለወጠ ሕይወት ለመኖር ቃል መግባት። | 5. መቀበል |
| ________ረ. የሐዘንና ትልቅ የኪሳራ ስሜት። | 6. ተስፋ |

ክርስቲያን ትክክለኛውን የክርስቶስ ኢየሱስን የወንጌል ተጽዕኖ በሕይወቱ መመልከት የሚችለው ምናልባት በአካላዊ ስቃይ ዘመኑ ሊሆን ይችላል። ቢሊ ግርሃም "በከፍተኛ ሥቃይ ውስጥ በነበሩ በአንዳንዶች ውስጥ የመንፈስን ታላቅ ውበት አይቻለሁ" ብለዋል። ብዙ ውብ መዝሙሮችና አስደናቂ የሆኑ ስብከቶች በከፍተኛ ህመም ውስጥ በማለፍ ላይ በነበሩ ሰዎች ተጽፈዋል። በትልቅ ፈተና ውስጥ ሆነው ደስታንና ሰላምን የሚፈነጥቁና፥ ክርስቶስን የሚያንፀባርቁ አማኞች እንዴት የሚባርኩና የሚያነሳሱ ናቸው!

(12). በመሞት ሁኔታ ውስጥ ወንጌል በምን ዓይነት መንገድ ልዩነት ሊያመጣ ይችላል?

# በስቃይና በሞት አፋፍ ላይ ያለን ሰው መርዳት

*ዓላማ 5 ክርስቲያን በመሰቃየት ወይም በመሞት ላይ ያሉትን መርዳት የሚችልባቸውን መንገዶች ለማየት።*

በዚህ ትምህርት ውስጥ በመሠቃየት ላይ ያሉትን የምናገለግልበትን ብዙ መንገዶችን ተመልክተናል። በዚህ ጊዜ በተለይ በእካላዊ ወይም ስሜታዊ ሕመም ወደ ሞት በመንካ የሚሰቃዩትን ለመርዳት የምንችልባቸውን መንገዶች እንመለከታለን።

## በአጠገባቸው ሁን

ምናልባት እጅግ አስፈላጊ ነገር ማድረግ የምትችለው በአቅራቢያቸው መገኘት ነው። ለእነርሱ ያለህ ቀረቤታ፣ ሩኅሩኅ ድምጽህና የእጆችህ መዳሰስ ከብዙ ቃላቶች ይልቅ ፍቅርህንና ለእነሱ ያለህን ትኩረት በከፍተኛ ድምጽ ይናገራል። በመሰቃየት ወይም በመሞት ላይ ለሚገኝ ሰውና ለቤተሰቡ ሁልጊዜ የምትገኝላቸው ሁን። እጠር ያለና የተዘወተረ ጉብኝት ለታመመ ሰው ማበረታቻ ነው። ረጅም ጊዜ የምትቆይ ከሆነ ጉብኝትህ ሸክም ይሆንበታል። ለቤተሰቡ ጉዳዮችን በመፈፀም፣ ልጆችን በመንከባከብ፣ ለታመመው ሰው በማንበብ ወይም እካላዊ ፍላጐቶቹን በማገልገል ፍቅርህን ልትገልጠው ትችላለህ።

## ታማኝ ሁን

ከታመመና በመሞት ላይ ካለ ሰው ጋር ስትነጋገር ታማኝና እውነተኛ ሁን። ክርስቶስ በፍርሃትና በተስፋ መቁረጥ ጊዜ አስደናቂ ኃይልህ እንደሆነ ስሜቶችህ ይገልጡ ዘንድ፥ እነርሱም ራሳቸው ያውቁ ዘንድ ፍቀድ። መንፈስ ቅዱስ የመጽናናት ቃል በአንተ በኩል ይናገር ዘንድ ፍቀድ። የሚያነሳሳና የሚያበረታታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍሎችን አካፍላቸው። አብረሃቸው በመሆን ለእነርሱ ጸልይ። ቀደም ሲል በተወያየነው ውስጥ ያነሳናቸውን ታማሚው ሰው ለሚያልፍባቸው ደረጃዎች ወይም ምላሾች ንቁ ሁን፤ በሽተኛው ለበሽታው ያለው ምላሽ የተሳሳተ እንደሆነ ለማሳመን አትሞክር።

## ንቁ ሁን

ምንም እንኳን ክርስቲያኖች ከሞት ፍርሀት ነፃ የወጡ ቢሆንም ሞት እስከ አሁን ድረስ ጠላት ነው። ድንገተኝነቱም መረበሽን ሊፈጥር ይችላል። በመሞት ላይ ባለው ሰውና በሐዘንተኛው ላይ ለሚከሰት የተለየ የብቸኝነት ስሜት ንቁ ሆነህ ልትረዳው ይገባል። ከሚያውቁት ሕይወት ሲርቁ፥



የሚሰማቸውን ስሜት በማቅለል ሊረዷቸው የሚችሉ በክርስቶስ ያሉ ወንድሞችና እህቶችን በአጠገባቸው መገኘትን ይሻሉ።

በመሞት ጉዞ ላይ ያሉ ሰዎች ሌሎች ሰዎች ከሰው በታች አድርገው እንደሚመለከቷቸው ዘወትር ይናገራሉ። የበለጠ መጽናናትና መበረታታት በሚያስፈልጋቸው ወቅት ሞትን ብቻቸውን ይጋፈጡ ዘንድ ብቻቸውን ትተዋቸው ሰዎች ይሄዳሉ። ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው ያሉበትን ሁኔታ፣ የበሽታቸውን ምልክቶችና ባህሪያቸውን በእነርሱ ፊት እንደሌሉ አድርገው ይወያያሉ። ንቁ ክርስቲያን ይህ ይሆን ዘንድ በፍጹም አይፈቅድም። በሽተኛው ምንም መናገር ባይችልም እንኳን ይሰማ ይሆናል። በዚህ ወቅት ተስፋንና መጽናናትን መናገር ነው የሚያስፈልግህ።

(13). ክርስቲያን በመሰቃየት ወይም በመሞት ላይ ያሉትን መርዳት የሚችልባቸውን መንገዶች የሚያንጸባርቁትን እውነተኛ ዐረፍተ ነገሮች ከፊት ለፊታቸው ያለውን ፊደል አክብብ። ክርስቲያን

ሀ. ከታማሚው ሰው ጐን በመሆን ለእርሱ እንደሚጠነቀቅ በማውራት ረዘም ያለ ጊዜን ማጥፋት አለበት።
ለ. የታማሚውን ስሜትና የሚያሳስበውን ጉዳዮች ከበሽተኛው ጋር በመካፈል ታማኝ መሆን አለበት።
ሐ. በሚያስፈልገው ማንኛውም መንገድ ለማገልገል ብዙውን ጊዜ በቅርብ የሚገኝ መሆን አለበት።
መ. ታማሚው በተገኘበት ስለ በሽተኛው ሁኔታ ከሌሎች ጋር መወያየትን ማስወገድ አለበት።
ሠ በሽተኛውን ችግሮቹን ከማስላሰል ለማውጣት የግል ችግሮቹን ከበሽተኛው ጋር መወያየት አለበት።
ረ. በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተስፋና የመጽናናትን ቃል መናገር አለበት።
ሰ. በመሞት ላይ ያለው ሰው እንደ ማንኛውም ሰው ፍላጎቱ ይሟላ ዘንድ ንቁ መሆን ይኖርበታል።

# ከሞት ጋር የተዛመዱ ችግሮች

*ዓላማ 6 በ1ቆሮ. 15:55-57 መሠረት ክርስቲያን ሲሞት በሐዘንተኛው ሕይወት የሚያልፈውን ብርታትና ሰላም ለመግለጽ።*

## መንፈሳዊ ሁኔታ

ሞትን ለሚጋፈጡ እጅግ እስጊው ችግር ይህ ነው። "እግዚአብሔርን ለመገናኘት ዝግጁ ነኝን?" ሰውየው የኃጢአት ችግሩን ካስወገደ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ከሆነ፥ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱና ከመቃብር በመነሣቱ ይህንን ችግር ስለፈታው ሞት ለእርሱ ችግር አይደለም። ይህ በ1ቆሮ. 15:55-57 ተገልጧል።

ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው። የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

ክርስቲያን ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር "ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና . . . ልሔድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ" (ፊልጵ. 1፡21፥ 23) ብሎ ያውጃል። መዝ. 116፡15 "የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው" ይላል።

## ሐዘንተኛ

ሞት፥ ወደ ጌታ ከሄደ ክርስቲያን ይልቅ በምድር ለቀሩ ወዳጆቹ ከፍተኛ ችግር ነው። ሐዘንተኞች ሐዘን በሕይወታቸው ውስጥ ያልፋል። ሞትን መከላከል ባለመቻላቸው ወይም ሊኖራቸው ከሚችለው ፀፀት የተነሳ በደለኝነት ሊሰማቸው ይችላል። ከመለየት የተነሳ በሚፈጠር ስሜት እጅግ ስለሚሰቃዩ ሞት በእርግጥ የመከሰቱን እውነታ መቀበል ያስፈልጋቸዋል። አብሮአቸው የሚቆምና የሚያዝን ሰው ሊኖር ይገባል።

ብዙዎቻችን ሐዘንተኛውን ለማጽናናት በምንሞክርበት ጊዜ ልንረዳው የማንችል መሆናችን ይሰማናል። ብዙ የምንናገራቸው ነገሮች ከሚጠቅሙ ይልቅ የሚጎዱ ናቸው። አሁንም እንደገና መጥቀስ የምንፈልገው የአንተ መገኘት፣ የእጆችህ መዳሰስ፣ ለመርዳት ፈቃደኛ መሆንህ፣ ከብዙ ቃላቶች ይልቅ ብዙ ስራን ያከናውናል። ድንጋጤው ሁሉ ከራቀ በኋላ ሕይወት ወደ ቀድሞው ጉዞዋ ከተመለሰች በኋላ ሕይወትን ከሚወዱት ሰው ውጭ ለመግፋት ብቻቸውን ለቀሩ ሐዘንተኞች የአንተ ጓደኝነት እጅግ አስፈላጊ ነው።

ከቤተሰባችን አንድ ሰው ሞቶብን የምናውቅ ሰዎች በዚህ ወቅት ወደ እግዚአብሔር ስንመለከት እርሱ መለኮታዊ ብርታትና ሰላም የሚሰጥበት ሰዓት እንደሆነ ተለማምደናል። በእያንዳንዱ ውሳኔያችንና የልብ ስብራታችን ይረዳናል። አንድ ቀን ከምንወደው ሰው ጋር በመንግሥት ሰማያት ለዘላለም እንደምንገናኝ የተባረከውን ተስፋ ያስረግጥልናል።

(14). በ1ቆሮ. 15፡55-57 መሠረት ክርስቲያን ሲሞት በሐዘንተኞቹ ውስጥ የሚያልፈውን ብርታትና ሰላም አብራራ።



# ክርስቲያናዊ አመለካከት

## የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ

*ዓላማ 7 በክርስቶስ ምሳሌ መሠረት ክርስቲያን ስቃይንና ሞትን ሲጋፈጥ ሊመራበት የሚገባውን መርህ ለማስቀመጥ።*

ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር።

> እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል (ኢሳ. 53፡10-11)።

ኢየሱስ ኃጢአትን አላደረገም። ንፁህ ሆኖ ሳለ ለበደለኞች ተሠቃየ። ይሁንና ወደ ምድር ከመምጣቱ ከረጅም ዘመን በፊት የእርሱ መምጣት ማለት ሐዘንና ስቃይን መስበር እንደሆነ ያውቀዋል። ኢየሱስ ከሞተና ከተነሣ በኋላ እንዲህ በማለት አብራርቶታል። "ክርስቶስ መከራ ይቀበላል። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል" (ሉቃ. 24፡46)።

(15). የሐዋ. 3፡16ንና የሐዋ. 26፡22-28ን አንብብ። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ክርስቶስ ስላደረገው የሚሉት ምንድን ነው?

አይሁዶች መሲሁ ሁሉን ቻይ ንጉስ ሆኖ ከፍተኛ የፖለቲካ ኃይልን ይዞ እንደሚመጣና ከሮማውያን ጭቆና ነፃ እንደሚያወጣቸው ይጠብቁ ነበር። የብሉይ ኪዳን ነብያት በመከራው የሚያገለግል አገልጋይ ሆኖ እንደሚመጣ የተናገሩትን አላስተዋሉም። ዛሬም ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት፥ የክርስቶስ የመከራውን ገጽታ ለማሰብ ደስ የማያሰኝ አድርገው ወስደውታል።

ምንም እንኳን የመከራው ከባድነት ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም በጌቴሴማኔ እንዲህ ብሉ እንዲጸለይ ምክንያት ነበር። "አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል። ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን" (ማር. 14፡36)። ኢየሱስ መከራው ዓላማ እንዳለው ያውቃል። ምንም እንኳን የሚቻል ከሆነ ከፈተናው መዳንን ቢፈልግም የእርሱ ፍጹም ፍላጐት ግን የአባቱን ፈቃድ መፈጸም ነው። በእርሱ መከራና ሞት በሚገኘው ዘላለማዊ ዋጋዎች ላይ ትኩረቱን አደረገ እንጂ ጊዜያዊ ወደሆነው ጭንቀትና ሐዘን አልተመለከተም። እርሱ የእኛ ፍጹም ምሳሌያችን ነው።

> "የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ

በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ" (ዕብ. 12:2-3)።

(16) ክርስቲያን ስቃይና ሞት ሲያጋጥመው ሊመራበት የሚገባውን በክርስቶስ ምሳሌ ላይ መሠረት ያደረገን መርህን አስቀምጥ።

## ለስቃይና ሞት የክርስቲያን ምላሽ

*ዓላማ 8 ክርስቲያን በስቃይና በሞት ላይ ያለውን አስተሳሰብ የሚያንፀባርቅ መሠረታዊ መርሆዎችን ለመለየት።*

*በእግዚአብሔር ላይ መታመን*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢዮብ መከራው ወደ እርሱ ለምን እንደመጣ አልተነገረውም። ይሁንና የእግዚአብሔር ዓላማ መልካም እንደሆነ ሊያጠፋው እንደማይፈልግ ነገር ግን ሊያነፃው እንደሆነ እምነት ነበረው። ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እንዲህ አለ። "የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ" (ኢዮ. 23:10)።

ኢዮብ እግዚአብሔርን መውደዱና መታመኑ ከእግዚአብሔር ማንነት የተገኘ እንጂ እግዚአብሔር በሚሰጠው ቁሳቁሳዊ ሀብትና እርካታ ወይም የጤንነት ሁኔታ የሚገኝ እንዳልሆነ አረጋገጠ።

እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ በሁሉን ቻይ ኃይሉና ጸጋው ከመከራችን ያወጣናል። ይሁንና አንዳንድ መከራዎች በእግዚአብሔር ፊት ብንጸልይም ሌሎችንም ነገሮች ብናደርግ እንኳን እንዳሉ ይሆናሉ። መከራ በእግዚአብ ሔር እቅድ ውስጥ እኛን ለማስልጠን (ዕብ. 12:7-11) ለመፈተን (ኢዮ. 23:10)፣ ለአገልግሎት ያዘጋጀን ዘንድ (2ቆሮ. 1:4-5) እና ክርስቶስን በውስጣችን ለመሳል አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል። "እርሱንና የትን ሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትን ሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ" (ፊልጵ. 3:10)።

*ደስታ*

በአዲስ ኪዳን በመከራና በደስታ መካከል የጠነከረ ግንኙነት እናያለን።

| | |
|---|---|
| ያዕቆብ 1:2 | ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት። |
| የሐዋ. 5:41 | እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ። |



| | |
|---|---|
| ቆላ. 1:24 | አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል። |
| 1ተሰ. 1:6 | ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ፥ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፤ |
| 1ጴጥ. 4:13 | ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሴት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፥ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ። |
| ዮሐ. 16:22 | እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደገና እያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም። |

ዕብ. 10:34ን፣ ያዕ. 5:11፣ ራዕ. 12:2፣ ሮሜ 8:18፣ ዮሐ. 18:20-22 እና ሉቃ. 6:21-23ን አንብብ።

ደስታ የክርስቲያን የሕይወት መንገዱ ነው። በመከራ ውስጥ ደስታን መለማመድ ብቻ ሳይሆን በጌታ ደስ መሰኘት የሐዘንና የለቅሶ ማርከሻ ነው (ነህ. 8:10፣ መዝ. 30:5 እና ቆላ 1:10-12 ተመልከት)።

ክርስቲያን ምንም እንኳን ከኃጢአት የተነሳ ሞት አስፈላጊ እንደሆነ ቢረዳም በክርስቶስ ድል እንደተነሣ ያውቃል። (ራዕ. 1:17-18፣ 1ቆሮ. 15:1-8፣ ዮሐ. 11:26) በክርስቶስ ያለን እምነት ወደ ፍርሃትና ወደ መከፋት አላመጣንም። ይህ ክርስቲያን ስለ ሞት ያለው ገጽታ አይደለም! ከሚወዱትና በሞት ከተለያቸው አካል ፊት የሚቆሙ የመለያየት ሐዘን ይሰማቸዋል። ይሁንና ለሄደው ሰው ግን የከበረና ደስ የሚያሰኝ አቀባበል ይደረግለታል።

> "ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰ በሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፈ ወደ በኲራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል (ዕብ. 12:22-24)።

*መማረክ*

መከራ በሚመጣበት ጊዜ ለመዳን እንጸልያለን፤ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር በምህረቱ ነጻ መውጣትን ያመጣልናል። ይሁንና ፀሎታችን እኛ

በምንመርጠው መንገድ የማይመለስልን ብዙ ጊዜያቶች አሉ። እነዚህ ወቅቶች ከእምነት ማነስ ጋር የምናያይዛቸው አይደሉም። ይልቁንም በከፍተኛ ፈተና ውስጥ ቀና መንፈስ መያዝ ከተአምራት ይልቅ የበለጠ እምነትን ይጠይቃል። በምንጸልይበት ጊዜ መልሱ ምንም ይሁን "የኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን" ብለን ከኢየሱስ ጋር ማጽናት ይኖርብን።

አንድ ሰው እንዲህ ብሏል "ስራስ ከመኖር ምርኮ ወጥቶ በሙሉ ኃይል ለእግዚአብሔር መቆም ዋጋ ያስከፍላል" የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበል ከሰውነታችን ጠባይ ጋር ይቃረናል። ምናልባትም መከራን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆንን ሊጠይቅ ይችላል።

> "መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፤ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል" (ማቴ. 10:38-39)።

> "እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁና፥ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ" (ሮሜ 8:13)።

ሮሜ 14:7 ከእኛ አንዳችን እንኳን ለራሳችን እንደማንኖር ለራሳችንም እንደማንሞት ያስተምረናል። በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፤ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። ይህንንም በማድረጋችን በአካባቢያችን ባሉት ላይ የጠነከረ ተጽዕኖ እናሳድራለን። መከራን እንድትቀበል ተጠርተህ ከሆነ የምታልፍበት ሕይወት ወይም የምትሰጠው ምላሽ በሰዎች ላይ ሕይወትን የመለወጥ ውጤት ይኖረዋል።

## *መለኮታዊ ራዕይ*

በዚህ ክፍል ያጠናኸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ሕይወትህን እንዴት ነው የሚለውጡት?

*ጊዜ፦* መዝሙር 90 የእግዚአብሔር ሰው የሙሴ ጸሎት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ እንዲህ በማለት ይጸልያል። "ጥበብን የተሞላ ልብ ይኖረን ዘንድ፣ ዕድሜያችንን መቁጠር አስተምረን።" ሞት ወደ እኛ መምጣቱን ማወቃችን እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ ለመጠቀም ጠንቃቃ እንዲያደርገን ያስፈልጋል። እግዚአብሔርን መውደድና ሌሎችን ማገልገል ዘላለማዊ ዋጋ ያለውና እግዚአብሔርንም የሚያስደስት ነው።

*ዋጋዎች* - የምድር ነገሮች የሚጠፉና ጊዜያዊ መሆናቸውን ስትረዳ በትክክለኛው ብርሃናቸው ትመለከታቸዋለህ። እነርሱ እዚህ ያሉት ልንጠቀምባቸው ሲሆን፥ ቀለል ባለ ሁኔታ መያዝ ግን ይኖርባቸዋል። ምድራዊ ለሆኑ ቁሳቁሳዊ ነገሮች አነስ ያለ ዋጋን፥ ለሰማያዊ ነገሮች ደግሞ



የበለጠ ዋጋን ስጥ። እውነተኛ ደስታ የእግዚአብሔርን መንግሥት በቅድሚያ ለሚፈልጉ በመከራ መካከል እንኳን ይገኛል።

*መጽናናት* - እንክብካቤን የሚያደርግ ክርስቲያን በመገኘቱ ብቻ በመሞት ላይ ያለውን ሰው ከበሽታዎች የተነሣ የሚከሰትን የሕመምና የብቸኝነት ስሜት፥ ወይም ሐዘንተኛውን ማገልገል ይችላል።

*መሰጠት* - የዘላለም ሕይወትን ቃል ኪዳን የሰጠህን ክርስቶስን ካወቅህ ጊዜ ጀምሮ ስለ ሞት ከመፍራትና ከመጨነቅ ድነሃል። ኢየሱስ የሰውነት ባህሪያችንን ተካፍሏል "እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው፤ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" (ዕብ. 2:14-15)። ራስህን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈህ መስጠት ትችላለህ፥ ታማኝ ፈጣሪህ ደግፎ መልካምን በማድረግ እንድትቀጥል ያደርግሃል (1ጴጥ. 5:2)።

(17). *ዐረፍተ ነገሩ መከራንና መሞትን በተመለከተ የክርስቲያኖች አስተሳሰብ መሆን የሚገባውን በትክክል ካመለከተ "ጥ" የሚለውን ፊደል ሙላ። ዐረፍተ ነገሩ ደካማ ከሆነ "ደ" የሚለውን ፊደል በመጻፍ ሙላ።*

ሀ. በእግዚአብሔር ላይ መታመን ከመከራና ከህመም ነፃ በመውጣት ላይ ነው።
ለ. እግዚአብሔር ሁልጊዜ መከራን እንድንቀበል ሲፈቅድ ዓላማ አለው።
ሐ. ክርስቶስን መከተል መከራውን ፈቅዶ መቀበልን ያካትታል።
መ. በመከራ መደሰት የሚኖረው አሁን በሚኖር ጥቅም ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት በሚኖር ክብር ነው።
ሠ. በጣም በጠበቀ ሁኔታ በቁሳቁሳዊ ንብረታችን ላይ ካተኮርን፥ ብዙ መከራ የምንቀበልበትና የምንፈተንበት ነገር ይኖራል።
ረ. ስለራሳችን መሞት ትክክለኛ ግንዛቤ ካለን ጊዜያችንን እንዴት መጠቀም እንደሚገባን ብዙ ትኩረትን እንሰጣለን።
ሰ. ለመከራችን ክርስቶስን በመሰለ መንገድ ምላሹን ከሰጠን በመከራ ውስጥ ያሉት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደርና ለማጽናናት እንችላለን።
ሸ. ክርስቲያን እምነቱን መፈተን እንዲችልና ሌሎችንም ማጽናናት እንዲችል ከፍተኛ መከራን መታገሥ ይኖርበታል።

## የመከራ ፈተና

1. ህመም እንደ በረከት የሚቆጠርበት አንዱ መንገድ

ሀ. ስለሚጐዳ ነው።
ለ. በሁሉም ሕይወት የሚያልፍ ስለሆነ ነው።
ሐ. ትኩረት የሚፈልግን ችግር ስለሚያስጠነቅቀን ነው።
መ. ኃጢአታዊ ባህርይን እንደወረስን እግዚአብሔር የሚያስታውሰን መን ገዱ ስለሆነ ነው።

2. አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ህመም በሕይወታችን እንዲያልፍ የሚፈ ቅድበት ምክንያት

ሀ. በሌሎች መንገዶች ሲናገረን ችላ ስለምንለው ነው።
ለ. መሰቃየት ስለሚገባን ነው።
ሐ. በመከራ ውስጥ ካላለፍን ሌሎችን መርዳት ስለማንችል ነው።
መ. በተሳሳቱ ምክንያቶች ስለምናመልከው ነው።

3. እግዚአብሔር መከራን በመፍቀድ ሊቀጣን የሚመርጠው

ሀ. ሊጐዳን ስለሚፈልግ ነው።
ለ. በእኛ ላይ ስለተቆጣ ነው።
ሐ. ለራሳችን ብቁ ሊያደርገን ስለሚፈልግ ነው።
መ. እጅግ ስለሚወደን ነው።

4. የመከራ መንፈሳዊ ጥቅሙ ልንሸከመው ከምንችለው ማንኛውም ህመም ይልቅ እጅግ የሚመዝን ነው። ምክንያቱም የአሁኑ መከራችን

ሀ. ወደ ሞት ይመራናል።
ለ. ወደ መረዳት ይመራናል።
ሐ. ወደ ወደፊት ክብር ይመራናል።
መ. ወደ ጊዜያዊ መዳን ይመራናል።

5. ምንም እንኳን ኢዮብ ህመምን የሚያስከትሉ ጥቂት አሉታዊ ምላሾች ቢታዩበትም ጠንካራው ምላሹ ግን

ሀ. እግዚአብሔርን ጥፋተኛ ማድረግ ነበር።
ለ. በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነቱን በመጠበቅ እርሱን ማምለክ ነው።
ሐ. ጓደኞቹ መከራን እየተቀበሉ ስላልነበር ይቃወማቸው ነበር።
መ. በእርሱ ላይ ለተፈጸመው ነገር ራሱን ጥፋተኛ ማድረግ ነበር።



6. ከሚከተሉት ውስጥ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት ለሞት ያለውን ምላሽ የሚያብራራው የትኛው ነው?

ሀ. ተስፋ ለ. መካድ ሐ. ቁጣ መ. መቀበል

7. አንድ ሰው እግዚአብሔር ከፈወሰው አሥራቱን በታማኝነት እንደ ሚከፍል ቃል ቢገባ፣ ለየትኛው ደረጃ ምሳሌ ይሆናል?

ሀ. ቁጣ ለ. ተስፋ ሐ. መደበት መ. መሟገት

8. ለውየው በመሞቱ እውነታ ላይና ቤተሰቡንና ለወደፊት ያለውን እቅድ ሳይፈጽም በመለየቱ ሐዘን ቢሰማው በየትኛው ደረጃ ውስጥ ነው ያለው?

ሀ. ቁጣ ለ. መደበት ሐ. መካድ መ. ተስፋ

9. ምናልባት ብትሞት እንኳን ስለ ቤተሰብ ጉዳይና ቤተሰቦችህ ያውቁ ዘንድ ስለምትፈልጋቸው ጉዳዮች ለመወያየት ጥሩው ጊዜ የትኛው ነው?

ሀ. ልትሞት በተቃረብክበት ወቅት
ለ. የሚገድል በሽታ እንዳለብህ ባወቅህ ጊዜ
ሐ. ጤነኛ ሆነህ ሳለህ
መ. ወደ ሰባዎቹ የእድሜ ዘመንህ ስትቃረብ

10. በመከራ ወይም በመሞት ላይ ያሉትን ለመርዳት ጥሩ መንገድ ያልሆነው ከእነዚህ ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ. ለእርዳታ የምትገኝ መሆን።
ለ. ስሜቶችህን በመግለጽ ታማኝ መሆን።
ሐ. ላላቸው የተለዩ ፍላጐቶች ንቁ መሆን።
መ. ከበሽታቸው እንደሚሻላቸውና እንደማይሞቱ አስመስለህ መናገር።
ሠ. ነጻ እንዲወጡና እንዲፈወሱ ለእነርሱ መጸለይ።

11. ክርስቶስ ለመከራ የሰጠው ምላሽ ለእኛ እንደ ምሳሌ ሆኖ የሚያገለ ግለው እንዴት ነው?

ሀ. እግዚአብሔር ከመከራ ነጻ እንዲያወጣው በመጠበቁ።
ለ. እግዚአብሔር ለእርሱ ያሰው ፈቃድ ነጻ መውጣት ስለሆነ፣ ነጻ ለመውጣት መጸለዩ።
ሐ. ውጭያዊ ስሜትን ያለማሳየት መከራውን መቀበሉ።
መ. የሚያልፍበትን ህመም በመፍራቱ።

12. ከሚከተሉት መካከል ስለ መከራ ክርስቲያናዊ አመለካከትን የማይወክለው የትኛው ነው?

ሀ. ማፈግፈግ
ለ. መታመን
ሐ. ደስታ
መ. መማረክ
ሠ. መለኮታዊ ራእይ

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

9. የአንተ መልስ

1. ህመም መፈታት ያለበት ችግር እንዳለብን ያስታውቀናል። በዚህ ሁኔታ ስለ መንፈሳዊ ችግር ማስጠንቀቂያ ይሆናል።

10. ከቤተሰብ አባላት ጋር አሁን በመወያየትና ለቤተሰብ መልካም የሆነውን በሚቻለው መንገድ በማዘጋጀት (ኢንሹራንስ መያዝ፣ ኑዛዜን ማድረግ፣ ልጆች የሚጠበቁበትን ሁኔታ በማዘጋጀት)

2. ሐ

11. ሀ. 2
ለ. 6
ሐ. 5
መ. 1
ሠ. 3
ረ. 4

3. ህመም እንክብካቤ የሚያስፈልገው አንድ የተሳሳተ ነገር እንዳለ ያስታውቀናል።

12. የአንተ መልስ። በክርስቶስ ላይ ባለኝ እምነት ሞት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው እንዳልሆነ አውቃለሁ። በእግዚአብሔር ላይ ባለኝ እምነት እና ሞትን እንደሚቆጣጠር በማወቄ የመሞትን ሀሳብ መጋፈጥ እችላለሁ።

4. ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ሊሆን ይችላል። ህመምን የሚያውቁ በህመም ውስጥ ያሉትን ለመንከባከብ የተሻሉ ናቸው፤ መከራ ያጠራናል፤ እምነታችንንም ያጠራዋል፤ መከራ የክርስቶስን ባህሪ በኛ ውስጥ ያዳብራል።

13. ሀ. ሐሰት
ለ. እውነት
ሐ. እውነት
መ. እውነት
ሠ. ሐሰት
ረ. እውነት
ሰ. እውነት

5. መጥፎ ባህሪ፣ መጥፎ አመለካከት፣ ስለራስ ያለ አመለካከት ዝቅ ማለት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ቁጣ፣ ተቃውሞ፣ ጥርጣሬ፣ ፍራቻ።



14. መልስህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት። ክርስቶስ የማስታረቁን ሥራ ለተቀበሉ ሞትን ድል እንደነሳ እናውቃለን፣ ከሞት በኋላ የምንወዳቸው ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ እናውቃለን፤ እኛም ከእነርሱ ጋር በእርሱ ፊት እንሆናለን። ይህ እውቀት የሞትን መውጊያ ወስዶ ሰላምን ይሰጣል።

6. በእነዚህ ነገሮች ሁሉ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ በማጽናት። እግዚአብሔርን ማምለኩን አላቆመም።

15. እርሱ መከራን ተቀብሏል።

7. የአንተ መልስ። በዚህ ጉዳይ ላይ አሁንም መፍትሔን የምትፈልግ ከሆነ የስጠንህ ችግርን መፍትሔ መስጫ መንገዶችን ተግባራዊ አድርግ፤ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ ጠብቅ።

16. የአንተ መልስ። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆን ይገባዋል። የእርሱ ፈቃድ ከሆነ እግዚአብሔር ከመከራና ከሞት ያድነኝ ዘንድ ይችላል። ነፃ ለመውጣት እጸልያለሁ፣ ይሁንና ለዘለዓለማዊ መልካም ይሆንልን ዘንድ የመረጠልኝን ነፃ መውጣት ቢሆን ወይም ሞት እቀበላለሁ።

8. የአንተ መልስ። በእርግጥም ሞት ጠላታችን በመሆኑ ቁጣ የመጀመሪያው ለሞት ዛቻ ተፈጥሮአዊ ምላሽ ነው (1ቆሮ. 15:26)። ይሁንና ክርስቶስ ሞትን ድል ስለነሣው ሕይወታችንን ለእርሱ ጥበቃ እስከሰጠን ድረስ የሚከሰተውን ሁሉ እንቀበላለን። እንደዚህም ሆኖ ለፈውስና በእግዚአብሔር ላይ እምነታችን የተጠበቀ ይሆን ዘንድ መጸለይ አለብን፤ ከሞት መዳንንም መሻት አለብን።

17. ሀ. ደካማ
ለ. ጥሩ
ሐ. ጥሩ
መ. ጥሩ
ሠ. ደካማ
ረ. ጥሩ
ሰ. ጥሩ
ሸ. ደካማ

# 10 ትምህርት

# ተስፋን ማጽናት

በዳንቴ ኢንፌርኖ ግጥም ውስጥ የገሀነም ደጆችን ገጣሚው እንዲህ በማለት ገልጾታል። በደጃፉ ላይ ያለው መልዕክት እንዲህ ይላል። "በዚህ የምትገቡ ተስፋ ቢሶች ሁሉ" ማናችንም ብንሆን ለመከራ ሙሉና የመጨረሻ መልስ የለንም። እግዚአብሔር ችግሮቻችን ለምን እንደተከሰቱብን አይገልጽልንም፥ ይሁንና እያንዳንዱ ችግር ለእኛ በጐ የሆነን ነገር እንደሚያከናውንልን እንድናምን ይፈልጋል። እግዚአብሔርን የምናውቅና የምንወድ ይህ የተባረከ ተስፋ አለን። ሕይወት የምንሮጠው የሩጫ እሽቅድድም ይመስላል፤ የውድድሩ መጨረሻ ሞት ሳይሆን፣ ሞት ወደ ዘለዓለም ሕይወት መግቢያ በር ሆኖ ያሸጋግረናል። እንዴት የከበረ ተስፋ ነው!

> "ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን። እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው። በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ" (ዕብ. 6፡19-20)።

እዚህ ባለን ሕይወት የወደፊቱ ኑሮአችን ምን እንደያዘ አናውቅም። ነገር ግን የወደፊት ሕይወታችን በማን እንደተያዘ እናውቃለን። በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያኖች ተስፋ ምን እንደሚልና ተስፋን መጠበቅ የምንችልባቸውን መንገዶች እንመለከታለን። አንድ ቀን ችግሮቻችን በሙሉ ከበስተጀርባችን ሆነው ዘላለማዊ ተስፋችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳለበት መንግሥተ ሰማያት ደጆች እንድንገባ እንጋበዛለን።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል



- በድል አድራጊው ክርስቶስ
- በማረጋገጥ ማጽናት
- በእምነት

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- በክርስቶስ ድል ነሺ የሚለውን አባባል ምን ማለት እንደሆነና እንዴት ተስፋ እንደሚሰጥ መግለጽ፤

- መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጣቸውን በምሳሌ መግለጽና በክርስቶስ ካለህ የግል ልምምድህ ጋር ማዛመድ፤

- በምንለማመደው መከራና በሰማይ ከጌታ ጋር በሚኖረን ህብረት የድል ነሺነት ተስፋ መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት፤

- በውስጥህ ያለውንና በእያንዳንዱ የሕይወት ጉዳና የሚያፀናህን ተስፋ መግለጽ መቻል አለብህ።

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንዳደረግከው ሁሉ ክፍለ ትምህርቱን አጥና። ይህንን ክፍለ ትምህርት በሚገባ ሁኔታ ለመረዳት የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ማንበብህን እርግጠኛ ሁን። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን ሁሉ ከመለስክ በኋላ መልሶችህን እኛ ከሰጠነው ጋር አመሳክር።

2. የሙከራ ፈተናውን ውሰድና መልሶችህን አመሳክር።

የትምህርቱ ዝርዝር

## በድል አድራጊው ክርስቶስ

***ዓላማ 1 ከተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተስፋችን በድል ነሺው ክርስቶስ መሠረት ላይ የቆመ መሆኑን ለመለየት።***

ይህን ክፍለ ትምህርት እነዚህን የኢየሱስ ቃሉች በመጥቀስ እንጀምራለን። "በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህንን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16:33)። ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው የኃጢአትና የሞትን ኃይል አሸንፏል። በሕይወቱ የጠላቱን የዲያብሎስን ፈተና ድል ነስቷል። እኛም በእርሱ ኃይል አሸናፊዎች መሆን እንችላለን።

*ኢየሱስ በሞትና በሲኦል ላይ ጌታ ነው።* የዮሐንስ ራዕይ ጸሐፊ ዮሐንስ ኢየሱስን በተመለከተ ጊዜ እንደሞተ ሰው በእግሮቹ ሥር ወደቀ። ኢየሱስም "አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ" አለው (ራዕ. 1:17-18)።

*ኢየሱስ ራሱ ከተሰቀለና ከተቀበረ በኋላ ተነስቷል።* ለደቀ መዛሙርቱ ለወዳጆቹና ከ500 ለሚበልጡ ተከታዮቹ በተመሳሳይ ወቅት ለብዙ ጊዜ ተገልጦአል (1ቆሮ. 15:1-8)።

*በጌታ ቃሉች መሠረት በእርሱ የሚኖሩና የሚያምኑ በፍጹም አይሞቱም።* ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ያስነሣበትን አጋጣሚ ይህንን ትምህርት ለማስተማር ተጠቅሞበታል። ለማርታ የተናገራት ቃል ለእያንዳንዱ አማኝ መጽናናትንና ተስፋን ወደ ሕይወታቸው የሚያመጣ ነው። "ኢየሱስም - ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚአለሽን? አላት" (ዮሐ. 11:25-26)።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክርስቶስን የሚወዱት እንደማይሞቱ ነገር ግን ቦታን ብቻ እንደሚለውጡ ግልጽ ነው። ጊዜያዊ ከሆነ ከዚህ መኖሪያቸው (ከአካላቸው) በመለየት ወዲያውኑ በጌታ ፊት ይሆናሉ (2ቆሮ. 5:8፣ 8)። ክርስቶስ ሞትንና ሐዘንን ስላሸነፈ እርግጠኛ የሆነ ተስፋ አለን። ከእርሱ ጋር የዘለዓለማዊ ሕይወት ተስፋ።

ክርስቶስ ያደረገልንን ማወቅና ከዚህ ሕይወት በንለይ ከእርሱ ጋር እንደምንሆን ማወቅ በጨለማው የሕይወታችን ጊዜያት የሚያጸናንን ተስፋ ይሰጠናል።



(1). የሐዋ. 24:15ን አንብብ። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደተገለጠው ተስፋችን በምን ላይ ነው የተመሰረተው?

(2). 1ጴጥ. 1:3ን አንብብ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የተስፋችን ምንጭ ምን እንደሆነ ነው የሚናገረው?

(3). ቆላ. 1:5፣ ቲቶ 2:13ና ዕብ 6:19ን አንብብ። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተስፋችን ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ የሚውልበት ወቅት መቼ እንደሆነ ነው የሚገልጡት?

ሀ. በምናልፍበት መከራ ውስጥ
ለ. በዳንበት ወቅት
ሐ. በመንግሥተ ሰማያት ከክርስቶስ ጋር ህብረት በምናደርግበት ጊዜ

## በማረጋገጥና ማጽናት

***ዓላማ 2 በተሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ይገባኛል የምንላቸው የተስፋ ቃሉችና ከተስፋ ቃሉቹ ጋር ተያይዘው የተሰጡትን ሁኔታዎች ለመለየት።***

በክፍለ ትምህርት 2 ውስጥ አንድ ሰው ክርስቲያን ለመሆን ማድረግ ከሚገባው አንዱና የመጀመሪያ ነገር ከሞት የተነሣው ኢየሱስ የሕይወቱ ጌታ እንደሆነ መናዘዝ ነው። መናዘዝ ወይም መመስከር የክርስትናን ተስፋ በመጠበቅ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የሕይወትን ጨለማ ጉን፣ ችግሮችንና ፈተናዎችን እየተመለከተ ካለማቋረጥ ስለዚሁ ጉዳይ ብቻ የሚናገር ሰው ተስፋ በመቁረጥና በፍርሀት ታሰሯል። ነገር ግን ባለበት ማናቸውም ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይል እንደሚረዳው በማስተዋል እግዚአብሔር በሕይወቱ ያደረገውን ብዙ በረከቶችንና መልካም ነገሮችን የሚናገር ሰው በሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ እንኳን ቢገኝ ተስፋ ይኖረዋል።

አንዳንድ ጊዜ መመልከት የምንችለው ነገር ከፊት ለፊታችን የተጋረጠውን ችግር ብቻ ይሆናል። አስቸጋሪ ችግሮች ሲያጋጥሙኝ፣ ተመሳሳይ በሆኑ ችግሮች ውስጥ እግዚአብሔር በድንቅ እንደረዳኝና በዘመናት ሁሉ በኔ ላይ ያፈሰሰውን በረከት እያስታወስ የሚረዳኝ አንድ ጓደኛ አለኝ። የእርሱን መልካምነትና በቃሉ ውስጥ ከእኛ ጋር ይሆኑ ዘንድ የተሰጡንን ቃል ኪዳኖችን ስናስብ እምነታችን እየበረታ ይሄዳል። በማናቸውም ፈተና ባለድሎች እንሆናለን።

የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ደግመህ አንብብ።

1. ተስፋዎቹ የሚታጠፉ አይደሉም (1ነገ. 8:56)።
2. የሰጠውን ተስፋ ሊፈጽም ይችላል (ሮሜ 4:2)።

3. የማዳንን ተስፋ ሰጥቶአል (መዝ. 34:19-20)፡፡
4. ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ ተስፋ ገብቷል (ኢሳ. 43:2)፡፡
5. ጸሎታችን እንደሚመልስ ተስፋ ገብቷል (ማር. 11:24)፡፡
6. እምነታችንን እንደሚያከብረው ተስፋ ገብቷል (ሉቃ. 17:8)፡፡
7. በነፃ ለሚሰጡ በረከትን እንደሚሰጥ ተስፋ ሰጥቷል (ምሳ. 3:9-10፣ ሉቃ. 6:38፣ 2ቆሮ. 9:6)፡፡
6. ከሚታዘዙ ጋር እንደሚሆን ተስፋ ገብቷል (ዮሐ. 14:23)፡፡
9. እርሱን የሚሹቱን ለመርዳት እንደሚመጣ ተስፋ ገብቷል (2ዜና. 7:14፣ ሉቃ. 11:9)፡፡
10. ዘለዓለማዊ ሕይወትን ተስፋ ሰጥቷል (1ዮሐ. 2:25፤ ያዕ. 2:5)፡፡

እነዚህ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከሚገኙት ተስፋዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እያንዳንዱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልግና አንብባቸው፡፡ የእርሱን ቃል ኪዳን ደጋግመን ስናነብ ልባችን በእርሱ ላይ ይታመን ዘንድ ይበረታታል፤ "ምን ዓይነት ኃያል ጌታ ነው የምናገለግለው" ብለን ቃሉን እናጸናለን፡፡ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ተስፋ ነብዩ ሚክያስ ከተመለከተ በኋላ "ከግብጽ ምድር እንደ ወጣህበት ዘመን ተዓምራትን አሳያቸዋለሁ" የሚለውን ትንቢት በመናገር (ሚክ. 7:15) በእነዚህ ማጽኛ ቃሎች ምላሽን ሰጠ፡፡

> "በደልን ይቅር የሚል፥ የርስቱንም ቅሬታ ዓመጽን የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? ምህረትን ይወድዳልና ቁጣውንም ለዘላለም አይጠብቅም፡፡ ተመልሶ ይምረናል ክፉታችንንም ይጠቀጥቃል፤ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል" (ሚክ. 7:18-19)፡፡

## እግዚአብሔር ተስፋ የገባውን . . . ያደርገዋል

አረጋግጣለሁ

(4). የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍሎች አንብብና በእያንዳንዱ ውስጥ ያለውን ተስፋ ከትክክለኛው ምንባብ ክፍል ጋር አዛምድ፡፡



| | |
|---|---|
| ሀ. እግዚአብሔር ለጸሎታችን ምላሽን ይሰጣል፡፡ | 1. መዝ. 34:19-20 |
| ለ. የሚሰጡትን ይባርካል፡፡ | 2. 1ነገ. 8:56 |
| ሐ. እርዳታውን ከጠየቅን ይሰጠናል፡፡ | 3. ሉቃ. 17:6 |
| መ. ከችግሮቻችን ያድነናል ፡፡ | 4. ማር. 11:24 |
| ሠ. እምነታችንን ያከብረዋል፡፡ | 5. ዮሐ. 14:23 |
| ረ. ከታዘዝነው ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡ | 6. ምሳ. 3:9-10 |
| ሰ. ተስፋዎችን በመጠበቅ አይታክትም፡፡ | 7. ሉቃ. 11:9 |

እግዚአብሔር ከሰጠን ውብ ከሆኑ ተስፋዎች አንዱ በመዝሙር 91 ውስጥ የሚገኘው ነው፡፡ በዚህ መዝሙር ውስጥ ሊጐዱን ከሚሹ የክፋት ኃይላት ሁሉ እንደሚጠብቀን ተስፋ ገብቷል፡፡

(5). መዝ. 9:13ን አንብብ፡፡ የእግዚአብሔር ጥበቃ በምን ላይ የተመሰረተ ነው? (ቁ. 1፣ 9 እና 14 ተመልከት) የተሻለውን መልስ ምረጥ፡፡

ሀ. እርዳታን በምንሻ ጊዜ የእርሱን ስም መጥራት አለብን፡፡
ለ. በእርሱ ውስጥ መሸሸግና እርሱን ማፍቀር አለብን፡፡
ሐ. ብርቱዎች መሆንና ጠላታችንን መዋጋት አለብን፡፡

(6). የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብና በእያንዳንዱ ውስጥ የሚገኘውን ተስፋ ለመቀበል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ግለጽ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 2ዜና 16፡፡9 | ሐ. ዮሐ. 15:7 | ሠ. 1ዮሐ. 3:21-22 |
| ለ. መዝ. 34:7 | መ. ማር. 11:24 | |

(7). መዝ. 91:15፤ ኢሳ. 58:9፣ 65:24 እና ዘካ. 13:9ን አንብብ፡፡ በእነዚህ በእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተሰጡት ተስፋዎች ምንድናቸው?

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን አስብ

*ዓላማ 3 የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችን መሠረት በማድረግ እግዚአብሔር ቀደም ባሉት ጊዜያት ያደረገውንና ወደ ፊት ያደርጋል ተብሎ የሚጠበቀውን ተስፋ ለማረጋገጥ፡፡*

በከፍተኛ ችግር ውስጥ አዎንታዊ ማጽኛ የሆኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች አሉ፡፡ አዎንታዊ ማጽኛ ስል አንድ ነገር ከሆነው እውነታ ውጭ የተለየ አድርጎ ማመልከት ማለቴ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔርን መልካምነትና በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ሊረዳን ከክፉትም ሊያድነን ይችላል ብሉ ማስተዋል ማለቴ ነው፡፡ ይህ ማጽኛ እግዚአብሔር ቀድሞውኑ በስራው የተመሠረተና ባለፉት ዘመናት እንደ ስራው ወደ ፊት መስራቱን ይቀጥላል በሚለው እምነታችን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

(8). ዳን. 3:13-18ን አንብብ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተሰጠው ማረጋገጫ ምንድነው?

በዕንባቆም 3:17-19 ነብዩ በእግዚአብሔር ላይ ስለ መታመን ይህንን ያረጋግጣል።

*ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥*
*በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥*
*የወይራ ሥራ ቢጐድል፥*
*እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥*
*በጎች ከበረት ቢጠፉ፥*
*ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ*
*እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል*
*በመድኃኒቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ።*
*ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ ነው*
*እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል።*
*በከፍታዎችም ላይ ያስኬደኛል።*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ታላቅ የማጽኛ መግለጫዎች አንዱ በመዝሙር 23 ውስጥ ይገኛል። ንጉስ ዳዊት ደስታንና ሐዘንን፣ ድልንና ሽንፈትን፣ መዳንንና አደጋን የሚያውቅ ሰው ነው። ብዙ ጊዜ ከጠላቶች ፊት መሸሽ ነበረበት። በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት መስራትና ይቅርታን መቀበል ምን እንደሆነ ያውቃል። ሕይወቱ የተረበሸ፣ በሐዘን፣ በስደት፣ በፀፀት፣ በጥርጣሬና በተቃውሞ የተሞላ ነበር። መዝሙሮቹ ወደ እግዚአብሔር ርዳታንና ምህረትን ለመሻት ባቀረባቸው ስቅሶዎች የተሞሉ ናቸው። ይሁንና መዝሙር 23 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት እጅግ አምንታዊ የማጽኛ መግለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው።

## መዝሙር 23

| ማጽኛ | እግዚአብሔር የሚሰጠን |
|---|---|
| እግዚአብሔር እረኛዬ ነው | ስንቅ |
| የሚያሳጣኝም የለም | |
| በለመለመ መስክ ያሳድረኛል | እርካታ |
| በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል | ሰላም |
| ነፍሴን መለሳት | መታደስ |
| ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ | ምሪት |
| በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ | ጥበቃ |
| አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም | |
| በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል | ማጽናናት |
| በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ | በአደጋ ጊዜ ያለ |
| በጠላቶቼ ፊት ለፊት | ዋስትና |
| ራሴን በዘይት ቀባህ | ክብር፣ በረከት |
| ጽዋዬም የተረፈ ነው | የማይቆጠር በረከት |
| ቸርነትህና ምህረትህ በሕይወቴ | ዘላለማዊ |
| ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል | መልካምነትና ፍቅር |
| በእግዚአብሔርም ቤት | ዘላለማዊ ተስፋ |
| ለዘላለም እኖራለሁ | |



(9). መዝ. 66:16-18ን አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች የምን ምስክርነቶች ወይም ማጽኛዎች ናቸው?

(10). በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተለይቶ የተገለጠው ሁለት የእግዚአብሔር ሥራ ምንድነው?

(11). እነዚህን ሁለት የእግዚአብሔር ሥራዎች ለመቀበል መሆን ያለበት ምንድነው?

(12). በ2ጢሞ. 3:11 ውስጥ የጳውሎስ ምስክርነት ምንድነው?

(13). በ2ጢሞ. 4:16-18 ውስጥ ጳውሎስ የሚሰጠው ሁለት ማጽኛዎች ምንድን ናቸው?

ሀ. ባለፈው ዘመን ለ. ወደፊት

(14). በተሰየ ማስታወሻ ደብተር እግዚአብሔር ባለፈው ዘመን ያደረገልህንና በዚያም መሠረት ወደፊት ያደርግልኛል ብለህ የምትጠብቀውን የራስህን ማጽኛ ጻፍ። ይህንንም ማጽኛ ለአንድ ሰው ንገር። "እግዚአብሔር ያደረገልኝን ልንገርህ፣ አድምጠኝ" ብለህ ዐረፍተ ነገርህን ጀምር።

## እግዚአብሔር አድኖኛል እንደገናም ያደርገዋል

አረጋግጣለሁ

*ዓላማ 4 ችግሮቻችንን ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት ከምንሆንበት ከታላቁና ከዘለዓለማዊው ተስፋ ጋር ለማዛመድ፣*

ተስፋን መጠበቅ በእግዚአብሔር ላይ ባለ ጠንካራ እምነት ይወሰናል። ዕብ. 11 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእምነት ምዕራፍ ይባላል። በቁጥር 1 እነዚህን ቃሎች እናነባለን። "እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።"

ዕብ. 11ን በሙሉ እንብብ። የዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው ክፍል በእግዚአብሔር ታላቅ እምነት ያላቸው ወንዶችና ሴቶች ያገኙትን ድል ይናገራል። እምነታቸው የእግዚአብሔር ኃይል በሕይወታቸው ይሰራ ዘንድ ገልጦታል።

(15). ከቁ. 35-36 ያሉት ጥቅሶች ከቁ. 4-34 ካሉት ጋር እንዴት ይለያሉ?

(16). በቁጥር 40 መሠረት ፍጹማን ያልሆኑት ለምንድነው?

እነዚህ ሰዎች በጠላቶቻቸው ላይ አሸናፊ ስለሆኑ አይደለም የተመሰገኑት፥ *ነገር ግን ተስፋ ላደረጉትና ላላዩት እርግጠኞች ስለሆኑ ነው* (ቁ. 1)። ምን ነበር ተስፋ ያደረጉት? በመንግሥተ ሰማያት ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም የመሆናቸውን ተስፋ! የእነዚህ ወንዶችና ሴቶች የእምነት ልምምዶች የተለያዩ እንደነበር አስተውል። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ሁለቱ እንኳን ተመሳሳይ ነገርን አልተለማመዱም። የተለያየ ፈተናና ድል ነበር የተለማመዱት። የእግዚአብሔር ክንድ በህይወታቸው ሲሰራ ያመለክተናል፣ እኛም በሕይወታችን በተመሳሳይ መንገድ ይሰራ ዘንድ እምነት ሊኖረን ይችላል።

*ዘ ፕሮብሌም ኦፍ ፔይን* በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ሲ.ኤስ.ሌዊስ የእያንዳንዱን ሰው ልዩነት አብራርቷል። እግዚአብሔር በመካከላችን ያለው ልዩነት ጥቅም የማይሰጥ ቢሆን ኖሮ ከአንድ በላይ ነፍስን አይፈጥርም ነበር በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል። እኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ነን (2ቆሮ. 6:16)። እግዚአብሔር በእናንተና በእኔ ውስጥ ያድራል። እኔ የእርሱ ቤተ መቅደስ ነኝ። ከመወለዴ በፊት እግዚአብሔር ያውቀኛል (መዝ. 139:13-16)፤ ድንቅ በሆነ ሁኔታ በእርሱ ተፈጥሬአለሁ። ለእርሱም ደስታ እስጥ ዘንድ ተፈጥሬአለሁ። ሕይወቴ በሞላ፣ ልቤ ሁልጊዜ እርሱን ይናፍቃል። ይሁንና በመለኮታዊ ባህርይ ውስጥ የሚታየውን እጅግ በጣም ጥቂቱ ብቻ ነው በእኔ ሕይወት የሚታየው (1ቆሮ. 13:12)። በመንግሥተ ሰማያት ቤታችን ለእኛ ያዘጋጀውን ድንቅ ነገር መገመት ብቻ ነው የምንችለው። ሆኖም በምድር በማልፍበት ፈተና፣ በሚያስለቅሱኝ ነገሮች፣ በደስታዎቼ፣ በመከራዎቼና በምለማመዳቸው ድሎች እርሱ ለእኔ ያዘጋጀልኝን ሥፍራ እንዲይዝ እየቀረፀኝ ነው። መልካምም ሆነ ክፉ በሆኑ



ልዩ ልዩ ልምምዶቼ እግዚአብሔር ማን መሆኑን በግሌ እንዳውቀውና እንድረዳው እያደረጉኝ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን በሚያልፍበት በራሱ የሕይወት ልምምድ ውስጥ እርሱ ብቻ ሊረዳ የሚችለውን እግዚአብሔርን በአንድ መልኩ እያወቀው ነው።



"መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ" (ማቴ. 25:21)

በራዕ. 2:7 እነዚህ ቃሎች ለቤተክርስቲያን ተጽፈዋል። "ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ። ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፤ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል።"

አስበው በዚህ ሕይወት ውስጥ አሸናፊ ሲሆን ሽልማቱ ለእግዚአብሔርና ለእኔ የታወቀን አዲስ ስም መቀበል ነው። ያ ስም በእግዚአብሔርና በእኔ መካከል፥ በእኔ በሚሠራው በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል እኔ ለሆንኩት ሁሉ፣ መከራን ለተቀበልኩበት ሁሉ፣ ድል ለነሣሁባቸው ሁሉ፣ ምልክት ነው! ከሌሎቹ ድል ነሺዎች በተለየ ሁኔታ እኔ በግሌ ከፈጣሪዬ ጋር ያለኝን ህብረት ይወክላል። በሰማይ በዕብራውያን 11 የተጠቀሱትን ታላላቅ የእምነት ሰዎች ጨምሮ በዘመናት ሁሉ ውስጥ ከነበሩት ቅዱሳን ሁሉ ጋር በአንድነት እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደገለጠልን መወያየት እንዴት ደስ የሚያሰኝ ሐሳብ ነው። እኔ ከአንተ ጋር ስካፈል አንተ ከእኔ ጋር ስትካፈል እያንዳንዳችን የነገስታት ንጉስ የጌቶች ጌታ የሆነውን ድንቅ አምላካችንን ታላቅ መረዳትና ማስተዋል እንቀበላለን።

በ1ቆር. 2:9 እንዲህ በማለት ተነግሮናል "ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ እንዲህ እንናገራለን" እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ድንቅ ነገር ሳስብ ማንኛውንም ዓይነት ፈተናና ችግር መቀበል እችላለሁ። ከእርሱ ጋር ለሚኖረኝ ዘለዓለማዊ ቦታ በሚያዘጋጀኝ ሁኔታ ይመራኛል። በዮሐ. 14:1-3 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በእነዚህ ቃሎች አጽናንቶአቸዋል፡ "ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔ ደግሞ እመኑ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ። እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተም ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ"

## የሙከራ ፈተና

እውነት -ሐሰት። ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ "እ" የሚለውን ፊደል ክፍት በሆነው ቦታ ጻፍ። ዐረፍተ ነገሩ ሐሰት ከሆነ "ሐ" የሚለውን ቃል ጻፍ።

1. ክርስቶስ ድል አድራጊ የሚለው አባባል ክርስቶስ ለእርሱና ለእኛ በሞትና በመቃብር ላይ ድልን እንዳገኘ ያስታውሰናል።
2. አካላዊ ሰውነት ሲሞት ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ይሔዳሉ።
3. ክርስቶስ በእርሱ የሚኖሩና የሚያምኑ እንደማይሞቱ ሲናገር ስለ አካላዊ ሥጋ ሞት ነበር የሚናገረው።
4. ድል ባደረገው በክርስቶስ ላይ ያሰነ ተስፋ የተመሠረተው በእርሱ ሞትና ትንሣኤ ከእርሱ ጋር በመንግሥተ ለማያት የዘላለም ሕይወት እንዳሰን በማወቅ ነው።
5. አዎንታዊ ማረጋገጫዎች ማለት መልሱን ከማየታችን በፊት እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደመለሰ መናገር ነው።
6. የእግዚአብሔር ኃይል በእያንዳንዱ ሁኔታዎች እንደሚረዳን አንዱ ማረጋገጫ ተስፋዎቹን እንደገና መመልከትና ማመን ነው።
7. እግዚአብሔር የሰጠንን አንዳንዶቹን ተስፋዎች ለመቀበል አንዳንድ ነገሮችን ማማሏት አለብን።
8. ዳዊት መዝሙር 23ን የፃፈው ጸሎቱ፥ ስላልተመለሰለት ተስፋ በቆረጠበት ወቅት ነበር።
9. እግዚአብሔር ኃይሉን በቀደመው ዘመን ስላረጋገጠልን ወደፊት ያከናውናል ብለን የምንጠብቀውን በእርግጠኝነት ማጽናት እንችላለን።
10. በዕብ. 11 የዕምነት ሰዎች ስማቸው የተዘረዘረው በሕይወታቸው ዘመናቸው ድል የነሱትን ተመሥርቶ ነበር።
11. መንግሥተ ሰማያትን ውብ የሚያደርገው አንዱ ነገር ቅዱሳን በያንዳንዱ ሁኔታ እግዚአብሔርን በመታመን ያሳለፉትንና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እርስ በርሳቸው መከፋፈላቸው ነው።
12. እያንዳንዳችን በመንግሥተ ሰማያት ከፈጣሪያችን የምንቀበለው አዲስ ስም ምንም ዓይነት ፈተና ውስጥ እንሰፍ፥ በዚህ ሕይወት አሸናፊ የመሆናችን ሽልማት ነው።



## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

9. እግዚአብሔር ለዘማሪው ያደረገው ነገር

1. የሙታን ትንሣኤ ይኖራል በሚለው እምነታችን

10. ጸሎትን መመለስና ፍቅርን መስጠት

2. የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

11. መዝሙረኛው በልቡ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ኃጢአት አስወግዷል፣

3. ሐ

12. ጌታ ከመከራውና ከስደቱ ሁሉ አድኖታል።

4. ሀ. 4 ሐ. 7 ሠ. 3 ለ. 2
ሰ. 6 መ. 1 ረ. 5

13. ሀ. እግዚአብሔር በጐኔ ቆሞ ብርታትን ሰጠኝ።
ለ. ጌታ ከማንኛውም የክፉ ጥቃት ያድነኛል፥ ወደ እርሱም ሰማያዊ መንግሥት በሰላም ያመጣኛል።

5. ለ

14. የአንተ መልስ። ይህ ምናልባት በዚህ ክፍሰ ትምህርት የምትሰራው በጣም አስፈላጊው መልመጃ ነው።

6. ሀ. ለእግዚአብሔር በሙላት የተሰጠ ልብ።
ለ. እግዚአብሔርን መፍራት ወይም ማክበር።
ሐ. በክርስቶስ መሆንና በአንተ እንዲኖር መፍቀድ።
መ. የጠየቅከውን እንደምትቀበል ማመን።
ሠ. የእርሱን ትዕዛዛት መታዘዝና የሚያስደስተውን ማድረግ።

15. ከቁ. 35-38 የሚናገረው ከፈተናቸውና ከስደታቸው ነፃ ላልወጡት ታላላቅ የእምነት ሰዎች ነው። መከራን በመቀበል ጌታን ለማገልገል ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጡ።

7. ወደ እርሱ ስንጣራ እግዚአብሔር ይመልስልናል።

16. እግዚአብሔር የተሻሰን ነገር አቅዶ ነበር (ለሁላችንም)። እውነተኛው መዳናቸው ምድራዊ ፈተና ከሆነው ጊዜያዊ ፈተና መዳን አልነበረም።

ለ. ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ ከፋ ይለዋል።
ሐ. ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ፍርድ በታች ያደርጋል።

10. የአንተ መልስ። እነዚህ መልስ ሊሆኑ ከሚችሉት ጥቂቶቹ ናቸው።
ሀ. 1ቆሮ. 8:12-13፣ 19-20 እና ምዕራፍ 7
ለ. 1ቆሮ. 7:3-4፤ ኤፌ. 5:22-23
ሐ. ዘጸ. 20:13፤ 1ቆሮ. 8 እና 7፤ ዮሐ. 8:11
መ. ሮሜ 1:18-32፤ ዘሌ. 18:22-23፤ 2ጴጥ. 2:6-10
ሠ. ማቴ. 5:6፤ 1ቆሮ. 6:11፤ ሉቃ. 7:50

## ክፍለ ትምህርት 8

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. እውነት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. እውነት
11. ሐሰት
12. ሐሰት
13. እውነት
14. እውነት
15. እውነት
16. መንፈሳዊ፣ አካላዊ
17. ኃጢአት

18. በመርዳት ወይም በመድረስ
19. ማስወገድ
20. ይቅርታ
21. ደስታ
22. ግድ እንደሚልህ አሳይ፤ አፍቃሪ ሁን፤ አዳምጥ፤ የምትገኝ ሁን፤ ሐዘንን ተካፈል፤ ርዳታን ስጥ፤ እጽናና፤ ተስፋን እና ማበረታታትን ስጥ።

## ክፍለ ትምህርት 9

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. ሐ
5. ለ
6. ሀ
7. መ
8. ለ
9. ሐ
10. መ
11. ለ
12. ሀ

## ክፍለ ትምህርት 10

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. ሐሰት
11. እውነት
12. እውነት